# የምርጫ ህጎች እና የምርጫ ክርክሮች በፍርድ ቤት የሚስተናገዱበት ስነስርአት ህግ

2013 ዓ.ም.

## በዚህ ጥራዝ ውስጥ የተካተቱት ህጎች የሚከተሉት ናቸው ፥

የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011.....05

የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011፣ የምርጫ ጉዳዮች በፍርድ ቤት የሚስተናገዱበ የሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ረቂቅ ደንብ.....103

የእጩ ተወዳዳሪዎች ምዝገባ፣ የድጋፍ ፊርማ አሰባሰብ እና መለያ ምልክት አመራረጥ መመሪያ ቁጥር 7/2013.....122

የመራጮች ምዝገባ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 6/2013.....145

የምርጫ ጉዳዮች በፍርድ ቤት የሚስተናገዱበት የሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ (ረቂቅ) ደንብ.....168

# <u>**የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ-ምግባር አዋጅ (1162/2011) ማውጫ**</u>


- <u>**ክፍል አንድ- ጠቅላላ**</u>
  - (አንቀፅ- 1-3)
- <u>**ክፍል ሁለት- ስለ ምርጫ እና አስፋፃሚ አካላት**</u>
  - ምዕራፍ 1- የምርጫ ስርአት፣ መርሆች እና አይነት (አንቀፅ- 4-11)
  - ምዕራፍ 2- የምርጫ ማስፈፀሚያና አደረጃጀቶች (አንቀፅ-12-17)
- <u>**ክፍል ሶስት- ስለ ምርጫ አፈፃፀም**</u>
  - ምዕራፍ 1- የመራጮች ምዝገባ (አንቀፅ- 18-29)
  - ምዕራፍ 2- የዕጩዎች ምዝገባ (አንቀፅ- 30-42)
  - ምዕራፍ 3- የምርጫ ዘመቻ (አንቀፅ- 43-46)
  - ምዕራፍ 4- ስለ ድምፅ አሰጣጥ (አንቀፅ 47-56)
  - ምዕራፍ 5- የድምፅ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ (አንቀፅ- 57-62)
- <u>**ክፍል አራት- ስለ ፖለቲካ ፓርቲዎች በጠቅላላ**</u>
  - ምዕራፍ 1- የፖለቲካ ፓርቲ አመሰራረት (አንቀፅ - 63- 65)
  - ምዕራፍ 2- ስለ ፖለቲካ ፓርቲ ምዝገባ (አንቀፅ- 66-70)
  - ምዕራፍ 3- የፖለቲካ ፓርቲ ሰነዶች (አንቀፅ 71-74)
  - ምዕራፍ 4- የፖለቲካ ፓርቲ መብትና ግዴታ (አንቀፅ- 75-86)
  - ምዕራፍ 5- የፖለቲካ ፓርቲ አባላት መብትና ግዴታ(አንቀፅ- 87-90)
  - ምዕራፍ 6- ስለ ፖለቲካ ፓርቲ መዋሃድ፣ ግንባር መፍጠር፣ መቀናጀት እና መተካት (አንቀፅ- 91-95)
  - ምዕራፍ 7 -የፖለቲካ ፓርቲ መሰረዝ ወይም መፍረስ (አንቀፅ 96-99)
  - ምዕራፍ 8- ስለ ፖለቲካ ፓርቲ የገቢ ምንጭና የንብረት ሁኔታ (አንቀፅ 100-113)
    - ንዑስ ክፍል 1- ከመንግስት ስለሚሰጥ ድጋፍ (አንቀፅ 100-107)
    - ንዑስ ክፍል 2- የገቢ ምንጭ (አንቀፅ 108-110)
    - ንዑስ ክፍል 3- ስለ ማህደር፣ ሂሳብ አያያዝና ቁጥጥር (አንቀፅ- 111-113)
- <u>**ክፍል 5- ስለ-ምርጫ ታዛቢዎች፣ የምርጫ ወኪሎች፣ ጋዜጠኞችና የምርጫ ትምህርት አሰጣጥ**</u>
  - አንቀፅ- 114-126
- <u>**ክፍል 6- የምርጫ ስነ-ምግባር**</u>
  - ምዕራፍ 1- የምርጫ ስነ-ምግባር ድንጋጌዎች (አንቀፅ- 127-137)
  - ምዕራፍ 2- የባለ ድርሻ አካላት የምርጫ ሀላፊነት (አንቀፅ 138-141)
  - ምዕራፍ 3- የስነ-ምግባር ጥሰትና ስለ ሚወሰዱ እርምጃዎች (አንቀፅ 142-147)
    - ንዑስ ክፍል 2- በተለያዩ አካላት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች (አንቀፅ 148-150)
- <u>**ክፍል ሰባት- በምርጫ ሂደት ስለሚነሱ አቤቱታዎችና እርምጃዎች (አንቀፅ 151-155)**</u>

- <u>**ክፍል ስምንት - የተከለከሉ ተግባራት (አንቀፅ 156-159)**</u>

- <u>**ክፍል ዘጠኝ- ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች (አንቀፅ 160-164)**</u>

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፺፯
አዲስ አበባ ጥቅምት ፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 97
ADDIS ABABA 16th October, 2019

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፪/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነምግባር አዋጅ............ገጽ ፲፩ሺ፰፻፸፫

## Content

Proclamation No. 1162/2019

The Ethiopian Electoral, Political Parties Registration and Election's Code of Conduct Proclamation …...Page 11873

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፪/፪ሺ፲፩

## የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነምግባር አዋጅ

ኢትዮጵያዊያን በማንኛውም ሁኔታ ልዩነት ሳይደረግባቸው በቀጥታ እና በነፃነት በመረጧቸው ተወካዮች አማካኝነት ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ስልጣናቸውን በተግባር ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ፤

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በየደረጃው በሚደረጉ ሁሉን አቀፍ ነፃ፣ ፍትሃዊና ሰላማዊ ምርጫዎች በእኩልነትና በነጻነት በሚስጢር ድምፅ አሰጣጥ ፈቃዱን በመግለጽ የመሳተፍ መብቱን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ማንኛውም የምርጫ እንቅስቃሴ ዓለም አቀፍ የምርጫ መርሆዎችን አካትቶ በያዘ ህግ እንዲመራ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያየ ዓላማና አመለካከታቸውን በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ ለመራጩ ሕዝብ በመግለጽ የሚሳተፉበት፣ መራጩ ሕዝብም በመረጃ ላይ በመመስረት ፈቃዱን በነፃነት በመግለፅ ወኪሎቹን የሚመርጥበት የምርጫ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ዜጎች በሚመሠርቱት ወይም በአባልነት በሚቀላቀሉት የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ የሚኖራቸውን መብትና ግዴታ፥ እንዲሁም ፓርቲው ሕጋዊ ሰውነት

Proclamation No. 1162/2019

## THE ETHIOPIAN ELECTORAL, POLITICAL PARTIES REGRISTATION, AND ELECTION'S CODE OF CONDUCT PROCLAMATION

**WHEREAS,** it has become necessary to enable all Ethiopians to exercise their right to self-administration, without any discrimination, through their representatives elected in a direct and free election;

**WHEREAS,** it has become necessary to ensure the participation of every Ethiopian in an all-inclusive, fair and peaceful elections held at every level on the basis of equal popular suffrage in which Ethiopians freely express their will in a secret ballot;

**WHEREAS,** it has become necessary that any electoral activity shall be guided by an electoral law that meets international election standards;

**WHEREAS,** it has become necessary to establish an electoral system that enables political parties with different views to participate by expressing their opinions to the electorate in a lawful and peaceful manner, and that enables the people to elect their representatives based on informed decisions and free expression of their will;

**WHEREAS,** it is necessary to provide the right and duty of citizens who form political parties or become members of political parties, and to determine mechanisms for parties to obtain legal personality and

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

የሚያገኙበትን ሁኔታ እና በድርጅትነት ሲንቀሳቀስ መከተልና ማክበር ያለበትን መሠረታዊ መርሆች መደንገግ በማስፈለጉ፤

የፖለቲካ ፓርቲዎች በመዋሀድ፣ ግንባር በመፍጠር ወይም በመቀናጀት ሊንቀሳቀሱ የሚችሉበትን ሁኔታ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ለፍትሃዊ፣ ሰላማዊ፣ ነፃና ዴሞክራሲያዊ የምርጫ ሥርዓት መስፈን በምርጫ የሚሣተፉ የፖለቲካ ድርጅቶችና የግል ዕጩዎች ገንቢ አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን ግልፅ አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ምርጫዎች በመልካም ሥነ ምግባር የሚመሩ ነጻ፣ ፍትሃዊ ፣ሰላማዊ፣ ሕጋዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆኑና እንዲሁም በህዝብ ዘንድ ተቀባይነትን እንዲያገኙ ለማድረግ በምርጫ ወቅት የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ እጩዎች፣ አባላት እና ደጋፊዎች የሚመሩባቸውን የሥነ ምግባር መርሆች መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በምርጫ ሂደት ለሚነሱ አለመግባባቶች አስተዳደራዊ እና የዳኝነት መፍትሔ የሚሰጡ ተቋማትን እና አሰራራቸውን መወሰን በማስፈለጉ፤

በገለልተኝነት ምርጫን እንዲያስፈጽም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፫/፪ሺ፲፩ መልሶ መቋቋሙን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል:-

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነምግባር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፪/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ:-

፩/ "ኢ.ፌ.ዴ.ሪ" ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ነው፡፡

፪/ "ህገ መንግሥት" ወይም "ህገ-መንግሥታት" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግሥት ወይም የክልል ህገ መንግሥት ማለት ነው፡፡

provide basic principles to be followed by the parties in their operation as organizations;

**WHEREAS,** it is necessary to regulate the manner in which political parties can merge, establish fronts or form coalitions;

**WHEREAS,** it has become necessary to put in place a system that enables political parties and independent candidates contesting in elections to play a constructive role to ensure a fair, peaceful, free and democratic elections system;

**WHEREAS**, it is necessary to issue codes of conduct for political parties, candidates, members and supporters of political parties during the elections period so that the elections are guided by ethical behavior and are conducted in a free, peaceful, legal, democratic and credible manner;

**WHERES,** it has become necessary to establish institutions that give administrative and judicial decisions on electoral disputes and to determine their operational procedures;

**WHEREAS,** by considering the re-establishment of the National Electoral Board of Ethiopia under Proclamation No. 1133/2019 to administer elections impartially;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "The Ethiopian Electoral, Political Parties Registration and Election's Code of Conduct Proclamation No. 1162/2019."

### 2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this Proclamation:

1/ "FDRE" means the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

2/ "Constitution" or "Constitutions" means the Constitution of the FDRE or Regional Constitutions, respectively.

፫/ "ክልል" ማለት በህገ መንግሥቱ አንቀጽ ፵፯(፩) መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል አዲስ የአበባን እና የድሬዳዋን አስተዳደርን ይጨምራል፡፡

፬/ "ቦርድ" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፫/፪ሺ፲፩ መልሶ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፡፡

፭/ "ምርጫ" ማለት በፌደራልና በክልል ህገ መንግሥታት እንዲሁም በሌሎች አግባብ ባላቸው ህጎች መሠረት የሚካሄድ የጠቅላላ፣ የአካባቢ፣ የማሟያ ወይም የድጋሚ ምርጫ ነው፡፡

፮/ "ጠቅላላ ምርጫ" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት የሚካሄድ የህዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው፡፡

፯/ "የአካባቢ ምርጫ" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት የሚካሄድ የብሔረሰብ ዞን፣ የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማ፣ የክፍለ ከተማ ወይም የቀበሌ ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው፡፡

፰/ "ማሟያ ምርጫ" ማለት በመራጮች ውሳኔ ከምክር ቤት መነሳትን ጨምሮ በማንኛውም ምክንያት በየደረጃው የሚገኙ የተጓደሉ የምክር ቤት አባላት መቀመጫዎችን ለመሙላት የሚካሄድ ምርጫ ነው፡፡

፱/ "ድጋሚ ምርጫ" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፫/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፯(፲፮) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ቦርዱ የምርጫ ውጤቱ እንዲሰረዝ ሲወስን፤ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፶፬ መሰረት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ሲወስን፤ ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምፅ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን ለመለየት የሚካሄድ ምርጫ ነው፡፡

፲/ "ህዝበ ውሳኔ" ማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግሥት ወይም አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ሲወሰን የህዝብ ፍላጎትን ለመለካት ወይም የህዝብን ውሳኔ ለማወቅ የሚደረግ የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት ነው፡፡

፲፩/ "የመራጮች መዝገብ" ማለት በየደረጃው ለሚካሄድ ምርጫ መራጩ ህዝብ በምርጫ ጣቢያው በመራጭነት የሚመዘገብበት መዝገብ ነው፡፡

፲፪/ "የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ ማለት አንድ ሰው በመራጭነት ሲመዘገብ ከመዘገበው የምርጫ ጣቢያ የሚሰጠው የመራጭነት ማረጋገጫ ነው፡፡

3/ "Region" means regions established in accordance with Article 47(1) of the Constitution and, for the purposes of this Proclamation, shall include Addis Ababa and Dire Dawa City administrations.

4/ "Board" shall mean the National Electoral Board of Ethiopia re-established under Proclamation No. 1133/2019.

5/ "Election" means general elections, local elections, by-election or re-election conducted in accordance with the FDRE Constitution and Regional Constitutions and other relevant laws.

6/ "General elections" means the elections of members of the House of Peoples' Representatives and Regional State Councils conducted in accordance with relevant laws.

7/ "Local elections" means the elections of representatives to nationalitie's Zone, Zone, Woreda, City or Sub-City or Kebele Councils conducted in accordance with relevant laws.

8/ "By-election" means elections conducted to fill in a vacant council member seat whose mandates are terminated due to recall or any other reason.

9/ "Re-election" means the rerun of an election upon cancellation of election result by the Board in accordance with the authority entrusted with it under Article 7(16) of Proclamation No. 1133/2019; upon the decision of the Federal Supreme Court to conduct a rerun election based on Article 154 of this Proclamation; or when candidates obtain equal number of votes and it is impossible to determine the winner.

10/ "Referendum" means voting conducted to assess the public interest or know the public's decision based on a decision made in accordance with the FDRE Constitution or other relevant laws.

11/ "Electoral Roll" means a record wherein voters are registered at polling stations to participate as voters for elections at all levels.

12/ "Voter Identification Card" means an identification card issued to a voter upon registration at a polling station.

፲፫/ “የፖለቲካ ፓርቲ” ወይም “የፖለቲካ ድርጅት” ማለት ዜጎች ተደራጅተው የሚመሠርቱት የፖለቲካ ፕሮግራም በማውጣት በሀገር አቀፍ፣ በክልል ወይም ከክልል በታች ባለ ደረጃ በምርጫ የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ በዚህ አዋጅ መሠረት ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ ተቋም ነው።

፲፬/ “የፖለቲካ ፓርቲ ሃላፊዎች” ማለት እንደሁኔታው የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ የሥራ አስፈጻሚ አባላት፣ ወይም በተመሳሳይ የሥልጣን ደረጃ ላይ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ናቸው፡፡

፲፭/ “የምርጫ ክልል” ማለት ለምርጫ አፈፃፀም እንዲያመች እና ህዝቡ ወኪሎቹን እንዲመርጥ በህግ መሠረት የሀገሪቱ ግዛት ተከፋፍሎ የሚደራጅ የምርጫ አካባቢ ነው፡፡

፲፮/ “የምርጫ ጣቢያ” ማለት በየደረጃው ለሚካሄዱ ምርጫዎች የመራጭ ምዝገባ የሚካሄድበት፣ መራጮች ድምፅ የሚሰጡበት እና የድምጽ ቆጠራ የሚካሄድበት ቦታ ነው፡፡

፲፯/ “የምርጫ አስፈፃሚ” ማለት በየደረጃው ምርጫን ለማስፈፀም በቦርዱ የሚመደብ ሰው ነው፡፡

፲፰/ “እጩ ተወዳዳሪ” ማለት በምርጫ ለመወዳደር በፖለቲካ ፓርቲ ወይም በግሉ የተመዘገበ ሰው ነው፡፡

፲፱/ “ታዛቢ” ማለት የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢና የውጭ የምርጫ ታዛቢዎችን ያካትታል፡፡

፳ “የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ” ማለት ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ከቦርዱ ፈቃድ አግኝቶ በወኪሉ አማካኝነት ምርጫን የሚታዘብ በህግ የተመዘገበ፣ ገለልተኛና ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ መንግሥታዊ ያልሆነ አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ነው፡፡

፳፩/ “የውጭ የምርጫ ታዛቢ” ማለት አገሪቱ በተቀበለቻቸው ስምምነቶች መሠረት፤ በመንግሥት ምርጫን እንዲታዘቡ የሚጋበዙ መንግሥታት ወይም ዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ፣ ክፍለ አህጉራዊ ተቋማት እንዲሁም በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ የሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ናቸው፡፡

፳፪/ **“ተቀማጭ ወኪል”** ማለት በምርጫ ለመወዳደር በተመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ ተወክሎ በምርጫ ክልልና በምርጫ ጣቢያ በመቀመጥ የምርጫ ሂደቱንና የወካዩን መብት መከበር የሚከታተል ሰው ነው፡፡

13/“Political Party” or “Political Organization" means an entity with a political program established by organized citizens and registered in accordance with this Proclamation to hold political power by contesting in elections at the National, Regional or Local levels.

14/“Political Party Leaders” means members of the executive committee, as appropriate, or political leaders who have similar executive-level authority.

15/“Constituency” means an electoral district established by dividing the nation's territories in accordance with the law and in a manner conducive for the election administration and for the people to elect their representatives.

16/ “Polling Station” means a place where voter registration, voting and counting of votes take place for various levels of elections.

17/“Election Officer” means a person assigned by the Board to administer elections at various levels.

18/“Candidate” means any person registered to compete in an election on behalf of a political party or independently.

19/ “Observer” includes both local and international observers.

20/ “Local Election Observer” means a legally registered, impartial and not-for-profit, non-Governmental Local Civil Society Organization which the Board has authorized, based on the organization’s request to observe elections through its representatives.

21/"International Election Observer" means a Foreign Government or International, Regional or Sub-Regional Organizations, or Governmental and Non-Governmental agencies operating in or out of the country and invited by the government to observe elections based on international treaties to which Ethiopia is a party.

22/ “Stationary Agent” means a person assigned by a political party or an independent candidate to a specific constituency or polling station to observe the election process on-site and ensure that the candidate’s rights are respected.

፳፫/ **"ተንቀሳቃሽ ወኪል"** ማለት በምርጫ ለመወዳደር በተመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት ወይም በግል እጩ ተወክሎ በአንድ ምርጫ ክልል ውስጥ በሚገኙ የምርጫ ጣቢያዎች እየተንቀሳቀሰ የምርጫ ሂደቱንና የወካዩን መብት መከበር የሚከታተል ሰው ነው፡፡

፳፬/ **"ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ"** ማለት በክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት፣ በምርጫ ክልል እና በምርጫ ጣቢያ ደረጃ ለሚነሱ ቅሬታዎች አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጥ በዚህ አዋጅ መሠረት ለምርጫ ወቅት የሚቋቋም ኮሚቴ ነው፡፡

፳፭/ "ውህደት" ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ በህግ የተመዘገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተናጠል ሕጋዊ ሰውነታቸውን በመተው አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ የሚመሰርቱበት ሂደት ነው፡፡

፳፮/ "ግንባር" ማለት ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተናጠል ሕጋዊ ህልውናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የጋራ የሆነ ስያሜ፣ የፖለቲካ ፕሮግራም እና መተዳደሪያ ደንብ ይዘው ለመንቀሳቀስ ሲወስኑ የሚመሠርቱት ድርጅት ነው፡፡

፳፯/ "መቀናጀት" ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተናጠል ሕጋዊ ሰውነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በምርጫ ወቅት ምርጫውን ለማሸነፍ ወይም ለሌላ መሰል ጊዜያዊ ዓላማ በጋራ ለመሥራት ተስማምተው የመቀናጀት የምስክር ወረቀት የሚያገኙበት ሁኔታ ነው፡፡

፳፰/ "መተካት" ማለት አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ነባር ስሙንና ፕሮግራሙን በመቀየር አዲስ ስምና ፕሮግራም በማዘጋጀት በዚሁ ስሙ እና ፕሮግራሙ እንዲታወቅ አስፈላጊውን መረጃ ለቦርዱ በማቅረብ በአዲስ የፖለቲካ ፓርቲነት የሚመዘገብበትና የሚንቀሳቀስበት ሁኔታ ነው፡፡

፳፱/ "የመንግሥት ሠራተኛ" ማለት በፌደራል ወይም በክልል መንግሥት መስሪያ ቤት ውስጥ በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ነው፡፡ ሆኖም ሚኒስተሮችን፣ ሚኒስቴር ዴኤታዎችን፣ እንዲሁም በተመሳሳይ ደረጃና ከዚያ በላይ የሆኑ የፌደራልና የክልል የመንግሥት ተሿሚዎችን፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትንና በየደረጃው ያሉ የክልል ምክር ቤት እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላትን አይጨምርም፡፡

፴/ "ሰው" ማለት ሕጋዊ ወይም የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡

፴፩/ በዚህ አዋጅ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

23/"Mobile Agent" means a person assigned by a political party or an independent candidate to observe the election process by moving around to different polling stations to ensure that the candidate's respect of rights.

24/ "Grievance Hearing Committee" means a committee established in accordance with this Proclamation during elections to render administrative decisions to complaints lodged at a Regional Branch Office, Constituency or Polling Station level.

25/"Merger" means the formation of a new party by two or more legally registered parties which have dissolved their distinct legal status.

26/"Front" means an alliance formed by two or more political parties following their agreement to have a common name, political program and by-laws without relinquishing their distinct legal status.

27/"Coalition" means a situation where two or more political parties secure coalition certificate during election with the purpose of winning election for a temporary purpose while maintaining their respective legal personalities.

28/"Substitution" means the replacement by a political party of its old name and program by new ones and it registers and operates under a new name when the request made to the Board is accepted following the submission of the required information.

29/"Civil Servant" means an individual who has been employed as a permanent staff by the federal or regional government offices; however, it does not include ministers, state ministers and other similar level appointments at the federal and regional level as well as members of the House of Peoples' Representatives, Regional Councils and House of Federation.

30/ "Person" means a legal or natural person.

31/ Provisions set out in the masculine gender in this Proclamation shall also apply to the feminine gender.

፫. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ:-

፩/ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚደረግ ጠቅላላ ምርጫ እንዲሁም እንደአግባብነቱ የአካባቢ ምርጫ፣ የማሟያ ምርጫ፣ የድጋሚ ምርጫ እና በህገ መንግሥቱ መሠረት በሚካሄድ ህዝበ ውሳኔ ላይ፤ እንዲሁም

፪/ የፖለቲካ ፓርቲ ለሚመሠርቱ ዜጎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና ኃላፊዎች፣ አባላት፣ ወኪሎች እና ተጠሪዎች፣ የፓርቲና የግል እጩ ተወዳዳሪዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር ወይም ውህደት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለምርጫ እና አስፈጻሚ አካላት
### ምዕራፍ አንድ
### የምርጫ ሥርዓት፣ መርሆች እና ዓይነቶች

፬. **<u>የምርጫ ሥርዓት</u>**

፩/ በፌደራል ህገ መንግሥት መሠረት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለሚደረግ ምርጫ በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሚወዳደሩት ዕጩዎች መካከል አብላጫ ድምጽ ያገኘው አሸናፊ ይሆናል። በክልል ህገ መንግሥታት መሠረት ለክልል ምክር ቤቶች የሚመረጡት ተወካዮች ከአንድ በላይ ሲሆኑ ከተወዳዳሪዎቹ መካከል በቅደም ተከተል አብላጫ ድምጽ ያገኙ ዕጩዎች አሸናፊ ይሆናሉ፡፡

፪/ የክልል ምክር ቤት አባላት ምርጫን የሚመለከቱ የክልል ህጎች በህገ መንግሥቱና በዚህ አዋጅ ከተቀመጡ ምርጫን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ጋር የተጣጣሙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

፭. **<u>የምርጫ መርሆዎች</u>**

፩/ ማንኛውም ምርጫ ሁሉን አቀፍ፣ ቀጥተኛ፣ በምስጢር ድምፅ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነፃነት የሚገልጽበት እና ያለ ምንም ልዩነት በሚደረግ ህዝባዊ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡

፪/ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብቱ በህግ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ያልተገደበ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ መምረጥ ወይም መመረጥ ይችላል፤ ሆኖም ለመምረጥም ሆነ ለመመረጥ አይገደድም፡፡

3. **<u>Scope of Application</u>**

This Proclamation shall be applicable to:

1/ All general elections conducted in Ethiopia and, as appropriate, local elections, by-election, re-election and referendum conducted in accordance with the Constitution; and

2/ Citizens who form a political party, political parties and their leaders, members, agents and representatives, party or independent candidates, and political parties' fronts, coalitions, or mergers.

## PART TWO
## ELECTIONS AND ELECTION ADMINISTRATION BODIES
### CHAPTER ONE
### ELECTORAL SYSTEMS, PRINCIPLES AND TYPES

4. **<u>Electoral System</u>**

1/ For the House of Peoples' Representatives' election, a candidate who gets the highest number of votes among the contestants shall be declared the winner in accordance with the FDRE Constitution, Where, in accordance with regional constitutions, more than one candidate is elected to regional councils, the candidates who get the highest number of votes shall, in the order of their votes, shall be declared winners.

2/ Regional elections laws that pertain to regional council elections shall be in accord with relevant elections provisions of the Constitution and this Proclamation.

5. **<u>Election Principles</u>**

1/ Any election shall be conducted based on universal suffrage and by direct and secret ballot through which the voters express their will freely without any discrimination and with popular participation.

2/ Any Ethiopian whose electoral rights have not been restricted by law or the decision of a court shall be eligible to vote or to be elected; however, he shall not be forced to vote or be elected.

፫/ እያንዳንዱ መራጭ የሚሰጠው ድምፅ እኩል ነው፡፡

፬/ እያንዳንዱ መራጭ ድምጽ መስጠት የሚችለው በአካል በመገኘት ነው፡፡

**፮. የምርጫ ዓይነቶች**

በኢትዮጵያ የሚካሄዱ የምርጫ ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፤

፩/ ጠቅላላ ምርጫ፤

፪/ የአካባቢ ምርጫ፤

፫/ ማሟያ ምርጫ፣

፬/ ድጋሚ ምርጫ፤

፭/ ህዝበ ውሳኔ፡፡

**፯. ጠቅላላ ምርጫ**

፩/ ጠቅላላ ምርጫ በየአምስት ዓመቱ የሚካሄድ የህዝብ ተወካዮች እና የክልል ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው፡፡

፪/ ጠቅላላ ምርጫ በመላ ሀገሪቱ በተመሳሳይ ጊዜ ይካሄዳል፡፡ ሆኖም ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እና ጉዳዩ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ውሳኔ ሲያገኝ በተለያየ ጊዜ እንዲካሄድ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፫/ ለኢ.ፌ.ደ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከአንድ የምርጫ ክልል አንድ ተወካይ ብቻ ይመረጣል፡፡

፬/ የክልል ምክር ቤቶች አባላት ቁጥር በየክልሉ ህግ መሠረት የሚወሰን ሆኖ ከአንድ የምርጫ ክልል ከአንድ ተወካይ በላይ ለክልል ምክር ቤቶች አባልነት ሊመረጥ ይችላል፡፡ ክልሎች የምክር ቤቶቻቸውን አባላት ቁጥር ለመቀየር የሚሰጡት ውሳኔ ከእጩዎች የምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ስድስት ወር አስቀድሞ መሆን ይኖርበታል፡፡

፭/ በህገ መንግሥቱ አንቀጽ ፷፩ (፫) መሠረት አንድ የክልል ምክር ቤት የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት በቀጥታ በህዝብ እንዲመረጡ ሲወስን ምርጫው ከጠቅላላ ምርጫ ጋር አንድ ላይ የሚካሄድ ይሆናል፡፡ ይህ ሲሆን የክልል ምክር ቤቱ ቀጣዩ ምርጫ ከመደረጉ ስድስት ወራት አስቀድሞ ውሳኔውን ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት።

**፰. የአካባቢ ምርጫ**

፩/ የአካባቢ ምርጫ በህግ በተደነገገው መሠረት በየደረጃው የሚካሄድ የብሔረሰብ ዞን፣ የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማ፣ የክፍለ ከተማ ወይም የቀበሌ ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው፡፡

3/ Each vote shall carry equal weight.

4/ Each person shall only be allowed to vote by appearing in person.

**6. Types of Election**

The following are the types of elections conducted in Ethiopia:

1/ General elections;

2/ Local elections;

3/ By-election;

4/ Re-election;

5/ Referendum.

**7. General Elections**

1/ General elections are elections of members of the House of Peoples' Representatives and Regional State Councils held every five years.

2/ General elections shall be conducted throughout the country simultaneously. However, if the Board deems it necessary, and when the issue is submitted to the House of Peoples' Representatives and is approved, the Board may decide to conduct them at different times.

3/ For the FDRE House of Peoples' Representatives, only one representative shall be elected from each constituency.

4/ The number of Regional Councils' members shall be determined by regional law and more than one representative may be elected from a constituency to the Regional Council. The region's decision to change the number of their council members shall take place six months prior to the commencement of candidates' registration.

5/ Where, a regional council decides, in accordance with Article 61(3) of the Constitution, for the election of members of the House of Federation by direct popular vote, the election shall be held simultaneously with the general elections. In this case, the regional council shall notify its decision to the Board six months prior to the next election day.

**8. Local Elections**

1/ Local elections are elections held at various levels, in accordance with the law, to elect council members of nationalitie's zone, zone, Woreda, city, sub-city or Kebele.

፪/ የአካባቢ ምርጫ ከአንድ ምርጫ ክልል በየደረጃው ለምክር ቤቶቹ የሚመረጡት ተወካዮች ቁጥር እያንዳንዱ ክልል በሚያወጣው ሕግ ይወሰናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፪) (መ) እና አንቀጽ ፶፩ (፲፭) መሠረት የአካባቢ ምርጫዎችን በተመለከተ ሁሉም ሊያደርጋቸው የሚገቡ መለኪያዎችን የሚያስቀምጥ ህግ ሊያወጣ ይችላል።

፬/ የአካባቢ ምርጫን የሚመለከቱ የክልል ህጎች በህገ መንግሥቱ እና በዚህ አዋጅ ከተቀመጡ ምርጫን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ጋር የተጣጣሙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

፭/ በዚህ አዋጅ ለጠቅላላ ምርጫ የተደነገገው እንደ አግባብነቱ በአካባቢ ምርጫ ላይም የሚፈጸም ሆኖ ቦርዱ በየደረጃው የምርጫ ክልሎች ወይም ጣቢያዎች አደረጃጀት፣ የምርጫ አስፈጻሚዎችና ታዛቢዎች አመዳደብ፣ የመራጭ እና የእጩዎችን ምዝገባ ቦታና ሂደት፣ የግል እጩ ተወዳዳሪዎች የድጋፍ ፊርማ ብዛት እና ሌሎች ጉዳዮችን ይህን አዋጅ መሠረት በማድረግ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል፡፡

**፱. የማሟያ ምርጫ**

፩/ የማሟያ ምርጫ የሚካሄደው:-

ሀ) በየደረጃው ያሉ ምክር ቤቶች በተለያየ ምክንያት የተጓደሉባቸው አባላት እንዲሟሉላቸው ለቦርዱ ጥያቄ ሲያቀርቡ፣ ወይም

ለ) ተፈጻሚነት ባለው ህግ መሠረት የቀረበ የይውረድልን ጥያቄ ተቀባይነት ሲያገኝ ነው፡፡

፪/ ቦርዱ ጥያቄው በደረሰው ስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የማሟያ ምርጫ ያካሂዳል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው ቢኖርም አንድ ምክር ቤት የሥራ ዘመኑ ሊጠናቀቅ የቀረው ጊዜ ስድስት ወርና ከዚያ በታች ከሆነ የማሟያ ምርጫ አይካሄድም፡፡

**፲. ድጋሚ ምርጫ**

፩/ ድጋሚ ምርጫ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊካሄድ ይችላል፣

ሀ) በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፫/፪ሺ፲፩ እና በዚህ አዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ቦርዱ የምርጫ ውጤት እንዲሰረዝና ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ሲወስን ወይም የፌደራል ጠቅላይ

2/ The number of representatives elected for councils at various level in a constituency for a local election shall be determined by regional laws.

3/ With out prejudice to the provision of sub-article (2) of this Article, the House of Peoples' Representatives may, in accordance with Article 55 (2) (d) and Article 51 (15) of the FDRE Constitution, pass a legislation related to local elections that sets standards applicable to these elections.

4/ Regional laws that pertain to local elections shall be in accordance with relevant elections provisions of the Constitution and this Proclamation.

5/ With out prejudice to the application of the provision of this Proclamation for general elections, as appropriate, to local elections; the Board shall, based on this Proclamation, issue a directive to determine the establishment of constituencies or polling stations, the assignment of polling officers and observers; voters and candidates' registration locations and processes; the the number of endorsement signatures for independent candidates and other matters.

**9. By-Election**

1/ By-election shall be conducted:

a) where councils at different levels request the Board to fill vacancies created for various reasons; or

b) where a recall request, lodged in accordance with the law, is accepted;

2/ The Board shall hold by-election within six months from receiving a request.

3/ Notwithstanding the provision of Sub-Articles (1) and (2) of this Article, no by-election shall be held to fill a vacancy of a council whose term ends within a period of six months or less.

**10. Re-Election**

1/ Re-election may be conducted for one of the following reasons:

a) When the Board decides to cancel an election result and order a re-election on the basis of the powers conferred on it by this Proclamation and Proclamation No.

ፍርድ ቤት በቀረበለት አቤቱታ ላይ ተመስርቶ የምርጫ መደገም ውጤትን የሚያስከትል ውሳኔ ሲወስን፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፩(፫) መሠረት እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምፅ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን መለየት ያልተቻለ እንደሆነ፡፡

፪/ ድጋሚ ምርጫ ሲካሄድ:-

ሀ) ሌላ አዲስ የመራጮች ምዝገባ ሳያስፈልግ በምርጫ ክልሉ ወይም ችግሩ በተከሰተባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ተመዝግበው በነበሩ መራጮች እንደገና ይካሄዳል፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) መሠረት ምርጫ እንዲካሄድ ሲወሰን አዲስ የእጩዎች ምዝገባ ሳያስፈልግ ቀድሞ በተመዘገቡ እጩዎች መካከል ብቻ ይደረጋል፤

ሐ) ለድጋሚ ምርጫ የምርጫ ቅስቀሳ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

፫/ የድጋሚ ምርጫ ዝርዝር አፈፃፀም ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፲፩. <u>ህዝበ ውሳኔ</u>**

፩/ ቦርዱ በህገ መንግሥቱ ወይም በሌሎች ህጎች መሠረት አግባብ ባለው አካል ሲወሰን የህዝብን ፍላጎት ለመለካት ወይም ለመወሰን ድምጽ እንዲሰጥ ህዝበ ውሳኔ የሚሰጥበትን ምርጫ ያዘጋጃል፡፡

፪/ ህዝበ ውሳኔው እንዲካሄድ ከወሰነው አካል ጋር በመመካከር ቦርዱ ህዝበ ውሳኔ ያስፈለገበትን ጉዳይ ለመለየት በሚያስችለው መልኩ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን በማደራጀት ህዝበ ውሳኔውን ያከናውናል፡፡

፫/ ቦርዱ በህገ መንግሥቱ ስልጣን ከተሰጠው አካል ጋር በመመካከር ድምጽ የሚሰጥበትን ቀን፣ በህዝበ ውሳኔው በድምጽ ሰጪነት ለመሳተፍ ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች በድምጽ መስጫ ወረቀቱ ላይ የሚሠፍረው ለውሳኔ የቀረበው አማራጭ አጻጻፍ እና የህዝበ ውሳኔውን አስመልክተው የሚደረጉ የቅስቀሳ ዓይነቶችን ይዘት ይወስናል።

፬/ ዝርዝር አፈፃፀሙ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

1133/2019; or when the Federal Supreme Court, based on a petition submitted to it, passes a decision that has the effect of a re-election;

b) Based on Article 61 (3) of this Proclamation, where two or more candidates get equal votes and it is impossible to determine the winner.

2/ In the event of a re-election:

a) Without the need for a new voter registration, it shall be conducted with only the voters who had registered previously in a constituency or polling stations where the irregularities occurred;

b) where it has been decided to conduct a re-election in accordance with the provision of Sub-Article (1) (a) of this Article, only those candidates registered previously shall be eligible to contest in the re-election without having to conduct new candidate registration;

c) campaigning shall be prohibited during the re-election period.

3/ The Particulars of re-election shall be determined by a directive to be issued by the Board.

**11. <u>Referendum</u>**

1/ When an appropriate body decides based on the constitution or other laws, the Board shall organize a referendum to assess public interest or know the decision of the public.

2/ The Board, in consultation with the body which decided the holding of the referendum, shall conduct the referendum by organizing polling stations in a way convenient to execute the referendum.

3/ The Board shall, in consultation with the constitutionally authorized body, determine the polling date, the voters' criteria to participate in a referendum, the choices to be put on the ballot paper and the types and contents of campaigns relating to a referendum.

4/ Details shall be determined by a directive to be issued by the Board.

## ምዕራፍ ሁለት

## የምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶች

**፲፪. ጠቅላላ**

በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፫/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፯ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ቦርዱ:-

፩/ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን በሁሉም ክልልሎችና ከዚያ በታች ባሉ የአስተዳደር እርከኖች ያደራጃል፡፡ እንደየክልሉ ሁኔታ በዞን ወይም በምርጫ ክልል እርከን የሚቋቋሙ ጽህፈት ቤቶች የሥነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት ይሰጣሉ፣ በእያንዳንዱ ጽሕፈት ቤት ውስጥ የሚቀመጥ ቋሚ የመራጮች መዝገብ ያደራጃሉ፤ በየጊዜው እያስተካከሉ የመረጃውን ወቅታዊነት እንዲጠበቅ ያደርጋሉ። የምርጫ ክልሎችን ለመወሰን ለሚደረጉ ጥናቶች ድጋፍ ይሰጣሉ፤ ሌሎች ለምርጫ የሚያስፈልጉ ዝግጅቶችና የማስተባበር ስራዎችን ያከናውናሉ፡፡ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ የምርጫ ክልሎችና የምርጫ ጣቢያዎችን በመላ አገሪቱ ያቋቁማል፡፡

**፲፫. የምርጫ ክልሎችን ስለማቋቋም**

፩/ ለጠቅላላ ምርጫ አፈፃፀም የሚያገለግሉ የምርጫ ክልሎች እንደሚከተለው ይደራጃሉ፡፡

ሀ) ለምርጫ አፈፃፀም ዓላማ የክልል መንግሥታት ድንበር እንደተጠበቀ ሆኖ አገሪቱ የወረዳ አስተዳደርን መሠረት በማድረግ የሚከፋፈሉ፥ በህዝብ ቆጠራ ውጤት መሠረት ማስተካከያ ሊደረግባቸው በሚችሉ ቋሚ የምርጫ ክልሎች ትከፋፈላለች፤

ለ) አገሪቱ እያንዳንዳቸው አንድ ተወካይ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚመረጥባቸው ከ፭፻፶ የማይበልጡ የምርጫ ክልሎች የሚኖሯት ሆኖ አከላለሉ የህዝብ ብዛትንና በልዩ ትኩረት ውክልና የሚሰጣቸው የህዝብ ብዛታቸው አነስተኛ የሆነ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ቁጥር መሠረት በማድረግ ይወሰናል። አነስተኛ የሕዝብ ብዛት ያላቸው ብሔረሰቦችና ህዝቦች የሚወከሉባቸውን የምርጫ ክልሎች ሳይጨምር ምርጫ ክልሎቹ ተቀራራቢ የሕዝብ ቁጥር ያላቸው ሆነው በመካከላቸው ያለው ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ልዩነት ከ፲፭ በመቶ መብለጥ የለበትም፤

## CHAPTER TWO

## ELECTION ADMINISTRATION LEVELS

**12. General**

The Board, in accordance with the powers bestowed on it by Article 7 of Proclamation No. 1133/2019, shall:

1/ Establish branch offices at regional and sub-regional levels. Depending on the circumstance of the region, zonal or constituency level branch offices may provide civic and voter education; prepare permanent voters' roll to be kept in each branch office; and periodically update information; support studies to determine constituencies and carries out other activities necessary for the preparation and coordination of election administration. The Board shall determine the in a directive.

2/ Establish constituencies and polling stations throughout the country.

**13. Establishing Constituencies**

1/ Constituencies serving for general elections shall be organized as follows:

a) For the purpose of holding elections, without affecting Regional States' Boundaries, the territories of the country shall be divided into permanent constituencies on the basis of Woreda administration, which may be re-arranged based on the census results;

b) The country shall have one representative per constituency to be elected to the House of Peoples' Representatives, where the total number of constituencies may not exceed 550; and the constituencies shall be determined on the basis of population and the number of minority nationalities and peoples with special representation. Except in the case of constituencies for the representation of minority nationalities and peoples, population of the constituencies shall be comparable and the highest number average population deviation between constituencies shall not exceed 15 percent;

ሐ) በህገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፬ መሠረት የተለየ ውክልና ያስፈልጋቸዋል ተብሎ የታመነባቸው ቁጥራቸው ከ፳ የማያንሱ የህዝብ ብዛታቸው አነስተኛ የሆነ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የሚወከሉባቸው የምርጫ ክልሎች ይኖራሉ፤

መ) የህዝብ ብዛታቸው አነስተኛ በመሆኑ የተለየ ውክልና የሚያስፈልጋቸው ብሔረሰቦች ማንነት እና ቁጥር ቀድሞ በሚዘጋጅ ግልፅ መስፈርት መሠረት በፌደሬሽን ምክር ቤት ይወሰናል፡፡ እነዚህን የምርጫ ክልሎች በሚመለከት ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፤

ሠ) የምርጫ ክልሎች ዝርዝር ቦርዱ በሚያቀርበው ጥናት መሠረት በፌዴሬሽን ምክር ቤት ከተወሰነ በኋላ የእጩዎች ምዝገባ ከሚጀመርበት እለት ፩፻፹ ቀናት አስቀድሞ ለህዝብ ይገለፃል፡፡

፪/ በየደረጃው የሚካሄዱ የአካባቢ ምርጫዎች በየክልሉ ህግ መሠረት ለየምክር ቤቱ የሚመረጡትን አባላት ቁጥርና የመራጩን ብዛት መሠረት ያደረጉ ተመጣጣኝ የምርጫ ክልሎች በማቋቋም ይከናወናሉ፡፡

፫. እያንዳንዱ የምርጫ ክልል እንደ አግባብነቱ በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፫/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፮ (፩) ላይ የተጠቀሱት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው እንደአስፈላጊነቱ ቦርዱ ሌሎች መስፈርቶችን ሊያወጣ ይችላል፤ ለስራ አመራር ቦርዱ አባልነት የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ፫ ሰዎችን የያዘ የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

፬/ ቦርዱ በእያንዳንዱ የምርጫ ክልል የአገር ውስጥ ወይም የውጭ ታዛቢ ተወካዮች በቋሚነት እንዲኖሩ ለማድረግ ጥረት ማድረግ አለበት።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚደረገው የምርጫ አስፈፃሚዎች ምልመላ እና ምደባ በምርጫ ክልሉ ለሚወዳደሩ የፓርቲና የግል ዕጩዎች ግልጽ እንዲሆን እና የምርጫ አስፈጻሚዎች ምልመላም የፆታ ተዋጽኦን የጠበቀ እንዲሆን ይደረጋል።

፮/ እያንዳንዱ ምርጫ ክልል ከህዝብ የሚመረጡ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የሚኖረው ሲሆን ኮሚቴው በምርጫ ክልሉ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ያለድምፅ የሚሳተፍበት ሆኖ የየትኛውም የፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆኑ መልካም ሥነ ምግባር ያላቸው ሦስት አባላት ይኖሩታል፤ የፆታ ስብጥርን ታሳቢ ማድረግ አለበት።

c) There shall be constituencies for the representation of minority nationalities and peoples whose number is not less than 20 and which are deemed to require special representation in accordance with Article 54 of the Constitution;

d) Minority nationalities which are deemed to require special representation shall be determined by the House of Federation based on clear criteria established in advance. The Board may issue a directive pertaining to these constituencies;

e) Once the list of constituencies is decided by the House of Federation based on the study submitted by the Board, it shall be announced to the public 180 days before the commencement of candidate registration.

2/ Local elections held at different levels shall be conducted by establishing proportional constituencies in accordance with the region's laws and based on the number of council seats and the voters.

3/ Notwithstanding the criteria set out under Sub-Article (1) of Article 6 of Proclamation No. 1133/2019, the Board, as appropriate, may establish other criteria. Each constituency shall have a three-member Election Administration Committee that fulfills the criteria for membership of the Management Board.

4/ The Board shall make an effort to allocate in every constituency a stationary local or international observer.

5/ The recruitment and assignment process for election officials conducted in accordance with Sub-Article (3) of this Article shall be transparent to political parties and independent candidates contesting in the constituency; and the recruitment of election officials shall ensure gender representation.

6/ Each constituency shall have a Grievance Hearing Committee selected from the public, and this Committee shall include a constituency election executive member as a non-voter and shall have three members who are not members of any political party and who are known for their integrity; and shall consider gender representation.

፯. የምርጫ አስፈፃሚ እና አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባላትን አመራረጥና ሌሎች የዚህን አንቀጽ አፈጻጸም በሚመለከት ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

**፲፬. የምርጫ ክልል ስልጣንና ተግባራት**

እያንዳንዱ የምርጫ ክልል የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩/ ቦርዱ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት:-

ሀ) የምርጫ ቁሳቁሶችን ለምርጫ ጣቢያዎች ያሰራጫል፤

ለ) ዕጩዎችን ይመዘግባል፣ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ዕጩዎች የመታወቂያ ካርድ ይሰጣል፡፡

፪/ ከምርጫ ጣቢያዎች የሚመጡ ሰነዶችና የምርጫ ቁሳቁሶች በአግባቡ ተሞልተው መምጣታቸውን ያረጋግጣል፣ ይረከባል፣ በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል፤

፫/ ምርጫ ጣቢያዎች ተግባራቸውን በአግባቡ ማከናወናቸውን ይቆጣጠራል፤

፬/ በህግ መሠረት ለሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ውሳኔ ይሰጣል፤

፭/ ከምርጫ ጣቢያ የመጡ የምርጫ ውጤቶችን በመደመር አሸናፊዎችን ከለየ በኋላ ጊዜአዊ ውጤት ለህዝብ ይፋ በማድረግ አስፈላጊ ቅጾችን በመሙላት ለቦርዱ ይልካል፤

፮/ የዕጩ ወኪሎችን ዝርዝር ለምርጫ ጣቢያዎች ያስተላልፋል፤

፯/ የምርጫ ክልሉን ሦስት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባላትን በዚህ አዋጅና ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ያስመርጣል፤

፰/ በምርጫ ክልሉ የሚወዳደሩ የፖለቲካ ድርጅቶችን የጋራ ምክክር ያስተባብራል፤

፱/ የምርጫ ሂደትንና ውጤትን በተመለከተ ከምርጫ ጣቢያ ለሚመጡ አቤቱታዎች አፋጣኝ ምላሽ ወይም ውሳኔ ይሰጣል፤

፲/ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የተመራጭነት መታወቂያ ለአሸናፊዎች ይሰጣል፤

፲፩/ ከቦርዱ ወይም ከክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**፲፭. የምርጫ ጣቢያዎች ስለማቋቋም**

፩/ የምርጫ ጣቢያዎች ቦርዱ የአካል ጉዳተኞችን ልዩ ሁኔታ ጨምሮ የተለያዩ ታሳቢዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት በሚወስነው ስፍራ

7/ The Board shall issue a directive pertaining to the selection of members of election administration and Grievance Hearing Committee and the implementation of this provision.

**14. Power and Duties of the Constituency**

Each constituency shall have the following power and duties:

1/ Based on the timetable issued by the Board

a) distribute election materials to polling stations

b) register candidates and issue identity card to candidates to those who fulfill the criteria.

2/ Ascertain that documents and election materials that come from polling stations are properly filled; receive and securely keep these items;

3/ Supervise the proper functioning of polling stations;

4/ Decide on grievances and complaints submitted in accordance with the law;

5/ Determine winners by adding up results collected from polling stations, announce to the public the provisional results and complete necessary forms and submit same to the Board;

6/ Dispatch the list of candidates' agents to polling stations;

7/ Oversee the elections of three members of the constituency Grievance Hearing Committee in accordance with this Proclamation and a directive to be issued by the Board;

8/ Coordinate joint consultation of political parties contesting in the constituency;

9/ Provide quick response or decisions on complaints coming from polling station pertaining to the election process and result;

10/Issue identification cards to winners of the election in accordance with a directive to be issued by the Board;

11/Perform other duties assigned by the Board or the Regional Branch Office.

**15. Establishment of Polling Stations**

1/ The Board shall establish polling stations at locations that take into consideration the special conditions of the disabled and other factors, and

የሚቋቋሙ ሲሆን፤ አድራሻውም ለህዝብ የመራጮች ምዝገባ ከመጀመሩ ፲፭ ቀናት አስቀድሞ በይፋ መገለጽ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ቦርዱ በተለይ በአርብቶ አደር አካባቢዎች የአርብቶ አደሩን ህዝብ አኗኗር መነሻ በማድረግ ተንቀሳቃሽ የምርጫ ጣቢያዎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ የሕዝቡን የእንቅስቃሴ አቅጣጫ ተከትሎ የሚሰየሙትን ጣቢያዎች አድራሻ አስቀድሞ ለሕዝቡ መገለጽ አለበት።

፫/ በይፋ ለሕዝብ የተገለጹ የምርጫ ጣቢያዎች የመራጮች ምዝገባ፣ የድምፅ መስጫ እና የቆጠራ ሥራዎችን የሚስተናገድባቸው ብቸኛ ስፍራዎች ናቸው።

፬/ ቦርዱ ለምርጫው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የምርጫ ጣቢያ ቦታዎችን ሊለዋውጥ ይችላል፡፡ ለውጡንም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለህዝብ እና ለተወዳዳሪዎች ይፋ መደረግ አለበት፡፡

፭/ ወታደራዊ ካምፖች፣ የፖሊስ ጣቢያዎች፣ ቤተክርስትያናትና መስጊዶች፣ ሆስፒታሎች፣ መጠጥ ቤቶች፣ የፖለቲካ ወይም የሀይማኖት ድርጅቶች ህንፃዎች፣ የግል መኖሪያ ቤቶች የምርጫ ምዝገባና የድምፅ መስጫ ሥፍራ በመሆን ሊያገለግሉ አይችሉም፡፡

፮/ እያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ የሚያስተናግደው የመራጮች ብዛት ከ፩ሺ፭፻ መብለጥ የለበትም፡፡

፯/ ለአንድ የምርጫ ጣብያ በተከለለ አካባቢ ከአንድ የምርጫ ጣቢያ በላይ ማቋቋም አይቻልም፡፡

፰/ እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ እንደአግባብነቱ በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፫/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፮(፩) ለቦርድ አባላት ምልመላ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ አምስት የምርጫ አስፈፃሚዎችን በአባልነት የያዘ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡ የምርጫ ጣቢያው ሃላፊ ኮሚቴውን በሰብሳቢነት ይመራል፡፡

፱/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፰) መሠረት የሚደረገው የምርጫ አስፈፃሚዎች ምልመላ ፆታዊ ውክልናን ታሳቢ በማድረግ እንዲከናወን ሂደቱም በምርጫ ክልሉ የሚወዳደሩ ፖለቲካ ፓርቲዎችና የግል ተወዳዳሪዎች እንዲያውቁት መደረግ አለበት።

the address of the polling stations shall be announced to the public 15 days prior to the commencement of voter registration.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the Board may establish mobile polling stations based on the lifestyle of pastoral communities. In this case, the Board shall announce to the public the address of the polling stations established based on the movement pattern of the pastoralists.

3/ The polling stations announced to the public shall serve as the only locations where voter registration, casting and counting of votes take place.

4/ The Board may, if it deems necessary for the election, change the location of polling stations. The public and candidates shall be notified of the changes in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

5/ Military camps, police stations, churches, mosques, hospitals, premises where alcoholic drinks are sold, buildings occupied by political or religious organizations and private residences shall not serve as a place where voter registration and voting take place.

6/ The number of voters assigned to each polling station shall not exceed 1500.

7/ There shall not be more than one polling station in an area designated for one polling station.

8/ Each polling station shall, as appropriate, have a committee comprised of five electoral officers who fulfill the criteria set out in Article 6 (1) of Proclamation No. 1133/2019. The head of the polling station shall chair the committee.

9/ The recruitment of election officials conducted in accordance with Sub-Article (8) of this Article shall consider gender representation and the process shall be made known to political parties and independent candidates contesting in the constituency.

፲/ እያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ በምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በሚመደብ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ሰብሳቢነት የሚመራ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይኖረዋል፤ ኮሚቴው ከሰብሳቢው በተጨማሪ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በምርጫ ክልሉ ከተመዘገቡ መራጮች መካከል የሚመረጡ፤ የማንም ፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆኑና በመልካም ሥነ ምግባራቸውና ሰብእናቸው የታወቁ አንድ ወንድ እና አንድ ሴት አባላት ይኖሩታል፡፡ ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፲፩/ ቦርዱ በእያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ ቢያንስ አንድ የሃገር ውስጥ ወይም የውጭ ታዛቢ በቋሚነት እንዲገኙ ጥረት ያደረጋል። የታዛቢዎቹ ስብጥር በተቻለ መጠን ፆታዊ ስብጥርን ታሳቢ ሊያደርግ ይገባል።

**፲፮. <u>የምርጫ ጣቢያ ስልጣንና ተግባራት</u>**

እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያና የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የሚያከናውናቸው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩/ መራጮችን ይመዘግባል፤

፪/ ከምርጫ ክልሉ የሚላኩ የምርጫ ቁሳቁሶችን ተቀብሎ በጥንቃቄ ይይዛል፤

፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ ምርጫ ያካሂዳል፣

፬/ በህጉ መሠረት የሚቀርቡለትን ቅሬታዎች ያስተናግዳል፣

፭/ የተሰጠውን የድምፅ ቆጠራ በማካሄድ ጊዜአዊ የምርጫ ውጤት በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ ለህዝብ ያሳውቃል፣

፮/ የምርጫ ሰነዶችና ቁሳቁሶች በአግባቡ ተሞልተው እና ተጠብቀው ለምርጫ ክልሉ እንዲላኩ ያደርጋል፣

፯/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ (፲) እና ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የምርጫ ጣቢያውን አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ሁለት አባላት ያስመርጣል፣

፰/ በምርጫ ሂደት ለሚከሰቱ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ፈጣን ምላሽ ይሰጣል፤ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣

፱/ ከቦርዱ፣ ከክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ ወይም ከምርጫ ክልል የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

10/ Each polling station shall have a Grievance Hearing Committee that is chaired by a member of the Elections Administration Committee selected by the head of the polling station; in addition to the chair, the Grievance Hearing Committee, based on a directive to be issued by the Board, shall have two members, selected from registered voters in the constituency, who are not members of any political party and known to have good ethics and integrity, and shall include one man and one woman. The Board shall determine the in a directive.

11/ The Board shall make an effort to assign at least one stationary local or international observer in each polling station. The allocation of observers shall consider gender representation.

**16. <u>Powers and Duties of Polling Stations</u>**

Each polling station shall have, in accordance with the directive and timetable issued by the Board, the following powers and duties:

1/ Register voters;

2/ Keep election materials dispatched from the constituency;

3/ Conduct elections that protects the secrecy of the ballot in accordance with this Proclamation;

4/ Entertain complaints submitted in accordance with the law;

5/ Count votes and announce provisional results to the public by posting on a notice board;

6/ Ensure proper completion, safeguarding and dispatching of election documents and materials to the constituency;

7/ Cause the selection of two members of the polling station Grievance Hearing Committee in accordance with Article 15 (10) of this Proclamation;

8/ Provide quick responses to grievances and complaints relating to electoral processes and take corrective measures.

9/ Perform other duties assigned by the Board, the Regional Branch Office or the Constituency Electoral Office.

**፲፯. በልዩ ሁኔታ የሚቋቋም የምርጫ ጣቢያ**

፩/ ቦርዱ ከምርጫ ክልላቸው ርቀው በካምፕ የሚኖሩ ወታደሮች፣ ሲቪል ሰራተኞች እና ቤተሰቦቻቸው፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ዜጎች፣ ከመኖሪያ ቀያቸው የተፈናቀሉ ዜጎች እንዲሁም በእስር ቤት የሚገኙ የመምረጥ መብታቸው ያልተገፈፈ ዜጎች በምርጫ የሚሳተፉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት መራጮቹ በሚገኙበት ቦታ ወይም አካባቢ ልዩ ምርጫ ጣቢያ ሊያቋቁም ይችላል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት መራጮች ድምፅ የሚሰጡበትን ቦታ፣ ድምጻቸው የሚቆጠርበትን የምርጫ ክልል እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል፡፡

፪/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱት መራጮች ከምርጫው ቀን ቀደም ብለው እንዲመዘገቡና ድምጽ እንዲሰጡ በመወሰን በምርጫ የጊዜ ሰሌዳው ውስጥ ሊያካትት ይችላል፡፡

፫/ ቦርዱ በውጭ ሃገር በመኖራቸው ወይም በሌላ ምክንያት በአካባቢያቸው መምረጥ ለማይችሉ ዜጎች በምርጫ የሚሳተፉበት ልዩ ሥርዓት የሚዘረጋበትን መንገድ አጥንቶ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለውሳኔ ያቀርባል፡፡

፬/ ዝርዝር አፈፃፀሙ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለምርጫ አፈጻጸም
## ምዕራፍ አንድ
## የመራጮች ምዝገባ

**፲፰. በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያበቁ መመዘኛዎች**

፩/ ማንኛውም ሰው:-

ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜጋ ከሆነ፤

ለ) በምዝገባው ዕለት ዕድሜው ፲፰ ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆነ፤

ሐ)በምርጫ ክልሉ ቢያንስ ስድስት ወር የኖረ ከሆነ፣

በመራጭነት ሊመዘገብይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተቀመጡት መስፈርቶች መሟላታቸው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩ መሠረት የሚረጋገጥ ይሆናል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ከዚህ በታች የተመለከቱት በመራጭነት ሊመዘገቡ አይችሉም፡፡

**17. Special Polling Stations**

1/ The Board may, for the purpose of enfranchising those living far from their constituency, establish special polling stations at or near the place where the voters are to be found: military who live in camps; civil servants and their family members; citizens attending higher learning institutions; internally displaced citizens; incarcerated citizens whose voting rights have not been stripped off. The Board shall determine the particulars in a directive for these voters, including the place where they will vote, the constituency where their votes are to be counted and other related matters.

2/ The Board, for the voters mentioned in Sub-Article (1) of this Article, may decide to allow them to register and vote earlier than the election day and incorporate the details in the election timetable.

3/ The Board shall conduct a study and submit same to the House of Peoples' Representatives for a decision on a special procedure to enfranchise citizens residing abroad or for those who cannot vote in their residence for other reasons.

4/ Implementation details shall be determined by a directive to be issued by the Board.

## PART THREE
## ELECTIONS ADMINISTRATION
## CHAPTER ONE
## VOTERS REGISTRATION

**18. Voter Registration Requirements**

1/ Any person may be registered as a voter, who:

a) is an Ethiopian citizen;

b) is 18 years old and above on the day of registration; and

c) has been residing within the constituency for at least 6 months.

2/ The fulfilment of the requirements listed under Sub-Article (1) of this Article shall be verified based on Article 21 of this Proclamation.

3/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the following shall not be eligible to register as a voter:

ሀ) በአዕምሮ ህመም ምክንያት የመወሰን አቅም የሌለው መሆኑ ስልጣን ባለው አካል ወይም በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠበት ሰው፤

ለ) የመምረጥ መብቱ በህግ ወይም አግባብ ባለው ህግ መሠረት በፍርድ ቤት ውሳኔ የተገደበበት ሰው፡፡

## ፲፱. የምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ

፩/ የጠቅላላ ምርጫ ምዝገባ በአገር አቀፍ ደረጃ ቦርዱ በሚወስናቸው ቀናት የሚጀመርና የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡ ቦርዱ የምዝገባ ቀናቱን ከመወሰኑ በፊት በምርጫው የሚሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ያማክራል፡፡

፪/ ቦርዱ የመራጮች ምዝገባ የሚጀመርበትን ዕለት በምርጫ የጊዜ ሰሌዳው በማካተት ምዝገባው ከመጀመሩ ከ፲፭ ቀን በፊት ጀምሮ በተከታታይ በመገናኛ ብዙሃንና በማስታወቂያዎች አማካኝነት ለህዝቡ ይገልፃል፡፡

፫/ ቦርዱ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም ልዩ የምዝገባ ቀን ሊወስን ይችላል፡፡

፬/ **ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ በማጋጠሙ ምክንያት የምዝገባ ጊዜ ያለፈበት ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያስችለውን መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በልዩ ሁኔታ ሊመዘገብ ይችላል፡፡**

፭/ ቦርዱ የአካባቢ ምርጫዎችን የምዝገባ ጊዜ ሰሌዳ የሚመለከተውን ክልል ህገ መንግሥት ወይም ሌሎች ተፈጻሚነት ያላቸውን ህጎች መነሻ በማድረግ ያወጣል፡፡ በጊዜ ሰሌዳው ዝግጅትን በተመለከተ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ይመካከራል፡፡

## ፳. የምዝገባ ቦታ

፩/ የመራጭ ምዝገባ በእያንዳንዱ ቀበሌ ውስጥ በሚቋቋሙና መራጮች ሂደው በሚመዘገቡባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ብቻ ይከናወናል፡፡ ከምርጫ ጣቢያው ውጭ ቤት ለቤት እየዞሩ ወይም በየመንገዱ እየተዘዋወሩ ምዝገባ ማከናወን የተከለከለ ነው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በአርብቶ አደሮች አካባቢ እንደ አስፈላጊነቱ ተንቀሳቃሽ የምዝገባ ጣቢያ በማቋቋም ወይም ቤት ለቤት በመሄድ የመራጮች ምዝገባ ማከናወን ይቻላል፡፡

፫/ እያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ የራሱ የመራጮች መዝገብ ይኖረዋል፡፡

a) A person who is proved to be incapable of making decisions due to mental disorder as confirmed by the relevant authority or sufficient evidence;

b) A person whose voting rights have been restricted by the decision of a court of law based on law or relevant law.

## 19. Registration Timetable

1/ Nationwide voter registration for general elections shall commence and conclude on dates fixed by the Board. The Board shall, before fixing the dates for registration, consult political parties contesting in the elections.

2/ The Board shall indicate the voter registration commencement date in its election timetable and continually announce the date to the public through mass media and advertisements 15 days prior to the commencement of the registration.

3/ The Board may decide a special registration date in case of force majeure.

4/ A person who fulfills the voter registration requirements under this Proclamation but was unable to register because of force majeure may be able to register in a special condition based on the directive to be issued by the Board.

5/ The Board shall issue voter registration timetable for local elections based on the Regional Constitution or other applicable laws. Preparation of the timetable shall be done in consultation with political parties.

## 20. Place of Registration

1/ Voter registration shall be conducted only at the polling stations established to register voters. It is prohibited to conduct registration outside the polling station, by going door-to-door or moving around.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, in pastoralist areas, voter registration may be conducted by establishing mobile registration stations or conducting door-to-door voter registration as necessary.

3/ Each polling station shall have its own Electoral Roll.

## ፳፩. የአመዘጋገብ ሥርዓት

፩/ ተመዝጋቢው በሚኖርበት የምርጫ ጣቢያ ማንነቱን የሚገልፅ የቀበሌ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት በመያዝ ለመመዝገብ ይችላል፡፡

፪/ የቀበሌ መታወቂያ ካርዱ ወይም ፓስፖርቱ ያልታደሰ ቢሆንም እንኳን ለምዝገባ ሊያገለግል ይችላል፡፡

፫/ የቀበሌ መታወቂያ ካርድ ማቅረብ ካልተቻለ በቅርቡ ፎቶግራፍ ተደርጎበት የተሰጠ እንደ የመንጃ ፈቃድ፣ የመኖሪያ የምስክር ወረቀት፣ ከውትድርና የተገለለበት ሰነድ፣ የትምህርት ቤት መታወቂያ የመሳሰሉ የመለያ ማስረጃዎች በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያስችሉ ሰነዶች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

፬/ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የመለያ ማስረጃዎች በማይኖሩበት ወቅት መዝጋቢዎች መራጩን ለይተው የሚያውቁት ከሆነ ወይም በገጠር አካባቢ ሲሆን በባህላዊና ልማዳዊ ዘዴ ተመዝጋቢውን ለመለየት የሚቻልበት ሁኔታ ካለ ቃለ ጉባኤ ተይዞ ምዝገባው ይከናወናል፡፡

፭/ የምርጫ ጣቢያው በተቋቋመበት ቀበሌ ኗሪ የሆኑ ለረዥም ጊዜ መኖራቸው የተረጋገጠ ሦስት ግለሰቦች ነዋሪዎች በሚሰጡት ምስክርነት ማስረጃ አልባውን ተመዝጋቢ ለመለየት ከተቻለ ሂደቱ በቃለ ጉባኤ ተይዞ ምዝገባው ሊከናወን ይችላል፡፡

**፮/ በዚህ አንቀጽ ከተመለከቱት ማረጋገጫ መስፈርቶች በአንዱ መስፈርት ብቻ የመራጩን የነዋሪነት ቆይታ ማረጋገጥ ያልተቻለ እንደሆነ መዝጋቢዎች ከአንድ በላይ መስፈርቶችን በመጠቀም ያረጋግጣሉ፡፡**

፯/ ለመመዝገብ ብቁ የሆኑና አቅም የሚያንሳቸው ሰዎች እና ዓይነስውራን በረዳቶቻቸው አማካኝነት በአካል ተገኝተው ሊመዘገቡ ይችላሉ፡፡

፰/ ለመራጭነት ብቁ የሆነ ሰው በተዘጋጀው የመራጮች መዝገብ ላይ ስሙ ይመዘገባል፡፡

፱/ በመራጭነት ለተመዘገበ ማንኛውም ሰው ሙሉ ስም ከነአያቱ፣ የሚኖርበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ የምርጫ ጣቢያ፣ የቤት ቁጥር፣ መንደር ወይም ጎጥ፣ የመዝገብ ቁጥር፣ የምዝገባ ተራ ቁጥር፣ የመዝገብ ገፅ፣ የመራጩ ፊርማ፣ የመዝጋቢው ፊርማ፣ የተመዘገበበት ቀን ተሞልቶ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ ይሰጠዋል፡፡

## 21. The Registration Procedure

1/ A voter may be registered in a polling station where he resides by producing a Kebele identification card or a passport that proves his identity.

2/ The Kebele identification card or passport, even if expired, may serve for the purpose of registration.

3/ In the absence of a Kebele identification card, evidence of identity bearing a recent photograph of the voter, such as a driving license, residence identification card, military discharge document or student identity card, shall be deemed to be sufficient document for registration purpose.

4/ In the absence of evidence of identity provided hereinabove, registration may be carried out: upon recognition of the voter's identity by the registration officers; or, in the case of rural areas, if the voter can be identified through traditional or customary means; and after the incident is recorded in the minutes.

5/ Undocumented voters can be registered based on the testimonies of three individuals, whose long residence in the Kebele where the polling station has been established has been proven and after this event has been recorded in the minutes.

6/ When the voter’s residency requirement cannot be established using one of the criteria stated in this Articles, the registration officers shall determine residency using more than one criterion.

7/ Eligible voters who are frail or blind can register in person with the assistance of their aid.

8/ The name of a person who is eligible to vote shall be entered the electoral roll.

9/ Any person duly registered as a voter shall be issued with a voter registration card bearing his full name including his grandfather’s, the region, zone, Woreda and Kebele where he resides, designated polling station, house number, village or locality, registration number, register’s serial number, electoral roll page, voter's signature, registrar's signature and date of registration.

፲/ የመራጮች ምዝገባ የሚከናወነው ከምርጫ አስፈጻሚዎች ቢያንስ ሦስቱ በጣቢያው ሲገኙ ነው፡፡

**፳፪.** <u>**የመራጮች መዝገብ ይዘት**</u>

የመራጮች መዝገብ በሚከተሉት አርዕስቶች ሥር መረጃ ለመሙላት የሚያስችሉ ዓምዶች ይኖሩታል:-

፩/ የምዝገባ ተራ ቁጥር፤

፪/ የምዝገባ ቀን፤

፫/ የተመዝጋቢው ሙሉ ስም ከነአያት፣

፬/ የትውልድ ቀን እና ዓ.ም፤

፭/ ዕድሜ፤

፮/ ፆታ፤

፯/ አካል ጉዳተኝነት፤

፰/ በምርጫ ክልሉ የኖረበት ጊዜ፣ (በወራት/በዓመት)፤

፱/ የምዝገባው ዕለት የፅህፈት ወይም የጣት ፊርማ፤

፲/ የምርጫ ዕለት የጽህፈት ወይም የጣት ፊርማ፤

፲፩/ የቤት ቁጥር/መንደር/ጎጥ/የቦታው ልዩ መጠሪያ፤

፲፪/ ልዩ አስተያየት/ምርመራ የሚሠፍርበት አምድ፣ በዚህ አምድ ጣቶች የሌሉት መራጭን አስመልክቶ ልዩ አስተያየት ይገለጽበታል፤

፲፫/ በልዩ ሁኔታ ለሚቋቋሙ የምርጫ ጣቢያዎች ከላይ ከተጠቀሱት መረጃዎች በተጨማሪ የመራጮቹ የተለዩ ሁኔታዎች የሚመዘገቡበት ዐምዶች፡፡

**፳፫.** <u>**የሰነዶች ስርጭትና ርክክብ**</u>

፩/ ቦርዱ በምርጫው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ለምዝገባ የሚያስፈልጉትን ሰነዶች በወቅቱ ለምርጫ ጣቢያዎች እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

፪/ ቃለ ጉባኤዎችን ጨምሮ በምዝገባ አገልግሎት ላይ የዋሉ ሰነዶች እና የመራጮች መዝገቦች ርክክብ ሥነ ሥርዓትና ጊዜ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

**፳፬.** <u>**አንድ ጊዜ እና በአንድ ቦታ ብቻ ስለመመዝገብ**</u>

፩/ ማንኛውም መራጭ በአንድ ምርጫ ጣቢያ ከአንድ ጊዜ በላይ መመዝገብ ወይም በሌላ የምርጫ ጣቢያ ድጋሚ መመዝገብ የለበትም፡፡

፪/ አንድ መራጭ አንድ የመራጭነት መታወቂያ ካርድ ብቻ ይኖረዋል፡፡

10/ Voter registration shall take place where a minimum of three of election officers are present.

**22.** <u>**Particulars of the Electoral Roll**</u>

The electoral roll shall have columns for entering the following particulars:

1/ Serial number of registrations;

2/ Registration date;

3/ Full name of voter, including grandfather's;

4/ Date and year of birth;

5/ Age;

6/ Gender;

7/ Disability;

8/ Duration of the residence within constituency (months/years);

9/ Signature or fingerprint on the day of registration;

10/ Signature or fingerprint on the day of voting;

11/ House number/village or locality/specific name of the area;

12/ A column to enter special remarks; in this column, a special remark shall be made for a voter who is missing all fingers;

13/ For special polling stations, besides the requirements listed above, a column to enter the voter's special conditions.

**23.** <u>**Distribution and Handover of Documents**</u>

1/ The Board, based on the election timetable, shall ensure the timely delivery of the necessary registration documents to polling stations.

2/ The timeline and procedure for the handover of documents used in registration and the electoral roll, including minutes, shall be determined based on a directive to be issued by the Board.

**24.** <u>**Registration Once and in One Place**</u>

1/ No voter shall be registered more than once in a polling station or in more than one polling station.

2/ A voter shall have only one voter's card.

፫/ ማንኛውም የመራጮች መታወቂያ ካርድ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት መራጭ ከድምፅ መስጫው እለት በፊት በማንኛውም የምርጫ ጣቢያው የሥራ ጊዜ ፣ በድምፅ መስጫው እለት ከሆነ ደግሞ ምርጫ ሰዓቱ ከመጠናቀቁ በፊት ለምርጫ ጣቢያው ሊያመለክት ይችላል፡፡ በምርጫ ጣቢያ ጽህፈት ቤቱም የአመልካቹ ማንነት ከመራጮች መዝገብ ጋር ተመሳክሮ እና ጉዳዩ በቃለ ጉባኤ ተይዞ በምትኩ ሌላ ካርድ ሊሰጠው ወይም ድምፅ እንዲሰጥ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

**፳፭. ስለመራጮች መዝገብ መዘጋት**

፩/ የቀኑ የምዝገባ ሥራ እንደተጠናቀቀ የመራጮች መዝገብ የዕለቱ የመጨረሻ ተመዝጋቢ ቁጥርና ቀኑን በተዘጋጀው የመፈራረሚያ ቅፅ ላይ ይሞላና የጣቢያው ምርጫ አስፈጻሚዎች ይፈራረሙበታል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተቀመጠው ሁኔታ የመራጮች ምዝገባ ወቅት እስኪጠናቀቅ ድረስ ምዝገባው ይቀጥላል፡፡ በምዝገባው የመጨረሻ ቀን በመዝገቡ ላይ ከመጨረሻው ተመዝጋቢ ቀጥሎ ባለው ክፍት ቦታ የጣቢያው ምርጫ አስፈጻሚዎች ተፈራርመውበት መዝገቡ ይዘጋል፡፡

፫/ ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር መዝገቡ ከተዘጋና ከተፈራረሙበት በኋላ በመዝገቡ ላይ አዲስ መራጭ አይመዘገብም የሚሰፍር ወይም የሚፃፍ ነገርም አይኖርም፡፡

**፳፮. የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ግልፅ ስለማድረግ**

፩/ የመራጮች ምዝገባ እንደተጠናቀቀ የመራጮች መዝገብ በምርጫ ጣቢያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ለ፲ ቀናት ይፋ ወጥቶ ህዝብ በግልፅ እንዲያየው መደረግ አለበት፡፡

፪/ በጣቢያው የሚወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች እንዲሁም የግል ተወዳዳሪዎች ወይም ተወካዮቻቸው ለምርጫ ጣቢያው ሃላፊ ጥያቄ በማቅረብ የመራጮችን መዝገብ መመልከት ይችላሉ፡፡

፫/ ምርጫው ከተጠናቀቀ በኋላ የመራጮች መዝገብ ወደ ቦርዱ ክልል ጽህፈት ቤት ወይም ለምርጫ ጣቢያው ቅርብ የሆነ የበታች እርከን የምርጫ ጽቤት ተወስዶ እንዲኖር መደረግ አለበት፡፡

3/ Any voter whose voter's card is lost or damaged may apply to the polling station during working hours prior to election day or before the end of voting hours if it is on election day. After verifying the identity of the voter against the voter register and recording the incident in the minutes, the voter may be issued a replacement card or allowed to vote.

**25. Closure of the Electoral Roll**

1/ Upon conclusion of each day's registration, the last registered voter's serial number and date shall be filled in the form prepared for this purpose and signed by polling station electoral officials.

2/ The registration procedures provided in Sub-Article (1) of this Article shall continue until the conclusion of the voter registration period. On the final day of the registration, the electoral officials, upon signing in the open space provided immediately after the last registered voter, shall close the electoral roll.

3/ Unless otherwise determined by the Board, once the electoral roll is closed, no new voter shall be registered; nothing shall be entered or written on it.

**26. Displaying the Electoral Roll to the Public**

1/ Upon conclusion of voter registration, the electoral roll shall be officially displayed to the public in the premises of the polling station for 10 days.

2/ Representatives of political parties or the independent candidates contesting in the polling station or their agents may inspect the electoral roll upon filing a request to the head of a polling station.

3/ At the end of the elections, the electoral roll shall be deposited in the Board’s regional branch office or a lower level elections office that is close to the polling station.

**፳፯. <u>የምዝገባ ተቃውሞን በተመለከተ</u>**

ማንኛውም ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት በመራጭ ምዝገባ ላይ ተቃውሞ ካለው ተቃውሞውን ከነምክንያቱ ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፶፪ መሰረት ይወስናል፡፡

**፳፰. <u>ከምዝገባ ስለመሰረዝ</u>**

፩/ ማንኛውም ተመዝጋቢ በአዕምሮ ህመም ምክንያት ለመወሰን ብቃት የሌለው መሆኑ ስልጣን ባለው አካል ወይም በበቂ ማስረጃ ካልተረጋገጠ ወይም በማጭበርበር የተመዘገበ ወይም በድጋሚ የተመዘገበ ወይም የሞተ ካልሆነ ወይም አግባብ ባለው ህግ መሠረት በተሰጠ የፍርድ ቤት ውሳኔ የመምረጥ መብቱ የተገደበ ካልሆነ በስተቀር በሚቀርብ ተቃውሞ ምክንያት ከመራጭነት ምዝገባ አይሰረዝም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ሲከሰት ፍርድ ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ እድሮች ወይም ሌሎች ስለጉዳዩ እውቀት ያላቸው የህብረተሰቡ አባላት ሁኔታው እንደተከሰተ በሁለት ቀናት ለቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ወይም ለምርጫ ክልል ወይም ለየምርጫ ጣቢያው ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

፫/ የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ወይም የምርጫ ክልሎች ወይም የምርጫ ጣቢያዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ማስረጃ እንደደረሳቸው በመራጭነት የተመዘገበው ሰው እንዲሰረዝ ማድረግ አለባቸው፡፡

**፳፱. <u>ቋሚ የመራጮች መዝገብ</u>**

፩/ ቦርዱ ለያንዳንዱ የምርጫ ክልል ቋሚ የመራጮች መዝገብ የሚዘጋጅበት እንዲሁም በየጊዜው የሚስተካከልበትና የሚከለስበት ሥርዓት እንዲኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪/ የመራጮች መዝገብ በክልልና ከዚያ በታች ባሉ እርከኖች በሚኖሩ የቦርዱ ጽህፈት ቤቶች በቦርዱ በሚሰየም ባለሙያ የሚመራና ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ተቋማት ጋር በመቀናጀት የሚዘጋጅና በየጊዜው የሚከለስ ይሆናል፡፡

፫/ የመራጮች መዝገብ አዘገጃጀት፣ የመዝገቡ አያያዝና አከላለስ እንዲሁም የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን አስመልክቶ ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

**27. <u>Registration Complaints</u>**

Any person or political organization with grievance on the voter's registration may lodge a complaint along with the reason with the Polling Station Grievance Hearing Committee. The Polling Station Grievance Hearing Committee shall decide in accordance with Article 152 of this Proclamation.

**28. <u>Cancellation of Registration</u>**

1/ No person, except when his insanity is verified by an authorized body or by sufficient evidence, registered fraudulently or more than once, deceased, or unless his voting rights have not been restricted by the decision of a court based on relevant law, shall be removed from the electoral roll because of a complaint lodged against him.

2/ When one of the incidents listed in Sub-Article (1) of this Article occurs, courts, hospitals, Idirs or other members of the community knowledgeable of the matter are obligated to report the matter to the Board's regional branch office, the constituency or the polling station within two days of the incident.

3/ The Board's regional branch office, the constituency or polling station shall, upon receiving evidence in accordance with Sub-Article (2) of this Article, cancel the name of the registered voter.

**29. <u>Permanent Electoral Roll</u>**

1/ The Board may set the procedures for the preparation of the permanent electoral roll, with periodic updates and revisions, for every constituency.

2/ The electoral roll shall be prepared and regularly revised by the Board's regional branch offices and lower level offices led by an expert appointed by the Board and in collaboration with the Central Statistic Authority and other relevant institutions.

3/ The Board shall issue a directive pertaining to the preparation, maintenance and revision of the electoral roll as well as the use of technology.

## ምዕራፍ ሁለት

## የዕጩዎች ምዝገባ

**፴. የእጩ የምዝገባ ቦታ**

የእጩ ምዝገባ ከምርጫው ዕለት ቢያንስ ፺ ቀን አስቀድሞ ቦርዱ ለእጩዎች ምዝገባ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በምርጫ ክልሎች ይከናወናል፡፡

**፴፩. ለእጩነት የሚያበቁ መመዘኛዎች**

፩/ ማንኛውም ሰው:-

ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሆነ እና ለመመረጥ የተመዘገበ፤

ለ) በምዝገባ ዕለት እድሜው ፳፩ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነው፣

**ሐ) ከምርጫው ዕለት አስቀድሞ በምርጫ ክልሉ ውስጥ በመደበኛነት አንድ ዓመት ከኖረ ወይም የትውልድ ቦታው በእጩነት ሊቀርብበት በፈለገበት የምርጫ ክልል ውስጥ ከሆነ፤**

መ) መወዳደር የሚፈልግበት ከተማ ወይም ወረዳ ከአንድ በላይ የምርጫ ክልሎችን የሚያቅፍ ከሆነ እና በከተማው ወይም በወረዳው ውስጥ ለሁለት ዓመት በመደበኛነት የሠራ ከሆነ በዚያው ከተማ ወይም ወረዳው በፈለገው የምርጫ ክልል፣

ሠ) በህግ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብቱ ያልተገፈፈ፤

ረ) በአዕምሮ ህመም ምክንያት ለመወሰን ብቃት የሌለው መሆኑ ስልጣን ባለው አካል ወይም በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠበት ካልሆነ፤

**ሰ) በግል የቀረበ እጩ ከሆነ ራሱ፣ ለውድድር ያቀረበው የፖለቲካ ድርጅት ከሆነ ድርጅቱ ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚያወጣውን የምርጫ ሥነ ምግባር ደንብ ተቀብሎ ከፈረመ፤**

**በእጩነት ሊቀርብ ይችላል፡፡**

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሰ) የተደነገገው መመዘኛ:-

ሀ) በሥራ ወይም በትምህርት ምክንያት ከምርጫ ክልሉ ውጭ የነበረን ሰው፤

ለ) ከዚህ በፊት በምርጫ ክልሉ ተመርጦ በመስራት ላይ ያለን ሰው አይመለከትም፡፡

## CHAPTER TWO

## REGISTRATION OF CANDIDATES

**30. Location of Candidates Registration**

Candidates registration shall be carried out in constituencies at least 90 days prior to the election day and in accordance with the Board's established timetable for candidate's registration.

**31. Criteria for Candidature**

1/ Any person shall be eligible to contest as a candidate who:

a) is an Ethiopian citizen and registered to be elected;

b) is 21 years of age or above on the date of registration;

c) has resided in the constituency of his intended candidature continuously for one year before the election day; or his place of birth is in the constituency of his intended candidature;

d) seeks to contest in a city or Worede that has more than one constituency and if he has been on a regular work duty for two years in the city or Woreda, then he can choose to contest in any constituency in that city or Woreda;

e) whose electoral rights have not been stripped of by law or the decision of a court;

f) is not declared as incapable of making effective decisions due to insanity verified by an authorized body or by sufficient evidence;

g) has accepted and signed, if an independent candidate himself or if put forward by political party that has put him forward as candidate – the party, the election code of conduct to be issued by the Board in accordance with this Proclamation.

2/ The criteria in Sub-Article (1) (g) of this Article shall not apply to a person:

a) who has been outside of the constituency on a duty or study;

b) who, having been previously elected in the constituency, is already in office.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተደነገገው መመዘኛ በተጨማሪ በግል የቀረበ እጩ በአካባቢው መስተዳድር የተረጋገጠ እድሚያቸው ፲፰ ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆናቸው እና የመምረጥ መብታቸው በህግ፣ በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም በአእምሮ ህመም ምክንያት ያልተገደበ የምርጫ ክልሉ ነዋሪዎች ውስጥ ከ፭ሺ የማያንስ የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ አለበት፡፡ ሆኖም የግል እጩ ተወዳዳሪው የአካል ጉዳተኛ ማቅረብ ያለበት የድጋፍ ፊርማ ብዛት ከ፫ ሺ የማያንስ ይሆናል፡፡

፬/ በግል እጩዎች የሚቀርቡ የድጋፍ ፊርማዎች የሚረጋገጡበት መንገድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፬ እና ፷፭ መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲ ምዝገባ የሚቀርቡ የመስራች አባላት ፊርማዎች ትክክለኛነት ከሚረጋገጥበት መንገድ ጋር ተመሳሳይ ይሆናል።

፭/ የግል እጩው ድጋፉን ያልሰጠ ሰው የሰጠ በማስመሰል፣ በሃሰት ስምና ፊርማ በማዘጋጀት፤ የሌለ ሰው እንዳለ በማስመሰል ወይም በሌላ የተጭበረበረ መንገድ የድጋፍ ፊርማ ማቅረቡ በማናቸውም ሰው በሚቀርብ ጥቆማ ወይም ቦርዱ በራሱ በሚያደርገው ማጣራት ከተረጋገጠበት አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት የሚወሰደው እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የእጩነት ምዝገባ ማመልከቻው ውድቅ ሆኖ ወይም ምዝገባው ተሰርዞ ለሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት በግል እጩነትም ሆነ በፖለቲካ ፓርቲ አመራር ወይም አባልነት እንዳይሳተፍ መደረግ አለበት፡፡

**፴፪. <u>የእጩ አቀራረብ</u>**

፩/ ማንኛውም በህግ የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚካሄድ ምርጫ መስፈርቱን የሚያሟላ እጩ በማቅረብ ሊወዳደር ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፖለቲካ ፓርቲ እጩዎች ሁሉ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፩(፩) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላታቸውን ከማረጋገጥ በተጨማሪ እያንዳንዱ እጩ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚወዳደር ከሆነ በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ከሚኖሩ መራጮች ሁለት ሺ፤ አካል ጉዳተኛ ከሆነ

3/ In addition to the criteria set out in Sub-Article (1) of this Article, an independent candidate shall secure endorsement signature of not less than 5,000 from the constituency's residents whose age is 18 years of age or above as verified by a local administrator; whose voting rights have not been restricted by law or a court decision or due to insanity. However, the endorsement signature for an independent candidate with physical disability shall not be less than 3,000.

4/ The verification process of authenticity of the endorsement signatures submitted by independent candidates shall be similar to the verification of the authenticity of the endorsement signatures of founding members required for political parties' registration in accordance with Articles 64 and 65 of this Proclamation.

5/ If an independent candidate has been found submitting fraudulent endorsement signatures from persons who did not express their support, uses fictitious name and signature or does any other act of fraud ascertained based a person's report or the Board's investigation, without prejudicing to the punishment based on the criminal law, the candidate's application shall be rejected or his registration revoked and the person shall be barred for three years from participating as an independent candidate or as a political party leader or member.

**32. <u>Candidates Nomination</u>**

1/ Any legally registered political party may compete in elections conducted in accordance with this Proclamation by nominating candidates who fulfill the criteria.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, political party candidates, besides fulfilling the criteria outlined in Article 31 (1) of this Proclamation, each candidate competing for a House of Peoples' Representative seat shall produce 3,000 endorsement signatures from voters residing in the constituency where he is contesting, and a candidate with physical disability shall

አንድ ሺ አምስት መቶ የድጋፍ ፊርማ፤ ለክልል ምክር ቤት የሚወዳደር ከሆነ ደግሞ አንድ ሺ፤ አካል ጉዳተኛ ከሆነ ሰባት መቶ ሃምሳ የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ ይኖርበታል።

፫/ በፖለቲካ ድርጅት ተወክለው የሚወዳደሩ እጩዎችን ዝርዝር ለቦርዱ የሚያሳውቀው የድርጅቱ፣ የግንባሩ ወይም የቅንጅቱ ሀላፊ ወይም ወኪሉ ይሆናል፡፡

፬/ በፖለቲካ ድርጅት ተወክሎ ለሚቀርብ እጩ በፓርቲው መወከሉን እና በእጩነት ለመቅረብ መስማማቱን የሚገልጽ ሰነድ ከእጩነት ማስረጃው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

፭/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ግንባር ወይም ቅንጅት በአንድ የምርጫ ክልል ለአንድ የምክር ቤት መቀመጫ ማቅረብ የሚችለው አንድ እጩ ተወዳዳሪ ብቻ ይሆናል።

፮/ ማንኛውም እጩ ተወዳዳሪ በግንባር በመቅረብ መመዝገብ አለበት፡፡በግንባር ቀርቦ መመዝገብ ካልቻለ ለእጩነት የሚያበቁ መስፈርቶች ማሟላቱን የሚያረጋግጡ ተጨባጭ የሰነድ እና እንደአግባብነቱ የሰው ማስረጃዎች ቀርበው እጩውን ባቀረበው ፖለቲካ ፓርቲ አማካኝነት ሊመዘገብ ይችላል፡፡

፯/ የእጩዎች ምዝገባ ከምርጫ ክልሉ የምርጫ አስፈጻሚዎች ቢያንስ ሁለቱ ባሉበት መከናወን አለበት።

**፴፫. <u>በምርጫ ስለሚወዳደሩ የመንግሥት ሰራተኞች</u>**

፩/ ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ፡-

ሀ) በግሉ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በመሆን ለምርጫ መወዳደር ይችላል፡፡

ለ) የመንግሥት ሰራተኛ በህዝብ ምርጫ ለመወዳደር ተወዳዳሪ ሆኖ ሲቀርብ የምርጫ ቅስቀሳ በሚካሄድበት ወቅት እና ምርጫው በሚከናወንበት ጊዜ ያለደመወዝ ፈቃድ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡

ሐ) በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ ምክር ቤቶች ምርጫ እንቅስቃሴ በሚሳተፍበት ጊዜ በማንኛውም የቀጣሪው የመንግሥት መስሪያ ቤት ንብረት መገልገል አይፈቀድለትም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ዳኞች፣ ዓቃቤ ሕጎች፣ ወታደሮች፣ ፖሊስ እና ሌሎች የጸጥታ ሃይሎች፣ የደህንነት

produce 1,500 endorsement signatures, respectively; and a candidate contesting for a regional council seat shall produce 1,000 endorsement signatures and the candidates with physical disability shall produce 750 endorsement signatures, respectively.

3/ The list of political party nominated candidates shall be submitted to the Board by the leader or representative of the political party, front or coalition.

4/ Political party nominated candidates shall present an evidence of nomination by a party and consent of the person to be nominated along with details of candidature.

5/ Front or coalition of political parties shall nominate only one candidate for a single council seat in a constituency.

6/ Any candidate shall register in person. Where the candidate is unable to register in person, he may register through the political party nominating him, provided that the documentary evidences are presented, and where necessary, witnesses ascertain that he fulfills the candidature criteria.

7/ Candidate registration shall be conducted where at least two election officials are present.

**33. <u>Civil Servants Contesting Elections</u>**

1/ Any civil servant:

a) may contest in an election as an independent candidate or as a member of a political party;

b) contesting in an election shall be granted leave without pay during the campaign period and election time;

c) contesting for council seats at any level is prohibited from using the properties of the employing government office when campaigning during the election time.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, judges, prosecutors, soldiers, the police and other law enforcement forces, security agency workers

ሰራተኞች፣ እና የቦርዱ ሰራተኞች በግል ወይም የፖለቲካ ፓርቲ እጩ ተወዳዳሪ ሆነው ከቀረቡ የያዙትን የመንግሥት ሥራ መልቀቅ አለባቸው፡፡

፫/ ዳኞች፣ ዐቃቤ ሕጎች፣ ወታደሮች፣ ፖሊስ እና ሌሎች የጸጥታ ሃይሎች፣ የደህንነት ሰራተኞች እና የቦርዱ ሰራተኞች በምርጫ ውድድር ጊዜ ማንኛውንም ተወዳዳሪ ለማስመረጥ በመደገፍ፣ በመናገር፣ በመፃፍና በመሳሰሉት ተሳታፊ መሆን የለባቸውም፡፡

**፴፬.** **<u>የእጩ የድጋፍ ፊርማ ስለመስጠት</u>**

አንድ የመምረጥ መብት ያለው ነዋሪ በምርጫ ክልሉ ለውድድር ከቀረቡት መቀመጫዎች ቁጥር እጥፍ በላይ ለሆኑ እጩዎች የድጋፍ ፊርማ መስጠት አይችልም፡፡

**፴፭.** **<u>የእጩነት የመታወቂያ ካርድ ስለ መስጠት</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፴፪ መሠረት ለውድድር የሚቀርበው እጩ ከተለየ በኋላ በዕጩዎች መመዝገቢያ ቅፅ ስሙ እንዲሰፍር ተደርጎ የእጩነት መታወቂያ ካርድ ይሰጠዋል፡፡

፪/ የፖለቲካ ድርጅት እጩዎች የእጩነት መታወቂያ ካርድ ለእጩዎቹ ወይም ላስመዘገባቸው ድርጅት ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፴፮.** **<u>እጩዎችን ለህዝብ ስለማሳወቅ</u>**

እጩዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ከተለዩ በኋላ የዕጩዎች ምዝገባ ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ የምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት የተወዳዳሪ እጩዎችን ስም ዝርዝር ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡

**፴፯.** **<u>የእጩዎች የመለያ ምልክቶች</u>**

፩/ ማንኛውም እጩ የሚወዳደርበትን መለያ ምልክት ሊያቀርብ ወይም ቦርዱ ከሚያዘጋጃቸው መለያ ምልክቶች መርጦ ሊይዝ ይችላል፡፡

፪/ የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ እጩዎች በሁሉም የምርጫ ደረጃዎች አንድ ዓይነት ምልክት ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

፫/ የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ እጩዎች ለየምክርቤቱ ምርጫ በሁሉም የምርጫ ክልሎች አንድ ዓይነት መለያ ምልክት መጠቀም አለባቸው፡፡

፬/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ባለፈው ምርጫ የተጠቀመበትን ምልክት ቅድሚያ ተሰጥቶት እንዲመርጥ መደረግ አለበት፡፡

and employees of the Board, shall resign from their positions in the event of their nomination as independent or political party candidates.

3/ Judges, prosecutors, soldiers, members of the police and other law enforcement forces, security agency workers and employees of the Board shall not participate in the support of the election of any candidate through speeches, writings and similar activities during the election period.

**34.** <u>Candidates Signature Endorsement</u>

A resident of a constituency who is eligible to vote shall not provide endorsement signatures for candidates whose number is more than twofold of the seats.

**35. <u>Issuance of Candidature Certificate</u>**

1/ A candidate identified in accordance with Article 32 shall be entered into the candidate registration form and issued with a candidature certificate.

2/ Candidature certificates of political organization candidates may be given to the candidate or to the nominating organization.

**36. <u>Announcement of Candidates to the Public</u>**

Once the candidates are identified in accordance with this Proclamation, commencing with the end of candidate registration, the constituency election office shall announce to the public the list of candidates.

**37. <u>Candidature Symbols</u>**

1/ Any candidate may submit his candidature symbol or choose from those prepared by the Board.

2/ Candidates of one political party may use the same symbol at all election levels.

3/ Candidates of a political party competing for council seats shall use the same symbol in all constituencies.

4/ A political party or independent candidate shall be given priority to choose the symbol he used in previous elections.

፭/ በምርጫ መለያ ምልክት ዙርያ በሚነሱ አለመግባባቶች ምክንያት አቤቱታ ሲቀርብለት የስራ አመራር ቦርዱ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፮/ ማንኛውም መለያ ምልክት:-

ሀ) ከሌሎች እጩዎች መለያ ምልክት ጋር የማይመሳሰል፤

ለ) በብሔር ብሔረሰብ፣ በዘር፣ በሃይማኖት መካከል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጥላቻና ግጭት ሊቀሰቅስ ከሚችል ነገር ወይም ሁኔታ ጋር ግንኙነት የሌለው፤

ሐ) የጦርነት ወይም የሌላ ህገወጥ ድርጊት መልዕክት የማያስተላልፍ፤

መ) ከፌደራልም ሆነ ከክልል መንግሥታት ሰንደቅ አላማ ወይም አርማ ወይም ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች አርማ ወይም ከልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዓርማና ሰንደቅ ዓላማ ወይም ከሃይማኖትድርጅቶች ምልክቶች ጋር የማይመሳሰል፣

ሠ) የህዝብን ሞራል፣ መልካም ሥነ ምግባር እና የመሳሰሉትን የማይጥስ መሆን፤

አለበት፡፡

፯/ ቦርዱ በድምጽ መስጫ ወረቀት ላይ የእጩዎች ምስልና የመለያ ምልክቶችን አቀማመጥ፣ ቅደም ተከተልና እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ለተወዳዳሪ ፓርቲዎች እና የግል እጩዎች ግልጽ በሆነ መንገድ በመመሪያ ይወስናል።

## ፴፰. የእጩ የመለያ ምልክት መለወጥና መተካት

፩/ ቦርዱ በአንቀጽ ፴፯ መሠረት አንድን የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ መለያ እንዲለውጥ ለማዘዝ ይችላል፡፡

፪/ የእጩ መለያ ምልክት እንዲለወጥ በቦርዱ ሲወሰን የእጩዎች ምዝገባ ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲው ወይም የግል እጩው ውሳኔውን እንዲያውቀውና ተለዋጭ ምልክት እንዲያቀርብ ወይም እንዲመርጥ መደረግ አለበት፡፡

፫/ የፖለቲካ ፓርቲም ሆነ የግል እጩ ቀደም ሲል የመረጠውን ምልክት በሌላ ለመለወጥ ሲፈልግ የእጩዎች ምዝገባ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ በአስር ቀናት ውስጥ ለውጡን ለቦርዱ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ፴፱. የእጩዎች ከውድድር መውጣትና መተካት

፩/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ከውድድር ራሱን ሊያገል ይችላል፡፡

5/ The Management Board shall give appropriate decision on disputes regarding elections symbols.

6/ Any symbol shall not:

a) be similar to that of other candidates;

b) be in anyway related to anything or condition that may trigger directly or indirectly hatred or conflict between nation and nationality, race or religion;

c) convey a message of war or any unlawful act;

d) have resemblance to the flags or emblems of the Federal or Regional Governments, other political parties' emblems; flags or emblems of various International Organizations, or Religious Organizations' symbols;

e) violate public moral, ethics and other related matters.

7/ The Board shall determine in a directive the ballot paper layout of the candidates' images and symbols, the sequence and related matters in a manner that is clear to political parties and independent candidates.

## 38. Change and Replacement of Candidature Symbols

1/ The Board may, in accordance with Article 37, order a political party or an independent candidate to change his symbol.

2/ When the Board decides for a change of a candidature symbol, it shall communicate that decision to the political party or the independent candidate within fifteen days after the closing of candidate registration and request him to submit or choose a replacement symbol.

3/ When a political party or an independent candidate is interested in replacing a symbol chosen earlier, the change shall be notified to the Board in writing within ten days after the closing of candidate registration.

## 39. Withdrawal and Replacement of Candidates

1/ A political party or an independent candidate may withdraw from an election.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከውድድር ራሱን ያገለለ የፖለቲካ ፓርቲ እጩ ለወከለው የፖለቲካ ፓርቲ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፫/ የፖለቲካ ፓርቲ እጩውን መለወጥ ወይም መተካት የሚችለው እጩው ራሱን ካገለለበት ቀን ጀምሮ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ወይም እጩው ራሱን ያገለለው የእጩ ምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ካለቀ በኋላ ከሆነ ከድምጽ መስጫው ቀን ከአንድ ወር በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፪ ላይ የተቀመጠው መስፈርት በተተኪነት በሚቀርብ እጩ ላይም ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## ፵. <u>የእጩ መሞት</u>

፩/ የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ እጩ ተወዳዳሪ የእጩ ምዝገባ ጊዜ ካለፈ በኋላ የሞተ እንደሆነ እጩው የሞተበት የፖለቲካ ድርጅት ከድምጽ መስጫው ቀን አንድ ወር በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ሌላ እጩ ሊተካ ይችላል፡፡

፪/ አንድ ወደ ውድድር የገባ የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በተባለው ጊዜ ውስጥ ተተኪ ካላቀረበ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ እጩ የሞተው የምርጫው ቀን ሊደርስ ከአንድ ወር ያነሰ ጊዜ ሲቀረው እንደሆነ ምርጫው ባሉት እጩዎች መካከል በተያዘለት ጊዜ ውስጥ ይከናወናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለፀው ቢኖርም እጩ የሞተበት የፖለቲካ ፓርቲ ተተኪ እጩ ማቅረብ እንደማይችል በጽሑፍ የገለፀ እንደሆነ የምርጫው ውድድር ባሉት እጩዎች መካከል በተያዘለት ጊዜ ይካሄዳል፡፡

፬/ በአንድ የምርጫ ክልል የቀረበው እጩ አንድ ብቻ ከሆነና የሞተ እንደሆነ ቦርዱ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አዲስ እጩዎች እንዲመዘገቡ ተደርጎ ምርጫ ይከናወናል፡፡

## ፵፩. <u>በአንድ ምርጫ ክልል ብቻ ስለመወዳደር</u>

፩/ አንድ ሰው በእጩ ተወዳዳሪነት መቅረብ የሚችለው በአንድ የምርጫ ክልል ብቻ፣ ለአንድ የሕዝብ ተወካዮች ወይም የክልል ምክር ቤት ወንበር ብቻ ይሆናል፡፡

፪/ አንድ እጩ ተወዳዳሪ በእጩዎች ምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ከአንዱ የምርጫ ክልል ወደ ሌላው የምርጫ ክልል ተዛውሮ በህጉ መሠረት እንደ አዲስ ተመዝግቦ ለመወዳደር ይችላል፡፡ አፈፃፀሙ በቦርዱ ይወሰናል፡፡

2/ A political party candidate who has withdrawn from the election in accordance with sub-article (1) of this Article shall notify his decision in writing to the political party that has nominated him.

3/ A political party may change or replace a candidate only within a week of the withdrawal of the candidate; or where the candidate withdraws after the end of candidate registration period, replacement can be done only during the month prior to voting day. The criteria provided uner Article 32 of this Proclamation shall be applicable to the replacement candidate.

## 40. <u>Death of a Candidate</u>

1/ Where a candidate of a political party dies after the end of the candidate registration time, the political organization of the deceased candidate may replace the candidate within a period of one month prior to voting date.

2/ Where a political party contesting for election has not submitted a replacement in accordance with Sub-Article (1) of this Article, or the political party's candidate dies in less than a month time to election day, the election shall continue with the remaining candidates in accordance with the scheduled timetable.

3/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, where a political party informs the Board in writing that it cannot replace the deceased candidate, the election shall continue with the remaining candidates in accordance with the scheduled timetable.

4/ Where there is a single candidate in a constituency and that candidate has died, then the election shall be conducted according to a timetable set by the Board to register new candidates.

## 41. <u>Contesting Only in One Constituency</u>

1/ A person may be nominated as a candidate only in one constituency and only for a single seat for House of Peoples' Representatives or Regional Council seat;

2/ A candidate may transfer from one constituency to another during the period of candidate registration and get registered afresh and contest there in accordance with the law. Implementation thereof shall be determined by the Board.

**፵፪. ለምርጫ የተመዘገቡ የእጩዎች ልዩ መብት**

፩/ ለምርጫ የተመዘገቡ እጩዎች ከባድ ወንጀል ሲፈፅሙ እጅ ከፍንጅ ካልተያዙ በስተቀር ምርጫው እስከሚጠናቀቅ ድረስ በወንጀል ተጠርጥረው አይያዙም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠቀሰው እጅ ከፍንጅም ባይሆን ዕጩዎች ህገወጥ ድርጊት የፈፀሙ እንደሆነ ሕጋዊ እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚችለው የምርጫው ውጤት በቦርዱ አማካኝነት በይፋ ለህዝብ ከተገለፀ በኋላ ብቻ ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም አሸናፊው ሰው በምርጫ ወቅት በፈፀመው ወንጀል የሚጠየቀው በሚመለከተው ምክር ቤት የህግ ከለላው ሲነሳ ብቻ ነው፡፡

## ምዕራፍ ሦስት
## የምርጫ ዘመቻ

**፵፫. የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ስለማካሄድ**

፩/ አንድ እጩ ተወዳዳሪ በእጩነት ተመዝግቦ የመታወቂያ ካርድ ካገኘበት ቀን አንስቶ ምርጫው አራት ቀን እስኪቀረው ድረስ ከአስተዳደሩም ሆነ ከማዘጋጃ ቤት ፈቃድ መጠየቅ ሳያስፈልገው፥ በጽሑፍ በማሳወቅ ብቻ እና ሕጋዊ ግዴታዎቹን በማክበር በራሱም ሆነ በደጋፊዎቹ አማካኝነት የድጋፍ ስብሰባዎችን የመጥራት ወይም ሰላማዊ ሰልፍ የማደራጀት መብት አለው፡፡ እንዲሁም ለምርጫ ውድድሩ ይጠቅሙኛል ያላቸውን መረጃዎች ከቦርዱ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

፪/ እጩዎችና ደጋፊዎቻቸው ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚያካሂዱት የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴ ድምጽ መስጠት ከመጀመሩ ከአራት ቀናት በፊት መጠናቀቅ አለበት፡፡

፫/ የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴ ህገ መንግሥቱና አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ህጎች፣ የመራጮችን መብት፣ የሌሎች እጩዎችን የመወዳደር መብት በማክበር በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ መካሄድ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱት መብቶች በህግ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ውጭ ተፈፃሚ ሊደረጉ አይችሉም፡፡

፭/ ምርጫውን ሰላማዊ እና ፍትሐዊ ለማድረግ እንዲቻል ቦርዱ የምርጫ ቅስቀሳ የሥነ ምግባር ደንብ ያወጣል፡፡

**42. Special Right of Candidates Registered for Election**

1/ Candidate registered for election shall not be arrested except in the case of flagrant delicto for a serious offence.

2/ Where the case is not flagrant delicto as stated in Sub-Article (1) of this Article, legal measures may be taken against a candidate who carried out illegal acts only after the elections results are officially declared to the public by the Board.

3/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (2) of this Article, the winner shall be answerable for the crime committed during the election period only if his immunity is set aside by the appropriate council.

## CHAPTER THREE
## ELECTION CAMPAIGN

**43. Conducting an Election Campaign**

1/ From the day a candidate received a certificate of candidature until four days to the election day, the candidate on his own or through his supporters has the right to call rallies and organize peaceful demonstrations without the need to request permission from the administration or municipality but by simply sending a written notification and respecting his legal duties. He has also the right to receive information he deems useful for his election contest from the Board.

2/ Election campaigns to be carried out by candidates and their supporters carried out based on the directive to be issued by the Board shall conclude four days prior to the commencement of voting.

3/ Election campaigns shall be conducted by respecting the constitution and other relevant laws, the rights of voters and the right of other candidates to contest in a peaceful and democratic manner.

4/ The rights indicated in Sub-Article (1) of this Article shall not be put in effect other than what is provided in law.

5/ The Board shall issue election campaign code of conduct to ensure that the election is peaceful and fair.

**፵፬.የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀም**

፩/ በመንግሥት ቁጥጥር ስር ያሉትን መገናኛ ብዙኃን ማለትም ሬድዮ፣ ቴሌቪዥንና ጋዜጦችን ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለ አድልዎ የመጠቀም መብት አላቸው፡፡

፪/ እጩዎች በመንግሥት የመገናኛ ብዙኃን ነፃ የአየር ጊዜ አግኝተው የመጠቀም መብት አላቸው፡፡

፫/ መንግሥት የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀምን በተመለከተ ቦርዱ ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ባለሥልጣን ጋር በመተባበር ተወዳዳሪ የፖለቲካ ድርጅቶችን ባሳተፈ አካሄድ በሚያወጣው የድልድል መመሪያ መሠረት ይከናወናል፡፡

**፬/ የመንግሥትም ሆነ የግል የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀም፥ የጋዜጠኞች የምርጫ አዘጋገብ እና ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን የሚመለከቱ የሥነ ምግባር እና የአፈጻጸም መርሆችን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል ፡፡**

**፵፭. የመንግሥት አካላት ግዴታ**

የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴዎችን ለማሳካት በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ የመንግሥት አካላት ኃላፊዎች የሚያስተዳድሯቸውን የሬድዮና የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን፣ ጋዜጦችና እንዲሁም የስብሰባ አዳራሾች፣ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ያለአድልዎ እንዲገለገሉባቸው ለማድረግ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ግዴታ አለባቸው፡፡ አፈጻጸሙን በሚመለከት ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

**፵፮.የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴ የተከለከለባቸው ቦታዎች**

፩/ በሚከተሉት ቦታዎች የምረጡኝ ቅስቀሳ ወይም ዘመቻ ማድረግ የተከለከለ ነው:-

ሀ) ቤተ ክርስትያኖች፤

ለ) መስጊዶች፣

ሐ) ወታደራዊ ካምፖች እና ፖሊስ ጣቢያዎች፤

መ) የመማር ማስተማር ሂደት ተግባር እየተከናወነ በሚገኝበት ወቅት በትምህርት ቤቶች እና በትምህርት ቤቶች አካባቢ በ፪ መቶ ሜትር ርቀት ዙሪያ፤

ሠ) ህዝብ የዕለት ተለት ግብይት በሚፈፅምባቸው እና በተወሰኑ ቀናት በገጠርም ሆነ በከተማ በይፋ ገበያ እየተካሄደ በሚገኝባቸው ቦታዎች በ፪ መቶ ሜትር ዙሪያ ክልል፤

**44. Use of the Mass Media**

1/ Political parties contesting elections are entitled to equal access to state-owned Mass Media such as Radio, TV and Newspapers.

2/ Candidates shall be entitled to get access to free airtime on state-owned Mass Media.

3/ The use of the state-owned Mass Media shall be carried out in accordance with the allocation directive to be issued by the Board in collaboration with the Ethiopian Broadcasting Authority and with the participation of the contesting political organizations.

4/ The principles pertaining code of conduct and implementation thereof to the use of private and State-Owned Mass Media, Journalists' coverage of elections News and related matters shall be determined by the directive to be issued by the Board.

**45. Obligation of Government Organs**

To ensure the success of campaigning activities, government officials at any level shall have the obligation to create conducive conditions for candidates to utilize such facilities as radio and Television Stations, Newspaper, and Assembly Halls under their respective authority without discrimination. The Board shall issue a directive pertaining to its implementation.

**46. Places Where Election Campaigns are Prohibited**

1/ It is prohibited to carry out elections' campaigns in the following Locations:

a) churches;

b) mosques;

c) military camps and police stations;

d) within 200-meter radius of educational institutions and their surrounding when school is in session;

e) within 200-meter radius of a permanent or periodic market place in a rural or urban area while trading is officially in progress;

ረ) የመንግሥት ወይም የህዝብ መደበኛ ሥራ በመከናወን ላይ የሚገኙባቸው የመንግሥትና የህዝብ ተቋማት ሥራቸውን በሚያከናውኑበት መደበኛ የሥራ ሰዓት እና ቦታ፣

ሰ) ሌላ ህዝባዊ ስብሰባ እየተካሄደ ባለባቸው ቦታዎች እና አካባቢዎች፡፡

፪/ ዝርዝር አፈፃፀሙ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ምዕራፍ አራት
## ስለ ድምፅ አሰጣጥ

### ፵፯. ስለምርጫ ጣቢያ ሥራ መጀመር

፩/ የድምጽ መስጠት ሂደት በሁሉም ምርጫ ጣቢያዎች ቦርዱ በሚወስነው ቀን አንድ ላይ ይጀመራል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የሚመለከታቸው ምርጫ ጣቢያዎች ስራቸውን በተለየ ቀን እንዲጀምሩ ቦርዱ ሊወስን ይችላል፡፡

፫/ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የድምፅ አሰጣጡ ሥራ:-

ሀ) የፖለቲካ ፓርቲ እና የግል እጩ ወኪሎች፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፣ ታዛቢዎች፣ እና የምርጫ አስፈፃሚዎች በተገኙበት፤ እና

ለ) የምርጫ ጣቢያ ኃላፊው የድምፅ መስጫ ሳጥን ባዶ መሆኑን ከላይ በፊደል ተራ (ሀ) ለተገለፁት አካላት በማሳየት የምርጫ ሳጥኑ በተዘጋጀው ማሸጊያ ታሽጎ በታዛቢዎች ፊት ለፊት በቅርብ እይታና በግልጽ ስፍራ ከተቀመጠ ወይም ከተሰቀለ በኋላ ስለ አጀማመሩ ቃለ ጉባኤ ተይዞ ቦርዱ ለዚሁ ተግባር ባዘጋጀው ቅፅ ላይ ከተሞላ በኋላ ይጀመራል፡፡

### ፵፰. የምርጫ ጣቢያዎች ደህንነት

፩/ የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ መስጫ ዕለት ከመድረሱ በፊት አስተማማኝ ጥበቃ ተደርጎላቸው ደኅንነታቸው ተጠብቆ መዘጋጀት አለባቸው፡፡

፪/ ከምርጫ አስፈፃሚዎች፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና የግል እጩ ወኪሎች ከቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት እና ከተፈቀደላቸው የምርጫ ታዛቢዎች በስተቀር መራጮች ያልሆኑና ድምፅ የሰጡ ሰዎች በምርጫ ጣቢያው ክልል ውስጥ መገኘት የለባቸውም፡፡

f) governmental and public institutions during regular working hours;

g) places and areas where other public meetings are in progress.

2/ The Board shall determine the particulars in a directive.

## CHAPTER FOUR
## VOTING PROCESS

### 47. Beginning of Operation of Polling Stations

1/ Voting shall commence in all polling stations simultaneously on a date the Board sets.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, in case of compelling circumstances, the Board may set different dates for polling stations affected by the circumstance.

3/ In accordance with the directive to be issued by the Board, voting shall begin:

a) In the presence of agents of political parties and independent candidates, members of Grievance Hearing Committee, observers and election officials;

b) The head of the polling station upon showing to the persons stated above Paragraph (a) that the ballot box is empty, after it is sealed by the provided seal, and placed or hung it in front of observers and within close proximity to them and in an open place; and once minutes are recorded about the opening of the poll in the form provided by the Board.

### 48. Security of Polling Stations

1/ Polling stations shall be made ready prior to election day by providing adequate protection and security.

2/ Except for election officers, agents of political parties and independent candidates, members of Grievance Hearing Committee and accredited election observers, anyone who is not a voter or who has already voted shall not be present in a polling station.

፫/ ማንኛውም ሰው ከምርጫ ጣቢያው አምስት መቶ ሜትር ዙሪያ መለስ ርቀት ውስጥ በስካር መንፈስ ውስጥ ሆኖ፣ የጦር መሳሪያ ይዞ ወይም በሌላ በማናቸውም ፀጥታን በሚያደፈርስ ሁኔታ ውስጥ መገኘት የለበትም፡፡ በዚህ ሁኔታ ከተገኘም የምርጫ ጣቢያ ኃላፊው የጸጥታ ሃይሎችን ድጋፍ በመጠየቅ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል::

፬/ የምርጫ ጣቢያ ደህንነት እንዲከበር የማድረግ ኃላፊነት በዋናነት የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ይሆናል፡፡ የምርጫ ጣቢያ ኃላፊው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ወይም የምርጫ ጣቢያ ታዛቢዎች የጣቢያውን ደህንነት ለማስከበር የፖሊስ ኃይል እንደሚያስፈልግ ካመኑ እንዲመደብላቸው የሚመለከተውን አካል መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ሆኖም የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፣ ታዛቢዎች እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ እና የግል እጩ ወኪሎች ጥያቄያቸውን የሚያቀርቡት በምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች አማካኝነት ይሆናል፡፡

፭/ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ ለመግባት ያልተፈቀደለትን ግለሰብ ወይም የምርጫውን እንቅስቃሴ ለማወክ የሞከረን ማንኛውም ሰው ከምርጫ ጣቢያው እንዲወጣ ሊያዝ ይችላል፡፡ ግለሰቡ ትዕዛዝ አክብሮ ያልወጣ እንደሆነ የፖሊስ ኃይል ጠርቶ ከምርጫ ጣቢያው እንዲወጣ ያደርጋል፡፡ ፖሊሱም ይህን ተግባሩን እንደፈፀመ ከምርጫ ጣቢያው ወጥቶ ወደ ምድብ ቦታው ይሄዳል፡፡

፮/ በምርጫ ጣቢያ ወይም በምርጫ ክልል ኃላፊ የምርጫ ደህንነትን የማስከበር ጥያቄ የቀረበለት ማንኛውም የፖሊስ ወይም የጸጥታ አካል ወይም ሌላ ሰው በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፫/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፳፯ በተደነገገው መሠረት የመተባበር፣ ፈጣን ምላሽ የመስጠት እና የማስፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

፯/ ሕጋዊነቱ አጠራጣሪ የሆነ ሰነድ ይዞ በምርጫ ጣቢያ ስለመገኘቱ አሳማኝ ጥቆማ የቀረበበትን ሰው የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎችና የግል እጩ ወኪሎች እንዲሁም ታዛቢዎች በተገኙበት ተጠርጣሪው ሊፈተሽ ይችላል፡፡ ጥርጣሬው እውነት ሆኖ ከተገኘም አስፈላጊ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

3/ No person shall be found within a radius of five hundred meters of the polling station inebriated, carrying a weapon or in any other condition that disrupts peace. In the event a person is found in such a state, the head of the polling station shall call for the support of security forces and take necessary measures.

4/ The responsibility of ensuring the security of polling stations rests primarily on the head of the polling station. Where the head of the polling station, members of Grievance Hearing Committee or polling station observers deem that a police force is needed to safeguard the polling station, they may make such requests to the appropriate body. However, Grievance Hearing Committee members, observers and political parties and independent candidates' agents shall make their request through the head of the polling station.

5/ The head of the polling station may order the person who is not authorized to be in the polling station or has attempted to disrupt the electoral process to leave the polling station. Where the person disobeys the order and refuses to leave, the head may call upon the police force to remove him. The police officer upon discharging his duty shall leave the polling station and return to his designated place.

6/ A police or security force or other person, receiving an election security request from the polling station head or chief election executive of the constituency, has the duty to cooperate, respond quickly and enforce the request in line with Article 27 of Proclamation No. 1133/2019.

7/ If a credible report emerges about a person appearing in a polling station in possession of suspicious documents, the person may be searched in the presence of the head of polling station, agents of all political organizations and independent candidates and observers. In the event that the suspicion is proven, appropriate measures shall be taken.

**፵፱.የድምፅ መስጫ ሰዓት**

፩/ ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር የድምጽ መስጫ ሰዓት ከጠዋቱ ፲፪ ሰዓት እስከ ምሽቱ ፲፪ ሰዓት ድረስ ይሆናል፡፡

፪/ ቦርዱ በተለየ ሁኔታ የድምፅ መስጫ ሰዓት የወሰነ እንደሆነ በልዩ ሁኔታ የተወሰነውን የድምፅ መስጫ ሰዓት ከምርጫው ዕለት ቢያንስ ሁለት ቀን አስቀድሞ ህዝቡ በይፋ እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡

፫/ የድምጽ መስጫ ሰዓት ሲያበቃ የምርጫ ጣቢያው ይዘጋል፡፡ ሆኖም በምርጫ ጣቢያው ድምፅ ለመስጠት በመጠባበቅ ላይ ያሉ መራጮች ድምፅ መስጠት አለባቸው፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ቢኖርም ቦርዱ የምርጫው ነፃና ፍትሃዊነት ይበልጥ ያሰፍናል ብሎ ካመነ የድምፅ መስጫ ሰዓቱን ሊያራዝም ይችላል፡፡

፭/ የምርጫ ጣቢያዎች ለምርጫ ከመከፈታቸው በፊትም ሆነ ድምፅ አሰጣጡ አልቆ ከተዘጉ በኋላ ከምርጫ አስፈፃሚዎች፣ ከህዝብ ከተመረጡ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፣ ከእጩ ተወካዮች እና ከተፈቀደላቸው የምርጫ ታዛቢዎች በስተቀር ማንኛውም ሰው ወደ ምርጫ ጣቢያው መግባት አይችልም፡፡

**፶. ድምፅ ስለመስጠት**

፩/ ማንኛውም መራጭ በአካል በመገኘት በሙሉ ነፃነት ድምፅ ይሰጣል፡፡

፪/ እያንዳንዱ መራጭ ድምፅ የሚሰጠው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

፫/ ማንኛውም መራጭ በመራጭነት በተመዘገበበት የምርጫ ጣቢያ ብቻም ቢሆን ድምፅ ለመስጠት የሚችለው:-

ሀ) የመራጮች መታወቂያ ካርድ ሲኖረው፣

ለ) በመራጮች መዝገብ ላይ ስሙ ሰፍሮ ሲገኝ፣ እና

ሐ)ድምፅ ያልሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ፣ ነው፡፡

፬/ ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር ሁሉም መራጮች በተመሳሳይ የጊዜ ገደብ ውስጥ ድምፃቸውን ይሰጣሉ፡፡

**፶፩. ድምፅ የመስጠት ሂደት**

፩/ እያንዳንዱ መራጭ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርዱን እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩ መሰረት የተመዘገበበትን ማስረጃ ለምርጫ ጣቢያው የምርጫ አስፈፃሚዎች ካስረከበ በኋላ የምርጫ አስፈፃሚዎች የመራጩን ማንነት ባቀረበው ማስረጃ መሠረት ይለያሉ፡፡

**49. Voting Hours**

1/ Unless the Board decides otherwise, voting hours shall run from 6:00 A.M. to 6:00 P.M.

2/ Where the Board decides special voting hours, it shall announce to the public the special voting hours at least two days prior to the voting day.

3/ Where the voting hour ends, the polling station shall be closed. However, voters queued at the premises of the polling station shall be allowed to vote.

4/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, where the Board is convinced that election's freeness and fairness will be further promoted, it may extend the voting hours.

5/ No person may be allowed to enter polling stations before the opening and after the closing of polling stations, except electoral officers, members of Grievance Hearing Committee elected from the public, candidates' agents and accredited election observers.

**50. Casting Vote**

1/ Any voter shall appear in person and cast his vote with full freedom.

2/ Each voter shall cast his vote only once.

3/ While a voter may cast his vote at a polling station where he is registered, he is allowed to cast vote if:

a) he carries his voter's card;

b) his name is listed in the electoral roll; and

c) it has been ascertained that he has not yet voted.

4/ Unless the Board determines otherwise, all voters shall cast their votes in a similar time frame.

**51. The Voting Process**

1/ Each voter shall hand over his voter's identity card, along with the document used to register in accordance with Article 21 of this Proclamation, to the electoral officers of the polling station, whereupon they shall proceed to verify his identity by examining information provided.

፪/ የመራጩ ማንነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከተለየና ቀደም ሲል ያልመረጠ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ በመራጮች መዝገብ ውስጥ ለፊርማ በተዘጋጀው አምድ ላይ እንዲፈርም ይደረጋል፡፡

፫/ መራጩ በመዝገብ ላይ ከፈረመ በኋላ አውራ ጣቱን፣ አውራጣት ከሌለው ማንኛውንም ሌላ ጣት በተዘጋጀው የማይለቅ ቀለም እንዲቀባ ከተደረገ በኋላ የድምፅ መስጫ ወረቀት ተሰጥቶት ወደ ሚስጢር ድምፅ መስጫው ክፍል ይገባል፡፡ መራጩ ጣቶች የሌሉት ከሆነ የምርጫ አስፈፃሚዎች አለመምረጡን ካረጋገጡ በኋላ በቀላሉ የሚታይ ቦታ ላይ የማይለቅ ቀለም ይቀባና እንዲመርጥ ይደረጋል፡፡

፬/ መራጩ ወደ ምስጢር ድምጽ መስጫው ክፍል ገብቶ የሚመርጠውን እጩ መለያ ምልክት በሚገኝበት ባለአራት ማዕዘን ቦታ ላይ የ"x" ወይም ሌላ የማያሻማ ምልክት ካደረገበት ወይም በጣት አሻራው ከፈረመበት በኋላ የድምጽ መስጫ ወረቀቱን አጥፎ በታዛቢዎች ፊት ለፊት በቅርብ እይታ በግልጽ ስፍራ በተቀመጠው የድምፅ መስጫ ሳጥን ወይም ኮሮጆ ውስጥ ያስገባል፡፡

፭/ የማያነቡና የማይፅፉ መራጮች ከጣቶቻቸው አንዱን ለዚህ በተዘጋጀው ቀለም ከነከሩ በኋላ ከሚመርጡት ዕጩ መለያ ምልክት ትይዩ በሚገኘው ባለ አራት ማዕዘን ክፍት ቦታ ላይ የጣት አሻራቸውን በማሳረፍ ድምፅ ይሰጣሉ፡፡

፮/ መራጩ የተሰጠውን የድምፅ መስጫ ወረቀት በአግባቡ ሳይጠቀምበት የቀረ ወይም የተበላሸበት እንደሆነ የተበላሸውን መልሶ በምትኩ ሌላ በመቀበል ድምፅ ለመስጠት ይችላል፡፡

፯/ የምርጫ ጣቢያ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት ተመላሽ የሆነውን የድምፅ መስጫ ወረቀት የተለየ ምልክት ሰጥቶ ወይም "የተበላሸ" የሚል ጽሑፍ በጀርባው ላይ ጽፎበት ለዚሁ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ይከተዋል፡፡

፰/ ቦርዱ የድምጽ አሰጣጡና እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፰ መሠረት የድምጽ ቆጠራው በቴክኖሎጂ ታግዞ እንዲከናወን ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይኸውም ከተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በመመካከር የሚደረግ ሲሆን ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

2/ Upon identifying the voter based on sub-Article (1) of this Article and after ascertaining that the voter has not voted, he shall be made to sign in the column of the electoral roll designated for the purpose.

3/ After the voter has signed on the electoral roll, his thumb, if he doesn't have a thumb any of his other fingers, shall be marked with indelible ink after which he shall be handed with a ballot paper and directed to the voting booth. If the voter doesn't have fingers, the electoral officers shall ascertain that he has not voted already before they allow him to vote, marking with indelible ink on a visible part of his body.

4/ In the voting booth, the voter shall put on the ballot paper an "X," an unequivocal mark or a thumb mark in the square corresponding to the symbol of the candidate for whom he wants to vote, after which he shall fold the ballot paper and insert it in the ballot box or bag placed in front of the observers and within clear sight.

5/ Illiterate voters shall vote by dipping one of their fingers in the ink made available and pressing the inked finger in the square corresponding to the symbol of the candidate for whom they want to vote.

6/ Where the voter fails to properly make use of or spoils the ballot paper, he may return the spoilt ballot paper and receive a replacement and cast his vote.

7/ The head of the polling station having given special mark or written "spoilt' at the back of the ballot box returned based on Sub-Article (6) of this Article, place it in a place provided for this purpose.

8/ The Board may deploy technology to assist with the voting and, in accordance with Article 58 of this Proclamation, the vote counting processes. This shall be done in consultation with contesting political parties and the particulars shall be determined by a directive to be issued by the Board.

**፶፪. <u>ድጋፍ የሚፈልጉ መራጮችን በተመለከተ</u>**

፩/ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን እና ነፍሰ ጡሮች በምዝገባም ሆነ በድምጽ አሰጣጥ ሂደት ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።

፪/ በምርጫ ድምፅ አሰጣጥ ምልክት ለማድረግና የድምፅ መስጫ ወረቀቱን ወደ ድምፅ መስጫው ሳጥን ለመክተት እርዳታ የሚያስፈልገው ማንኛውም መራጭ የሚረዳውን ሰው እራሱ የመወሰን መብት አለው፡፡ ምርጫ አስፈጻሚው መራጩ መብቱን አውቆ እንዲጠቀምበት ለማድረግ በተቻለው አቅም ያስረዳዋል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ በድጋፍ ፈላጊው የተመረጠው ሰው ዕድሜ ፲፰ ዓመት እና ከዚያ በላይ ሆኖ እጩ ወይም የእጩ ተወካይ መሆን የለበትም፡፡

**፶፫. <u>ድምፅ የመስጠት ሂደት የማይቋረጥ ስለመሆኑ</u>**

፩/ ድምፅ የመስጠት ሂደት ሊቋረጥ ወይም ሊቆም አይችልም፣

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ:-

ሀ) የድምፅ አሰጣጡ ሂደት በተለየዩ አስገዳጅ ምክንያቶች ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ከተቋረጠ በኋላ ሁኔታው መስተካከሉ በምርጫ አስፈፃሚዎች ከታመነበት በቃለ ጉባኤ ተይዞ ወዲያውኑ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ሊቀጥል ይችላል፡፡

ለ) የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ የተቋረጠበት ምክንያት ከአቅም በላይ ሆኖ ሊስተካከል ካልቻለ ሁኔታው በቃለ ጉባኤ ተይዞ የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ባለበት ቆሞ ወዲያውኑ አጠቃላይ ሁኔታው ለበላይ ምርጫ ጽህፈት ቤት ሪፖርት ይደረጋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ለ) መሠረት የተቋረጠ የድምፅ መስጠት ሂደት ቦርዱ በሚወስነው መሠረት በሌላ ጊዜ ይካሄዳል፡፡

**፶፬. <u>ድምፅ መስጠትን ስለመቃወም</u>**

፩/ ለማንኛውም መራጭ የድምፅ መስጫ ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት ድምፅ በመስጠት ሂደት ላይ ያለው ሰው ግለሰቡ ድምጽ የመስጠት መብት የሌለው ወይም በምርጫ ጣቢያው በመራጭነት ያልተመዘገበ ነው በማለት የእጩ ተወካይ ተቃውሞ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**52. <u>Voters Who Need Assistance</u>**

1/ The disabled, the elderly and pregnant women shall be given priority during registration as well as voting.

2/ Any voter who needs assistance to put a mark on his ballot paper and insert it into the ballot box has the right to select his own assistant. The election officer, to the extent possible, shall explain to the voter his rights so that he can properly understand and use it. The particulars shall be determined in a directive.

3/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the person selected by the voter requiring assistant shall be of 18 years old or above and shall not be a candidate or an agent of a candidate.

**53. <u>Non-interruption of the Voting Process</u>**

1/ The voting process shall not be interrupted or stopped.

2/ With out prejudice to the provision of Sub-Article (1) of this Article:

a) Where voting is interrupted for any compelling reason, even for a short period of time, and when the electoral officers are convinced that the problem has been resolved, voting may resume immediately once the incident has been recorded in the minute.

b) Where voting cannot be resumed due to force majeure and the problem cannot be resolved, the incident shall be recorded in the minute and voting shall be discontinued where it is; and the matter shall be immediately reported immediately to a higher elections branch office.

3/ A voting process discontinued in accordance with Sub-Article (2) (b) of this Article shall be conducted at another time determined by the Board.

**54. <u>Disputing the Right to Vote</u>**

1/ An agent of a candidate may, before the issuance of ballot papers to any voter, challenge a person who is in the process of voting on the grounds that he is not eligible to vote or has not been registered to vote in that particular polling station.

፪/ አንድ መራጭ የድምፅ መስጫ ወረቀት ቢከለከል ራሱ ወይም ከእጩ ተወካዮች አንዱ ተቃውሞ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፫/ የእጩ ተወካይ ወይም መራጩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ከተደነገጉት የመቃወሚያ ነጥቦች ውጭ በሆነ ምክንያት በማንኛውም የምርጫ አስፈፃሚ፣ የእጩ ተወካይ ወይም በሌላ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ በተገኘ ሰው አግባብ ያልሆነ ድርጊት ተቃውሞ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፬/ የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ከላይ የቀረበውን አቤቱታ ከተመለከተ በኋላ አቤቱታ ላቀረበው ሰው ወይም አካል ውሳኔውን የድምጽ መስጫው ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

፭/ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በዚህ አንቀጽ መሠረት የቀረቡ ቅሬታዎችንና ለቅሬታዎቹ የተሰጡ መልሶችን በፅሁፍ አስፍሮ በመረጃነት ይይዛል፡፡

## ፶፭.ጊዜያዊ ድምፅ ስለመስጠት

፩/ ከላይ በአንቀጽ ፶፬ መሠረት ድምፅ እንዳይሰጥ ተቃውሞ የቀረበበት ሰው ጊዜያዊ ድምፅ መስጠቱ አስፈላጊ ነው ብሎ የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ካመነ መራጩ ለዚህ በተዘጋጀው ፖስታ ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ መደረግ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰጠ ጊዜያዊ ድምፅ በአንቀጽ ፩፻፶፫ መሠረት ውሳኔ እንዳገኘ በቆጠራ የሚካተት ወይም ውድቅ የሚደረግ ይሆናል፡፡

## ፶፮. ስለድምፅ መስጫ ወረቀት እና ስለድምፅ መስጫ ሳጥን

፩/ ቦርዱ ለእያንዳንዱ የምርጫ አይነት መራጩ በግልጽ ሊረዳው የሚችል እስከሚቻለው ድረስ ለማጭበርበር የማይመች የድምፅ መስጫ ወረቀት ያዘጋጃል፡፡

፪/ ቦርዱ የሚያዘጋጀው የድምጽ መስጫ ወረቀት የእጩዎች ፎቶግራፍ፣ የእጩ መለያ ምልክት፣ የእጩዎች ሙሉ ስምና የፖለቲካ ፓርቲያቸው መጠሪያን አካቶ ሊይዝ ይገባል፡፡

፫/ ቦርዱ በየምርጫ ጣቢያው በተመዘገበው መራጭ ቁጥር ልክ የሆኑ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ከጥቂት መጠባበቂያ ጋር ይልካል፡፡

፬/ ቦርዱ እና በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈፃሚዎች ለድምፅ መስጫ ወረቀቶች ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥበቃ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

2/ Where a voter is denied a ballot paper, a complaint may be submitted by the voter himself or a candidate's agent.

3/ An agent of a candidate or a voter may object improper action of an election officer, agent of a candidate or on other person found within the polling station on grounds other than the provisions of Sub-Article (1) and (2) of this Article.

4/ The Polling Station Grievance Hearing Committee shall, after assessing the complaints made in accordance with the provisions of this Article, notify its decision in writing to the person or body lodging the complaints prior to conclusion of voting.

5/ The head of the polling station shall keep a written record of the complaints submitted in accordance with this Article and responses provided to the complaints.

## 55. Voting on a Provisional Ballot

1/ Where Grievance Hearing Committee of the polling state is convinced that a person whose right to vote has been challenged in accordance with Article 54 should be allowed to cast a provisional vote, such a person shall cast a provisional ballot in an envelope prepared for thisurpose.

2/ A vote cast in accordance with Sub-Article (1) above may be counted or rejected based on a decision made in accordance with Article 153.

## 56. The Ballot Paper and Ballot Box

1/ The ballot papers to be prepared by the Board for any type of election shall be user friendly and secure against fraud.

2/ The ballot paper to be prepared by the Board shall contain the candidates' photographs, candidates' symbols, full names of candidates and names of their political party.

3/ The number of ballot papers the Board sends to each polling station shall be equal to that of registered voters in each polling station, with a few extra ballot papers for contingency.

4/ The Board and electoral officers at every level shall handle the ballot papers with high standard of care and security.

፭/ ማንኛውም ድምጽ የሚሰጥበት የድምጽ መስጫ ሳጥን በግልጽ በሚያሳይ ቁስ የተሰራ መሆን አለበት፡፡

፮/ ማንኛውም የምርጫ ሰነድ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ በሚተላለፍበት ጊዜ ሕጋዊ የርክክብ ሥርዓትን ተከትሎ መፈፀም አለበት፡፡ዝርዝሩ በቦርዱ መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ምዕራፍ አምስት
## የድምፅ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ

### ፶፯. የቆጠራ ቦታ

፩/ የማንኛውም ምርጫ ድምፅ ቆጠራ የሚካሄደው ድምፅ በተሰጠበት ምርጫ ጣቢያ ነው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በጸጥታ መደፍረስ ወይም ተመሳሳይ አስገዳጅ ምክንያት የምርጫ ጣቢያው የምርጫ አስፈፃሚ ለምርጫ ክልሉ ጥያቄ አቅርቦ ሲፈቀድ ወይም የምርጫ ክልሉ የምርጫ አስፈፃሚ ሲወስን የድምጽ ቆጠራው በምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት ይካሄዳል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት የሚካሄደው ቆጠራ የምርጫ ጣቢያው የእጩ ወኪሎች፣ ከህዝብ የተመረጡ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት እና የምርጫ ታዛቢዎች በተገኙበት መደረግ አለበት፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ዝርዝርን ቦርዱ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

### ፶፰. የድምጽ ቆጠራ አጀማመርና ሂደት

፩/ ድምፅ አሰጣጡ እንደተጠናቀቀ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ቆጠራ ለመጀመር የእጩ ወኪሎች፣ ከህዝብ የተመረጡ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት እና የምርጫ ታዛቢዎች እና ሌሎች ምርጫ አስፈጻሚዎች እንዲገኙ በማድረግና በቂ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ብርሃን መኖሩን በማረጋገጥ:-

ሀ/ ለምርጫ ጣቢያው የደረሰውን የድምፅ መስጫ ወረቀት ብዛት ይመዘግባል፤

ለ/ በዕለቱ ድምፅ የሰጡ መራጮችን ብዛት ይመዘግባል፣

ሐ/ የተበላሹና ሥራ ላይ ያልዋሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ብዛት ይመዘግባል፡፡

5/ all ballot boxes shall be made from translucent material.

6/ Any transfer of election documents from one person to another shall follow the legal receiving procedures for such transfers. The Board shall determine the in a directive.

## CHAPTER FIVE
## VOTE COUNTING AND ANNOUNCEMENT OF RESULTS

### 57. Place of Vote Counting

1/ Vote counting of any election shall take place at the polling station where voting took place.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the vote counting shall take place at the secretariat of the constituency, where due to disruption of security or other similar compelling reason, such a request is made to the constituency by the polling station electoral officer and the request is granted by the constituency or when electoral officer of the constituency decides.

3/ The vote counting to be conducted at the secretariat of a constituency in accordance with Sub-Article (2) above, shall be made in the presence of agents of candidates, members of the Grievance Hearing Committee elected by the public and election observers.

4/ The Board may issue a directive to determine the implementation of this Article.

### 58. Commencement and Process of Voting

1/ Upon the closure of polls, the head of the polling station, in the presence of candidates' agents, Grievance Hearing Committee members elected by the public, election observers and other election officers and after establishing the existence of sufficient natural or artificial light, shall:

a) record the number of ballot paper issued for that polling station;

b) record the number of voters who have cast their votes on that day; and

c) count and record the number of invalid and unused ballot papers.

፪/ ድምፅ ቆጠራ ከመጀመሩ በፊት የድምፅ መስጫው ሳጥን እሽጉ ያልተከፈተ እና ድምፅ መስጠት ከመጀመሩ በፊት በታሸገበት ሁኔታ መቆየቱን፣ የድምጽ ሳጥኑም ያልተቀደደ፣ ያልተሰበረ ወይም ብልሽት ያልደረሰበት መሆኑን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱት አካላት ካረጋገጡ እና ቃለጉባኤ ከተያዘ በኋላ እሽጉን በመክፈት ድምፅ የተሰጠባቸው ወረቀቶች በሙሉ ይወጣሉ፡፡ የድምጽ መስጫ ሳጥኑም ባዶ መሆኑ ይረጋገጣል፡፡

፫/ ምርጫው የተካሄደው ለተለያዩ ምክር ቤቶች ከሆነ በመጀመሪያ ለየምክር ቤቱ የተሰጡት የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ከተለዩ በኋላ የአንዱ ምክር ቤት ተቆጥሮ እና ለእያንዳንዱ እጩ የተሰጠው የድምጽ ቁጥር ተመዝግቦ እንዳለቀ የሌላው ምክር ቤት ቆጠራ በተመሳሳይ ይካሄዳል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሰረት ቆጠራ ለመጀመር የሚያስችል በቂ ብርሃን የሌለ እንደሆነ የእጩ ወኪሎች፣ ከህዝብ የተመረጡ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት እና የምርጫ ጣቢያው ሃላፊ ይህንኑ በመግለጽ ቃለጉባኤ ይፈራረማሉ፡፡ ይህም ሲሆን ሁሉም የድምጽ መስጫ ወረቀቶች አስፈላጊው የጥበቃ ሃይል እንዲኖር በማድረግ ደህንነታቸው በተረጋገጠ ሁኔታ እንዲያድሩ መደረግ አለበት፡፡ በዚህ ንዑስ አንቀጽ የተጠቀሱት ሰዎች ከፈለጉ በምርጫ ጣቢያው መቆየት ይችላሉ፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሰረት የተቋረጠ የድምጽ ቆጠራ ሂደት በሚቀጥለው ቀን እጅግ ቢዘገይ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል፡፡

፮/ በድምፅ ቆጠራው ሂደት ግድፈት አለ በማለት አንድ የምርጫ አስፈፃሚ፣ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ወኪል ቅሬታ ያቀረበ እንደሆነ የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ጉዳዩን መርምሮ ወዲያውኑ ወይም ቢዘገይ ከ፲፪ ሰዓት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ በምርጫ ጣቢያው ወይም በምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ የድምጽ ቆጠራው ሁኔታዎች እስኪጣሩ እንዲቋረጥ ወይም እንዲቆም እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ ዳግም ቆጠራ እንዲካሄድ ሊደረግ ይችላል፡፡

## ፶፱. ስለ ዋጋ አልባ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች

፩/ ድምፅ የተሰጠባቸው ወረቀቶች ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ዋጋ አልባ ሊሆኑ ይችላሉ:-

ሀ) የመራጩ ማንነት በስም የተገለፀበት ከሆነ፤

2/ After the bodies indicated in Sub-Article (1) of this Article have ascertained that the ballot box has not been opened, the seals are in the same condition as they were prior to commencement of voting, that the ballot box has not been broken, damaged or tampered with, and the same has been recorded in the minute, then the seal shall be broken and the ballot box shall be opened; and the ballot papers taken out. It shall be ascertained that the ballot box is empty.

3/ Where the election is to different councils, after the votes given to each council are sorted, the votes for one council shall be counted and those for each candidate registered; and the same procedure shall be followed for the other council.

4/ Should there not be sufficient light to commence counting in accordance with Sub-Article (1) of this Article, agents of the candidates, members of the Grievance Hearing Committee elected by the public, and the head of the polling station shall sign a record stating this matter. When this happens, all ballot papers shall be kept properly with appropriate security measures provided. The individuals listed in this sub-article can remain in the polling station should they chose to do so.

5/ The vote counting that was interrupted in accordance with Sub-Article (4) of this Article, shall resume no later than 7 A.M on the next day.

6/ If an election officer, a political party or an agent of an independent candidate submits a complaint alleging flawed counting process, the Polling Station Grievance Hearing Committee has to investigate and decide on the matter immediately or no later than twelve hours. Based on the decision of the polling station or Constituency Grievance Hearing Committee, the voting process may be discontinued or stopped or where necessary, re-counted.

## 59. Invalid Votes

1/ A vote shall be deemed invalid for one of the following reasons:

a) if it identifies the voter by name;

ለ) ለምክር ቤቱ ሊመረጥ ከሚቻለው ተመራጮች ቁጥር በላይ ላላቸው እጩዎች ምልክት የተደረገበት ከሆነ፤

ሐ)ምንም ምልክት ያልተደረገበት ከሆነ፤

መ) መራጩ ማንን እንደመረጠ መለየት የሚያስቸግር ከሆነ፤

ሠ) ሕጋዊ የድምፅ መስጫ ወረቀት ያልሆነ ወይም በምርጫ ጣቢያው ያልተሰራጨ የድምፅ መስጫ ወረቀት ከሆነ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ዋጋ አልባ የተደረጉ ወረቀቶች በጀርባቸው "ውድቅ" የሚል በጉልህ ተፅፎባቸው ለብቻቸው ተቆጥረው ይታሸጋሉ፡፡

**፷. ስለድምፅ ቆጠራ መጠናቀቅ**

በምርጫ ጣቢያ የሚካሄደው የድምጽ ቆጠራ እንደተጠናቀቀ:-

፩/ በወቅቱ በቦታው የተገኙ የምርጫ አስፈፃሚዎች፤ እና የእጩ ወኪሎች አጠቃላይ የድምፅ አሰጣጥ እና የቆጠራው ሂደት እንዲሁም ውጤቱ ትክክል ስለመሆኑ ለዚሁ ዓላማ በሚዘጋጀው ቃለ ጉባኤ እና የምርጫ ጣቢያ ውጤት መተማመኛ ቅፅ ላይ ይፈራረማሉ፡፡ ሆኖም በሂደቱና በውጤቱ ቅሬታ ያለው የእጩ ወኪል ቅሬታውን አስመዝግቦ ይፈርማል፡፡

፪/ የተቆጠረው የድምፅ መስጫ ወረቀት ታሽጎ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተፈረመው የምርጫ ጣቢያ ውጤት መተማመኛ ቅፅ፣ ቃለጉባኤ እና የምርጫ ውጤት ማሳወቂያ ቅፅ ለምርጫ ክልሉ ወዲያውኑ ይላካል፡፡

፫/ የድምፅ ቆጠራ ውጤት መተማመኛውን ለፈረመው የእጩ ወኪል አንድ ቅጂ ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡

**፷፩. የቆጠራ ውጤት አገላለፅ**

፩/ በምርጫ ጣቢያ የተደረገ የቆጠራ ውጤት ለጣቢያው የደረሰውን የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ብዛት፣ በጣቢያው የተመዘገቡና ድምጽ የሰጡ መራጮችን ብዛት፣ ጥቅም ላይ የዋሉ፣ ያልዋሉ፣ የተበላሹና ዋጋ አልባ የሆኑ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ብዛት እና እያንዳንዱ እጩ ያገኘውን የድምጽ ብዛት በመለየት ቆጠራው በተጠናቀቀ በአንድ ሰዓት ውስጥ በምርጫ ጣቢያው ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ወጥቶ ለህዝብ በይፋ መገለጽ አለበት፡፡

b) if it contains marking for more candidates to the council than the voter is allowed to make;

c) if it is blank;

d) it does not clearly indicate the voter's intent;

e) where, the ballot paper is not legal or issued by the polling station.

2/ Ballot papers invalidated in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be clearly marked "INVALID" on back, counted separately and sealed.

**60. Conclusion of Vote Counting**

Upon conclusion of vote counting at a polling station:

1/ Electoral officers and agents of candidates present shall ascertain that the voting and counting process and the results thereof are valid by signing on the minutes and form designated for this purpose. However, any agent of a candidate who has complaints regarding the process and results may register his complaints on the form and affix his signature thereto.

2/ The votes counted shall be sealed and immediately sent to the constituency together with the polling station results confirmation form, minutes and the polling station results announcement form that have been signed in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

3/ A copy of the vote counting results confirmation form shall be issued immediately to the agent of a candidate who has signed the form.

**61. Announcement of Results**

1/ Results of the vote counting conducted at a polling station shall be posted on a notice board of the polling station within an hour after the conclusion of ballot counting indicating the number of ballot paper issued for that polling station; the number of registered voters in the polling station; number of voters who cast their vote; the number of used, unused, invalid and spoiled ballot papers; and the number of votes obtained by each candidate.

፪/ የምርጫ ክልል የምርጫ ጽህፈት ቤቶች የህዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ውጤት ከየምርጫ ጣቢያው እንደደረሳቸው ወይም የተረጋገጠ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር በምርጫ ክልሉ የድምጽ መስጫ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኋላ ከአምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተወዳዳሪዎች ወይም ወኪሎቻቸው በተገኙ በት ደምረው የተገኘውን ውጤት ለህዝብ ይፋ ማድረግ አለባቸው፡፡

፫/ እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምጽ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን ለመለየት አስቸጋሪ የሆነ እንደሆነ እኩል ድምፅ ያገኙት ተወዳዳሪዎች ብቻ ተለይተው ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ ድጋሚ ምርጫ እንዲሰጥባቸው ይደረጋል፡፡

፬/ የምርጫ ክልል የምርጫ ኃላፊዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ይፋ ያደረጉትን ውጤት:-

ሀ) ለተወዳዳሪዎች ወይም ወኪሎቻቸው የውጤት መተማመኛ ይሰጣሉ፤

ለ) በውጤት ማሳወቂያ ቅፅ ሞልተው አንድ ቅጂ ለቦርዱ ጽህፈት ቤት፣ እንዲሁም ሌሎች ቅጂዎች በየደረጃው ለሚገኙ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ይልካሉ፡፡

፭/ ቦርዱ በአጠቃላይ የምርጫ ውጤት ከየምርጫ ክልሉ ተጠናቆ እስኪደርሰው ድረስ ከየምርጫ ክልሉ የመጣለትን የህዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች አባላት የምርጫ ውጤት በጊዜያዊነት በቦርዱ ጽህፈት ቤት ሊገልጽ ይችላል፡፡ ሆኖም የምርጫው ይፋዊ ውጤት በ፲ ቀናት ውስጥ ካልተገለጸ ቦርዱ ጊዜያዊ ውጤቱን ይፋ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፮/ በምርጫ ክልሎች የተሰበሰቡ ድምጽ የተሰጣባቸው ወረቀቶች ታሽገው ከምርጫ ክልሉ በቅርበት በሚገኝ የቦርዱ እርከን ጽህፈት ቤት ወይም በክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት እንዲቀመጡ ይደረጋል፡፡

፯/ ድምጽ የተሰጠባቸው ወረቀቶችን አያያዝ እንዲሁም አወጋገድ አስመልክቶ ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

## ፷፪. <u>ይፋዊ መግለጫ</u>

፩/ የምርጫው ሂደት ከተጠናቀቀና አስፈላጊ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ የተረጋገጠ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር ከምርጫው ቀን ቀጥሎ ባሉት ፲ ቀናት ውስጥ ቀጥሎ የተመለከቱትን ነጥቦች የያዘ ይፋዊ መግለጫ ያወጣል፡፡

2/ Upon receiving the results of the elections to the House of Peoples' Representatives and Regional Councils from each polling station, constituency electoral officers shall, in the presence of candidates or their agents, add up and announce the elections results to the public within five days of the conclusion of ballots unless prevented by circumstances that are evidently beyond their control.

3/ Where two candidates receive equal number of votes and it is impossible to determine the winner, a re-election shall be conducted only between the candidates who have received equal number of votes at a later date to be determined by the Board.

4/ The electoral officers of a constituency, concerning the results they announced in accordance with Sub-Article (2) above shall:

a) issue a copy of result confirmation form to candidates or their agents;

b) fill in the result announcement form and send a copy to the Board Secretariat as well as to electoral branch offices at every level.

5/ The Board, until it receives all results from each constituency, may announce at its Secretariat provisional results from constituencies for elections to House of Peoples' Representatives and Regional Councils. The Board shall announce the provisional election results where the final official results have not been determined within 10 days.

6/ The ballot papers cast in each constituency should be sealed and transported to and stored at the nearest Board Office or Regional Board Secretariat.

7/ The Board shall issue a directive pertaining to keeping and disposal of ballot papers after elections.

## 62. <u>Official Declaration</u>

1/ Upon the conclusion of electoral process and collection of the necessary information, the Board, unless prevented by circumstances that are evidently beyond its control, within 10 days after the election day shall make an official declaration containing the following particulars:

ሀ) የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር፣

ለ) ድምፅ የሰጡ መራጮች ቁጥር፣

ሐ) ድምፅ የሰጡና ያልሰጡ የተመዘገቡ መራጮች መጠን በመቶኛ፣

መ) የተመረጡ እጩዎች የስም ዝርዝርና የተመረጡበት የምርጫ ክልል፣

ሠ) የአሸናፊ ፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሁም የግል ተወዳዳሪዎች ስምና ለየምክር ቤቱ ያሸነፉትን መቀመጫ ብዛት፣

ረ/ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ያልዋለ፣ ከጥቅም ውጭ የሆነ የድምፅ መስጫ ወረቀት እያንዳንዱ እጩ በየምርጫ ጣቢያው ያገኘው የድምፅ ውጤት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎች፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በምርጫ ክልል ደረጃ በተገለጹ ውጤቶች ላይ የቀረቡ አቤቱታዎች ውጤት መግለጹን እንዲዘገይ የሚያደርግ ከሆነ ይፋዊ ውጤት የሚገለጽበት ጊዜ እስከ ፳ ቀን ድረስ ሊዘገይ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት
## ስለ ፖለቲካ ፓርቲዎች በጠቅላላ

## ምዕራፍ አንድ
## የፖለቲካ ፓርቲ አመሰራረት

### ፷፫. የፖለቲካ ፓርቲ ስለ መመስረት

፩/ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ፓርቲ የማቋቋም ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አባል የመሆን መብት አለው::

፪/ ማንኛውም እድሜው ከ፲፰ ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊ በዚህ አዋጅ መሠረት የአገር አቀፍ ወይም የክልል የፖለቲካ ፓርቲ አባል የመሆን መብት አለው፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው ቢኖርም የሚከተሉት ሰዎች የፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆን አይችሉም:-

ሀ) ዳኛ፣

ለ) ዓቃቤ ሕግ፣

ሐ) የመከላከያ ሰራዊት አባል፣

መ) የፖሊስ፣ የደህንነት እና የጸጥታ አካላት ሰራተኛ፣

ሠ) የቦርዱ ባለስልጣናት እና ሰራተኞች፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተጠቀሱት ሰዎች በፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ለመንቀሳቀስ ከፈለጉ የመንግሥት ስራቸውን መልቀቅ አለባቸው፡፡

a) The number of registered voters;

b) The number of voters that have cast their vote;

c) The percentage of registered voters that have cast their votes and of those that have not;

d) The list of elected candidates and their respective constituency;

e) The list of winner political parties and independent candidates as well as the number of seats they have won for each council;

f) The number of used, unused and invalid ballot papers and the total votes each candidate obtained in each polling station and other relevant information.

2/ With out prejudice to the provisions of Sub-Article (1) above, if complaints lodged on results at constituency level has the effect of delaying the declaration of result, the official declaration of result may be extended up to 20 days.

## PART FOUR
## POLITICAL PARTIES IN GENERAL

## CHAPTER ONE
## FORMATION OF POLITICAL PARTY

### 63. Political Party Formation

1/ Every Ethiopian has the right to form a political party or be a member of a political party.

2/ Every Ethiopian 18 years of age and above has the right to be a member of a National or Regional Party in accordance with this Proclamation.

3/ Notwithstanding the provision of sub-articles (1) and (2), the following persons shall not be members of a political party:

a) Judge;

b) Prosecutor;

c) Member of the defense;

d) Employee of the police force, intelligence units and security forces;

e) The official of the Board and employees.

4/ If the persons listed in sub-article (3) intend to be members of a political party, they shall resign from their government service.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገውን የጣሰ ሰው ከያዘው የመንግሥት ሥራ በራሱ ፈቃድ እንደለቀቀ ተቆጥሮ በሚመለከተው አካል አስፈላጊው እርምጃ ይወሰዳል፡፡

፮/ በፍርድ ቤት ወሳኔ የመምረጥና የመመረጥ መብቱ የታገደበት ሰው እገዳው በሚቆይበት ዘመን የፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆን አይችልም፡፡

## ፷፬. አገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ ስለመመስረት

፩/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲነት የሚመሰረተው:-

ሀ) ፲ሺ. መሥራች አባላት ሲኖሩት፤

ለ) ከመስራች አባላቱ ውስጥ ከ፵ በመቶ የማይበልጡት የአንድ ክልል መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑ፤

ሐ) የተቀሩት መሥራች አባላት ነዋሪነታቸው በኢትዮጵያ ከሚገኙት ሌሎች ክልሎች ውስጥ ቢያንስ በአራቱ ክልሎች መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑ፤ እና

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሐ) መሠረት ከየክልሉ ለሀገር አቀፍ ፓርቲ መሥራችነት ከሚመዘገቡት አባላት በእያንዳንዱ ክልል አሥራ አምስት በመቶው መደበኛ ነዋሪ ሲሆኑ ነው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱት መስራች አባላት እድሜያቸው ፲፰ ዓመትና ከዚያ በላይ ሆኖ በህግ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ የመምረጥ መብታቸው ያልተገፈፈ፣ የፖለቲካ ፓርቲው አባል ለመሆን መስማማታቸው ከሙሉ ስማቸው ጎን ባኖሩት ፊርማቸው የገለፁና በተመዘገቡበት አካባቢ ነዋሪ ስለመሆናቸው ለፓርቲው ማረጋገጫ ያቀረቡ መሆን አለባቸው፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሥር የተመለከተው የመሥራች አባላት መረጃ የአባሉን ሙሉ ስም፤ ፆታ፣ እድሜ፣ ቀበሌ ወይም ወረዳ፤ እንደየአግባብነቱ የሚኖሩበትን ቦታ ልዩ ስም ወይም የቤት ቁጥር፣ የነዋሪነት ማረጋገጫ ዓይነት፣ ያቀረበው የነዋሪነት ማረጋገጫ መለያ ቁጥር ያለው ከሆነ መለያ ቁጥሩ፤ ፊርማ እና የምዝገባ ቀን የሚገልጽና እንዲሁም የመረጃ ሰብሳቢውን ስምና ፊርማ የያዘ መሆን አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) በተመለከተው መሠረት ፓርቲው የሚያቀርበው የመስራች አባላት መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ፓርቲው ወይም ፓርቲውን ለማስመዝገብ

5/ A person who violates sub-article (3) of this Article shall be deemed to have willingly resigned from his government service and the necessary measures will be taken on him by the relevant authority.

6/ A person who has been deprived of his right to vote and be elected by a judicial decision shall not become a member of a political party for the duration of his ban.

## 64. Formation of a Nationwide Political Party

1/ A political party shall be formed as a nationwide political party where:

a) it has at least 10,000 founding members;

b) not more than 40 Percent of its founding members are residents of a single region;

c) the remaining founding members are permanent residents of at least four other regions of Ethiopia; and

d) the number of members registered as founders in each region as laid down in Sub -Article (1) (c) of this Article constitutes at least fifteen percent (15%) of the total founding members.

2/ The founding members specified under sub-article (1) of this Article: must be at least 18 years old; not deprived of the right to vote by law or a court's decision; their consent to be members of the political party expressed by their signature affixed next to their full name; and must have submitted to the party evidence of their residence in the place of their registration.

3/ The document signed by the founding members in accordance with sub-article(2) of this Article, shall specify the member's full name, sex, age, Kebele or Woreda, as appropriate special name for their residence area or house number; type of proof of residence, identification number of proof of residence if available, signature and the date of registration as well as the name and signature of the person who took down these particulars.

4/ In accordace with Sub-Article (2) and (3) of this Article the party or the person who presents the party's document to have the party registered shall attach a statement of oath confirming that

የሚያመለክተው ሰው ቃለ መሃላ ያቀርባል። አጠራጣሪ ሁኔታ ሲያጋጥም ቦርዱ መስራች አባላቱ በሚኖሩበት አካባቢ የነዋሪነት ማረጋገጫ የመስጠት ስልጣን ካለው አካል ጋር በመተባበር ሊያጣራ ይችላል፡፡

፭/ በአባልነት ያልተመዘገበ ሰውን የተመዘገበ በማስመሰል፣ ሐሰተኛ ስምና ፊርማ በማዘጋጀት፣ የሌለን ሰው እንዳለ በማስመሰል ወይም በሌላ የተጭበረበረ መንገድ የቀረበ መረጃ በማናቸውም ሰው በሚቀርብ ጥቆማ ወይም ቦርዱ በራሱ በሚያደርገው ማጣራት የተደረሰበት እንደሆነ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት የሚወሰደው እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ፣

ሀ) ከላይ የተጠቀሰው የማጭበርበር ተግባር የታወቀው ፓርቲው በምዝገባ ላይ እያለ ከሆነ ያቀረበው የምዝገባ ማመልከቻ ውድቅ ተደርጎ ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ፓርቲው በፖለቲካ ፓርቲነት ከመመዝገብ ይከለከላል፣ እንዲሁም ከማጭበርበር ተግባሩ ጋር ግንኙነት ያለው ማንኛውም የፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ እና ግለሰብ በፓርቲ መሪነት ወይም አባልነት ከመሳተፍ ይታገዳል፡፡

ለ) ከላይ የተጠቀሰው የማጭበርበር ተግባር የታወቀው ፓርቲው ተመዝግቦ ፈቃድ ከተሰጠው በኋላ ከሆነ የተሰጠው ፈቃድ ተሰርዞ ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ፓርቲው በፖለቲካ ፓርቲነት ለመመዝገብ እንዲሁም ከማጭበርበር ተግባሩ ጋር ግንኙነት ያለው ማንኛውም የፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ እና ግለሰብ በፓርቲ መሪነት ወይም አባልነት መሳተፍ እንዳይችል መደረግ አለበት፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የፖለቲካ ፓርቲው መስራች አባላትን በሚያሰባስብበት ጊዜ የፆታን እና የተለያዩ በአከባቢው ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተዋጽኦ ባገናዘበ መልክ መሆን አለበት፡፡

፯/ ቦርዱ አንድ የተመዘገበ አገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ዝቅተኛውን የአባላት ቁጥር ያሟላ መሆኑን ፓርቲው በየሁለት አመቱ የሚያቀርበውን የአባላት ዝርዝር ሪፖርት መሠረት በማድረግ ያረጋግጣል፡፡

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት መስራች አባላት የፈረሙበት ሰነድ ለሕዝብ ይፋ የሚሆን ሰነድ ነው፡፡

the particulars of the founding members are correct. When doubtful circumstances happen, the Board may, in collaboration with the body mandated to grant proof of residence in the founding members' place of residence, investigate the circumstance.

5/ Where a fraudulent registration of a person as a member; using fictitious name and signature; or fraudulent impersonation or other presentation of fraudulent information by a party has been established following complaint by any person or investigation by the Board, without prejudice to the sanctions to be imposed in accordance with the relevant criminal law:

a) if the above-mentioned party involved in fraud is in the process of getting registered, its registration application shall be rejected, and the party shall be barred from registering as a political party for the next five years. A leader or member of the party's management or any other person who have been implicated in the fraud will be barred from party leadership or membership.

b) if the abovementioned party involved in fraud has already been registered, the registration shall be cancelled, and the party shall be barred from registering as a political party for the next five years and leader or member of the party's management or any other person who have been implicated in the fraud will be barred from party leadership or membership.

6/ The recruitment of founding members in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall reflect gender considerations and the contribution of members of the local community.

7/ The Board shall verify that a registered Nationwide Political Party has the requisite minimum number of members specified under Sub-Article (1) of this Article, based on a members' list that the party will presents every two years.

8/ The document signed by the founding members in accordance with the Sub–Article (2) of this Article shall be a document open to the public.

፱/ በማናቸውም ደረጃ ምርጫ በሚካሄድበት ዘመን የሚቀርብ የምዝገባ ጥያቄ የመራጮች ምዝገባ ከመጀመሩ ከ፺ ቀናት በፊት የቀረበ ከሆነ የእጩዎች ምዝገባ ከመጀመሩ በፊት መጠናቀቅ አለበት፡፡

**፷፭. <u>የክልል የፖለቲካ ፓርቲ ስለ መመስረት</u>**

፩/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በክልል የፖለቲካ ፓርቲነት የሚመሰረተው፤

ሀ/ ፬ መቶ ሺ መስራች አባላት ሲኖሩት፤ እና

ለ/ ከነዚህ መስራች አባላት ውስጥ ከስልሳ በመቶ በላይ የሆኑት የክልሉ መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑ ነው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱት መስራች አባላት እድሜያቸው ፲፰ ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፣ በህግ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ የመምረጥ መብታቸው ያልተገፈፈ፣ የፖለቲካ ፓርቲው አባል ለመሆናቸው ስምምነታቸውን የገለፁና በተመዘገቡበት አከባቢ ነዋሪ ስለመሆናቸው ለፓርቲው ማረጋገጫ ያቀረቡ መሆን አለባቸው፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ስር የተመለከተው የመስራች አባላት መረጃ የአባሉን ሙሉ ስም፤ ፆታ፣ እድሜ፣ ቀበሌ ወይም ወረዳ፤ እንደየአግባብነቱ የሚኖሩበትን ቦታ ልዩ ስም ወይም የቤት ቁጥር፣ የነዋሪነት ማረጋገጫ ዓይነት፣ ያቀረበው የነዋሪነት ማረጋገጫ መለያ ቁጥር ያለው ከሆነ መለያ ቁጥሩ፤ ፊርማ እና የምዝገባ ቀን የሚገልጽና እንዲሁም የመረጃ ሰብሳቢውን ስምና ፊርማ የያዘ መሆን አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) በተመለከተው መሠረት ፓርቲው ያቀረበው የመስራች አባላት መረጃ የሚረጋገጥበት መንገድ እንዲሁም የተጭበረበረ መረጃ ከተገኘ የሚወሰደው እርምጃ ከላይ በአንቀጽ ፷፬(፬) እና (፭) በተቀመጠው መሠረት ይሆናል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የፖለቲካ ፓርቲው መስራች አባላትን በሚያሰባሰብበት ጊዜ የፆታን እና የተለያዩ በአከባቢው ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተዋጽኦ ባገናዘበ መልክ መሆን አለበት፡፡

፮/ ቦርዱ አንድ የተመዘገበ የክልል የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፩) የተመለከተውን ዝቅተኛ የአባላት ቁጥር ያሟላ መሆኑን ፓርቲው በየሁለት ዓመቱ በሚያቀርበው የአባላት ዝርዝር ሪፖርት መሠረት ያረጋግጣል።

9/ Registration requests submitted at any level during any election period shall be addressed before commencement of candidates' registration if submitted 90 days prior to commencement of voter registration.

**65. <u>Formation of a Regional Political Party</u>**

1/ A political party shall be formed as a Regional Political Party where:

a) it has 4000 founding members;

b) more than sixty percent (60%) of the founding members are permanent residents of the same regional state.

2/ The founding members provided under Sub-Article (1) of this Article: must be 18 years of age and above; not deprived of the right to vote by law or a court's decision; must have expressed their consent to be members of the political party; and must have submitted to the party proof of their residence in the place of their registration.

3/ The document signed by the founding members in accordance with the Sub-Article (2) above shall specify the member's full name, sex, age, Kebele or Woreda, as appropriate special name for their residence area or house number; type of proof of residence, identification number of proof of residence if available, signature and the date of registration as well as the name and signature of the person who took down these particulars.

4/ The verification of the information about the founding members that the party presents in accordance with Sub-Articles (2) and (3) of this Article and the sanctions to be imposed if fraudulent information is discovered, shall be in accordance with Article 64 (4) and (5).

5/ The recruitment of founding members in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall reflect gender considerations and the involvement of members of the local community.

6/ The Board shall verify that a registered Regional Political Party has the requisite minimum number of members specified under Sub-Article (1) of this Article, based on a members' list that the party presents every two years.

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት መስራች አባላት የፈርሙበት ሰነድ ለሕዝብ ይፋ የሚሆን ሰነድ ነው፡፡

፰/ በማናቸውም ደረጃ ምርጫ በሚካሄድበት ዘመን የሚቀርብ የምዝገባ ጥያቄ የመራጮች ምዝገባ ከመጀመሩ ከ፺ ቀናት በፊት የቀረበ ከሆነ የእጩዎች ምዝገባ ከመጀመሩና የምርጫ ዘመቻ የጊዜ ሰሌዳ ከመውጣቱ በፊት መጠናቀቅ አለበት፡፡

፱/ ቦርዱ በአንቀጽ ፷፬ እና በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ተግባራት አፈጻጸም በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## ስለፖለቲካ ፓርቲ ምዝገባ

### ፷፮. ስለምዝገባ

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በኢትዮጵያ ውስጥ በፖለቲካ ፓርቲነት ለመንቀሳቀስ የሚችለው በዚህ አዋጅ መሠረት በቦርዱ ተመዝግቦ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ የፖለቲካ ፓርቲ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በስሙ ውል መዋዋል፣ መክሰስና መከሰስ፣ የንብረት ባለቤት ወይም ባለይዞታ መሆን፣ መሸጥ፣ መለወጥ በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ንብረት ማስተላለፍ ወይም ዓላማውን ተከትሎ ማናቸውንም ሕጋዊ ተግባሮች ማከናወን ይችላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም የፓለቲካ ፓርቲ ለማቋቋም የሚፈልጉ የዜጎች ስብስብ ለቦርዱ ጊዜያዊ የምዝገባ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ማመልከት ይችላሉ፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ፤ በጽሑፍ የሚቀርብ የምዝገባ ጥያቄ፣ ለአገር አቀፍ ፓርቲነት ቢያንስ ሁለት መቶ፣ ለክልል ፓርቲነት ቢያንስ አንድ መቶ አመልካቾች የፈረሙበት የስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ የሚመሰረተው የፖለቲካ ፓርቲ ጊዜያዊ ስም፣ የምርጫ ህጉንና ተያያዥ ህጎችን የሚያከብሩ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ እና ቦርዱ የሚወስነውን የአገልግሎት ክፍያ መፈጸማቸውን የሚገልጥ ማስረጃ ማካተት አለበት፡፡

7/ The document signed by the founding members in accordance with the Sub–Article (2) of this Article shall be a document open to public.

8/ Registration requests submitted at any level during any election period shall be addressed before commencement of candidate's registration and the announcement of the elections timetable if submitted 90 days prior to commencement of voter registration.

9/ The Board shall issue a directive to determine particulars required to implement Article 64 and this Article.

## CHAPTER TWO
## REGISTRATION OF POLITICAL PARTY

### 66. Registration

1/ Any political party can operate as a Political Party in Ethiopia only upon registration by the Board and receipt of a certificate of legal personality in accordance with this Proclamation.

2/ A Political Party that has obtained legal personality in accordance with Sub-Article (1) of this Article may enter into a contract with third parties; sue and be sued; to be owner or possessor of a property; sell, exchange, or transfer assets in any other way or execute any other lawful act that is in line with its purpose.

3/ With out prejudice to the provision of Sub-Article (1) of this Article, citizens intending to establish a political party may apply to the Board to be granted a certificate of provisional registration.

4/ The application in accordance with Sub-Article (2) above should be presented with: a written request for registration; meeting minutes with 200 signatures for a Nationwide Party or 100 signatures for a Regional Party; the provisional name of the party to be established; a confirmation to abide by the election law and other relevant laws; and receipt showing the payment of the Board's service fee.

፭/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ላይ የተጠቀሱት ሰነዶች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ጊዜያዊ የምዝገባ ፈቃድ ይሰጣል፡፡ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጠው ጊዜያዊ የምዝገባ ፈቃድ የሚያገለግለው ለሦስት ወራት ብቻ ነው፡፡ ሆኖም አመልካቾች በቂ ምክንያት ያቀረቡ እንደሆነ ጊዜያዊ ፈቃዱ ለተጨማሪ ሦስት ወራት ሊራዘም ይችላል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ጊዜያዊ የምዝገባ ፈቃድ ያገኘ የፖለቲካ ፓርቲ፣ ጊዜያዊ ፈቃዱን መጠቀም የሚችለው በዚህ አዋጅ መሠረት ፓርቲውን ለማስመዝገብ የሚያስፈልጉ ተግባራትን ለማከናወን ብቻ ይሆናል፡፡

**፷፯. <u>በፖለቲካ ፓርቲነት ለመመዝገብ ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የምዝገባ ማመልከቻ በፖለቲካ ፓርቲው መሪ ተፈርሞ ለቦርዱ መቅረብ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤

ሀ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፸፪ መሠረት የተዘጋጀ የፖለቲካ ፓርቲ መመስረቻ ጽሑፍ፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፫ መሠረት የተዘጋጀ የፖለቲካ ፓርቲው ፕሮግራም፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፬ መሠረት የተዘጋጀ የፖለቲካ ፓርቲው የመተዳደሪያ ደንብ፤

መ) የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች ስምና አድራሻ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች በኃላፊነት ለመስራት መስማማታቸውን የሚያስረዳ በፊርማቸው የተረጋገጠ ሰነድ፤

ሠ) መስራቾች የፈረሙበትና ለሕዝብ በይፋ የሚገለጽ ሰነድ፤

ረ) የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች በፓርቲው የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት ነጻና ዴሞክራሲያዊ በሆነ ምርጫ የተመረጡ መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተዘረዘሩት ሰነዶች አምስት ቅጂ ከምዝገባ ማመልከቻው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

5/ The Board shall, upon verifying that the documents specified under Sub-Article (4) of this Article have been submitted, issue a provisional registration certificate. The provisional registration certificate is valid for only three months. However, if the applicants present a satisfactory reason, the validity of provisional registration certificate may be extended for additional three months.

6/ A political party that has obtained a provisional registration certificate can use the certificate only for the purpose of conducting activities required by this Proclamation for the registration of the party.

**67. <u>Application for Registration of as a Political Parties</u>**

1/ Any application for registration of a political party shall be signed by the party leader and submitted to the Board.

2/ The application submitted in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be accompanied by the following documents:

a) the memorandum of association of the party done in accordance with Article 72 of this Proclamation;

b) the political program of the party done in accordance with Article 73 of this Proclamation;

c) the by-laws of the Poletical Party prepared in accordance with Article 74 of this Proclamation;

d) the names and addresses of the party leaders, and a document showing their consent to be leaders and endorsed by their signature;

e) the document signed by founding members which will be made available to the public;

f) the document showing that the political party leaders are elected in accordance with the party's by-law and in a free and democratic process.

3/ Each document provided under the preceding Sub-Article (2) of this Article shall be accompanied by five copies and submitted together with the application for registration.

፬/ የምዝገባ ጥያቄ ማመልከቻ ያቀረበ የፖለቲካ ፓርቲ፦

ሀ) የምዝገባ የአገልግሎት ክፍያ፤ እና

ለ) በየጊዜው ለሚደረጉ የመሠረታዊ ሰነዶች ማሻሻያ አገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) (ሀ) የተደነገገውን ክፍያ የከፈለበት ደረሰኝ ከምዝገባ መጠየቂያ ማመልከቻው ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው የአገልግሎት ክፍያ መጠን በቦርዱ ይወሰናል፡፡

፯/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ ሰነዶች ለሕዝብ ግልፅ መሆን አለባቸው፡፡

**፷፰. የቦርዱ ኃላፊነት**

፩/ ቦርዱ በአንቀጽ ፷፯ መሠረት የቀረበለትን የምዝገባ ማመልከቻ በ፳፩ ቀናት ውስጥ ከመረመረ በኋላ አመልካቹ የፖለቲካ ፓርቲው ማሟላት ያለበትን ሁሉ ያላሟላ እንደሆነ ይህንኑ በ፴ ቀናት ውስጥ እንዲያሟላ በጽሑፍ ያሳውቀዋል፡፡

፪/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በሚያደርገው ምርመራ ማመልከቻው የተሟላ ሆኖ ካገኘው በ፲፭ ቀናት ውስጥ አግባብነት ባለው የመገናኛ ብዙሃን እንዲሁም በድረ ገጹ እና በሶሻል ሚዲያ ገጾቹ በፖለቲካ ፓርቲነት ለመመዝገብ ማመልከቻ ባቀረበው ፓርቲ ስም፣ አርማ ወይም ሌሎች ጉዳዮች ላይ ተቃውሞ ያለው ማንኛውም ሰው ተቃውሞውን እንዲያቀርብ በመጋበዝ ለህዝብ እንዲገለጽ ያደርጋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ተቃውሞ ያለው ሰው ማስታወቂያው በወጣ በ፲፬ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡ ቦርዱ በዚህ ጊዜ ውስጥ ለአመልካቹ ፈቃድ አይሰጥም፡፡

፬ ቦርዱ ለምዝገባ አስፈላጊ የሆኑ ተያያዥ መረጃዎች ወይም ማብራሪያ እንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፭/ ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፯ መሠረት የሚቀርብለትን ማመልከቻና አባሪ ሰነዶች ተቀብሎ በመመርመር ሰነዶቹ በዚህ አዋጅ በተመለከተው መሠረት የተሟሉ እና ትክክለኛ መሆናቸውን አረጋግጦ፣ ፓርቲው ህገ መንግሥቱ፣ ይህንን አዋጅ፣ ሌሎች ተዛማጅ ሕጎችንና የሥነ

4/ A party applying for registration shall pay:

a) registration fee; and

b) fee for revision of basic documents when required.

5/ Receipt for payment made in accordance with Sub-Article (4) (a) of this Article shall be submitted together with the application for registration.

6/ The amount payable under sub-article (4) of this Article shall be determined by the Board.

7/ The documents of the political party registered in accordance with this Proclamation shall be made available to the public.

**68. The Board's Responsibility**

1/ The Board shall examine the application for registration based on Article 67 within 21 days; and where a political party has failed to fulfill the requirements, give the party a written notice of 30 days to fulfill the requirements.

2/ Where the Board's examination of the application as per Sub-Article (1) of this Article shows that the requirements are fulfilled, it shall, within 15 days, make a public announcement on the appropriate Mass Media, its website, social media sites, enquiring of any opposition to the party requesting registration proposed name or symbol or other related issues.

3/ Any person opposing the registration in accordance with Sub-Article (2) of this Article, shall present such opposition to the Board within 14 days from the date of the public announcement. The Board shall not issue registration permit within this period.

4/ The Board may request for supporting documents and information that are necessary for the registration process.

5/ The Board shall, upon receiving the application and supporting documents in accordance with Article 67 of this Proclamation, examine and ascertain the submission of the requisite documents and their authenticity. It shall, after requesting the party to submit a confirmation to

ምግባር ደንቦችን የሚያከብር መሆኑን ማረጋገጫ እንዲሰጥ በማድረግ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲውን ዋና ጽሕፈት ቤት በመጎብኘት የምዝገባ ማመልከቻውን በተቀበለ በ፵፭ ቀናት ጊዜ ውስጥ የምዝገባውን ሥርዓት አጠናቅቆ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለአመልካቹ ይሰጠዋል፡፡

፮/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የተመዘገበን የፖለቲካ ፓርቲ አግባብ ሆኖ ባገኘው የመገናኛ ብዙኃን ለሕዝብ ያሳውቃል፡፡

፯/ ቦርዱ በዚህ ክፍል ምዕራፍ ስምንት መሠረት የፖለቲካ ፓርቲን የገቢ ምንጭ የወጪ ዝርዝር እና ንብረት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ህገ ወጥ ድርጊት ተፈጽሞ ሲያገኝም በዚህ አዋጅ መሠረት ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

፰/ ቦርዱ:-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻ መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግሥት የተደረገ ድጋፍና የድጋፉ አጠቃቀም ዝርዝር፤እና

ለ) ስለ ፖለቲካ ፓርቲዎች አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወቅታዊ እና ዓመታዊ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፱/ ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፭ በተደነገገው መሠረት የኦዲት ሪፖርት እንደደረሰው ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም እንዲመረመር ሊያዝ ይችላል፡፡

## ፷፱. መመዝገብ ስለማይችል የፖለቲካ ፓርቲ

፩/ ለመመዝገብ ማመልከቻ ያቀረበው የፖለቲካ ፓርቲ:-

ሀ) የመረጠው ስም፣ አሕጽሮተ ስም፣ አርማ ወይም የመለያ ምልክት ከአገሪቱ ባህልና የስነ ምግባር እሴቶች አኳያ ተቀባይነት የሌለው ከሆነ፤ወይም

ለ) የመረጠው ስም፣ አሕጽሮተ ስም፣ አርማ ወይም የመለያ ምልክት በሌላ ፓርቲ የተያዘ ከሆነ ወይም ከሌላ ፓርቲ ስም፣ አሕጽሮተ ስም፣ አርማ ወይም የመለያ ምልክት ጋር መራጮችን ሊያሳስት በሚችል ደረጃ የሚቀራረብ ከሆነ፤ ወይም

abide by the Constitution, this Proclamation, other relevant laws and codes of conduct as well as visiting the party's head office, process the formalities of registration within 45 days and issue to the applicant a certificate of legal personality.

6/ The Board, using the appropriate mass media, shall notify the public of the registered political party in accordance with sub-article (5) of this Article.

7/ The Board shall, in accordance with Chapter eight of this section, monitor the income source, expenditure list and assets of a Political Party; where illegal acts are found the Board shall take the necessary measures in accordance with this Proclamation.

8/The Board shall submit periodical and yearly reports to the House of Peoples' Representatives pertaining to:

a) government's funding of political parties based on Article 100 of this Proclamation and the utilization of the fund; and

b) the overall activity of political parties.

9/ The Board shall, upon receiving the audit report as per Article 105 of this Proclamation, publicize it; and where it deems necessary it may order inspection.

## 69. Political Party Barred from Registration

1/ The political party that has submitted a registration application shall not be registered if :

a) its name; abbreviation of its name; emblem; or symbol is culturally and ethically unacceptable in the country; or

b) its name; abbreviation of its name; emblem; or symbol is in use by another party or is similar to that of another party that it is likely to result in voters' confusion; or

ሐ) የመረጠው ስም፣ አሕጽሮተ ስም፣ አርማ፣ የመለያ ምልክት፣ የመመስረቻ ጽሑፍ ወይም የመተዳደሪያ ደንብ በዘር፣ በኃይማኖት እና በመሳሰሉት ልዩነቶች ላይ የተመሰረተ ጥላቻና ጠላትነት በዜጎች፣ በብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና በሕዝቦች መካከል በማስፋፋት ጦርነትና ግጭት መፍጠርን ዓላማ ያደረገ ወይም ሰዎችን በዘር፣ በኃይማኖት ወይም በማንነት ላይ ተመስረቶ ከአባልነት ወይም ከደጋፊነት የሚያገል ከሆነ፤ ወይም

መ) የፖለቲካ ዓላማውን በትጥቅ ለማራመድ የተደራጀ ከሆነ፤ ወይም

ሠ) የውጭ ሀገር ዜጎች አባል የሆኑበት የፖለቲካ ድርጅት ከሆነ፣ ወይም

ረ) ሕገወጥ ዓላማ ለማካሄድ የተቋቋመ የፖለቲካ ድርጅት ከሆነ፣

ቦርዱ አይመዘግበውም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ውሳኔው በጽሑፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ፴ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ አቤቱታ ያቀረበው አካል ለዚህ ጉዳይ አፈፃፀም ሕጋዊ ሰውነት እንዳለው ተቆጥሮ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ተመርጦ በምዝገባ ማመልከቻው ላይ ፈርሞ ያቀረበው የፓርቲው መሪ የፓርቲው ሕጋዊ ወኪል እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

**፸. <u>በፖለቲካ ፓርቲነት ለመመዝገብ ስለማይችል ድርጅት ወይም ማኅበር</u>**

የሚከተሉት ድርጅቶች ወይም ማኅበራት በዚህ አዋጅ መሠረት በፖለቲካ ፓርቲነት ሊመዘገቡ አይችሉም፡-

፩/ በንግድ ሕግ ወይም በፍትሐብሔር ሕግ ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት፣ የንግድና ኢንዱስትሪ ሥራዎችን ለማከናወን የተቋቋሙ ማኅበሮች ወይም ድርጅቶች፤

፪/ ዓላማቸው ትርፍ ለማግኘት ያልሆነ ወይም ለበጎ አድራጎት ተግባር የተቋቋሙ ማኅበራት ወይም ድርጅቶች፤

፫/ የመገናኛ ብዙኃን፣ የሠራተኛ እና የሙያ ማሕበራት፤

፬/ የመረዳጃ ማኅበራት፤

፭/ የሃይማኖት ድርጅቶች፤

፮/ ዕድርና ዕቁብን የመሳሰሉ ማኅበራዊ ተቋሞች.

c) its name; abbreviation of its name; emblem; symbol; founding document or rules aim to foment conflict and violence based on ethnicity, religion and other similar differences and by spreading hatred and enmity among Nations, Nationalities and Peoples; or exclude people from being members or supporters on the basis of ethnicity, religion or identity; or

d) aims to fulfill its purpose through armed struggle; or

e) it has members with foreign Nationality; or

f) formed for the purpose of pursuing unlawful activities.

2/ A party that objects the decision of the Board made in accordance with Sub-Article (1) of this Article may appeal to the Federal High Court within 30 days of receiving such decision. The party that has filed the petition shall be considered as having a legal personality, and the party leader, who was elected based on the party's by-law and is the signatory of the registration application, shall be deemed to be the party's lawful representative.

**70. <u>Organization or Associations Barred from Registration as Political Party</u>**

The following organizations or associations may not be registered as political parties under this Proclamation:

1/ associations or organizations formed for the purpose of carrying on commercial and industrial activities in accordance with the Commercial Code or the Civil Code or other relevant laws;

2/ not for profit or welfare associations or organizations;

3/ Mass Media, Trade Unions and Professional Associations;

4/ Mutual help Associations;

5/ Religious Organizations;

6/ social associations such as idir, equb, and the like.

## ምዕራፍ ሦስት
## የፖለቲካ ፓርቲ ሰነዶች

**፸፩. የፖለቲካ ፓርቲ ሰነዶች**

፩/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሚከተሉት ዋና ዋና ሰነዶች ይኖሩታል፤

ሀ) የመመስረቻ ጽሑፍ፣

ለ) የፖለቲካ ፕሮግራም፣

ሐ) የመተዳደሪያ ደንብ፣

መ) የሃብትና ንብረት፣ የገቢና የወጪ ሰነዶች፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከ(ሀ) እስከ (ሐ) የተጠቀሱትን ሰነዶች ለማሻሻል የፈለገ የፖለቲካ ፓርቲ አስቀድሞ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፡፡ ቦርዱ የቀረበለትን የማሻሻያ ጥያቄ ተቀብሎ እንደ አግባብነቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፰ ድንጋጌዎች መሠረት ያስተናግዳል፡፡

**፸፪. ፖለቲካ ፓርቲ መመስረቻ ጽሑፍ**

፩/ የፖለቲካ ፓርቲ መመስረት የሚፈልጉ ግለሰቦች መስራች ሆነው ለማደራጀት የፈለጉትን የፖለቲካ ፖርቲ ማቋቋማቸውን የሚገልጹበት የመመስረቻ ጽሑፍ ይኖራቸዋል፡፡

፪/ የመመስረቻ ጽሑፉ የሚከተሉትን ዝርዝሮች የያዘ ይሆናል፤

ሀ) የፓርቲው መጠሪያ ሙሉ ስም እና አህፅሮተ ስም፤

ለ) የፓርቲው ዓርማ፤

ሐ) የፓርቲው ዓላማ፤

መ) የፓርቲው ንብረትና የገቢ ምንጭ፤

ሠ) ፓርቲው የተመሰረተበት ቀን እና ዓመተ ምህረት፤

ረ) የፓርቲው ዋና መሥሪያ ቤት እና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች አድራሻ፤

ሰ) የመተዳደሪያ ደንቡ አወጣጥ ሥርዓት.

፫/ የፓርቲው የመመስረቻ ጽሑፍ በመስራች ጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ መሆን አለበት፡፡

**፸፫. የፖለቲካ ፓርቲ ፕሮግራም**

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ዓላማው አድርጎ የያዘውን የፖለቲካ እምነት የሚቀርጽበት በፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ የሚጸድቅና የሚሻሻል የፖለቲካ ፕሮግራም ይኖረዋል፡፡

## CHAPTER THREE
## DOCUMENTS OF POLITICAL PARTY

**71. Document of a Political Party**

1/ A political party shall have the following basic documents:

a) memorandum of association;

b) political program;

c) by-laws;

d) documents related to ownership, property and revenue and expenditure.

2/ A political party that intends to amend the documents listed under Sub-Article (1) from (a) to (c) of this Article shall first notify the Board of its intention. The Board shall, as appropriate, accept and process the request for amendment in accordance with the provisions of Article 68.

**72. A Political Party's Memorandum of Association**

1/ Individuals who desire to establish a political party must have a memorandum of association in which they declare the establishment of the political party they want to organize.

2/ A memorandum of association shall include the following particulars:

a) the full name of the party and its abbreviation;

b) the emblem of the party;

c) the objectives of the party;

d) the party's assets and source of income;

e) the day and year of establishment of the party;

f) the addresses of the party's head office and branch offices;

g) the procedures of issuing the by-laws.

3/ The memorandum of association of a political party shall be adopted at the general meeting held to establish the party.

**73. Political Party's Program**

Any political party must have a program in which the political belief it pursues as its objective is formulated and the adoption and amendment of the program shall be done at the party's general meeting.

## ፸፬. የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የመተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል፡፡ የመተዳደሪያ ደንቡም የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

ሀ) የአባላት ቅበላና ስንብት ሁኔታ፤

ለ) የአባላቱ መብትና ግዴታ፤

ሐ) የፖለቲካ ፓርቲው ልዩ ልዩ አካላት፣ የሚመረጡበት ሥርዓት፣ የአገልግሎት ዘመን እና የስራ ኃላፊነታቸውን፤

መ) የአባልነት መዋጮ ዓይነትና አከፋፈል እንዲሁም አባላቱ በፓርቲው ሥራ ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ፤

ሠ) የፓርቲው የስብሰባ እና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት፤

ረ/ በአባላቱ ላይ ስለሚወሰድ የሥነ ሥርዓት እና የሥነ ምግባር እርምጃ፤

ሰ) የጠቅላላ ጉባኤ አባላትን ቁጥር ቢያንስ በዚህ አዋጅ መሠረት ፓርቲ ለመመስረት ከተቀመጠው ከዝቅተኛው የመስራች አባላት ቁጥር አምስት በመቶ በማድረግ የሚወስን ድንጋጌ፤

ሸ) የፖለቲካ ፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ቢያንስ በሦስት ዓመት አንድ ጊዜ መካሄድ ያለበት መሆኑን የሚገልጽ ድንጋጌ፣

ቀ) የፓርቲው ቅርንጫፎች አወቃቀርና አሠራርን ጨምሮ የፓርቲውን መዋቅራዊ አደረጃጀትና የስልጣን ተዋረድ፤

በ) የፓርቲውን ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የሚፈልጉ ጉዳዮችን ዝርዝር፤

ተ) የፖለቲካ ፓርቲው ከሌላ ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች ጋር ውህደት፣ ቅንጅት ወይም ግንባር የሚፈጥርበት፣ እንዲሁም ፓርቲው የሚፈርስበትን የውሳኔና የድርጊት ሂደቶች፤

ቸ) የፓርቲው አባላት ለአገር አቀፍና በየደረጃው ላሉ አገራዊ ምርጫዎች የሚታጩበት ሥርዓት፣

ኀ) የፖለቲካ ፓርቲው የሰው ኃብት፣ የፋይናንስ እና የኦዲት አስተዳደር ሥርዓት አሰራር፣

ነ) የፓርቲውን ገንዘብና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት፣ የገቢ ማስገኛ አሰራር እና በነዚህ ጉዳዮች ላይ ለመወሰን ስልጣን ያለውን አካል ወይም ኃላፊን የሚገልጽ ድንጋጌ፣

## 74. Political Party's By-Laws

1/ Any political party must have its own by laws. Such by-laws shall include the following particulars:

a) conditions for admission and expulsion of members;

b) details of the right and duty of members;

c) details of the various organs of the party, the procedure for their election, their tenure and description of their respective functions;

d) types of membership fees and payment structure as well as the members' participation level in the party's activities;

e) the party's procedures for convening meetings and passing decisions;

f) details of measures of procedure and code of conduct applicable to members;

g) a stipulation that the quorum for the party's general meeting shall be constituted by at least 5 percent of the minimum number of founding members required in this Proclamation;

h) a stipulation that the party's general meeting shall be held at least once every three years;

i) organizational structure of the party and positions within the party including the establishment and functions of party's branch offices;

j) list of matters that require the decision of the party's general Assembly;

k) the course of action and decision-making process for forming a merger, coalition, or front with other political parties, as well as for the party's dissolution;

l) The procedure for the nomination of party members for national and other various level elections;

m) The party's human resource, financial and audit administration process;

n) The party's financial and asset administration policy, income mobilization process as well as an explanation of the person or organ of the party mandated to decide on such matters;

ኘ) የፖለቲካ ፓርቲው የውስጥ አለመግባባቶች አፈታት ሥርዓት፣

አ) ማንኛውም አባል እኩል ድምፅ ያለው መሆኑን የሚገልጽ ድንጋጌ፤

፪/ የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ የፖለቲካ ፓርቲው አባል በዜግነቱ የተረጋገጠለትን መብት የሚቀንስ ወይም የተጣለበትን ግዴታ የሚሽር ሊሆን አይችልም፡፡

፫/ የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ የፓርቲው አመራሮችና በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች አመራረጥ ግልጽ፥ ነጻና ፍትሃዊ እንዲሁም በሚስጢር በሚሰጥ ድምጽ መንገድ የሚመረጡ መሆናቸውን መደንገግ አለበት፡፡

፬/ በማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ለኃላፊነት ቦታ የሚደረጉ ምርጫዎች የጾታ ተዋጽኦን ያገናዘቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

፭/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፸፭ እና ከአንቀጽ ፹፮ እስከ አንቀጽ ፺ የተደነገጉትን ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡

፮/ በፖለቲካ ፓርቲ አባላት መሀከል የፓርቲውን ሕገ ደንብ አፈፃፀም እና ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች አለመግባባት ተፈጥሮ ለቦርዱ አቤቱታ ሲቀርብ ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሃሳብ ለቦርዱ የሚያቀርብ የባለሙያዎች ጉባኤ ቦርዱ ያቋቁማል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ምዕራፍ አራት
## የፖለቲካ ፓርቲ መብት እና ግዴታ

### ፸፭. የፖለቲካ ፓርቲ በራሱ ጉዳይ ላይ ስላለው ነፃነት

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ:-

፩/ የፖለቲካ ፕሮግራሙንና የመተዳደሪያ ደንቡን የሚያፀድቅበትንና የሚያሻሽልበትን እንዲሁም ስብሰባ የሚያካሂድበትን ሥነ ሥርዓት በመተዳደሪያ ደንቡ ይወስናል፡፡

፪/ በመተዳደሪያ ደንቡ በሚወሰነው መሠረት የፖለቲካ ሥራውን የሚመሩ፣ ውሣኔ የሚሰጡ እና የሚያስፈፅሙ የአመራር አካላት ይኖሩታል፡፡

### ፸፮. ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ስለማቋቋም

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የፖለቲካ ሥራውን ለማካሄድ በሀገሪቱ ውስጥ በየትኛውም ቦታ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊያቋቁም ይችላል፡፡

o) The procedure for resolving political party's internal disputes; and

p) details as to the equality of votes between every member of the Political Party.

2/ Any by-law of political party shall not abridge the right of a member of the political party guaranteed to him as citizen or of release him from his duties as a citizen.

3/ The by-law of every political party shall stipulate that the election of its leadership and other officials at all levels must be conducted in a transparent, free and fair manner, where secrecy of the ballot is protected.

4/ Any political party when conducting election for leadership position shall ensure gender representation consideration.

5/ The by-law of every political party shall be consistent with the provisions of Article 75 and from Article 86 to Article 90 of this Proclamation.

6/ When dispute arises between members of a political party regarding the implementation of the by-law of the party and other related issues and an application is made to the Board, it shall establish a panel of experts that shall investigate and provide a recommendation on the matter. The implementation particulars will be determined by a directive to be issued by the Board.

## CHAPTER FOUR
## RIGHT AND DUTY OF A POLITICAL PARTY

### 75/ Independence of a Political Party in Respect to its Own Affairs

Every political party:

1/ Shall determine in its by-laws the procedures of adopting and amending its political program and by-laws as well as holding meetings;

2/ In accordance with its by-laws, shall have leading organs to direct, decide and implement its political activity.

### 76. Establishing Branch Offices

1/ Any Political Party may establish branch offices anywhere within the country for the purpose of carrying out its political activity.

፪/ በአገር አቀፍ ደረጃ፣ በክልልና ከክልል በታች ቅርንጫፎች ያሉት የፖለቲካ ፓርቲ በቅርንጫፎቹ መካከል ያለውን ግንኙነትና የስልጣን ተዋረድ በመተዳደርያ ደንቡ መደንገግ አለበት፡፡

**፸፯. <u>ከገቢ ግብር ነፃ ስለመሆን</u>**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከአባላቱና ከደጋፊዎቹ በሚገኘው ገቢ ላይ ምንም ዓይነት የገቢ ግብር አይከፍልም፡፡

፪/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ቀጥሮ ከሚያሰራቸው ሠራተኞች ደመወዝ ላይ በሕግ በተወሰነው መሠረት የገቢ ግብር ሰብስቦ ለመንግሥት ገቢ ከማድረግ ነፃ ነው፡፡

**፸፰. <u>ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ</u>**

፩/ ማንኛውም በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ፤

ሀ) የአባላቱን ብዛት፣ የፆታ ስብጥር፣ የእድሜ ሁኔታ እና የመኖሪያ ቦታ የሚያሳይ ዓመታዊ ሪፓርት የማቅረብ፤

ለ) ቦርዱ ሲጠይቅ በሕጉ መሠረት የሚፈለገው ዝቅተኛ የአባላት ቁጥር እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን መስፈርቶች ተሟልተው መገኘታቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ የማቅረብ፤

ሐ) ግንባር ለመፍጠር ወይም ለመዋሃድ ወይም ለመቀናጀት የሚደረጉ ስብሰባዎች ሲኖሩ ቦርዱ በስብሰባው ላይ እንዲገኝ ቢያንስ ከ፴ ቀናት በፊት የማሳወቅ፤

መ) በዚህ አዋጅ መሠረት በየዓመቱ ወይም ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ ፓርቲው እንደየአግባብነቱ በኦዲተር ወይም በሂሳብ ባለሙያ የተረጋገጠ የሃብትና ዕዳ መግለጫ በፓርቲው መሪ ፊርማ ለቦርዱ የጽሑፍ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ፤

አለበት፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (መ) የተጠቀሰው ሪፖርት የፖለቲካ ፓርቲውን የገቢ ወይም የሃብቱን ምንጭ የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

፫/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገውን ግዴታ በማያሟላ የፖለቲካ ፓርቲ ላይ የአንድ ወር ጊዜ ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ በአንቀጽ ፺፰ መሠረት አስፈላጊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

፬/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ፓርቲው መሪ በዚህ አንቀጽ መሠረት ለቦርዱ በጽሑፍ ያሳወቀው የሃብትና ዕዳ መግለጫ

2/ A political party that has branch offices at the National, Regional and Sub-Regional levels shall stipulate in its by-law, the relationship between various branches and their power structure.

**77. <u>Exemption from Income Tax</u>**

1/ Any political party shall not be liable to pay any kind of income tax on income collected from its members and supporters.

2/ Political party does not have the obligation to collect and transfer to the government, employees' salaries' income tax in accordance with the law.

**78. <u>Duty to Submit Report</u>**

1/ A political party registered in accordance with this Proclamation has the duty to:

a) Submit an annual report that outlines the number of its members, their gender and age distribution and their place of residence;

b) At the request of the Board, submit a document showing compliance with the minimum number of members required and other standards set under this Proclamation;

c) Where it intends to convene a meeting to form a front, merger, or coalition, notify the Board to attend the meeting at least 30 days in advance;

d) Submit a written report signed by the leader annually or within a timeline determined by the Board, on the party's assets and liabilities certified, as appropriate, by an auditor or an accountant.

2/ The report provided under Sub-Article (1) (d) of this Article shall disclose the income or asset sources of the political party.

3/ The Board may, after giving a one-month warning for a political party that does not comply with the obligations under Sub-Article (1) take necessary measures in accordance with Article 98 of this Proclamation.

4/ Where the property and debt in accordance with this Articles submitted in writing to the Board by a political party or a leader of a political

ሐሰተኛ ሆኖ ከተገኘ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፰ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ይጠየቃል፡፡

፭/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፮ መሠረት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ያቋቋመ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱን አድራሻ እና የመሥሪያ ቤቱን ኃላፊዎች ወይም ተወካዮች ቅርንጫፉን ባቋቋመ በአንድ ወር ውስጥ ለቦርዱ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

**፸፱. <u>መረጃ የመስጠት ግዴታ</u>**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ የተዘረዘሩ መረጃዎች እንዲያቀርብ በቦርዱ ሲጠየቅ በሰነድ የተረጋገጠ የጽሑፍ መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ የሚካሄድ ሲሆን የቦርዱ ተወካይ በስብሰባው ላይ እንዲገኝ ፴ ቀናት አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት፡፡

፫/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተጠየቀውን መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም የሰጠው መረጃ ሃሰት መሆኑን እያወቀ የሰጠ እንደሆነ ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፺፰ (፩) (መ) በተደነገገው መሠረት እርምጃ ይወስዳል፡፡

**፹. <u>የአመራር አባላትን ስለማሳወቅ</u>**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አዲስ አመራር አባላትን የመረጠ እንደሆነ ይህንኑ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በተለያየ ምክንያት የአመራር አባላቱ የተጓደሉና ቁጥራቸውም ከ፶ በመቶ ሲደመር ፩ በታች ከሆነ በ፴ ቀናት ውስጥ ምርጫ በማካሄድ ማሟላት አለበት፣ ይህንንም ክንውን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፡፡

**፹፩. <u>የፖለቲካ ፓርቲ ሰነዶች አጠባበቅ</u>**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ ምዕራፍ ስምንት ንዑስ ክፍል ሁለት የተመለከቱትን የሂሣብ መዝገብ፣ የስጦታ ሰርተፊኬት፣ የባለንብረትነት ማረጋገጫ ሰነዶችን በሚገባ የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በቦታው መጣበብና በሠራተኛ እጥረት ምክንያት ከ፲ ዓመት ዕድሜ በላይ ያስቆጠሩ የሂሣብ ሰነዶችን ማስወገድ ይችላል፡፡

party has been found untrue, notwithstanding the provisions of Article 98 of this Proclamation, it shall be liable under the appropriate provisions of the Criminal Code.

5/ A political party that has established branch office in accordance with Article 76 of this Proclamation shall notify in writing the branch office address and leaders or representatives of the office to the Board within one month of establishing the branch office.

**79. <u>Duty to Provide Information</u>**

1/ A political party has an obligation under this Proclamation to give a written information in certified documents when requested by Board.

2/ When a political party convenes a general meeting, it has to notify 30 days in advance for a Board representative to attend the meeting.

3/ Where a political party required to give information in accordance with Sub-Article (1) of this Article is unwilling to provide such information or gives intentionally untrue information, the Board shall take measures stipulated under Article 98(1) (d) of this Proclamation.

**80. <u>Notification of Management Members</u>**

1/ Any political party, when it elects new leaders, shall notify the Board in writing within one month.

2/ When a political party that loses leading members for various reasons and such number is below 50%+1, the party shall elect in their replacement within 30 days. The party shall inform this incident within a month to the Board.

**81. <u>Keeping Documents of Political Parties</u>**

1/ Any political party shall have the duty to keep proper record of the matters provided under chapter eight sub-section two of this Proclamation such as, books of account, certificates of donation, ownership deed.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, based on the reasons of space constraint and manpower shortage, books of accounts aged over 10 years may be disposed.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የፓርቲውን ሌሎች ሰነዶች በአግባቡ ጠብቆ መያዝ አለበት፡፡

**፹፪. ስለፖለቲካ ፓርቲ ዓመታዊ የሂሳብ ምርመራ**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የገቢ፣ የወጪ፣ የሃብትና የእዳ መዛግብቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ መግለጫና ሰነዶቹን በአግባቡ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡ እነዚህ መዛግብት ሊይዟቸው የሚገቡ አርእስቶችና ዝርዝሮችን ቦርዱ በመመሪያ ይወስናል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወራት ውስጥ በሚመለከተው ሕጋዊ አካል የተረጋገጠ የሙያ ብቃት ባለው የውጭ ኦዲተር ወይም ቃለ መሃላ በፈጸመ የሂሳብ ባለሙያ ወይም በቦርዱ በሚሾም ኦዲተር ሂሳቡን አስመርምሮ ለቦርዱ የኦዲት ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

፫/ የሂሳብ ምርመራው ከሚካሄድበት የበጀት ዓመት በፊት በነበረው የበጀት ዓመት የሂሳብ እንቅስቃሴው ከብር ፫ መቶ ሺ (ከብር ሶስት መቶ ሺ) በታች የሆነ የፖለቲካ ፓርቲ ዓመታዊ የሂሳብ ምርመራውን ቃለ መሃላ በፈጸመ የሂሳብ ባለሙያ አስመርምሮ ሪፖርቱን ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

፬/ የሂሳብ ምርመራው ከሚካሄድበት የበጀት ዓመት በፊት በነበረው የበጀት ዓመት የሂሳብ እንቅስቃሴው ከብር ፫ መቶ ሺ (ሦስት መቶ ሺ) በላይ የሆነ የፖለቲካ ፓርቲ ዓመታዊ የሂሳብ እንቅስቃሴውን በተመሰከረለት የወጭ ኦዲተር ወይም በቦርዱ በሚሾም ኦዲተር አስመርምሮ ሪፖርቱን ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት የሚሾመው የውጭ ኦዲተር በፖለቲካ ፓርቲው የሥራ አስፈጻሚ አካል ይሾማል፡፡

፮/ ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የሂሳብ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር እንዲመረመሩ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**፹፫. የኦዲተር ወይም የሂሳብ ባለሙያ መብት**

የፖለቲካ ፓርቲን ሂሳብ የሚመረምር ኦዲተር ወይም የሂሳብ ባለሙያ ማንኛውንም ከፖለቲካ ፓርቲ ሀብትና ንብረት ጋር የተያያዘ ሰነድ እንዲቀርብለት የመጠየቅና የመመርመር መብት አለው፡፡

3/ With out prejudice to the provision of Sub-Article (1) and (2) of this Article, every political party shall keep other documents of the party properly.

82. **Political Party Annual Audit**

1/ Any political party must keep properly its income, expenditure, assets and liabilities records, bank statements and documents. The Board will issue a directive to determine the titles and details that these documents must contain.

2/ Unless stated otherwise in this Proclamation, every political party shall commission within three months of the end of the budget year, an external auditor whose professional competency has been approved by the mandated body; an accountant who has taken a professional oath; or a Board appointed auditor to conduct the financial audit and submit to the Board an audit report.

3/ Where its financial position for the budget year preceding the one to be audited is less than Birr 300,000 (Birr three hundred thousand) the political party can assign an accountant who has taken a professional oath to conduct the annual financial audit and submit the report to the Board.

4/ Where its financial position for the budget year preceding the one to be audited is more than Birr 300,000 (Birr three hundred thousand), the political party can engage a certified external auditor, or an auditor assigned by the Board to conduct the annual audit and submit the report to the Board.

5/ The external auditor, provided in Sub-Article (2) and (3) of this Article, shall be appointed by the political party executive organ.

6/ As appropriate, the Board may request the Auditor General to investigate financial documents of any political party.

**83. Rights of Auditor or Accountant**

The auditor or accountant auditing a political party's finances has the right to request for, and examine any document related to the assets and properties of the political party.

**፹፬. ለፖለቲካ ፓርቲ ኦዲተር ሆኖ ሊሾም ወይም የሂሳብ ባለሙያ ሆኖ ሊያገለግል ስለማይችል ሰው**

ማንኛውም ሰው የፓርቲው ጠበቃ፣ ተቀጣሪ፣ የቦርድ አባል በመሆን አገልግሎ ወይም እያገለገለ ከሆነ ወይም በማንኛውም መልኩ የጥቅም ግጭት በሚያስከትል ደረጃ ከተመርማሪው የፖለቲካ ፓርቲ ጋር ግንኙነት ያለው ከሆነ የፖለቲካ ፓርቲው ኦዲተር ወይም የሂሳብ ባለሙያ ሆኖ ሊሰራ አይችልም፡፡

**፹፭. በፖለቲካ ፓርቲ ኦዲተር አሰራር**

፩/ የፖለቲካ ፓርቲ ኦዲተርም ሆነ የሂሳብ ባለሙያ ወይም እንዲሁም እርሱ ቀጥሮ ያሰማራቸው ባለሙያዎች ሥራቸውን በቅንነት፣ በታማኝነትና በገለልተኝነት ማከናወን አለባቸው፡፡

፪/ የኦዲተር የኦዲት ወይም የሂሳብ ባለሙያ የምርመራ ሪፖርት በጽሑፍ ሆኖ ለፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች መሰጠት አለበት፡፡

፫/ የፖለቲካ ፓርቲው ከሚያቀርበው የሂሳብ ሪፖርት ጋር የኦዲተሩ ወይም የሂሳብ ባለሙያው የሙያ ብቃት ሰርተፊኬት ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

**፹፮. የፖለቲካ ፓርቲ ስያሜና አርማ**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የሚመርጠው ስያሜ ከተመሳሳይ የፖለቲካ ፓርቲ ጋር የማይመሳሰል ወይም የማያደናግር የፓርቲው ብቸኛ መጠሪያ መሆን አለበት፡፡

፪/ የፓርቲው ዓርማ እና መለያ ምልክት:-

ሀ) ከሌሎች ፓርቲዎች ዓርማና መለያ ምልክት ጋር የማይመሳሰል፤

ለ) በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በዘር፣ በሃይማኖት መካከል ጥላቻና ግጭትን የማይፈጥር፤

ሐ) የጦረኝነት ወይም የሌላ ሕገወጥነት መልዕክት የማያስተላልፍ፤

መ) ከኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ወይም ዓርማ ወይም ከልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዓርማና መለያ ምልክት ወይም ከሃይማኖት ድርጅቶች ምልክቶች ጋር የማይመሳሰል፤

ሠ) የሕዝብን ሞራል፣ ሥነ ምግባር እና የመሳሰሉትን የማይነካ;

መሆን አለበት፡፡

**84/ A Person Incapable of Appointment as Political Party Auditor or Serving as an Accountant**

Whosoever served or is serving a political party in the capacity of a lawyer, an employee, a Board member, or in any manner that may cause conflict of interest, shall not be engaged as the political party auditor or accountant.

**85. Procedure of Auditor of Political Party**

1/ A political party's auditor or accountant and the professionals they engage to assist with the work shall perform their work ethically, honestly and independently.

2/ The auditor's audit or the accountant's investigation report shall be submitted in writing to the political party leaders.

3/ The certificate of professional competence of the auditor or the accountant shall be attached to the audit report to be submitted by a political party.

**86. Designation and Emblem of Political Party**

1/ The designation of any political party shall not be similar to or create confusion with the designation of another political party and shall be the sole designation of the party.

2/ The emblem and symbols of the party:

a) Shall not be similar with the emblems and symbols of other political parties;

b) Shall not create hatred and conflict among Nation, Nationalities, Race, Religion;

c) Shall not convey messages of war and other unlawful acts;

d) Shall not be similar with the symbols or emblem of Ethiopia or with those of the various international organizations or with the symbols of religious organizations;

e) Shall not be against public morality or ethics or other similar interests.

## ምዕራፍ አምስት
## የፖለቲካ ፓርቲ አባላት መብትና ግዴታ

**፹፯. በፖለቲካ ፓርቲ የመሳተፍ መብት**

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በፓርቲው ስብሰባዎች የመሳተፍ፣ ሐሳቡንና አስተያየቱን በነፃ የመግለፅ፣ ድምፅ የመስጠት እና የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት አለው፡፡

**፹፰. ስለአባልነት መዋጮ**

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ወይም የፖለቲካ ፓርቲው በሚወስነው መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲው በየጊዜው የአባልነት መዋጮ ሊከፍል ይችላል፡፡

**፹፱. ከአባልነት ስለመወገድ**

፩/ የፖለቲካ ፓርቲ አባል የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ በሚወስነው መሠረት ከአባልነት ሊወገድ ይችላል፡፡

፪/ ከፓርቲ አባልነት የተወገደ አባል በውሳኔው ላይ ቅሬታ ሲኖረው በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በየደረጃው ላሉ አካላት ማቅረብ ይችላል፡፡

**፺. ስለአባልነት**

፩/ የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባላት መስራቾቹንና ከምስረታ በኋላ ፓርቲውን በአባልነት የተቀላቀሉትንም ሁሉ ያካተተ ነው፡፡

፪/ አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ከአንድ የፖለቲካ ፓርቲ በላይ አባል መሆን አይችልም፡፡

፫/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል ወይም አመራር ለፓርቲው በጽሁፍ በቅድሚያ በማሳወቅ ከአባልነቱ ሊለቅ ይችላል፡፡ አባሉ የፌደራል ወይም የክልል ምክር ቤት አባል ከሆነ ከፓርቲው በተጨማሪ አባል ለሆነበት ምክር ቤትም ከፓርቲው ስለመልቀቁ መግለጽ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት መልቀቂያ የደረሰው ፓርቲ ወይም ምክር ቤት በ፲፭ ቀናት ውስጥ ስለጉዳዩ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፡፡ ቦርዱም ማስታወቂያው እንደደረሰው የአባሉ ስም ከፓርቲው የአባላት ዝርዝር እንዲሰረዝ ያደርጋል፡፡

፭/ በዚህ አዋጅ ስለፓርቲዎች መቀናጀት፣ ውህደት እና ስለፓርቲ መተካት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ



## CHAPTER FIVE
## RIGHT AND OBLIGATION OF MEMBERS OF A POLITICAL PARTY

**87. Political Party's Participation Right**

Any member of a political party shall have, in accordance with the by-laws of the party, the right to participate in the meetings of the party, to express freely his views and comments, to elect or to be elected.

**88. Membership Dues**

A member of a political party may pay membership dues periodically to the political party in accordance with the by-laws or decisions of the political party.

**89. Expulsion from Membership**

1/ A member of a political party may be expelled from membership in accordance with the by-law of the political party.

2/ A member aggrieved by the party's decision to expel him, may take his grievance to the various levels established according to the party's by-laws.

**90. Membership**

1/ Any political party shall have members including the founders and members admitted after the formation of the party.

2/ A person cannot be a member of more than one political party at the same time.

3/ Any member or leader of a political party may at any time withdraw membership by notifying the party in writing. If the person is a member of the Federal or State Council, in addition to the party, the person must notify his party membership withdrawal to the council where he is a member.

4/ A party or a council who received a party membership withdrawal notification in accordance with Sub-Article (3) of this Article must notify the matter to the Board within 15 days. Upon receiving the notification, the Board shall delete the name of the member from the party's membership list.

5/ With out prejudice to the provision of this Proclamation on coalition, merger and succession of political parties, if a member or

አባል ወይም አመራር ሌላ የፖለቲካ ፓርቲ የመሰረተ ወይም በምስረታ ሂደት ውስጥ የተሳተፈ ወይም የተቀላቀለ ወይም የሌላ ፖለቲካ ፓርቲን መመስረት አስመልክቶ በይፋ የቀሰቀሰ ወይም የሌላ ፓርቲን ፕሮግራም፣ ፍላጎት ወይም ፖሊሲ ያስፋፋ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተደነገገው መሰረት መልቀቂያ ባያቀርብም ከነበረበት የፖለቲካ ፓርቲ እንደለቀቀ ይቆጠራል፤ ፓርቲው እና ቦርዱም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገውን ይፈጽማሉ፡፡

፮/ የፖለቲካ ፓርቲ አባልነት በውርስም ሆነ በሌላ በማናቸውም መንገድ ለሌላ ተላልፎ የማይሰጥ በአባሉ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ነው፡፡

፯/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በማንኛውም ጊዜ አባልነቱን ሊተው ይችላል፡፡

፰/ የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ የዚህን ምዕራፍ ድንጋጌዎች መቃረን የለበትም፡፡

## ምዕራፍ ስድስት
## ስለፖለቲካ ፓርቲዎች መዋሀድ፣ ግንባር መፍጠር፣ መቀናጀት እና መተካት

### ፺፩. የፖለቲካ ፓርቲዎች ውህደት

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገቡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተዋህደው አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ለመመስረት ይችላሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለመዋሃድ የፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥያቄያቸውን የጠቅላላ ምርጫ ወይም የአካባቢ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ከመውጣቱ ከሁለት ወራት በፊት በጽሑፍ ለቦርዱ ያቀርባሉ፤ ምዝገባውም በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት በቦርዱ ይፈፀማል፡፡

፫/ ለውህደት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ማካተት አለበት:-

ሀ/ እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ በፓርቲው የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት የፓርቲው ጉባኤ ውህደቱን የተቀበለ ስለመሆኑ የሚገልፅ ውሳኔ፤

ለ/ ፓርቲዎቹ ስለውህደቱ ዝርዝር ጉዳዮች ያደረጉት የጽሁፍ ስምምነት፣ እና

ሐ/ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ሲዋሀዱ የሚኖረው አዲስ ስምና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፯ የተዘረዘሩት ሰነዶች፡፡

leader of political party establishes another political party; participates or joins in the process of establishing another party; publicly advocates the establishment of another political party; or promotes the program, interest and policy of another party; the person shall be deemed as withdrawing from his existing party even if he does not submit a withdrawal request according to Sub-Article (3) of this Article and his party and the Board will take measures stipulated in sub-article 4 of this Article.

6/ Membership of a political party may not be devolved by succession or by any other manner to another person and shall be limited to its members.

7/ Any member of political party may withdraw his membership at any time.

8/ The by-laws of a political party may not contradict the provisions of this Chapter.

## CHAPTER SIX
## MERGER, FRONT FORMATION, COALITION, AND SUBSTITUTION OF POLITICAL PARTIES

### 91. Political Parties Merger

1/ Two or more political parties registered in accordance with this Proclamation may merge and form a political party.

2/ Political parties interested in merging in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall submit their request in writing to the Board two months prior to the issuance of timetable for local or general elections; the registration shall be in accordance with the provisions of this Proclamation.

3/ The application for merger shall consist of the following:

a) Each political party, in accordance with its by-laws, should provide a decision that demonstrates the party's assembly acceptance of the merger;

b) The parties' written agreement outlining the details of the merger; and

c) The new designation for the merged political parties, and the documents listed under Article 67 of this Proclamation.

፬/ ቦርዱ የቀረበለት የውህደት ጥያቄ በዚህ አዋጅ መሰረት ቀርቧል ብሎ ሲያምን፤

ሀ) ለተዋሃዱት የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሰጥቶ የነበረውን የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰርዛል፣ አዲሱን ፓርቲ በዚህ አዋጅ መሠረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይመዘግባል፤

ለ) ቦርዱ የእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ንብረት፣ ገንዘብና አስፈላጊ ሰነዶች በውህደት ወደ ተመሰረተው የፖለቲካ ፓርቲ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ እንዲተላለፍ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

፭/ በውህደት የሚመሠረት የፖለቲካ ፓርቲ እንደሁኔታው የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፷፬ ወይም አንቀጽ ፷፭ መስፈርት ማሟላት አለበት፡፡

፮/ ውህደት ለመፈጸም የሚፈልገው የፖለቲካ ፓርቲ ለመሰረዝ ወይም ለመፍረስ በሚያደርስ የወንጀል ክስ የቀረበበት እንደሆነ ፓርቲው ክሱ ውሳኔ ሳያገኝ ወይም ሳይዘጋ ሊዋሀድ አይችልም፡፡

**፺፪. <u>የፖለቲካ ፓርቲ መዋሀድ የሚያስከትለው ውጤት</u>**

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፩(፬) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የውህደት ውጤት የሆነው አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ:-

ሀ) የተዋሃዱት የፖለቲካ ፓርቲዎች ወራሽ ይሆናል፤

ለ) የተዋሃዱት የፖለቲካ ፓርቲዎች መብትና ግዴታ ይተላለፍለታል፤

ሐ) የተዋሃዱትን የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለፈ የሂሳብ እንቅስቃሴ ሪፖርት በቦርዱ ሲጠየቅ ያቀርባል፣

መ) የተዋሃዱት የፖለቲካ ፓርቲዎች ከዚህ በፊት ያለባቸውን ፍርድ ወይም መብት ወይም በአንቀጽ ፺፩(፮) የተመለከተውን የወንጀል ክስ ሳይጨምር፣ የፍትሐብሔር ወይም አስተዳደራዊ ክርክር ተተክቶ ያስፈጽማል፣ ይፈጽማል፡፡

፪/ የውህደቱ ውጤት ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበው አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ በተመዘገበ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ውህደቱ ያስገኘውን ሀብት፣ ንብረትና ዕዳ የሚያሳይ የሂሳብ ሪፖርት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፻፲፪ እና ፻፲፬ መሠረት ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

4/ When the Board accepts the application for merger is in accordance with this Proclamation, then the Board shall:

a) Cancel the registration certificate of each political party requesting the merger and register the new party within one month in accordance with this Proclamation;

b) Order the transfer of each political party's property, funds and other necessary documents to the party created by the merger within six months.

5/ The political party created by the merger shall fulfill, as necessary, the requirements of Article 64 or Article 65 of this Proclamation.

6/ If a political party is charged with crime that can potentially deregister or dissolve the party, the party may not merge before a decision is given on the charge or the case is closed.

**92. <u>Effects of Merger of Political Parties</u>**

1/ With out prejudice to Article 91(4) of this Proclamation, the new political party created from the merger:

a) shall be the successor of the merged political parties;

b) the right and duty of the merged political parties shall be transferred to it;

c) shall submit report on the past financial activity of the merged political parties, when requested by the Board;

d) shall execute or cause the execution of decision or right or disputes of civil or administrative body pending at court previously concerned with each or either political party of the merger, excluding the criminal charges stated under Article 91(6).

2/ The new political party created from the merger and registered in accordance with this Proclamation shall submit to the Board within six months of its registration, a financial report in accordance with Article 112 and 114 of this Proclamation showing the asset, property and debt generated by the merger.

፫/ ውህደት የፈጠሩ ፖለቲካ ፓርቲዎች አባል የነበረና በማናቸውም ደረጃ ያሉ ምክር ቤቶች ተመራጭ ሆኖ በማገልገል ላይ የነበረ ሰው በውህደቱ የተፈጠረው የፖለቲካ ፓርቲ አባል ሆኖ መቀጠል የማይፈልግ ከሆነ የግል ተመራጭ እንደሆነ ተቆጥሮ የቀረውን የምርጫ ዘመን ያጠናቅቃል፡፡

**፺፫. <u>ግንባር ስለመፍጠር</u>**

፩/ የራሳቸው ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ እና አባላት ያላቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ግንባር መፍጠር ይችላሉ፡፡

፪/ ግንባር ለመፍጠር የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ማካተት አለበት:-

ሀ/ እያንዳንዱ ፓርቲ የግንባሩን ምስረታ የተቀበለ መሆኑን የሚገልፅ የጉባኤ ውሳኔ፤

ለ/ ፓርቲዎቹ ስለሚመሰርቱት ግንባር ዝርዝር ጉዳዮች ያደረጉት የጽሑፍ ስምምነት፤ እና

ሐ/ ግንባሩ የሚኖረው ስም እና እንደ አስፈላጊነቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፯ የተዘረዘሩ ሰነዶችን፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ግንባር ለመፍጠር የፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥያቄያቸውን ለቦርዱ በጽሑፍ ያቀርባሉ፣ ቦርዱም በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ምዝገባውን ይፈፀማል፡፡

፬/ ቦርዱ ከላይ የተመለከቱ ሁኔታዎችን አሟልቶ የቀረበን የግንባር ምሥረታ ጥያቄ ተቀብሎ:-

ሀ) የግንባሩ አባል ድርጅቶች የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሳይሰረዝ ለግንባሩ ሌላ የምዝገባ የምስክር ወረቀት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይሰጠዋል፡፡

ለ) የእያንዳንዱ የግንባሩ አባል ድርጅቶች በተናጠል የሚኖራቸው ሀብትና ንብረት እንደተጠበቀ ሆኖ ግንባሩ የራሱ ሀብትና ንብረት ይኖረዋል፡፡

**፺፬. <u>የፖለቲካ ፓርቲዎች መቀናጀት</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገቡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለተወሰነ ጊዜ እና በተወሰኑ ጉዳዮች ዙሪያ ተቀናጅተው እንደ ሁኔታው በአገር አቀፍ ወይም በክልል ደረጃ ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ፡፡

3/ A member of the merged political parties who is serving in an elected office at any council level and does not want to continue as a member of the new merged party shall be deemed as an independent elected official for the rest of electoral period.

**93. <u>Formation of Front</u>**

1/ Two or more political parties that have their own programs, by-laws and members may form a common front.

2/ The application to form a front shall include the following:

a) a decision expressing acceptance of the front formation by the assembly of each party;

b) a written agreement between the parties with details about the front to be created; and

c) the name of the front, and where appropriate, the documents listed under Article 67 of this Proclamation.

3/ Political parties interested in forming a front in accordance with sub-article (1) of this Article shall submit their request in writing to the Board; the registration shall be effected in accordance with the provisions of this Proclamation by the Board.

4/ The Board by accepting the request of front formation applicant full filled the condition listed above:

a) without canceling the certificate of registration of member parties of the front, the Board shall give another certificate of registration to the front within one month;

b) With out prejudice to the assets and properties of each of the front's political party, the front shall have its own asset and property.

**94. <u>Political Parties Coalition</u>**

1/ Two or more political parties registered in accordance with this Proclamation may, for a limited period and specified objectives, form a coalition to work Nationwide or at Regional level.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ለመቀናጀት የፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥያቄያቸውን የጠቅላላ ምርጫ ወይም የአካባቢ ምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ከመውጣቱ ከሁለት ወራት በፊት በጽሑፍ ለቦርዱ ማቅረብ አለባቸው፡፡

፫/ ተቀናጅተው ለመንቀሳቀስ የፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች እያንዳንዳቸው በየፓርቲው የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት የፖለቲካ ፓርቲው ከፍተኛ አመራር የተስማማበት መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ በማያያዝ የጽሑፍ ማመልከቻ ለቦርዱ ማቅረብ አለባቸው፡፡ ቦርዱ የመቀናጀት ጥያቄው በዚህ አዋጅ የቀረበ መሆኑን አረጋግጦ ጊዜያዊ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

፬/ ለመቀናጀት የፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ እንቅስቃሴ የስምምነት ነጥቦችን የያዘ ሰነድ ለቦርዱ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ሕጋዊ ሰውነቱን እንደያዘ ይቀጥላል፡፡

### ፺፭. የፖለቲካ ፓርቲ መተካት

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በፓርቲው ጉባኤ ውሳኔ ስሙንና ፕሮግራሙን ለውጦ በአዲስ የፖለቲካ ፓርቲነት ሊመዘገብ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በአዲስነት የተቋቋመው የፖለቲካ ፓርቲ የፈረሰው የፖለቲካ ፓርቲ መብት እና ግዴታ ይተላለፍለታል፡፡

፫/ አዲስ የተተካው የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ መሠረት መመዝገብ አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሰባት
## የፖለቲካ ፓርቲ መሰረዝ ወይም መፍረስ

### ፺፮. የፖለቲካ ፓርቲን ከምዝገባ መሰረዝ

የፖለቲካ ፓርቲ ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ምክንያት ከፖለቲካ ፓርቲነት ሊሰረዝ ይችላል፤

፩/ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በራሱ ፈቃድ ከምዝገባ እንዲሰረዝ ሲጠይቅ፤

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት ቦርዱ ሲወስን፤ ወይም

፫/ የፖለቲካ ፓርቲው ከምዝገባ እንዲሰረዝ በዚህ አዋጅ መሠረት ፍርድ ቤት ውሳኔ ሲሰጥ፡፡

2/ Political parties interested in working in a coalition in accordance with Sub-Article (1) of this Article must submit their application to the Board two months prior to the issuance of timetable of the general or local elections.

3/ Political parties interested in working in a coalition shall submit to the Board a written application attached with a document expressing the agreement of each political party's respective top leaders. The Board, when it accepts the application in accordance with this Proclamation, shall give temporary certificate.

4/ Political parties interested in working in a coalition shall submit to the Board a document consisting of the points of agreement concerning their common activity.

5/ Notwithstanding the provision of this Article, each political party of the coalition shall retain its independent legal personality.

### 95. Political Party Substitution

1/ Any political party may register as a new political party by changing its name and program upon the decision of the party assembly.

2/ The right and duty of the dissolved political party shall be transferred to the newly established political party in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

3/ The newly replaced political party shall be registered in accordance with this Proclamation.

## CHAPTER SEVEN
## CANCELLATION AND DISSOLUTION OF POLITICAL PARTY

### 96. Canceling the Registration of Political Party

A political party may be cancelled for one of the following reasons:

1/ when the party, in accordance with its by-laws, requests to be canceled;

2/ when the Board decides based on this Proclamation; or

3/ the cancellation of the registration of the political party is ordered by a court based on this Proclamation.

**፺፯. <u>በፖለቲካ ፓርቲው ጥያቄ ከምዝገባ ስለመሰረዝ</u>**

፩/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ራሱ ከፖለቲካ ፓርቲነት እንዲሰረዝ ቦርዱን በጽሑፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከፖለቲካ ፓርቲነት ለመሰረዝ የቀረበ ማመልከቻ በፓርቲው መሪ የተፈረመ መሆን ይገባዋል፡፡

፫/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተገለፀው ማመልከቻ ጋር የሚከተለውን አያይዞ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት:-

ሀ) የፖለቲካ ፓርቲውን የኦዲት፣ የሃብትና ንብረት መግለጫ ሪፖርት፣ እና

ለ) ስለፓርቲው መፍረስ በፖለቲካ ፓርቲው ጉባኤ የተወሰነበት ሰነድ፡፡

፬/ ከፖለቲካ ፓርቲነት ለመሰረዝ ማመልከቻ ባቀረበ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ላይ ተቃውሞ ወይም ሌላ የመብት ጥያቄ ያለው ማንኛውም ሰው ተቃውሞ ማቅረብ እንዲችል ቦርድ የመሠረዝ ማመልከቻ መቅረቡን በተለያየ የማስታወቂያ መንገድ ለሕዝብ ይገልፃል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ተቃውሞ ያለው ሰው ማስታወቂያው በወጣ በ፲፭ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡ ቦርዱ በዚህ ጊዜ ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲውን አይሰርዝም፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ቦርዱ ለመሰረዝ ላመለከተው ፓርቲ ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) የተመለከተው ጊዜ ባበቃ በ፴ ቀናት ውስጥ ለጠያቂው ፓርቲ በጥያቄው መሠረት ከፓለቲካ ፓርቲነት መሰረዙን በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡ የፓርቲውን መፍረስም ሕዝቡ እንዲያውቀው መደረግ አለበት፡፡

**፺፰. <u>የፖለቲካ ፓርቲን በቦርዱ ውሳኔ ከምዝገባ ስለመሰረዝ</u>**

፩/ ቦርዱ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የፖለቲካ ፓርቲን ከምዝገባ ሊሰርዝ ይችላል:-

ሀ) የፖለቲካ ፓርቲው የስም፣ የመለያ ምልክት፣ የሰነድ፣ የአመራር፣ የዋና ጽሕፈት ቤት እና የመሳሰለውን ለውጥ ሲያደርግ ያለ በቂ ምክንያት በዚህ አዋጅ መሠረት

**97. <u>Canceling Registration upon the Request of the Political Party</u>**

1/ A political party may, in accordance with its by- laws, request in writing for the Board to cancel its registration.

2/ The application for cancellation presented in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be signed by the party leader.

3/ The political party shall attach the following particulars with its application to the Board as referred in Sub-Article (1) of this Article :

a) the political party's audit, asset and property report; and

b) the document in which the assembly of the political party decided to dissolve the party.

4/ The Board shall make a public announcement of the cancellation application submitted by a political party, through various advertisement means, to enable any person who has an objection to such application or a right's claim, to present his objection.

5/ A person who has an objection in accordance with Sub-Article (4) of this Article, shall present the objection to the Board within 15 days from the date of announcement; the Board shall not cancel the political party within this period.

6/ In accordance with this Article, and within 30 days after conclusion of the time period outlined in Sub-Article (5) of this Article, the Board shall notify in writing to the party that requested cancellation that the political party has been cancelled in accordance with its request; The public shall be notified of the party's dissolution.

**98. <u>Canceling Registration of Political Party Upon the Decision of the Board</u>**

1/ The Board may cancel the registration of a political party for one of the following reasons:

a) the political party has not notified the Board without appropriate reason and in accordance with the provisions of this Proclamation when it changes its name,

ለቦርዱ ሳያሳውቅ የቀረ እንደሆነና ይህንኑ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ እንዲያስተካክል በቦርዱ ተጠይቆ ሳያስተካክል የቀረ እንደሆነ፣

ለ) የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ መሠረት ለቦርዱ ማቅረብ ያለበትን ዓመታዊ የስራ፣ የሂሳብ፣ ወይም ሌሎች ሪፖርቶች በአዋጁ በተወሰነው ጊዜ ሳያቀርብ የቀረ እንደሆነና ይህንኑ በ፴ ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ በቦርዱ ተጠይቆ ያለ በቂ ምክንያት ሳያቀርብ የቀረ እንደሆነ፣

ሐ) የፖለቲካ ፓርቲው በዚህ አዋጅ እና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ማካሄድ ከሚገባው ጊዜ በሦስት ወር የዘገየ እንደሆነ እና ከዚህ በኋላ ቦርዱ በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉባኤውን ሳያካሂድ የቀረ እንደሆነ፣

መ) የፖለቲካ ፓርቲው በሁለት ተከታታይ የምርጫ ወቅቶች በጠቅላላ ወይም የአካባቢ ምርጫ ውድድር ሳይሳተፍ የቀረ እንደሆነ፣

ሠ) የፖለቲካ ፓርቲው በማጭበርበር ወይም እያወቀ ወይም ማወቅ የተገባው ሆኖ ሳለ አሳሳች መረጃ በማቅረብ የተመዘገበ ከሆነ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት መረጃ ሲጠየቅ የሐሰት መረጃ ለቦርዱ የሰጠ እንደሆነ፡፡

ረ) አግባብነት ባላቸው ሌሎች ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፖለቲካ ፓርቲው ኃይልን መሠረት ያደረገ የአመጻ ተግባር፣ ከሙስና ጋር ተያያዥነት ያላቸው የወንጀል ድርጊቶች እና የማጭበርበር ድርጊቶች የፈጸመ እንደሆነ፣

፪/ ቦርዱ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን ጥሷል ብሎ ሲያምን ፓርቲው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስህተቱን እንዲያስተካክል የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡ በማስጠንቀቂያው መሠረት ያላስተካከለ እንደሆነ እንደ አግባብነቱ ከምዝገባ ሊሰርዘው ይችላል፡፡

፫/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ መሠረት በተጠሪው የፖለቲካ ፓርቲ ላይ ውሳኔ ከማሳለፉ በፊት ፓርቲው መከላከያውን አቅርቦ እንዲያሰማ ማድረግ አለበት፡፡ ቦርዱ የፖለቲካ ፓርቲውን ከምዝገባ ከመሰረዙ በፊት ፓርቲው ታግዶ እንዲቆይ ሊወስን ይችላል፡፡

emblem, document, leadership, head office and other similar change and when it has not responded within two months the Board's request to correct such actions.

b) Where the political party fails to submit to the Board annual performance, audit, or other periodical reports required in accordance with this Proclamation within the stipulated timeframe and having been granted a 30 days extension by the Board, fails to submit the same without sufficient reason;

c) Where a political party has delayed in holding a members' general meeting by three months from the time stipulated in this Proclamation or its by-laws and fails to convene the assembly within the subsequent deadline granted by the Board;

d) the political party fails participate for two successive elections at general or local elections;

e) the political party has been registered by fraud, knowingly or when it should know presents false information or when requested in accordance with this Proclamation submits false information to the Board.

f) With out prejudice to the provisions of other relevant laws, if the party has been engaged in violent rebellion, crimes related to corruption or fraudulent activities.

2/ Where the Board is of the opinion that a political party has contravened the provisions of this Proclamation to the same degree as those listed under Sub-Article (1) of this Article, it shall issue the party a written warning requesting it to rectify the situation within one month. If the political party fails to comply with the warning, the Board may, where appropriate, cancel the registration of the party.

3/ The Board shall, before taking a decision against a political party in accordance with this Article, give such party the opportunity to present its defense. The Board may, prior to cancelling the registration of the political party, may decide to suspend the party.

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ቦርዱ ያሳለፈውን ውሳኔ የተቃወመ የፖለቲካ ፓርቲ ውሳኔው በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**፺፱. የፖለቲካ ፓርቲ መሰረዝ ወይም መፍረስ ውጤት**

፩/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በራሱ፣ በቦርዱ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ከፈረሰበት ቀን ጀምሮ ፓርቲው ወይም የፓርቲው ሃላፊዎች በፓርቲው ስም መንቀሳቀስ አይችሉም፡፡

፪/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በራሱ፣ በቦርዱ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ሲፈርስ የፓርቲው ንብረት ላለበት ዕዳ መሸፈኛ ይውላል፡፡

፫/ የፖለቲካ ፓርቲው ዕዳ የሌለበት ከሆነ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ዕዳውን ከፍሎ የተረፈ ቢኖር ቀሪው ገንዘብና ንብረት በቦርዱ ትእዛዝ ለሥነ ዜጋና መራጮች ትምህርት እንዲውል ይደረጋል፡፡

## ምዕራፍ ስምንት
## ስለፖለቲካ ፓርቲዎች የገቢ ምንጭ እና የንብረት ሁኔታ

### ንዑስ ክፍል አንድ
### ከመንግሥት ስለሚሰጥ ድጋፍ

**፻. በመንግሥት የሚሰጥ ድጋፍ መጠንና መስፈርቶቹ**

፩/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ህጋዊ ስራቸውን ለማከናወንና ሃላፊነታቸውን ለመወጣት ይችሉ ዘንድ መንግስት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተጠቀሱት መስፈርቶች መሰረት የሚያደርገውን ድጋፍ ቦርዱ ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሠረት አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሚያገኘው የገንዘብ ድጋፍ መጠን በሚከተሉት መስፈርቶች መሠረት ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል:-

ሀ) ለፌደራል እና ለክልል ምክር ቤቶች በተደረጉ ምርጫዎች ያገኘው የመራጮች ድምጽ ብዛት፣

ለ) ከአባላቱና ደጋፊዎቹ ከሚያገኘው ገቢ መጠን፣

ሐ) ፓርቲው ለውድድር የሚያቀርባቸው የሴት እጩዎች ብዛት፣

4/ A political party that objects the decision of the Board in accordance with this Article may appeal within 30 days to the Federal High Court.

**99. Effect of Cancellation or Dissolution of Political Party**

1/ Where a political party is dissolved by a decision made by the party itself, the Board or a court decision, the party or the party leaders shall not operate in the name of the party starting on the effective date of the dissolution.

2/ Where a political party is dissolved by a decision made by the party itself the Board or a court decision, the property of the party shall be expended to cover its debt.

3/ Where the political party has no liabilities or there remains an amount after covering the debt as referred in sub-article (1) of this Article, the remaining fund or property shall be expended, upon the order of the Board, on civic and voter education.

## CHAPTER EIGHT
## SOURCE OF INCOME AND PROPERTY AFFAIRS OF POLITICAL PARTIES

### SUB-SECTION ONE
### SUPPORT GRANTED FROM GOVERNMENT

**100/ Government Funding Amount and Eligibility Criteria**

1/ To enable political parties to conduct legal operations and carry out their obligations, the Board shall seek approval of the FDRE House of Peoples' Representatives, government's support to parties, based on the criteria established under sub-article2 this Article.

2/ The amount of financial support that a political party receives, in accordance with Sub-Article (1) of this Article, shall be determined by a directive to be issued by the Board based on the following criteria:

a) the number of votes it wins at Federal and State Council elections;

b) the income it receives from members and supporters;

c) the number of female candidates it nominates;

መ) የፓርቲው የሴቶች አባላት ብዛት እና የሴቶች አመራር አባላት ብዛት፤

ሠ) ፓርቲው ለውድድር የሚያቀርባቸው የአካል ጉዳተኛ እጩዎች ብዛት፤

ረ) የአካል ጉዳተኞች አባላት እና የአካል ጉዳተኛ አመራሮች ብዛት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም አንድ ፓርቲ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከተሰጠው ጠቅላላ የመራጮች ድምጽ ያገኘው ዜሮ ነጥብ ሃያ ፭፭ ከመቶ ወይም ለተወዳደረበት የክልል ምክር ቤት ነጥብ ፭ ከመቶ ያነሰ ከሆነ ከመንግሥት የሚሰጠውን ድጋፍ አያገኝም፡፡ ሆኖም ይህ የመቶኛ ቅድመ ሁኔታ አነስተኛ ቁጥር ያለውን ብሔረሰብ ወይም ህዝብ ለመወከል የተደራጁ ፓርቲዎችን አይመለከትም፡፡

፬/ መንግሥት ከላይ ከተገጸው የገንዘብ ድጋፍ በተጨማሪ የቁሳቁስና የአገልግሎት ድጋፎችን ሊያደርግ ይችላል።

፭/ የግል እጩ ተወዳዳሪዎች ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ከመንግሥት የሚሰጥ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

**፻፩. <u>በመንግሥት ስለሚሰጥ ድጋፍ ምንጭ</u>**

በመንግሥት የሚሰጠው ድጋፍ:-

፩/ ከመንግሥት የሚመደብ፣

፪/ ከውጭ፣ ከሀገር ውስጥ ወይም ከሌላ ከማንኛውም አካል ከሚገኝ ድጋፍ ወይም እርዳታ ይሆናል፡፡

**፻፪. <u>መ ር ሀ</u>**

፩/ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጥ የመንግሥት ድጋፍ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት በፍትሃዊነት እና ያለ አድልዎ መፈጸም አለበት፡፡

፪/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግሥት የተሰጣቸውን ድጋፍ በአግባቡ እና ለታለመለት ተግባር ማዋላቸውን የሚያሳውቁበት የግልጽነትና የተጠየቂነት መርህ መከተል አለባቸው፡፡

**፻፫. <u>በመንግሥት የሚሰጥ ድጋፍ አስተዳደርና የሚከፋፈልበት ሁኔታ</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፻ (፪) መሠረት በመንግሥት የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ የሚተዳደረውና የሚከፋፈለው በቦርዱ ነው፡፡

d) the number of female members of the party and the number of females in leadership positions;

e) the number of people with disability candidates that it nominates; and

f) the number of people with disability members of the party and the number of people with disability in leadership positions.

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (3) (a) of this Article, a party shall not receive government funding if it receives less than 0.25 percent of the total number of votes for the House of Peoples' Representatives or less than 0.5 percent of the total votes cast for the State Council. However, this minimum percentage requirement shall not be applicable to parties established to represent minority Nations or Nationalities.

4/ In addition to the financial support stated above, the government may provide support in kind or service donation.

5/ Independent candidates shall receive government funding based on a directive to be issued by the Board.

**101. <u>Source of Government Support</u>**

The support granted by the government comes from:

1/ government allocation;

2/ support or aid received from foreign, domestic or any other body.

102. **<u>Principle</u>**

1/ The government support for political parties shall be rendered equitably and without discrimination in accordance with this Proclamation.

2/ Political parties shall, to demonstrate that the support granted by the government has been utilized properly and for the intended purpose, follow principle of transparency and accountability.

**103. <u>The Management and Distribution of Government Support</u>**

1/ The financial support provided by the government in accordance with Article 100 (2) shall be managed and distributed by the

ቦርዱ ለዚህ ተግባር አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ይይዛል፡፡

፪/ በመንግስት የሚሰጠው ዓመታዊ የገንዘብ ድጋፍ በሁለት ጊዜ ክፍያ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

፫/ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻ (፪) መሠረት በበጀት ዓመቱ የሚሰጣቸው የገንዘብ ድጋፍ መጠን ተሰልቶ እንዲሰጣቸው ከመስከረም ፴ ቀን በፊት ጥያቄ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ቦርዱ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚደረገውን ድጋፍ መጠን እስከ ነሃሴ ፴ ቀን ድረስ መወሰን አለበት፡፡

፬/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ጥያቄ ሲቀርብለት የፖለቲካ ፓርቲው በሚያቀርበው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የሚገባውን የገንዘብ መጠን ይሰጣል፡፡ ሆኖም በበጀት ዓመቱ የገንዘብ ድጋፍ እንዲሰጠው ለሚጠይቅ የፖለቲካ ፓርቲ ገንዘቡን ከመስጠቱ በፊት ቦርዱ ፓርቲው በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት በመንግሥት የተሰጠን የገንዘብ ድጋፍ የሂሳብ መዝገብ አስቀርቦ መመርመርና ችግር እንደሌለበት ማረጋገጥ አለበት፡፡ ቦርዱ ፓርቲው የሂሳብ መዝገብ ምርመራ ሪፖርት የሚያቀርብበትን ጊዜ በአንድ ወር ሊያራዝምለት ይችላል፡፡

፭/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲ የሚሰጥ ድጋፍ:-

ሀ) የፖለቲካ ፓርቲው የመንግሥት ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ከሚያደርጉት መስፈርቶች ውስጥ **ለመስፈርቱ የተቀመጠውን ድጋፍ ያጣል**፣

ለ) መመዘኛው ከተጓደለበት ቀን ጀምሮ የተሰጠውን ድጋፍ መጠቀም አይችልም፤

ሐ) መመዘኛው ከተጓደለበት ቀን ጀምሮ የተሰጠውን ድጋፍ ተመላሽ ያደርጋል፤

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) (ለ) እና (ሐ) የተደነገጉት ቢኖሩም የፖለቲካ ፓርቲው የተሰጠውን ድጋፍ ሥራ ላይ ለማዋል መመዘኛው ከተጓደለበት ቀን አስቀድሞ የገባቸው የውል ግዴታዎች ካሉ ቦርዱ ተመላሽ መደረግ ከሚገባው ገንዘብ ታሳቢ ሊያደርግለት ይችላል፡፡

Board. The Board shall keep information necessary for this purpose.

2/ The government's annual financial support shall be made in two installment payment.

3/ Political parties shall submit their request for financial support before Meskerem 30, so that the amount they will receive for the financial year can be calculated and allocated in accordance with Article 100 (2). The Board shall determine the amount to be allocated to political parties up to Nehase 30.

4/ The Board shall allocate the appropriate amount to a party that has submitted a request in accordance with Sub-Article (3) based on the timetable submitted by the party. The Board shall however, before granting the party the financial support for the coming financial year, request and examine the financial statements for government funding for the previous year and ascertain that there are no anomalies. The Board may extend by one month the timeframe for the party to submit the financial record investigation report.

5/ The support granted to political party in accordance with this Proclamation shall be denied:

a) When the political party fails to meet one of the requirements for eligibility for government funding shall lose the support;

b) shall stop utilizing the support from the date it fails to meet the eligibility requirements;

c) shall refund the support from the date it fails to meet the requirements;

d) notwithstanding the provisions of Sub-Article (4) (b) and (c), the Board may allow the party to withhold part of the fund it requires to meet contractual obligations entered prior to the time it failed to meet the requirements for state funding ended.

**፩፻፬. ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጥ ድጋፍ ስለሚመራበት አሰራር**

፩/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግሥት የተሰጣቸውን ድጋፍ አጠቃቀማቸውን በወጪ አርዕስት በመዘርዘር በኦዲተር ወይም በሂሳብ ባለሙያ የተረጋገጠ ወቅታዊ የሂሳብ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው፡፡

፪/ ቦርዱ መንግሥት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠውን በጥቅም ላይ ያልዋለ ድጋፍ ተመላሽ የሚደረግበትን፣ የድጋፍ አጠቃቀምን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፡፡

**፩፻፭. የፖለቲካ ፓርቲ የሂሳብ አያያዝ**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ:-

ሀ) በመንግሥት የሚሰጠውን ድጋፍ በአገር ውስጥ ባለ ባንክ በተከፈተ የተለየ የባንክ ሂሳብ ማስቀመጥ አለበት፤

ለ) አግባብ ባለው ህግ መሠረት ሂሳቡን ማንቀሳቀስ አለበት፤

ሐ) የተሰጠውን ድጋፍ በተለየ የሂሳብ መዝገብ በየወጪ አርዕስቱ ዘርዝሮ መያዝ አለበት፤

መ) በፋይናንስ ህግ መሠረት በበጀት ዓመቱ ከመንግሥት የተሰጠውን የገንዘብ መጠን እና ገንዘቡን ለምን ተግባር እንዳዋለ የሚያሳይ በኦዲተር ወይም በሂሳብ ባለሙያ የተረጋገጠ ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ ኦዲተሩ ወይም የሂሳብ ባለሙያው የመረመረውን ሂሳብ ከህግና መመሪያ ውጭ ወጪ የተደረገ መሆን አለመሆኑን በኦዲት ሪፖርቱ ላይ አስተያየት መስጠት አለበት፡፡

፫/ የፌደራል ዋና ኦዲተር ከመንግሥት የተሰጠን ድጋፍ አጠቃቀም በተመለከተ በማንኛውም ጊዜ የፖለቲካ ፓርቲዎችን መመርመር ይችላል፡፡

**፩፻፮. ስለተጠያቂነት እና ቅጣት**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከመንግሥት የሚሰጠውን ድጋፍ ከታለመለት ዓላማ ውጭ ካዋለ ወይም በወቅቱ ሪፖርት ካላቀረበ ወይም ሐሰተኛ የሂሳብ ሰነድ ያቀረበ እንደሆነ፣ ወይም ከሚሰጠው ድጋፍ ጋር በተያያዘ ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ፤

ሀ) የሚሰጠው ድጋፍ ሊቀነስበት ወይም ሊቋረጥበት ይችላል፤

**104/ The Rule Applicable to the Support Granted to Political Parties**

1/ Political parties shall submit a report, certified by an auditor or an accountant, with details of government grant support utilized listed under expenditure heading.

2/ The Board shall issue a directive on the use and refund of unused government grants to political parties.

**105. Political Party's Books of Account**

1/ Any political party shall:

a) deposit the government grant support in a locally opened, separate bank account;

b) transact the account in accordance with the relevant law;

c) keep the granted support in specific books of account by listing under every expenditure heading; and

d) submit an annual audit report, certified by an auditor or an accountant, in accordance with the financial law, specifying the amount granted by the government in the budget year and the for which the money has been expended.

2/ The political party shall forward its comment on the audit report as to whether the audit has been conducted outside the scope of the law and directive.

3/ The Federal Auditor General may at any time inspect political parties concerning the utilization of the government support grants.

**106. Responsibility and Penalty**

1/ Where any political party utilizes the government grant outside the purpose of the support, fails to submit report on time, submits a false financial document, or is in default on its grant's obligation:

a) the support for the party may be reduced or terminated;

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመለከተውን ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ህግ ይጠየቃል፡፡

፪/ ቦርዱ በፖለቲካ ፓርቲ አላግባብ ወጪ የሆነን ገንዘብ ክስ በመመስረት ወይም በማቻቻል ሊያሰመልስ ይችላል፡፡

፩፻፯. **ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስለሚቀርብ የሂሳብ ሪፖርት**

፩/ ቦርዱ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የተደረገውን ድጋፍ አስመልክቶ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ውስጥ ሪፖርቱን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማቅረብ አለበት፡፡ ይህ ሪፖርት:-

ሀ) በበጀት ዓመቱ ለፓርቲዎች ድጋፍ እንዲውል በመንግሥት የተመደበውንና ከሌላ ምንጭ የተገኘውን ጠቅላላ መጠን፣

ለ) በበጀት ዓመቱ ለእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ የተመደበውን የድጋፍ መጠን፣

ሐ) ህግ በሚፈቅደው መሠረት በእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ በበጀት ዓመቱ ወጪ የተደረገ የገንዘብ መጠን፣

መ) በበጀት ዓመቱ የታየውን የሂሳብ ሚዛን ያካተተ፤

መሆን አለበት፡፡

፪/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ሪፖርት ለዋናው ኦዲተር ጭምር መላክ አለበት፡፡

፫/ ዋና ኦዲተሩ ይህ የሂሳብ ሪፖርት በደረሰው በ፷ ቀናት ውስጥ በጉዳዩ የሚያዘጋጀውን የሂሳብ መግለጫ ጋር በማያያዝ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መላክ አለበት፡፡

**ንዑስ ክፍል ሁለት**

**የገቢ ምንጭ**

፩፻፰. **የፖለቲካ ፓርቲ የገንዘብ ምንጭ**

፩/ የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ የገንዘብ ምንጭ:-

ሀ) ከአባላቱ የሚሰበሰብ የአባልነት መዋጮ፤

ለ) ቦርዱ አጥንቶ በሚያሰቀምጠው ጣሪያ መሠረት በኢትዮጵያዊያን ግለሰቦች ወይም ኢትዮጵያዊያን በሚቆጣጠሯቸው ኩባንያዎች የሚደረግ ስጦታ ወይም እርዳታ፤

ሐ) በአንቀጽ ፻ በተደነገገው መሠረት ከመንግሥት ከሚሰጠው ድጋፍና ዕርዳታ፣

ሊሆን ይችላል፡፡

b) any political party or person found guilty in accordance with Sub-Article (1) of this Article may be penalized in accordance with the appropriate criminal law; and

2/ The Board may request a political party to return the amount of expenditure not utilized properly through a court suit or set-off.

107. **Submission of Audit Report to the House of Peoples' Representatives**

1/ The Board shall, within a month after the end of the budget year, submit a report to the House of Peoples' Representatives on the support granted to political parties. The report shall include:

a) the total amount of government support allocated to political parties and any other sources in the budget year;

b) the amount of support allocated to each political party in the budget year;

c) the amount of expenditure in the budget year by each political party as allowed by law; and

d) the balance of account resulted in the budget year.

2/ The Board shall send the report mentioned in Sub-Article (1) of this Article to the Auditor General as well.

3/ The Auditor General shall, within 60 days of receiving the audit report, attach the report along with related financial analyses and send it to the House of Peoples' Representatives.

**SUB-SECTION TWO**

**SOURCE OF INCOME**

108. **Political Party's Source of Income**

1/ The income source of a political party may be:

a) membership dues collected from members;

b) donations or grants by Ethiopian Nationals or Companies controlled by Ethiopians in accordance with the limit to be set by the Board based on a study the Board conducts;

c) government grant and support to be provided in accordance of Article 100 of this Proclamation.

፪/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የገንዘብ አቅሙን ለማጎልበት የሚያግዙ የገቢ ማስገኛ ኮንፍረንሶችን እና ግብዣዎችን በማዘጋጀት፣ የተለያዩ ሁነቶችን በማስመልከት የሚያዘጋጇቸውን አልባሳት እንዲሁም የሚያዘጋጇቸውን የምርምር ውጤቶች፣ መጽሃፍትን እና መጽሔቶችን በመሸጥ ዝግጅቶች በማደራጀት ገንዘብ ለማሰባሰብ ይችላል፡፡

፫/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፮ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ የፖለቲካ ፓርቲ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በንግድና ኢንዱስትሪ ሥራዎች መሰማራት አይችልም፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች በሚመለከት ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

**፩፻፱. <u>ለመቀበል የተከለከለ ስጦታ ወይም እርዳታ</u>**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከሚከተሉት ሰዎች ወይም አካላት የሚቀርብለትን ስጦታ ወይም እርዳታ መቀበል አይችልም:-

ሀ) ከውጭ ሀገር ዜጎች፣ ተቋማት ወይም ድርጅቶች፤

ለ) ከውጭ ሀገር መንግሥት ወይም ከውጪ ሀገር የፖለቲካ ድርጅት፤

ሐ) ከበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት፣

መ) ከሃይማኖት ድርጅት፣

ሠ) ከፍርድ እስረኞች፤

ረ) በህገ-መንግሥቱ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሥልጣን ለመያዝ ከተደራጀ ቡድን ወይም ሰው፤

ሰ) በሽብርተኛነት ከተሰየመ ድርጅት፣

ሸ) የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፲፩(፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ካልታወቀ ምንጭ የሚቀርብ ስጦታ ወይም እርዳታ፤

ቀ) ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመንግሥት ከሆኑ የልማት ድርጅቶች፤

በ) አንድን ነገር ወደፊት ለማስፈጸም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ከህግ ውጭ ጥቅም ለማግኘት ከሚያልም ማንኛውም አካል የሚሰጥ ስጦታ ወይም እርዳታ፡፡

፪/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተከለከለ ስጦታ ወይም እርዳታ በማንኛውም መንገድ የተቀበለ እንደሆነ ስጦታውን ወይም እርዳታውን በተቀበለ በ፳፩ ቀናት ውስጥ ከተያያዥ መረጃዎች ጋር ለቦርዱ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

2/ With out prejudice to the provision of this Article, a political party, to enhance its financial position, may organize fundraising conferences and events, as well as sell its paraphernalia, research findings, booklets and magazines.

3/ Notwithstanding the provision of Article 66 (2) of this Proclamation, a political party which has attained legal personality shall not directly or indirectly engage in commercial and industrial activities.

4/ The Board shall issue a directive to determine the particulars of this Article.

**109. <u>Prohibited Donation or Grant</u>**

1/ Any political party is prohibited from accepting gift or donation from the following persons or bodies:

a) foreign national institutions or corporations;

b) foreign governments or foreign political party;

c) welfare organizations or non-governmental organizations;

d) religious organizations;

e) prisoners servicing sentence;

f) an organized group or person planning to assume state power outside the provisions under the Constitution;

g) organization designated as a terrorist;

h) With out prejudice to the provision of Article 111(2), gifts or donations from unknown sources;

i) full- or semi-government developmental organizations; and

j) gifts or donations from anybody or person hoping to execute future objective or envisages to execute future object.

2/ Where a political party in any way receives a gift or donation prohibited under Sub-Article (1) of this Article, the party shall return the donation or grant to the Board together with related information within 21 days from the date it received the donation or grant.

**፩፻፲. <u>ከህግ ውጭ ስለተገኘ ሀብትና ንብረት</u>**

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ ከተፈቀደለት ውጭ ገንዘብ፣ ወይም ንብረት፣ በስጦታ፣ በዳረጎት፣ በውርስ፣ በንግድና ኢንዳስትሪ ሥራ ወይም በማናቸውም መንገድ ተቀብሎ ቢገኝ ያገኘው የገንዘብ ጥቅም ቦርዱ ይቀጣዋል፤ በተጨማሪ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል፡፡

**<u>ንዑስ ክፍል ሦስት</u>**

**<u>ስለማህደር፣ ሂሳብ አያያዝና ቁጥጥር</u>**

**፩፻፲፩. <u>የፖለቲካ ፓርቲ ማህደርና ኦዲት</u>**

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የሚከተሉትን ጉዳዮች ያካተተ ትክክለኛና ቋሚ ማህደር በፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት በአግባቡ መያዝ አለበት፤

፩/ ማንኛውም በዓይነትም ሆነ በገንዘብ የሚደረግ መዋጮ፣ ስጦታ፣ እና ቃል የተገባለት ስጦታ ወይም መዋጮ፣

፪/ ከዚህ የሚከተሉትን ያካተተ የሂሳብ መግለጫ:-

ሀ) የተለያዩ የገቢ ምንጮችን በሚያሳይ መልኩ የተደራጀ የፓርቲው የገንዘብ ምንጭ ዝርዝር፤

ለ) ከ ፭ ሺ ብር በላይ መዋጮ ያደረገውን ወይም ስጦታ የሰጠውን ወይም ቃል የገባውን ሰው ስም፤

ሐ/ ቃል የተገባ መዋጮ ወይም ስጦታ ካለና የሚከፈልበት ጊዜ፤ እና

መ/ አጠቃላይ የፖለቲካ ፓርቲው የሂሳብ እንቅስቃሴ፡፡

፫/ የፖለቲካ ፓርቲ ቋሚ ንብረቶች ዝርዝር፣ መቼ እና እንዴት በባለቤትነት እንዲያዘው፤

፬/ የፖለቲካ ፓርቲውን የእዳ ዝርዝር፤

፭/ ከዚህ ጋር በተያያዘ ቦርዱ የሚፈልጋቸው ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን፤

መያዝ አለበት፡፡

**፩፻፲፪. <u>የሂሳብ መዝገብ</u>**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የገቢና ወጪ ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ይኖረዋል፡፡

፪/ የፖለቲካ ፓርቲ የገቢና ወጪ ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት በሂሳብ አያያዝ ልምድ ተቀባይነት ባለው መንገድ የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡

110. **<u>Unlawfully Acquired Asset and Property</u>**

Where a political party is found to have received money or any property in the form of donation, gratuity, inheritance or proceeds from commercial and industrial activities, or in any other way, the Board shall issue a fine. The party may also be held liable under the appropriate criminal law.

**<u>SUB-SECTION THREE</u>**

**<u>RECORD, BOOK KEEPING AND AUDIT</u>**

**111. <u>Political Party's Records and Audit</u>**

Any political party shall keep an accurate and permanent record appropriately at its head office, which includes the following matters:

1/ Any in-kind or monetary contribution, donation and pledged contribution or donation;

2/ Financial statement consisting the following:

a) Income statement outlining the political party's different sources of income;

b) The name of the person who made a contribution, donation or pledge of more than Birr 5000;

c) The pledged contribution or donation, along with the timeline for the fulfillment; and

d) The general financial activities of the political party.

3/ List of the fixed assets of the political party, and when and how it came to own these assets;

4/ The party's detailed debt; and

5/ Other relevant information required by the Board.

**112. <u>Books of Account</u>**

1/ Any political party shall have an accounting procedure relating to its income and expenditure.

2/ The procedure of account of income and expenditure of every political party shall be in accordance with the generally accepted practice of accounting.

፫/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ አባል በማንኛውም ጊዜ አባል የሆነበትን የፓርቲውን የገቢና ወጪ ሂሳብ መረጃ የማግኘት መብት አለው፡፡

፬/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሚያወጣቸው ወጪዎች ሁሉ ለፖለቲካ ዓላማው መዋላቸውን ለቦርዱ የማስረዳት ኃላፊነት አለበት፡፡

## ፩፻፲፫. ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በየዓመቱ በራሱ ኦዲተር የሂሳብ ምርመራ ያካሂዳል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲው በቦርዱ ከተመዘገበ ከስድስት ወር ጀምሮ የሂሳብ ሪፖርቱን የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በሦስተኛው ወር ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ለቦርዱ የሚያቀርበው ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት፤

ሀ/ ዝርዝር የገቢ መጠን እና የገቢ ምንጭ፤

ለ/ የወጪ አርእስቶችን የያዘ የወጪ ዝርዝር፤

ሐ/ የቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶችና ዕዳ ዝርዝር መግለጫ፤

መ/ የሂሳብ እንቅስቃሴ መግለጫ፤እና

ሠ/ ስለትክክለኛነቱ የፖለቲካ ፓርቲው መሪ ፊርሞበት በፓርቲው ማህተም የተረጋገጠ ሰነድን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

፫/ ፓርቲው ከላይ የተመለከቱትን የገቢ፣ የወጪ፣ የንብረትና እዳ ዝርዝር መግለጫዎች ለቦርዱ ከነማብራሪያቸው ማቅረብ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ በሌላ አኳኋን የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የዓመት የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ በይፋ ያወጣል፡፡ ይህ የዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት በዚህ አዋጅ መሠረት ተመርምሮ ተቀባይነት ያገኘ መሆን ይገባዋል፡፡

፭/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሪፖርት ካላቀረበ ወይም ፓርቲው ሪፖርት አቅርቦም ቦርዱ በተላከለት ሪፖርት ላይ ጥርጣሬ ሲኖረው ቦርዱ የውጭ ኦዲተር በመላክ ሂሳቡ እንዲመረመር ያደርጋል፡፡

3/ Any member of a political party shall have a right to seek, at any time, information concerning the income and expenditure accounts of his political party.

4/ Any political party shall have the responsibility to demonstrate to the Board that its expenditures are spent for its political objective.

## 113. Annual Audit Report

1/ Any political party shall undertake financial investigation annually by its auditor. Starting from 6 months after registration, the political party shall submit its audit report to the Board on the third month after the end of each budget year.

2/ Any political party submitting the annual audit report to the Board shall include:

a) a list of the sources and amounts of income;

b) a list of expenditures under the expenditures title;

c) a list of movable and immovable properties and liabilities;

d) bank statements; and

e) a document signed by the political party leader and containing the seal of the party seal to authenticate the content of the document.

3/ The party shall submit to the Board the details of the abovementioned income, expenditure, asset and debt with corresponding analysis.

4/ With out prejudice to the provisions of this Proclamation, every political party shall prepare and officially issue annual audit reports. Such annual audit reports shall be one inspected and accepted in accordance with this Proclamation.

5/ Where a political party fails to submit the report in accordance with the provisions of sub-article (1) of this Article, or if the Board has reason to doubt the authenticity of the report, the Board may assign an external auditor to inspect the account.

## ክፍል አምስት
## ስለምርጫ ታዛቢዎች፣ የዕጩ ወኪሎች፣ ጋዜጠኞችና የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ

### ፩፻፲፬. ስለ ምርጫ ታዛቢዎች

፩/ የምርጫ ሂደት ለመታዘብ የሚፈልጉ የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች ለቦርዱ በማመልከትና ሲፈቀድላቸው የሚሰጣቸውን የታዛቢነት የምስክር ወረቀት በመያዝ ምርጫ ለመታዘብ ይችላሉ፡፡

፪/ የውጭ የምርጫ ታዛቢዎች በመንግሥት ግብዣ መሰረት ምርጫ ለመታዘብ ይችላሉ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ምርጫን የሚታዘብ የውጭ ታዛቢ ቡድን ወይም ድርጅት ከቦርዱ የታዛቢነት የምስክር ወረቀት መውሰድ አለበት፡፡

፬/ ምርጫውን ለመታዘብ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው የምርጫ ታዛቢዎች በቦርዱ የሚዘጋጀውን የምርጫ ታዛቢዎች የሥነ ምግባር መመሪያ መቀበላቸውን በድርጅቶቹና በወኪሎቻቸው ፊርማ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

፭/ ቦርዱ ምርጫ ለመታዘብ ከተፈቀደላቸው ታዛቢዎች ጋር በመመካከር ታዛቢ ቡድኖቹን ያሰማራል፡፡

### ፩፻፲፭. የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች

፩/ ቦርዱ የምርጫ ታዛቢነት ጥያቄ ሲቀርብለት ጥያቄውን ያቀረበው ድርጅት:-

ሀ) ህጋዊ ሰውነት ያለው አገር በቀል ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት መሆኑን፤

ለ) ከማንኛውም የፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻና ለትርፍ ያልተቋቋመ መሆኑን፣ እንዲሁም የማንኛውም መንግሥታዊ ተቋም አካል አለመሆኑን፤

ሐ) የድርጅቱ የቦርድ አባላትና መሪዎች የማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባላት አለመሆናቸውን፤

መ) ድርጅቱ የሚያሰማራቸው ግለሰቦች ምርጫ በገለልተኝነት ለመታዘብ ችሎታ ያላቸው መሆኑን በማጣራትና ድርጅቱ ያለውን የማስፈጸም አቅም አረጋግጦ በቦርዱ የተዘጋጀውን የምርጫ ታዛቢዎች የሥነ ምግባር ደንብ መቀበላቸውን ድርጅቱንና ወኪሎቹን በማስፈረም አረጋግጦ የታዛቢነት ሰርቲፊኬት ይሰጠዋል፤

## PART FIVE
## ELECTION OBSERVERS, CANDIDATES' AGENTS, JOURNALISTS AND VOTER EDUCATION

### 114/ Election Observers

1/ Interested local election observers may observe the electoral process by obtaining the Board's observer accreditation to be issued based on their request.

2/ International observers may observe the electoral process upon the invitation of the government.

3/ An international observers' group or organization observing elections according to Sub-Article (2) of this Article shall take an observers' accreditation from the Board.

4/ Election observers who have received observers' accreditation shall demonstrate their acceptance of the Board's election observers' code of conduct through signatures of the organizations and their respective representatives.

5/ The Board shall, in consultation with accredited observers, deploy observer groups.

### 115. Local Election Observers

1/ The Board, when presented with a request to observe elections, shall ascertain that the requesting organization:

a) is a local civil society organization with a legal personality;

b) is non-partisan, not-for-profit and not part of a government organ;

c) leaders and board members are not members of any political party;

d) That the individuals to be deployed are capable of impartially observing elections; upon verifying this and the organization's capacity as well as ensuring by the signatures of the organization and representatives its acceptance of the election observers' code of conduct the Board prepared, it shall issue observer accreditation;

ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከ(ሀ) እስከ (መ) ድረስ የተዘረዘሩትን በተመለከተ ቦርዱ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣል፡፡

፪/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገውን ባለመሟላቱ ምክንያት የቀረበለትን የታዛቢነት ማመልከቻ ያልተቀበለ እንደሆነ ይህን ውሳኔውን ማመልከቻውን በተቀበለ በ፴ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በፅሁፍ ያሳውቃል፡፡ አመልካቹ በቦርዱ ውሳኔ ካልተስማማ በ፲፬ ቀን ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንዲታይለት አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፫/ ማንኛውም የምርጫ ታዛቢ ከሥነ ምግባር ደንቡና ከገባው ግዴታ ውጭ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ ቦርዱ እንደ አግባብነቱ የተፈጸመውን ስህተቱ ጠቅሶ ለግለሰቡና ለወከለው ድርጅት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስህተቱን እንዲታረም ለማዘዝ አልያም ግለሰቡ ወይም ወካዩ ድርጅት ከታዛቢነት ለማገድ ይችላል፡፡

**፩፻፲፮. የምርጫ ታዛቢዎች መብት**

፩/ የምርጫ ታዛቢነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው የድርጅት ወኪል በምርጫ ጣቢያ በመዘዋወር የምርጫውን ሂደት የመከታተልና ተገቢ መረጃ ጠይቆ የማግኘት መብት አለው፡፡ታዛቢዎች የምርጫ ሰነዶችን የመመልከት፤ የድምጽ አሰጣጥ እና የድምጽ ቆጠራ ሂደቱን የመታዘብ መብት አላቸው፡፡

፪/ የምርጫ ታዛቢዎች በምርጫው ሂደት የታዘቧቸውን ወይም ያጋጠሟቸውን ጉድለቶች ለቦርዱ ጽህፈት ቤት የማቅረብ መብት አላቸው፡፡ዝርዝሩ በቦርዱ መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፩፻፲፯. የምርጫ ታዛቢዎች ግዴታ**

፩/ ከቦርዱ የምርጫ ታዛቢነት የምስክር ወረቀት ያገኘ የምርጫ ታዛቢ:-

ሀ) የታዛቢነት መታወቂያውን መያዝና ሲጠየቅ ማሳየት አለበት፤

ለ) የምርጫ አስፈፃሚዎች የሚሰጡትን መመሪያ ማክበር አለበት፤

ሐ) የምርጫው ሂደት በትክክልና በብቃት እንዳይካሄድ ከሚያደናቅፍ ተግባር መቆጠብ አለበት፤

መ) ቦርዱ ያወጣውን የስነ-ምግባር ደንብ ማክበር አለበት፤

ሠ) ዝርዝር ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

e) The Board shall issue a directive to determine the particulars of sub-articles “a” to “d” of this Article.

2/ Where the Board rejects a request to observe elections on account of unfulfillment of the provision of Sub-Article (1) of this Article, it shall notify in writing the decision to the applicant within 30 days of receiving the request. An applicant aggrieved by the decision of Board may appeal to the Federal High Court within 14 days.

3/ Where an election observer is engaged in activities in violation of the code of conduct and the commitments it made, the Board may, according to the circumstance of the case, issue warning to the organization and its representative, pointing out the error and telling them to make amends or may suspend the individual or the organization from observing the election.

**116. Right of Election Observers**

1/ A representative of an accredited election observation organization has the right to move around in the polling station to monitor the election process; and request and obtain appropriate information. The observers have the right to look at the election materials and observe the voting and counting processes.

2/ Election observers have the right to report to the Board Secretariat any irregularities they observed or encountered in the election process. The particulars shall be determined in a directive to be issued by the Board.

**117. Duty of Election Observers**

1/ An election observer who has received an accreditation from the Board shall:

a) Carry his accreditation card and display it upon request;

b) Abide by instructions of election officials;

c) Refrain from any act which may obstruct the proper and efficient conduct of the election process;

d) Respect code of conduct enacted by the Board; and

e) Prepare and submit a detailed report to the Board.

፪/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ የምርጫ ታዛቢ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በገለልተኝነት፣ የሀገሪቱን ሕጎች ፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን እና የቦርዱን መመሪያ በማክበር የምርጫውን ሂደት መታዘብ ይችላል፡፡

**፩፻፲፰. <u>የፖለቲካ ፓርቲ እና የግል ዕጩ ወኪሎች</u>**

፩/ ማንኛውም ለምርጫ ዕጩ ያቀረበ የፖለቲካ ፓርቲ የምርጫውን ሂደት የሚከታተሉ:-

ሀ) ለሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ጽህፈት ቤት ሁለት እየተቀያየሩ የሚሰሩ ተቀማጭ ወኪሎች፤

ለ) በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ስር በሚገኝ በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ እየተቀያየሩ በጣቢያው የሚሰሩ ሁለት ተቀማጭ ወኪሎችን፤

መሰየም ይችላል፡፡

፪/ ማንኛውም የግል ዕጩ:-

ሀ) በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ጽ/ቤት ሁለት እየተቀያየሩ የሚሰሩ ተቀማጭ ወኪሎች፣

ለ) በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ስር በሚገኝ በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ በፈረቃ በጣቢያው የሚቀመጡ ሁለት ወኪሎችን፤

መሰየም ይችላል።

፫/ እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ በአንድ የምርጫ ክልል ከሰባት የማይበልጡ ተዘዋዋሪ ወኪሎችን መመደብ ይችላል፡፡

**፩፻፲፱. <u>የወኪሎችን ስም ዝርዝር ስለማሳወቅ</u>**

፩/ ማንኛውም ዕጩ ያቀረበ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ዕጩ የተቀማጭና የተዘዋዋሪ ወኪሎችን ስም ዝርዝር ተጠባባቂ ወኪሎችን ጨምሮ ከድምፅ መስጫው ዕለት ሰባት ቀን አስቀድሞ ለሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ጽህፈት ቤት በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ የምርጫ ክልሉ ኃላፊም የታዛቢዎቹ ስም ዝርዝር የያዘ ደብዳቤ ዝርዝሩ በደረሰው በሁለት ቀናት ውስጥ ለፖለቲካ ፓርቲው መስጠት አለበት፡፡

፪/ የምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት በየምርጫ ጣቢያው የተመደቡ ተቀማጭና ተዘዋዋሪ ወኪሎችን ለየምርጫ ጣቢያው በወቅቱ ያሳውቃል፡፡

**፩፻፳. <u>የወኪሎች መብት</u>**

፩/ የማንኛውም እጩ ተቀማጭ ወኪል በተመደበበት ቦታ የምርጫውን ሂደት የመከታተል፣ ቅሬታውን በየደረጃው የማቅረብ እና መረጃ የማግኘት መብት አለው፡፡

2/ With out prejudice to the provision of Sub-Article (1) of this Article, an international observer may, in accordance with the directive to be issued by the Board, observe the election process impartially and by abiding by the laws of the country, international agreements and the Board's direction.

**118. <u>Political Parties and Independent Candidates' Agents</u>**

1/ Any political party which has fielded candidates in an election to monitor the election process may:

a) assign two stationary agents, who shall work in turns, to its constituency election office; and

b) assign two stationary agents, who shall work in turns, to each of the polling stations in his constituency;

2/ Any independent candidate may:

a) assign two stationary agents, who shall work in turns, to his constituency election office; and

b) assign two stationary agents, who shall work in turns, to each of the polling stations in his constituency;

3/ Each political party or an independent candidate may assign not more than seven mobile agents to a constituency.

**119. <u>Presenting the Agents</u>**

1/ Any political party fielding candidates or any independent candidate shall submit to his constituency electoral office a written list of the names of the stationary and mobile agents, including the substitutes, seven days prior to election day. The constituency chief electoral administrator shall, within two days of receiving the list, provide to the political party a letter containing the list of the agents.

2/ The constituency electoral office shall, in due time, notify the polling stations the stationary and mobile agents assigned to their polling station.

**120. <u>Rights of Agents</u>**

Any stationary agent of a candidate in his assigned location has the right to:

1/ Monitor the election process, submit complaints at every level and obtain information;

፪/ በምርጫው ሂደት የታዘባቸውን ጉዳዮች መዝግቦ የመያዝ እና ከምርጫ ጣቢያው ሃላፊዎች ማብራሪያ የመጠየቅ መብት አለው፡፡

፫. የማንኛውም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ተዘዋዋሪ ወኪል በተመደበበት ቦታ የምርጫውን ሂደትን በሚመለከት ተገቢ መረጃ የማግኘት መብት አለው፡፡

፬/ የማንኛውም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ወኪል ያለ ምንም ተፅእኖ በህግ የተሰጠውን የውክልና ተግባር የማከናወን መብት አለው፡፡

፭/ ስለ አፈፃፀሙ ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

### ፻፳፩. የወኪሎች ግዴታ

ማንኛውም ተዘዋዋሪም ሆነ ተቀማጭ ወኪል:-

፩/ የምርጫ ኃላፊው የሚሰጠውን ትእዛዞች ማክበር አለበት፡፡

፪/ የእጩ ወኪል የሆነ ሰው የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ማክበርና የምርጫ ሂደቱን ከሚያውኩ ተግባራት መቆጠብ አለበት፡

፫/ አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ መታወቂያውን ማሳየት አለበት፡፡

፬/ የምርጫ ህጉን ማክበር አለበት፡፡

፭/ የምርጫውን ሂደት የመከታተል ተግባሩን ሲያከናውን መራጮች ማንን መምረጥ እንዳለባቸው አስተያየት ከመስጠት ወይም ተጽእኖ ለማሳደር መሞከር የለበትም፡፡

፮/ የምርጫ ቁሳቁሶችን መያዝ፥ ማንሳት፣ መነካካት ወይም በቁሳቁሶቹ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ተግባራትን መፈጸም የለበትም፡፡

፯/ የምርጫ ጣቢያውን ሃላፊ ወይም ሰራተኛ ከማስፈራራት ወይም ስራውን ከሚያደናቅፉ ተግባራት መቆጠብ አለበት፡፡

፰/ ወደ ድምጽ መስጫ ክፍሎች መግባት የለበትም፡፡

፱/ ቦርዱ የሚያወጣውን የወኪሎች የሥነ ምግባር ደንብ መፈረም እና ማክበር ይገባዋል፡፡

### ፻፳፪. የወኪል አለመኖር

፩/ ማንኛውም እጩ ወይም የእጩ ወኪል በራሱ ምክንያት በተመደበበት ቦታ ባልተገኘበት ወቅት የተከናወኑ የምርጫ ተግባራት ውድቅ እንዲደረጉ ሲል ለመጠየቅ አይችልም፡፡

2/ Record his observations during the election process and request explanations from polling station election officials;

3/ Get appropriate information regarding the elections process;

4/ Carry out his legal responsibility as an agent without any influence.

5/The Board shall determine the particulars in a directive.

### 121. Duty of Agents

Any stationary or mobile agent shall:

1/ Abide by the head of the polling station's orders;

2/ A Candidatae Agent have to abide by the head of the polling station's orders and Refrain for any act that disrupts the election process ;

3/ Present his credentials when asked by an authorized body;

4/ Respect the electoral law;

5/ Refrain from advising or influencing voters on their decision who to elect when he follow up election precess activity;

6/ Not possess, pick or tamper with election materials or engage in acts that destruct the materials;

7/ Refrain from acts that intimidate the head of the polling station or election officials or disrupt their work;

8/ Not enter the ballot casting area; and

9/ Sign and abide by the agents' code of conduct to be issued by the Board.

### 122. Absence of an Agent

1/ No candidate or his agent shall request for the annulment of the electoral activities conducted in his absence from his assigned place due to his own failure.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ወኪሉ ያልተገኘው ሆን ተብሎ በተቀነባበረ መሰናክል ምክንያት መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ወኪሉ ሳይኖር የተከናወኑ የምርጫ ተግባራት ወኪሉ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት እንደአግባብነቱ በምርጫ ክልሉ ወይም በምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል፡፡

**፩፻፳፫. <u>መታወቂያ ካርድ ስለመስጠት</u>**

ቦርዱ ለታዛቢዎች፣ ለተቀማጭና ተዘዋዋሪ ወኪሎች፣ ለጋዜጠኞች እና ለምርጫ ታዛቢዎች መታወቂያ ካርድ አዘጋጅቶ መስጠት አለበት፡፡

**፩፻፳፬. <u>የስነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት</u>**

፩/ ቦርዱ መራጮች በቂ ምርጫ ነክ ግንዛቤ የሚያገኙበትን ስልት በመቀየስና የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የሥነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት ይሰጣል፡፡

፪/ ቦርዱ የሥነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት መስጠት እንዲችሉ ህጋዊ ሰውነት ላላቸው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና የትምህርት ተቋማት፤ የማስተማር ፈቃድ ይሰጣል፡፡ ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ መሰረት በቦርዱም ሆነ በቦርዱ ፈቃድ በሚሰጣቸው ተቋማትና ድርጅቶች የሚሰጥ ትምህርትና ስልጠና ቦርዱ የሚያዘጋጃቸውን የማስተማሪያ ሰነዶች መሠረት ያደረገ ይሆናል፡፡

**፩፻፳፭. <u>የፈቃድ አሰጣጥ</u>**

መራጮችን ለማስተማር የሚፈልግ ድርጅት ፈቃድ እንዲሰጠው ሲያመለክት ቦርዱ:-

፩/ አመልካቹ:-

ሀ) በህግ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ አገር በቀል የሲቭል ማህበረሰብ ድርጅት ወይም እውቅና ያለው የከፍተኛ ትምርህት ተቋም መሆኑን፤

ለ) ለመራጮች ትምህርት ያወጣውን መስፈርት የሚያሟላ መሆኑን፤፣

ሐ) ተግባሩን ለመወጣት የሚያስችል ብቃት ያለው መሆኑን፤

መ) ከማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ገለልተኛ መሆኑን፤

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, where it is established that the agent's absence was a result of an obstacle deliberately designed to hinder his presence, the activities carried out in his absence may, on his request, be reviewed and decided upon, as appropriate, by the constituency or polling station grievance hearing committee.

**123/ <u>Issuance of Accreditation Cards</u>**

The Board shall prepare and issue accreditation cards to stationary and mobile agents, journalists and election observers.

**124/ <u>Civic and Voter Education</u>**

1/ The Board shall provide civic and voter education by devising a strategy of creating election related awareness and adopting various engagement approaches.

2/ The Board shall issue accreditation to registered civic society organizations and educational institutions to conduct civic and voter education. The particulars shall be determined by a directive to be issued by the Board.

3/ Education and training provided, in accordance with this Proclamation, by the Board or through institutions and organizations accredited by the Board, shall be based on curriculum developed by the Board.

**125. <u>Issuance of Accreditation</u>**

1/ When an organization planning to provide voter education applies for an accreditation, the Board, prior to providing accreditation, shall ascertain that the organization:

a) is a legally registered, local civil society organization or an accredited higher learning institution;

b) fulfills the established voter education criteria;

c) has the capacity to discharge its responsibilities;

d) is independent of any political activity;

ሠ) በማጣራትና ቦርዱ ያዘጋጀውን የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ሥነ ምግባር መመሪያ መቀበላቸውን ድርጅቱንና ወኪሎቹን በማስፈረም የማስተማር ፈቃድና መታወቂያ ይሰጣል፡፡

፪/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ለማያሟላ ድርጅት ፈቃድ አይሰጥም፤ አለመፍቀዱንም ከነምክንያቱ በጽሑፍ ለአመልካች ያሳውቃል፡፡ የስነ ዜጋና መራጮች ትምህርት ለማስተማር አመልክቶ በቦርዱ የተከለከለ ማንኛውም ድርጅት ወይም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፫/ ማንኛውም የማስተማር ፈቃድ የተሰጠው ድርጅትም ሆነ ተወካይ ከስነ ምግባር ደንቡና ከገባው ግዴታ ውጭ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ ቦርዱ እንደአግባብነቱ ለግለሰቡም ሆነ ለወከለው ድርጅት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስህተቱን እንዲያርም ለማድረግ ወይም ፈቃዱን እስከመሰረዝ የሚደርስ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

**፩፻፳፮. <u>ስለጋዜጠኞች</u>**

፩/ የምርጫ ሂደትን መዘገብ የሚፈልግ ጋዜጠኛ ስራውን የሚገልጽ መታወቂያና ከሚሰራበት የመገናኛ ብዙኃን ተቋም የተሰጠ ማረጋገጫ በመያዝ የምርጫውን ሂደት መከታተል ይችላል፡፡ ከምርጫ ጣቢያ ፪ መቶ ሜትር ርቀት ዙሪያ ውስጥ ገብቶ ለመዘገብ የፈለገ ጋዜጠኛ ከምርጫው ቀን አስቀድሞ ከቦርዱ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

፪/ ማንኛውም ጋዜጠኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፩) የተጠቀሰውን ሥራውን ሲያከናውን በመራጮች ውሳኔ ላይ እና ምርጫ አስፈጻሚዎች ተግባራት ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድር ድርጊት መቆጠብ አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም ጋዜጠኛ ቦርዱ ከዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ጋር በተጣጣመ መንገድ የሚያወጣውን የምርጫ አዘጋገብ የሥነ ምግባር ደንብ ማክበር አለበት፡፡

e) And after ensuring that the requesting organization and its representatives have accepted and signed the code of conduct for voter education, issue a voter education accreditation.

2/ The Board shall not issue an accreditation to any organization that does not fulfill the criteria in Sub-Article (1) of this Article; shall notify the applicant in writing the decision to reject the accreditation application along with the reasons. Any organization or a higher learning institution aggrieved by the decision of the Board may appeal the Federal High Court.

3/ Where any accredited institution violates the code of conduct and operates outside its duties, the Board may, as appropriate, issue a correction warning to the organization and its representative or take measures including cancellation of accreditation.

**126. <u>Responsibilities of Journalists</u>**

1/ A journalist planning to cover the election process shall bring an ID Card indicating his status and a support letter from his employing media institution to cover the election process. Any journalist intending to report from within 200 meters of a polling station shall obtain authorization from the Board prior to election day.

2/ Any journalist engaged in activities stated in the provisions of Sub-Article (1) of this Article shall refrain from any act that interferes with the voters' decision and polling officers' duties.

3/ Any journalist shall respect the Board's election coverage code of conduct to be issued in a directive in accordance with provisions of this Article.

## ክፍል ስድስት
## የምርጫ ሥነ ምግባር
## ምዕራፍ አንድ
## የምርጫ ሥነ ምግባር ድንጋጌዎች

### ፩፻፳፯. መርህ

፩/ በመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲ ሥርዓት የሚመረጥ መንግሥት ህጋዊነት በሚከተሉት መርሆዎች ላይ ይመሠረታል:-

ሀ) መራጮች በምርጫ ዘመቻው አማካኝነት ስለ ፖለቲካ ፓርቲዎች ፖሊሲዎችና ስለ እጩዎች ማንነት የተሟላ መረጃ ሲሰጣቸውና የራሳቸውን በእውቀት ላይ በተመሰረተ እና ከግል ፍላጎት የሚመነጭ ውሳኔ ሲያደርጉ፤ እና

ለ) መራጮች በነፃነት፣ ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት፣ ያለፍርሃት፣ ያለተፅእኖ፣ ያለጫና፣ እንዲሁም ከጉቦ እና ከተለያዩ መደለያዎች ነፃ በሆነ መልኩ ድምፅ መስጠት፤

ሲችሉ ነው፡፡

፪/ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በቅን ልቦና እየተመሩ:-

ሀ) የምርጫ ሥነ ምግባር መርሆዎች እንዲከበሩ፤

ለ) ምርጫ የመላው ህዝብ ነፃ እና ተቀባይነት ያለው ውሳኔ መግለጫ ሆኖ እንዲታወቅ፤

ሐ)የመራጩ ህዝብ ውሳኔ በሁሉም ዘንድ የተከበረ እንዲሆን፣

መስራት አለባቸው፡፡

፫/ ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዙ ማናቸውም ጉዳዮች ዙሪያ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎችና የግል እጩ ተወዳዳሪዎች ከዚህ አዋጅ ጋር በተጣጣመ አኳኋን መንቀሳቀስ አለባቸው፡፡

### ፩፻፳፰. ለአዋጁ የሥነ ምግባር ድንጋጌዎች መገዛት

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ዕጩ ተወዳዳሪ:-

ሀ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት መንቀሳቀስ አለበት፤

ለ) መሪዎቹ፣ ኃላፊዎቹ፣ እጩዎቹ እና አባላቱ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እንዳይጥሱ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለበት፤

ሐ)የፓርቲው ኃላፊዎች እጩዎችና አባላት የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚጥስ ተግባር እንዳይፈጽሙ፤ ደጋፊዎቹም የተከለከሉ ድርጊቶች ከመፈጸም

## PART SIX
## ELECTORAL CODE OF CONDUCT
## CHAPTER ONE
## ELECTORAL CODE OF CONDUCT PROVISIONS

### 127. Principle

1/ The legitimacy of a government elected in a multiparty democratic election shall rest on the following principles:

a) The voters are able to make an informed decision based on comprehensive information provided during the electoral campaign regarding the policies of political parties and characters of candidates; and when they are able to decide based on their own free will; and

b) When voters are able vote freely, without any interference, fear, pressure, undue influence as well as without bribery and other inducements.

2/ All parties shall, in good faith, work to ensure that:

a) The principles of the electoral code of conduct are respected;

b) Elections are recognized as expressions of the free and legitimate decision of the people;

c) The decision of the voters is respected by all.

3/ In any matter relating to the election process, parties and independent candidates shall conduct their activities in accordance with the provision of this Proclamation.

### 128. Abiding by the Ethical Provisions of the Proclamation

1/ Any political party or independent candidate:

a) Shall conduct his activities in accordance with the provisions of this Proclamation;

b) Shall take appropriate measures to ensure that its leaders, officials, candidates and members do not infringe this Proclamation;

c) Shall take appropriate measures to prevent party officials, candidates and members from committing any acts in contravention of this Proclamation and restrain supporters

እንዲቆጠቡ ለማድረግ የሚያስችሉ ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፤

መ) ዓላማ እና ፕሮግራማቸውን ወደ ሕዝብ በሚያደርሱበት ጊዜ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ያለ አድልዎ ተፈጻሚ ማድረግ አለባቸው፡፡

፪/ የፓርቲው አባላት ወይም ደጋፊዎች የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲያከብሩ ቦርዱ በሚያወጣው ዕቅድ መሠረት ማስተማርና ሌሎች ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች መውሰድ አለበት፡፡

፫/ ቦርዱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሥነ-ምግባር የሚያስተምሩበትና አቋማቸውን የሚገልጹበትን መንገድ እንዲሁም የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማቸውን አስመልክቶ ዝርዝር መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

**፻፳፱. <u>የምርጫ ዘመቻ አካሄድ</u>**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ:-

ሀ) የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ዘመቻ የማካሄድ የፖለቲካ ሀሳቦችንና መርሆዎቻቸውን ያለ ስጋት የማሰራጨት መብቶቻቸውን ማክበር፤

ለ) እንቅስቃሴው የሌላውን የፖለቲካ ፓርቲ፣ የመራጩን ሕዝብ እና የሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች መብቶችን ያከበረ መሆን፤

ሐ) የመገናኛ ብዙኃን ነፃነትን ማክበር፤

መ) ተወዳዳሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ለመራጩ ሕዝብ ያላቸውን የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ማክበር፤

ሠ) በፖለቲካ እንቅስቃሴ ለመሳተፍ የሚሹ የመምረጥና የመመረጥ መብት ያላቸው ዜጎች ሁሉ በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ የበኩሉን አስተዋጽዖ ማድረግ፤

አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ:-

ሀ) የግል ወይም የመንግሥት ጋዜጠኞች በሙያዊ ስራቸው ላይ እንዳይሰማሩ ማዋከብ፣ እንቅፋት መፍጠር፤ በማንኛውም አይነት ድርጊት የሌሎች ፓርቲዎች የምርጫ ዘመቻ እንዲስተጓጎል፣ እንዲቋረጥ፣ እንዲበላሽ፣ እንዲዳከም ማድረግና መተባበር፤

ለ) የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ ማስታወቂያ፣ በራሪ ጽሑፍ ወይም ፖስተር እንዳይሰራጭ ማወክ፤

from engaging in activities that are prohibited by this Proclamation;

d) Shall impartially implement the provisions of this Proclamation when communicating their objectives and programs to the public.

2/ To ensure that its members and supporters abide by the provisions of this Proclamation, a party shall educate them in accordance with the plan to be developed by the Board as well as take other appropriate measures.

3/ The Board shall issue a directive that detail out how political parties should teach ethical conducts and communicate their positions as well as how they should use social media.

**129. <u>Rules of Election Campaign</u>**

1/ Any Political party shall:

a) Respect the rights and freedoms of all other parties to organize election campaigns and disseminate their political views and principles without fear;

b) Conduct itself in a manner that respects the rights of other parties, voters and other members of the community;

c) Respect the freedom of the mass media;

d) Respect competing parties' voter outreach efforts; and

e) Contribute to ensure all citizens who wish to participate in political process and who are eligible to vote and be elected can do so freely.

2/ Any political party shall not:

a) Harass or obstruct private or government journalists who are engaged in their professional activities; engage in activities that in any way disrupt, destroy or frustrate the election campaign of other parties or cooperate in such acts;

b) Hinder the smooth distribution of election handbills, leaflets or posters of other parties and candidates;

ሐ) የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች ፖስተሮችን ማበላሸት፣ ማጥፋት ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ እንዳይታዩ ወይም እንዳይነበቡ ማድረግ፤

መ) ሌላ የፖለቲካ ፓርቲ ሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ፣ ስብሰባ፥ የእግር ጉዞ፥ ሰላማዊ ሰልፍ እንዳያደርግ በአመራሩ፣ በአባላቱ፣ ወይም በደጋፊዎቹ አማካኝነት ማገድ፣ ማወክ፣ ቅስቀሳ ማድረግ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ማደናቀፍ፤

ሠ) ማንኛውም ሰው በሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች የፖለቲካ ድጋፍ ሰልፍ እንዳይሳተፍ መከልከል፤

ረ) ደጋፊዎቹ በዚህ ክፍል የተከለከሉ ማናቸውንም ተግባራት እንዲፈፅሙ መቀስቀስና ማነሳሳት፤

የለበትም፡፡

**፩፻፴. ስለ ምርጫ ሂደት**

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፡-

፩/ ከምርጫ አስፈፃሚዎች ጋር በመተባበር ድምጽ የመስጠት ሂደቱ በሰላማዊ ሁኔታ፣ የመራጮችን የመምረጥ መብት ከሚያደናቅፉ ማንኛውም ሁኔታዎች በፀዳ፣ ነፃ፣ ፍትሃዊና **ዴሞክራሲያዊ** በሆነ መልኩ ተግባራዊ እንዲተገበር መስራት አለበት፡፡

፪/ ከምርጫው ዕለት በፊት፥ በምርጫው ዕለትና ከምርጫው ቀን በኋላ ባሉት ጊዜያት ሁሉ የምርጫ አስፈጻሚዎችን ደኅንነት ለማረጋገጥ የበኩሉን ማድረግ አለበት::

፫/ የታዛቢነት ፈቃድ ያላቸውን ታዛቢዎች እና ኃላፊዎች ማክበር እና ከነርሱ ጋር መተባበር አለበት፤

፬/ የድምጽ አሰጣጥ ሚስጢራዊነትን ማክበርና እንዲከበር ማገዝ አለበት፡፡

፭/ የድምጽ መስጫ ጣቢያን በኃይል በመቆጣጠር ወይም በሌላ በማንኛውም ህገወጥ መንገድ ድምፅ ለማግኘት መንቀሳቀስ የለበትም፡፡

፮/ የምርጫ አስፈፃሚዎችን ሥራ፣ እንዲሁም የድምጽ አሳጣጥ ወይም የድምፅ ቆጠራ ሂደትን ማወክ ወይም ያለ አግባብ በሥራውም ሆነ በሂደቱ ጣልቃ መግባት የለበትም፡፡

፯/ የድምጽ አሰጣጡ ሚስጢራዊ አይደለም የሚል እንደምታ ያለው የሀሰት መረጃ ለመራጮች መስጠት የለበትም፡፡

c) Deface or destroy or otherwise prevent the visibility or legibility of the posters of other political parties or candidates;

d) Have its leadership, members or supporters stop, disturb or agitate against or otherwise hamper other political party from staging a public demonstration, meeting, rally or march;

e) Prevent any person from attending the political rallies of another party; or

f) Incite and agitate its supporters to commit any of the acts prohibited under this Part.

**130. The Election Process**

Any political party shall:

1/ In cooperation with election officials, ensure the voting process is conducted in a peaceful manner, without any interference in the right of voters, and in a free, fair and democratic way;

2/ Make a contribution to ensure the safety of electoral officials before, during and after election day;

3/ Respect and cooperate with accredited observers and officials;

4/ Respect and support the upholding of the secrecy of the ballot;

5/ Refrain from acts that control polling stations by force or secure votes through illegal means;

6/ Refrain from disturbing or unduly interfering with the work of election officers or the voting or vote counting processes; and

7/ Not provide false information to voters which implies violation of the secrecy of the ballot.

**፩፻፴፩. የምርጫ ውጤትን ስለመቀበል**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ተወዳዳሪ በሚመለከተው ህጋዊ አካል የተረጋገጠን የምርጫ ውጤት መቀበል አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ተወዳዳሪ ቅሬታውን በሕጉ መሠረት ለሚመለከተው አካል ማቅረብ ይችላል፡፡

፫/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ተወዳዳሪ ቦርዱ ጊዜያዊ ውጤቱን ይፋ ካደረገ በኋላ በምርጫው ሂደትና ውጤት ላይ ያለውን አስተያየትና ቅሬታ የሚመለከት ይፋዊ መግለጫ ለመገናኛ ብዙኃን መስጠት ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚሰጥ መግለጫ ይዘት ቅሬታ በተነሳባቸው ነጥቦች ብቻ የተወሰነ ሆኖ መግለጫው በሚሰጥበት ወቅት ባለው ሁኔታ ላይ የሚያተኩር መሆን አለበት፤

፭/ በፖለቲካ ፓርቲ ወይም በግል ተወዳዳሪ የምርጫ ውጤትን አስመልክቶ የሚሰጥ መግለጫ ግጭትን ከሚቀሰቅስና ተወዳዳሪ ፓርቲም ሆነ ግለሰብን ከሚያጣጥል ቋንቋ የጸዳ መሆን አለበት፡፡

**፩፻፴፪. ለምርጫ ዘመቻ ጥቅም ላይ ስለሚውል የቋንቋ ይዘት እና ሰላማዊነት**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ:-

ሀ/ የምረጡኝ ዘመቻውን ሲያደራጅና ሲያካሂድ ለአጠቃላይ የምረጡኝ ዘመቻ፣ ለድምፅ አሰጣጥ፣ ለቆጠራ እና ለድህረ ምርጫ ሂደቱ ሰላማዊነትና ስኬት አስተዋፅኦ በሚያደርግ አኳኋን ማድረግ አለበት፡፡

ለ/ ከሚጣልበት ኃላፊነትና ካለው ክብር ጋር በተመጣጠነ ደረጃ መንቀሳቀስ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውምሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ ላይ ንግግር የሚያደርግ ሰው:-

ሀ) ግጭት ቀስቃሽ የሆነ ወይም የግል ስብዕናን የሚነካ ቋንቋ ማስወገድ አለበት፡፡

ለ) በማንኛውም መልኩ ለአመጽ የሚጋብዝና በግለሰቦች ወይም ቡድኖች ላይ ስጋትን የሚጭር የቋንቋ አጠቃቀም ማስወገድ አለበት፡፡

**131. Accepting Election Result**

1/ Any political party or independent candidate shall accept the outcome of an election that has been certified by appropriate authorities.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, any political party or independent candidate may present any grievances to the appropriate body in accordance with the law.

3/ Any political party or independent candidate may, after the Broad announces the provisional results, provide official statements to the Mass Media to express his opinions or complaints on the election process and results.

4/ The content of the statement issued in accordance with sub-article (3) of this Article shall focus on the grievance points and be limited to existing situation at the time of the delivery of the statement.

5/ Any statement on election results issued by a political party or independent candidate shall be free from language that incites conflict or disparages a contesting party as well as an individual.

**132. The Peacefulness and Content of the Language to Be Used in Election Campaigns**

1/ Any political party shall:

a) Organize and conduct election campaign in a manner that contributes to the peacefulness and success of the overall campaign, voting, vote counting and post-election processes;

b) Conduct itself with a sense of responsibility and dignity befitting its status.

2/ Any one delivering a speech at a public rally may not:

a) Use inflammatory or defamatory language; or

b) Use language that in anyway incites violence or increases threat to individuals or groups.

፫/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በይፋም ሆነ በስውር አመፅ የሚቀሰቅስ ወይም በማንኛቸውም የመገናኛ ብዙሃን የሚያበረታታ የቋንቋ ይዘት ያለው በራሪ ወረቀት፣ የዜና መጽሔት ወይም ፖስተር ማሳተም ወይም ማሰራጨት የለበትም፡፡

**፩፻፴፫. <u>ያልተገባ የምልክቶች አጠቃቀም</u>**

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ:-

፩/ የሌሎች ፓርቲዎችን አርማ ወይም የምርጫ ምልክት በማመሳሰል መጠቀም፤

፪/ የሌሎች ፓርቲዎች የፖለቲካ ወይም የምርጫ ቁሳቁስ መስረቅ፣ ምልክት ማንሳት፣ ማበላሸት፥ ማጥፋት፤ወይም

፫/ ደጋፊዎቹ በዚህ ክፍል የተከለከለ ማንኛውንም ተግባር እንዲፈጽሙ ማነሳሳት፤

የለበትም፡፡

**፩፻፴፬. <u>ማስፈራራትና አመጽ መቀስቀስ ክልክል ስለመሆኑ</u>**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ማንኛውንም ዓይነት ማስፈራራት ወይም ወከባ የተከለከለ መሆኑን ተቀብሎ:-

ሀ) የፓርቲው ኃላፊዎች፣ እጩዎች፣ አባላት እና ደጋፊዎች መቼም ቢሆን ማንንም ሰው የሚያስፈራሩ፥ የሚያሸማቅቁና የሚያዋክቡ ድርጊቶችን እንዳይፈጽሙ የሚከለክሉ መመሪያዎች ማውጣት፤

ለ) አመፅንና አመጽ ቀስቃሽ ድርጊቶችን መቃወምና አባላቱንም ማስተማር፤

ሐ) በኃላፊዎቹ፣ በእጩዎቹ፣ በአባላቱ ወይም በደጋፊዎቹ የሚፈፀሙ አውዳሚ ወይም ሰላምን የሚያናጉ ድርጊቶችን ወይም ይህን የሚጋብዝ ዛቻን በመቃወም ማስተማር፤

መ) የሌላውን ግለሰብ ሆነ ፓርቲ መብት፣ ንብረትና ጥቅሞች ማክበር፤

አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ የፓርቲው ኃላፊዎች፣ እጩዎች፣ አባላት እና ደጋፊዎች ለፖለቲካ የድጋፍ ሰልፍ፥ ለስብሰባ፣ የእግር ጉዞ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሲወጡ ማናቸውንም ባህላዊ ወይም ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎች መያዝ ክልክል መሆኑን ማስተማር፤

አለበት፡፡

3/ No political party shall publish or distribute any pamphlets, newsletters or posters containing inflammatory language or material that blatantly or covertly incites violence or encourages such acts through mass media.

**133. <u>Inappropriate Use of Symbols</u>**

Any political party shall not:

1/ Imitate the emblems or candidature symbols of other parties;

2/ Steal, remove, disfigure or destroy political or campaign materials of other parties; or

3/ Incite its supporters to commit any of the acts prohibited under this Part;

**134. <u>Prohibition of Intimidation and Incitement of Violence</u>**

1/ Any political party, accepting the prohibition of any form of intimidation or harassment, shall:

a) Issue instructions that expressly prohibit any act of intimidation, humiliation or harassment by party officials, candidates, members and supporters against any person at any time;

b) Denounce as well as educate members against all violence and violence inciting acts;

c) Condemn as well as educate against officials, candidates, members or supporters' destructive or violent acts or threats that invite violence; and

d) Respect the rights, property and interests of other individuals as well as parties.

2/ The leader of any political party shall instruct the party's officials, candidates, members and supporters not to bring along any traditional or modern weapons to any political rally, meeting, march or demonstration.

፫/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ:-

ሀ) በማንኛውም የሁከት ወይም የአመጽ እንቅስቃሴ መሳተፍ ወይም እንዲደረግ መፍቀድ የለበትም፤

ለ) በህዝብ ወይም በግለሰብ ንብረት ላይ ውድመት እንዳይደርስ የተቻለውን ሁሉ በማድረግ መከላከል አለበት፤

ሐ) ደጋፊዎቹ በዚህ ክፍል የተደነገጉ ማናቸውንም ክልከላዎች እንዲጥሱ ማነሳሳት የለበትም፡፡

**፻፴፭. ስልጣንን ያለ አግባብ መጠቀም**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ:-

ሀ) ያለውን የሥልጣን ኃላፊነትና የተለየ ዕድል ወይም ተፅዕኖ የማሳደር ችሎታ ለፖለቲካ ፍላጎቱ ለመጠቀም መደለያ ማቅረብን፣ ቅጣትን ወይም ማንኛውንም ህገወጥ ተግባር መጠቀም፤

ለ) የፌደራል መንግሥትን፣ የክልል መንግሥትን፣ የከተማ ማዘጋጃ ቤትን ወይም ሌላ የህዝብ ሀብትን በምርጫ ህጉ ከተፈቀደው አኳኋን ውጭ ለምርጫ ቅስቀሳ ዓላማ መጠቀም፣

የለበትም፡፡

፪/ በዚህ ክፍልውስጥ "ስልጣን፣ ልዩ መብት ወይም ጫና" ማለት የወላጅ፣ የዝምድና፣ የመንግሥት፣ የፖሊስ፣ የአካባቢ ታጣቂ ኃይል፣ የወታደራዊ ወይም ልማዳዊ ወይም ባህላዊ ስልጣንን ያካትታል፡፡

**፻፴፮. ስለ ሙስና ተግባር**

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ:-

፩/ ኃይል በመጠቀም ወይም የገንዘብም ሆነ ሌላ ዓይነት መደለያ በመስጠት መራጩ ህዝብ ለአንድ ፓርቲ ወይም እጩ ድምጽ እንዲሰጥ ወይም እንዳይሰጥ ወይም ድምፁን ከመስጠት እንዲታቀብ ማድረግ፤

፪/ ኃይል በመጠቀም ወይም የገንዘብም ሆነ ሌላ ዓይነት መደለያ በመስጠት ሰዎች እጩ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀርቡ ወይም እንዳይቀርቡ ወይም ከእጩ ተወዳዳሪነታቸው እንዲወጡ ወይም ከእጩ ተወዳዳሪነት እንዳይወጡ ማድረግ፤

፫/ ማንኛውም የሥራ ኃላፊ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ በሚመራው ወይም በሚሰራበት ተቋም አግባብ ያልሆነ ድጋፍ ወይም እርዳታ በመጠቀም እጩ ተወዳዳሪን ማስተዋወቅ ወይም

3/ Any political party:

a) May not engage in or permit any act of violence;

b) Shall do everything under its power to prevent the destruction of any public or private property; and

c) May not encourage its supporters to commit any of the acts prohibited under this Part.

**135. Abuse of Power**

1/ Any political party may not:

a) Use its position of power, special opportunity or influencing ability to offer bribes or penalties or use any other illegal acts to further its political interest; or

b) Use Federal, Regional, Municipal or other public resources for campaign purposes other than those allowed by the election laws.

2/ In this section, "a position of power, special opportunity or influencing ability" includes parental, familial, governmental, police, local armed militia as well as military, traditional or customary authority.

**136. Corrupt Practices**

Any political party shall not:

1/ Coerce, offer bribe or offer other inducements to voters so they can vote for or against a particular party or candidate, or to abstain from voting;

2/ Coerce, offer bribe or offer other inducements to influence whether a person becomes a candidate or withdraws from an election;

3/ Any government official or civil servant uses his official time, responsibilities and resources to promote candidates or discourage other candidates from promoting themselves through

የሌሎች ተወዳዳሪዎችን የማስተዋወቅ ዕድል ማደናቀፍ፤

የለበትም፡፡

**፩፻፴፯. ቀጣይ ግንኙነት ስለመፍጠር**

፩/ ማንኛውም በህጋዊነት የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር ቀጣይ ግንኙነት ፈጥሮ መንቀሳቀስ ይችላል፡፡

፪/ የፖለቲካ ፓርቲዎች የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ጠብቀው በምርጫ ዘመቻ ወቅት እና በማናቸውም ጊዜ በጋራ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት የሚያገለግል የጋራ መድረክ ሊመሰርቱ ይችላሉ፡፡

**ምዕራፍ ሁለት**

**የባለድርሻ አካላት የምርጫ ኃላፊነት**

**፩፻፴፰. የፖለቲካ ፓርቲዎችና እጩ ተወዳዳሪዎች ኃላፊነት**

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ እና እጩ ተወዳዳሪ ይህ የምርጫ አዋጅ በመራጩ ህዝብ ዘንድ እንዲታወቅ የበኩሉን ጥረት ማድረግ አለበት፤ በተለይም አዋጁን ለእጩዎቹ ለአባላቱና ለደጋፊዎቹ በማስተማር በሁሉም ዘንድ መታወቁንና መከበሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፪/ እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ በምርጫው ሂደት የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች ለመራጮች ለማስተማር የሚደረጉ ጥረቶችን መደገፍና ማስተዋወቅ አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ እና እጩ ተወዳዳሪ:-

ሀ/ የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች ማክበር፤

ለ/ እጩዎቹ ባለስልጣኖቹ፣ ወኪሎቹ፣ አባሎቹና ደጋፊዎቹ ይህን አዋጅ አክብረው እንዲንቀሳቀሱ መምራት እና ማክበራቸውንም የሚያረጋግጡ ተገቢ እርምጃዎች መውሰድ፤

አለበት፡፡

፬/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ እና እጩ ተወዳዳሪ ፤ሁሉም ሰው:-

ሀ) የፖለቲካ እምነቱን እና አስተያየቱን በነፃ የመግለፅ፤

ለ) በሌሎች የፖለቲካ እምነት እና አስተያየት ላይ የመከራከር እና የመተቸት፤

ሐ) የራሱን የምርጫ ቅስቀሳ ቁሳቁሶች የማተምና የማሰራጨት፤

መ) ፖስተሮችን፣ ባነሮችንና ቢልቦርዶችን የመስቀል፤

legal means.

**137. Continued Communications**

1/ Any legally registered political party may undertake its activities by forging an enduring relationship with other parties.

2/ Political parties may, preserving the provisions of this Proclamation, form a joint forum to discuss issues of mutual interest during electoral campaign period or any other time.

**CHAPTER TWO**

**RESPONSIBILITIES OF STAKEHOLDERS**

**138. Responsibilities of Political Parties and Candidates**

1/ Every political party and candidate shall make an effort to popularize this Proclamation among the voters; in particular, by educating this Proclamation to its candidates, members and supporters, it shall ensure that it is understood and respected by all.

2/ Evert political party, in the election process, shall support and promote efforts to educate voters the provision of this Part.

3/ Every political party and candidate shall:

a) Abide by this Proclamation; and

b) Provide leadership to its candidates, officials, agents, members and supporters to comply with this Proclamation and take appropriate measures that ensure compliance.

4/ Every political party and candidate shall have the duty to publicly declare that everyone has the right to:

a) Freely express his political belief and opinions;

b) Debate and challenge the political views and opinions of others;

c) Publish and disseminate his own campaign materials;

d) Display banners, billboards and posters;

ሠ) ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ማንኛውም ዓይነት ገንዘብ፣ የቁሳቁስና የሰው ኃይል የምርጫ ድጋፍ የማሰባሰብ፤

ረ) አባላትን የመመልመል፤

ሰ) ህዝባዊ ስብሰባዎችን የማካሄድ፤

ሸ) በህዝባዊ ስብሰባዎች የመገኘት፤

መብቶች እንዳሉት በይፋ የመግለፅ፣ ግዴታ አለበት፡፡

፭/ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ዕጩ ተወዳዳሪዎች አዋጁንና በአዋጁም ለመገዛት ያላቸውን ቁርጠኝነት ለህዝብ ይፋ ማድረግ አለባቸው፡፡

፮/ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና እጩ ተወዳዳሪዎች ነፃና ፍትሀዊ ምርጫን የሚጎዳ ወይም የሚያጣጥል ማንኛውንም ተግባር በይፋ ማውገዝ አለባቸው፡፡

**፻፴፱. <u>የቦርዱና የሌሎች የምርጫ አስፈፃሚ አካላት ኃላፊነት</u>**

፩/ ቦርዱ ይህ አዋጅ በምርጫው ሂደት ላይ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ሚና የሚጫወቱ መንግሥታዊና ሌሎች አካላት ዘንድ እንዲታወቅ ማድረግ አለበት፡፡

፪/ ቦርዱ የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች ለሚመለከተው ሁሉ የማሰራጨት ኃላፊነት አለበት፡፡

፫/ በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈፃሚ አካላት በዚህ አዋጅ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲይዙ ለሚመለከታቸው ሁሉ ትምህርት መስጠት አለባቸው፡፡

**፻፵. <u>የሌሎች አካላት ሚና</u>**

፩/ የመገናኛ ብዙሃን የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች አስመልክቶ ለህዝብ ትምህርት እንዲሰጡ ቦርዱ ድጋፍ ያደርግላቸዋል፡፡

፪/ በቦርዱ በሚወጣው መመሪያ መሰረት ከቦርዱ ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች አስመልክቶ ትምህርት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

**፻፵፩. <u>የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት</u>**

፩/ በምርጫ የሚወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የዚህን ክፍል ድንጋጌዎችና ሌሎች የጋራ ጉዳዮችን ተግባራዊ ለማድረግና በምርጫው ሂደት በሚነሱ ልዩ ልዩ የአፈፃፀም፣ የዴሞክራሲ፣ የሰብአዊ መብት ጉዳዮችንና የህግ የበላይነትን በኢትዮጵያ ለማጎልበት በሚያግዙ ጉዳዮች ላይ በመመካከር ችግሮችን እያቃለሉ ለመጓዝ ይችሉ ዘንድ የጋራ ምክር ቤት መመስረት ይችላል፡፡

e) Mobilize financial, material and human resource support for the election, in accordance with the law;

f) Recruit members;

g) Hold public meetings;

h) Attend public meetings.

5/ Political parties and candidates shall publicly declare their commitment to abiding by the Proclamation.

6/ Political parties and candidates shall publicly condemn any action that may harm or undermine the conduct of free and fair elections.

**139. <u>Responsibilities of the Board and Other Election Officials</u>**

1/ The Board shall familiarize this Proclamation among governmental and other institutions that have direct or indirect roles in the election process.

2/ The Board has the responsibility to disseminate the provisions of this Part to all concerned bodies.

3/ Election officials at all levels shall provide training on the Proclamation to raise awareness for all concerned persons.

**140. <u>Role of Other Organs</u>**

1/ The Board shall support the media in their effort to educate the public about the provisions of this Part.

2/ Institutions accredited based on the directive to be issued by the Board shall teach the contents of this Proclamation.

**141. <u>Council of Political Parties</u>**

1/ Political parties contesting in elections may establish a joint council to help them enforce this Proclamation and other common agenda; amicably resolve various implementation, democracy, human rights issues that may arise during the election process; and discuss issues that help promote supremacy of the rule of law in Ethiopia.

፪/ የጋራ ምክር ቤቱ አደረጃጀት፣ አሠራርና ሥርዓት አስመልክቶ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ በሚወስኑት መሠረት ይፈጸማል፡፡ሆኖም የፖለቲካ ፓርቲዎቹ የሚመሠርቱት የጋራ መድረክ አደረጃጀትና የአሠራር ሥርዓት ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የማይቀረን መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

## ምዕራፍ ሦስት
## የስነ ምግባር ጥሰቶች እና ስለሚወሰዱ እርምጃዎች
### ንዑስ ክፍልአንድ
### የስነ-ምግባር ጥሰቶች

**፩፻፵፪. መደለያ መስጠትና ኃይልን ወይም ሥልጣንን አለ አግባብ መጠቀም**

አንድ የፖለቲካ ፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ:-

፩/ ማንኛውንም መደለያ ወይም ጉቦ የሰጠ ወይም የተቀበለ፤

፪/ በድምጽ አሰጣጡ ወይም በቆጠራው ጣልቃ የገባ ወይም ያወከ፤

፫/ ኃይል በመጠቀም፣ መደለያ በመስጠት ወይም በሌላ በማንኛውም አድራጎት መራጩ ሕዝብ ለአንድ ፓርቲ ወይም እጩ ድምጽ እንዲሰጥ ወይም እንዳይሰጥ ወይም ከመስጠት እንዲታቀብ ያደረገ፤

፬/ የድምጽ መስጫ ጣቢያን በሀይል የተቆጣጠረ ወይም በሕገ-ወጥ መንገድ ድምጽ ለማግኘት የሞከረ፤

፭/ ሥልጣኑን መከታ በማድረግ መደለያ ወይም ቅጣት ወይም ሌላ የማስፈራሪያ ዘዴ የተጠቀመ፣

፮/ ማንኛውንም መደለያ በመስጠት ኃይል በመጠቀም፣ ወይም በማንኛውም ዓይነት ድርጊት እጩ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀርቡ ወይም እንዳይቀርቡ ወይም ከእጩ ተወዳዳሪነት እንዲወጡ ወይም እንዳይወጡ ያደረገ፤

፯/ የመንግሥት ሰራተኛ እና ኃላፊ ሆኖ በራሱ የግል ሳይሆን በመንግሥት የስራ ሰዓት እና ኃላፊነት ተቋሙን በመጠቀም እጩዎችን ያስተዋወቀ ወይም ሌሎች እጩዎች ራሳቸውን በሕጋዊ መንገድ እንዳያስተዋውቁ ያደናቀፈ፤

፰/ የመንግሥት ንብረት ለምርጫ ቅስቀሳ የተጠቀመ እንደሆነ፤

የስነ ምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ይቆጠራል፡፡

2/ Political parties shall determine the organizational structure, procedures and operating procedure of the joint council. However, the organization and procedures of the joint council established by political parties shall not contradict the provisions of this Proclamation.

## CHAPTER THREE
## ETHICAL MISCONDUCT AND APPLICABLE MEASURES
### SUB- SECTION ONE
### ETHICAL MISCONDUCT

**142. Bribery and Abuse of Power and Force**

Any political party, independent candidate, Coalition, Front, Alliance, Movement; and party leader, official, candidate, member, agent or representative of a party who:

1/ Offers or receives any kind of inducement or bribe;

2/ Interferes or disturbs the process of voting or counting;

3/ Coerces, offers bribe or influence by other means to induce voters to vote for or against a particular party or candidate or to abstain from voting;

4/ Controls polling station by force or tries to obtain votes illegally;

5/ Abuses power by offering a bribe, threatening a penalty or uses any other means of intimidation;

6/ Coerces, offers bribes or use any other means to influence whether a person becomes a candidate or withdraws from an election;

7/ A civil servant or a government official, uses his official time, responsibilities and resources to promote candidates or discourage other candidates from promoting themselves through legal means;

8/ Uses public property for election campaigns;

shall be deemed to have committed an act of ethical violation.

**፩፻፵፫. ፍርሃት በመቀስቀስ ወይም ሁከት መፍጠር ማንኛውንም የምርጫ እንቅስቃሴ ማስተጓጎል**

ማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ:-

፩/ በምርጫ ሂደት ጫና ወይም ተጽዕኖ በመፍጠር ጣልቃ የገባ፤

፪/ ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎችሀሳባቸውንበነጻነት እንዳያሰራጩ ስጋት እና ፍርሀት የፈጠረ፤

፫/ በማንኛውም መንገድ የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የመራጩን ሕዝብ እንቅስቃሴ ያደናቀፈ ወይም ያወከ፤

፬/ ሕዝባዊ ቅስቀሳ ወይም ስብሰባ ወይም ውይይት ወይም ትምህርትና ስልጠና እንዳይካሄድ ያደናቀፈ ወይም ሁከት የፈጠረ፣

፭/ ሕዝብ ድምጽ ሲሰጥ ያወከ ወይም ድምጽ እንዳይሰጥ ችግር የፈጠረ፤

፮/ የሌሎች ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ ዘመቻ እንዲስተጓጐል ወይም እንዲቋረጥ ወይም እንዲበላሽ ወይም እንዲዳከም ያደረገ፤

፯/ ሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ፣ ስብሰባ፣ የእግርጉዞ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ያደናቀፈ ወይም ሌላ ሰው እንዳይሳተፍ የከለከለ፤

፰/ መራጮችን የሰደበ ወይም ያንጓጠጠ ወይም የመምረጥ መብታቸውን ያደናቀፈ፤

፱/ ለምርጫው ሂደት የምርጫ አስፈፃሚዎችን እና የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ፀጥታና ደህንነት ለማረጋገጥ በሚደረግ ጥረት ከጊዜና ቦታ አኳያ እገዛ ማድረግ እየቻለ ያላደረገ ወይም ያወከ፤

፲/ በማንኛውም ዓይነት መንገድ መራጩ ህዝብ እንዳይመዘገብ ወይም እንዳይመርጥ ያደረገ፤

፲፩/የድምጽ አሰጣጡን ሚስጢራዊነት ያላከበረ ወይም እንዲከበር እገዛ ማድረግ ሲገባው ያላደረገ፤

፲፪/ የሥነ ምግባር አዋጁ ተጥሷል በሚል ሽፋን የሀሰትና የተጋነነ አቤቱታ በማቅረብ ቅሬታ የማሰማት መብቱን ያለአግባብ የተጠቀመ እንደሆነ፤

የሥነ ምግባር ጥሰት እንደፈፀመ ይቆጠራል፡፡

**፩፻፵፬. በምርጫ ሂደት ሰላምና ፀጥታ የሚያናጉ መልዕክቶችን ማስተላለፍ**

ማንኛውም የፖለቲካፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ፡-

**143. Obstruction of Election Campaign through Intimidation and Disturbances**

Any political party, independent candidate, Coalition, Front, Alliance, Movement; and party leader, official, candidate, member, agent or representative of a party who:

1/ interferes in the election process through pressure and undue influence;

2/ intimidates or threatens other political parties not to share their views freely;

3/ in any way prevents or hampers the activities of political parties or voters;

4/ creates obstacles or chaos to prevent campaigns, meetings, discussions or any training or education;

5/ disturbs or prevents the process of voting;

6/ prevents or disturbs stopes, weakens the campaign of other political parties or candidates;

7/ obstructs the conduct of rallies, meetings, marches or demonstrations or prevents others from participating in such activities;

8/ insults, belittles or hampers the rights of voters;

9/ fails to cooperate, despite being in a position to do so, in efforts during the election process to ensure the security of election officials and candidates;

10/ in any manner prevents the voters from registering or voting;

11/ violates the secrecy of the voting process or fails to ensure its observance;

12/ abuses its right by lodging false and exaggerated complaints under the pretext of violation of this Proclamation;

shall be deemed to have committed ethical violation.

**144. Disseminating Information that Destabilizes Peace and Security During the Election Process**

Any political party, independent candidate, Coalition, Front, Alliance, Movement; as well as any party leader, official, candidate, member, agent or representative of a party who:

፩/ የምርጫ ዘመቻውን ሰላም የሚያናጋ ወይም ግጭት የሚቀሰቅስ ወይም አመፅ የሚጋብዝ ወይም ስጋት የሚፈጥር ንግግር ያደረገ፤

፪/ በይፋም ሆነ በስውር አመፅን የሚቀሰቅስ ይዘት ያለው በራሪ ወረቀት፣ የዜና መጽሔት ወይም ፖስተር ያሰራጨ፤

፫/ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ሚስጥራዊነት አይጠበቅም የሚል የሀሰት መረጃ የሰጠ እንደሆነ፤

የስነ ምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ይቆጠራል፡፡

**፩፻፵፭. <u>የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ እንቅስቃሴ ማደናቀፍ</u>**

ማንኛውም የፖለቲካፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ:-

፩/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል እንዳይመለምልና ጽህፈት ቤት እንዳይከፍት በማናቸውም መንገድ ያደናቀፈ፣ ወይም የተከፈቱ ጽህፈት ቤቶች በነፃነት እንዳይሠራባቸው በግልፅም ሆነ በስውር ያወከ ወይም ሁከት እንዲፈጠር ያደረገ ወይም በማንኛውም ዓይነት ድርጊት የማንኛውንም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪ የምርጫ እንቅስቃሴ ያደናቀፈ፣

፪/ ፓርቲዎች ያዘጋጁት የድርጅት ልሳን፣ የምርጫ ማስታወቂያ፣ በራሪ ጽሑፍ፥ ወይም ፖስተር እንዳይሰራጭ፣ እንዳይታይ ወይም እንዲበላሽ ያደረገ ወይም እንዳይለጠፍ ያወከ ወይም የተለጠፈውን የቀደደ፣ ያበላሸ፣ ያነሳ፥ ያጠፋ፣

፫/ የሌላን የፖለቲካ ፓርቲ ምልክት ወይም አርማ የቀዳ ወይም አስመስሎ የተጠቀመ፣

፬/ የሌላ ፖለቲካ ፓርቲን የምርጫ ቁሳቁስ የሰረቀ ወይም ያበላሸ ወይም ያጠፋ እንደሆነ፤

የሥነ ምግባር ጥሰት እንደፈፀመ ይቆጠራል፡፡

**፩፻፵፮. <u>ከጋዜጠኞች ወይም ከታዛቢዎች ጋር አለመተባበር</u>**

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ:-

፩/ የመገናኛ ብዙኃንን ነፃነትን የተጋፋ፣

፪/ በምርጫ ሂደት ጋዜጠኛን ያዋከበ ወይም ሥራውን ያደናቀፈ፤

1/ delivers a speech that destabilizes the peaceful conduct of election campaigns, foments violence, incites clashes or triggers threats;

2/ distributes pamphlets, newsletters or posters containing language or material that overtly or covertly incites violence; or

3/ provides false information by stating that the voting process does not maintain secrecy of the ballot;

shall be deemed to have committed an act of ethical violation.

**145. <u>Disrupting the Election Campaign of Other Parties or Candidates</u>**

Any political party, independent candidate, Ccoalition, Front, Alliance, Movement; as well as any party leader, official, candidate, member, agent or representative of a party who:

1/ prevents a political party from recruiting a member or an opening office, prevents opened offices from operating freely by creating overt or hidden chaos, or in any manner disrupts the election activity of a party or a candidate;

2/ hinders the dissemination and visibility, defaces or prevents the posting and sharing of another party's publication, campaign flyers or posters;

3/ imitates or uses the logo or symbols of another party; or

4/ steals, disfigures or destroys campaign materials of another party;

shall be deemed to have committed an ethical violation.

**146. <u>Failure to Cooperate with Journalists and Election Observers</u>**

Any political party, independent candidate, Coalition, Front, Alliance, Movement; as well as any party leader, official, candidate, member, agent or representative of a party who:

1/ encroaches the freedom of the press;

2/ harasses or obstructs journalists during electoral process; or

፫/ የተፈቀደላቸውን ታዛቢዎች ያላከበረ ወይም ያልተባበረ እንደሆነ፣

የስነ ምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ይቆጠራል፡፡

## ፩፻፵፯. የሥነ ምግባር ድንጋጌዎቹን አለማስተዋወቅና ሕገ ወጥ ድርጊቶችን አለማውገዝ

አንድ የፖለቲካ ፓርቲ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ:-

፩/ በአባሉ፣ በአቀረበው እጩ ተወዳዳሪ ወይም በመሪው የተፈፀመን የአመፅ ድርጊት ወይም ለአመፅ የሚጋብዝ ተግባር በይፋ ማውገዝ ሲገባው ያላወገዘ፡፡

፪/ ኃላፊዎቹ፣ እጩዎቹ፣ አባላቱና ደጋፊው መቼም፣ ማንንም ማስፈራራት እንደሌለባቸው በግልጽ የሚከለክል መመሪያ ያላወጣ እንደሆነ፣

የስነ ምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ተቆጥሮ ቦርዱ የሚወስነውን ቅጣት የሚፈጸምበት ሲሆን የፈጸመው ጥፋት በሌሎች ሕጎችም የሚያስቀጡ እንደሆነ ቦርዱ ጉዳዩን ለሚመለከተው አካል ሊመራው ይችላል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## በተለያዩ አካላት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

## ፩፻፵፰. በቦርዱ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

በሌሎች ህጎች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በክፍል ስድስት ንዑስ ክፍል አንድ ቦርዱ እንደየጥፋቱ ሁኔታ ጉዳዩን ወደ አቃቤ ህግ ሊመራው የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቅጣቶች በጥፋተኛው ላይ ማስተላለፍ ይችላል:-

፩/ ጥፋቱን ለፈፀመ ሰው ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ይፋ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣

፪/ ጥፋቱን የፈፀመ እጩ ወይም ፓርቲ ለአጭር ጊዜ በከፊል ወይም በሙሉ በመገናኛ ብዙሃን እንዳይጠቀም ማገድ፣

፫/ ጥፋቱን የፈፀመ ፓርቲ በመንግሥት ለፖለቲካ ፓርቲዎች ድጎማ ከሚመድበው ገንዘብ ፓርቲው ተጠቃሚ እንዳይሆን ማድረግ፣

፬/ ጥፋተኛውን የፓርቲ ወይም የግል እጩ ተወዳዳሪ እንደጥፋቱ ክብደት ከምርጫ ተወዳዳሪነት መሰረዝ፣

3/ disrespects or fails to cooperate with accredited election observers;

shall be deemed to have committed an ethical violation.

## 147. Failure to Popularize the Code of Conduct and to Condemn Illegal Acts

Any political party, Party Coalition, Front, Alliance, Movement as well as political party leader who:

1/ fails to publicly condemn any act of violence or acts which incite violence carried out by its members, candidates or leaders;

2/ fails to issue a directive that clearly restrains leaders, candidates, members and supporters from intimidating others at any time;

shall be deemed to have committed acts of ethical violation and will be subject to the Board's measures and if the act is punishable by other laws, the Board shall refer the matter to the relevant body.

## SUB-SECTION TWO
## MEASURES TO BE TAKEN BY DIFFERENT ORGANS

## 148. Measures to be Taken by the Board

With out prejudice to the provisions of other laws and to the Board's authority to refer to the prosecutor offenses depending on the gravity of the offense in accordance with Part Six sub section one of this Proclamation, the Board may take the following measures on those who committed the act:

1/ Give official warning to the person or political party who committed the act;

2/ Partially or fully suspend the candidate or party who committed the act from using the media for a short period of time;

3/ Prohibit the party who committed the act from accessing government grant to parties;

4/ Cancel a party or independent candidate from contesting in the elections, subject to the gravity of the act;

፭/ ጥፋተኛው የፖለቲካ ፓርቲው በምርጫ ውድድር እንዳይሳተፍ ማገድ፡፡ ቦርዱ ከላይ የተዘረዘሩትን ቅጣቶች በጥፋተኛው ላይ ቢያስተላልፍ እንደ ጥፋቱ ሁኔታ ጉዳዩን ወደ ዓቃቤ ሕግ ሊመራው ይቻላል፡፡

**፻፵፱. አቤቱታ ስለማቅረብ**

ቦርዱ ከላይ የተመለከቱትን የስነምግባር ጥሰቶች ተከትሎ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን አቤቱታውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

**፻፶. በፍርድ ቤት የሚሰጡ ውሳኔዎች**

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ በቀጥታ ቀርቦለትም ሆነ ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፻፵፰ መሰረት በሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበለትን አቤቱታ በመመልከት ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## ክፍል ሰባት
## በምርጫ ሂደት ስለሚነሱ አቤቱታዎችና ክርክሮች

**፻፶፩. መርህ**

፩/ ቦርዱ በምርጫ ሂደት የሚነሱ አለመግባባቶችን በውይይትና በስምምነት ለመፍታት የሚያስችል የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረክ በየደረጃው እንዲቋቋም ያስተባብራል፡፡

፪/ የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረክ ፓርቲዎች በመካከላቸው የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በውይይት የሚፈቱበት መድረክ ሆኖ ያገለግላል፡፡

፫/ በፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረክ አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚደረግ ጥረት በባለጉዳይ ፓርቲዎቹ ፈቃድ ላይ ብቻ የተመሰረተ ይሆናል፡፡

፬/ የጋራ መድረኩ አባላት የሆኑ ፓርቲዎች ወይም አባሎቻቸው ቅሬታቸውን በዚህ አዋጅ ለተቋቋመ አግባብነት ያለው የአቤቱታ ሰሚ አካል የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

፭/ በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በየደረጃው የሚቋቋሙ የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴዎች አባላት ስብጥር፣ ኃላፊነት እና የኮሚቴው የአሰራር ሥርዓት ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ነው፡፡

5/ Suspend the political party from running for elections. The Board, depending on the gravity of the offense and after taking the abovementioned measures on the person who committed the act, may also refer the matter to the prosecutor.

**149. Lodging Complaints**

A party aggrieved by the Board's decision on the ethical violations outlined in Article 148 may apply to the Federal High Court .

**150. Court Decisions**

The Court shall render appropriate decisions on matters it receives at first instance level or an appeal made against the decision of the Board in accordance with Article 148 of this Proclamation.

## SECTION SEVEN
## GRIEVANCES AND DISPUTES ARISING IN THE ELECTORAL PROCESS

**151. Principle**

1/ The Board shall organize, at every level, the establishment of Political Organizations' Joint Forum that would enable resolutions of disputes related to the election process through dialogue and agreement.

2/ Political Organizations' Joint Forum shall serve as a platform at which parties resolve inter-party disputes through dialogue.

3/ Dispute resolution efforts initiated within Political Organizations' Joint Forum shall be based only on the consent of interested parties.

4/ The members of the Joint Forum or their respective members' right to lodge complaints to the appropriate grievance hearing body established under this Proclamation is guaranteed.

5/ With out prejudice to the provision of this Proclamation, the composition, responsibility and procedure of the grievance hearing committee to be established at various levels shall be determined by a directive to be issued by the Board.

፮/ በዚህ ክፍል መሰረት ክርክሮች ወይም አቤቱታዎች የቀረቡለት ውሳኔ ሰጪ አካል የምርጫው ሂደት ነፃ፣ ፍትሀዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ ሆኖ እንዲቀጥል ለማስቻል የምርጫውን የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በማድረግ መቀበልና አፋጣኝ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

፯/ ማንኛውም አቤቱታም ሆነ በማንኛውም አቤቱታ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ በፅሁፍ መሆን አለበት፡፡

፰/ አቤቱታ ሰሚ አካላት የሚቀርብላቸው አቤቱታ የደረሳቸው መሆኑን የሚያሳይ እና አቤቱታው የቀረበበትን ቀን እና ሰዓት የሚገልጽ ማስረጃ ሊሰጡ ይገባል፡፡

፱/ ለቦርዱ ሚቀርቡለት አቤቱታዎች በወቅቱ መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችለው አሰራር በየደረጃው በሚገኙ የምርጫ ፅህፈት ቤቶች ይዘረጋል፡፡

፲/ ቦርዱ በምርጫ ሂደት በሚቀርቡለት አቤቱታዎች ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሚያግዙ የፍሬ ነገር፣ የማስረጃ እና የሕግ ጉዳዮች አጣርቶ የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርብለት አግባብነት ካላቸው የሙያ ዘርፎች የተውጣጡ ባለሙያዎችን የያዘ አጣሪ ጉባኤ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

፲፩/ ቦርዱ ወይም በየደረጃው የሚገኙ የምርጫ አስፈፃሚዎች የቀረቡ አቤቱታዎችን ለመፍታት የሚያስፈልገውን መረጃ እንዲያቀርብለት ማንኛውንም የሚመለከተውን ሰው ወይም የመንግሥት ድርጅት መጥራትና የሚፈለገውን ጉዳይ በአካል ቀርቦ እንዲያስረዳ ወይም እንዲያቀርብ ሊያዝ ይችላል፡፡

፲፪/ ቦርዱ የምርጫ ሂደትን የሚያደናቅፍ ማናቸውም ወንጀል መፈፀሙን ወይም በመፈፀም ላይ መሆኑን ሲያውቅ ወይም በመረጃ የተደገፈ አቤቱታ ሲደርሰው ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ጉዳዩን ወደ ሚመለከተው አካል ይመራል፣ ይከታተላል፡፡

፲፫/ በዚህ ምዕራፍ ከአንቀጽ ፩፻፶፪ እስከ አንቀጽ ፩፻፶፭ በተደነገገው መሰረት በተቀመጠው ጊዜ አቤቱታውን ያላቀረበ ማንኛውም ሰው አቤቱታ የማቅረብ መብቱ በይርጋ ይታገዳል፡፡

፲፬/ በእያንዳንዱ ክልል እና በፌደራል በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የምርጫ ጉዳይ ችሎቶች የመራጮች ምዝገባ ከመጀመሩ አንድ ወር ቀደም ብሎ እንደየአስፈላጊነቱ ይደራጃሉ፡፡

6/ A decision-making body to which disputes or petitions are submitted under this Section shall promptly settle disputes based on the elections timetable to ensure that the electoral process is conducted in a free, fair and peaceful way.

7/ Any grievance as well as any decision on the grievance shall be made in writing.

8/ Grievance hearing organs shall give proof about its receipt of the grievance application by providing a document that shows the date and time of receipt of the application.

9/ The Board shall put in place a system in electoral offices at every level to give a timely decision on complaints submitted.

10/ The Board may establish an inquiry council, composed of professionals from relevant disciplines, which investigates facts, evidences and legal issues and comes up with a recommendation that helps the Board to render decision on application presented in the election process.

11/ The Board or electoral officers at every level may order any person or government body to produce evidence necessary for the resolution of disputes submitted or appear in person and give the necessary explanation or produce the required information.

12/ Where the Board learns or receives a complaint supported by credible evidence that a criminal act that obstructs the election process has been committed or is being committed, it shall refer the case to appropriate authority for a legal action and follow up the matter.

13/ Any person who has not submitted his complaint within the period specified in Articles 152 to 155 shall be barred from submitting his complaint.

14/ Election benches shall be organized, as necessary at different levels of regional and Federal Courts one month prior to the commencement of voter registration.

፲፭/ ቦርዱ አግባብነት ካለው የፌደራል ወይም የክልል የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጋር በመመካከር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲፬) መሰረት የምርጫ ችሎቶች እንዲደራጁና በቂ ዳኞች እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

፲፮/ ቦርዱ ከፌደራልና ከክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ጋር በመተባበር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፲፭) መሰረት በምርጫ ችሎቶች ላይ የሚመደቡ ዳኞች በቂ ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

**፻፶፪. <u>በመራጮች ምዝገባ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች</u>**

፩/ ማንኛውም ሰው በመራጭነት ከመመዝገብ የተከለከለ እንደሆነ ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታውን አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡

፪/ መብት የሌለው ወይም በመራጭነት መመዝገብ የሌለበት ሰው ያለአግባብ ተመዝግቧል የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ተቃውሞውን ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሰረት የሚቀርብ አቤቱታ የማቅረቢያ ጊዜ ከመራጮች የምዝገባ ቀን ጀምሮ የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ይፋ የሚሆንበት ጊዜ እስከሚያልቅ ድረስ ይሆናል፡፡

፬/ የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በ፭ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሑፍ ይሰጣል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) ለቀረበው አቤቱታ የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ፭ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ አቤቱታ አቅራቢው ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ፭ ቀናት ውስጥ አቤቱታ በማቅረብ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡

፮. በምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሚቀርብ አቤቱታ ውሳኔ ከተሰጠበት በ፭ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

፯/ የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በ፭ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሁፍ ይሰጣል፡፡

15/ The Board, in consultation with relevant Federal and Regional Judicial Administration Commissions, shall cause the organization of election benches and availability of sufficient judges for the election benches established under Sub-Article (14) of this Article.

16/ The Board, in cooperation with the federal and regional Supreme Courts, shall make sure that judges assigned to the election benches organized in accordance with Sub-Article (15) of this Article receive sufficient training.

**152. <u>Disputes Arising During Voter Registration</u>**

1/ Any person prevented from registering as a voter is entitled to present his grievance to the Polling Station Grievance Hearing Committee and get decision.

2/ Any person or a Political Organisation protesting that a person who has no eligibility or right to register as a voter has been registered has the right to submit its protest to the Polling Station Grievance Hearing Committee and get a decision.

3/ Grievances under Sub-Articles (1) or (2) of this Article shall be presented from the commencement of the voter registration day until the end of the public display of the electoral roll.

4/ The Grievance Hearing Committee of Polling Station shall examine the submitted complaint and give its decision in writing within five days.

5/ In the event that the Polling Station Grievance Hearing Committee fails to give its decision within five days on the complaint presented to it in accordance with Sub-Articles (1) or (2) of this Article, the complainant is entitled to submit the same to the Constituency Grievance Hearing Committee within five days and get a decision.

6/ A complaint objecting the decision of the grievance committee of the polling station shall be submitted to the Constituency Grievance Hearing Committee within five days of the decision.

7/ The Grievance Hearing Committee of the constituency shall examine the objection and give its decision in writing within five days.

፰/ ምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ፭ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ቅሬታ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በተሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ እንደሆነ በ፭ ቀናት ውስጥ ስልጣን ላለው በየደረጃው ላሉ የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ጉዳዩ እንዲታይለት አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የቀረበለትን አቤቱታ ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፱/ የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት የምርጫ ጣቢያው ፅህፈት ቤት ስራውን ያከናውናል፡፡

**፻፶፫. በዕጩዎች ምዝገባ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች**

፩/ ማንኛውም ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት በእጩነት ከመመዝገብ የተከለከለ እንደሆነ ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን አቅርቦ መልስ የማግኘት መብት አለው፡፡

፪/ አንድ በዕጩነት የተመዘገበ ሰው በእጩነት መቅረብ የለበትም የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታውን አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሰረት የሚቀርብ አቤቱታ የማቅረቢያ ጊዜ ከእጩዎች የምዝገባ ቀን ጀምሮ የተመዘገቡ እጩዎች ይፋ እስከሚሆንበት ቀን ድረስ ይሆናል፡፡

፬/ የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በ፭ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሑፍ ይሰጣል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሰረት በምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በተሰጠ ውሳኔ ቅር የተሰኘ የፖለቲካ ድርጅት እጩ ወይም የግል እጩ በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ለሚቋቋም ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ፯ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

፮/ የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በጽህፈት ቤቱ ሀላፊ ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የሚሰየሙ ሁለት ተጨማሪ አባላት ይኖሩታል፡፡

፯/ የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ ሲቀርብለት በ፯ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሑፍ ይሰጣል፡፡

8/ If the Grievance Hearing Committee of the constituency did not give its decision within five days or if the complainant is aggrieved by the decision of the Committee, he is entitled to apply within five days to the competent federal or regional Court. The Court to which the application is made shall, having ordered the production of evidences and after examining same shall give its decision.

9/ The polling station shall carry out its activities based on the decision given by the Grievance Hearing Committee of the constituency.

**153. Complaints Relating to Candidate Registration**

1/ Any person or political party denied of registration for candidature shall have the right to lodge a complaint to the Constituency Grievance Hearing Committee and get a decision.

2/ Any individual or Political Organisation that objects to the registration of a candidate shall have the right to lodge a complaint to the Constituency Grievance Hearing Committee and get a decision.

3/ Complaints presented based on sub-articles (1) or (2) of this Article can be lodged from the date of commencement of candidate registration until the date of public announcement of registered candidates.

4/ The Grievance Hearing Committee of the constituency shall investigate and give its decision in writing on the complaint submitted to it within five days.

5/ In accordance to Sub-Article (4) of this Article, a candidate of a political party or an independent candidate aggrieved by the decision of the Grievance Hearing Committee of the constituency may apply to the Grievance Hearing Committee to be established in Regional Branch Office within seven days.

6/ The Regional Branch Office Grievance Hearing Committee shall be chaired by the head of the Regional Branch Office and shall have two other members who are appointed in accordance with a directive to be issued by the Board.

7/ The Grievance Hearing Committee of the Regional Branch Office shall give decision in writing within seven days on appeals submitted to it.

፰/ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ፯ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማማ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው። ችሎቱም የቀረበለትን አቤቱታ ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመመርመር በ፲፭ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፱/ የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት የምርጫ ክልሉ ስራውን ያከናውናል፡፡

**፻፶፬. <u>በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች</u>**

፩/ አንድ የተመዘገበ መራጭ ድምፅ ከመስጠት የሚያግደው ሁኔታ ሲፈጠር ቅሬታውን ወዲያውኑ ምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በማቅረብ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡

፪/ የምርጫጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴም፡-

ሀ) ጉዳዩን በማጣራት መራጩ ድምጹን እንዲሰጥ ሊወስን ይችላል፤ወይም

ለ) ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ በማድረግ ጉዳዩን ወደ ምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት በመላክ ውሳኔ እንዲያገኝ ሊያደርግ ይችላል ፣

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪(ለ) መሰረት ጊዜያዊ ድምፅ የሰጠ መራጭ ከምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም እንደሁኔታው ስልጣን ካለው የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት የመምረጥ መብት እንዳለው የሚገልፅ ውሳኔ የድምፅ መደመሩ ከመጠናቀቁ በፊት ለምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት ካላቀረበ የሰጠው ጊዜያዊ ድምፅ ውድቅ ይደረጋል፡፡

፬/ በምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ቅር የተሰኘ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪(ለ) በተመለከተው መሰረት ጊዜያዊ ድምጽ የሰጠ መራጭ ወዲያውኑ ቅሬታውን ስልጣን ላለው የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ ችሎቱም የድምጽ መዳመሩ ሂደት ውሳኔውን እስኪሰጥ ድረስ እንዲዘገይ ሊያዝ ይችላል።

፭/ የአንድን መራጭ ድምፅ መስጠት የሚቃወም ሰው ከላይ በተደነገገው መሰረት አቤቱታውን በየደረጃው የማቅረብና ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡

8/ The aggrieved party has the right to appeal to the Regional Supreme Court where the Grievance Hearing Committee of the Regional Branch Office fails to give decision within seven days, or it is dissatisfied with the decision of the Committee. The Court, having ordered the production of evidences necessary for its decision and after examining same, renders decision within 15 days.

9/ The constituency shall carry out its activities based on the decision given by the Grievance Hearing Committee of the Regional Branch Office.

**154. <u>Complaints Related to Voting</u>**

1/ Where a voter is denied of voting, he shall have the right to promptly lodge a complaint with the Polling Station Grievance Hearing Committee and get a decision.

2/ The Polling Station Grievance Hearing Committee may:

a) investigate the matter and allow the voter to cast his vote; or

b) allow temporary voting and refer the case to the Constituency Electoral Office for a decision.

3/A vote cast in accordance with Sub-Article (2) (b) of this Article shall be made invalid unless the complainant presents to the constituency electoral office, before the tabulation of votes is completed, a decision from the Constituency Grievance Hearing Committee or a competent Federal or Regional Court confirming his right to vote.

4/ Any person who cast a temporary vote in accordance with Sub-Article (2) (b) of this Article and is dissatisfied by the decision of the Constituency Grievance Hearing Committee may immediately submit his application to the competent federal or regional court. The court may order the stay of the vote count until it hands down its decision on the matter.

5/ Any person objecting to the voting right of a voter has the right to lodge his complaint at various levels and get decision in accordance with what is provided hereinabove.

**፩፻፶፭. <u>በድምጽ ቆጠራና ውጤት ስለሚነሱ ክርክሮች</u>**

፩/ በድምፅ ቆጠራ ሂደትና በውጤቱ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ ወይም ወኪል ቅሬታውን ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፰(፬) መሰረት ወዲያውኑ በማቅረብ ሊያስወስን ይችላል፡፡ በኮሚቴው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን አቤቱታውን በ፪ ቀናት ውስጥ ለምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪/ የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በ፪ ቀናት ውስጥ ውሳኔ በጽሑፍ ይሰጣል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አቤቱታ አቅራቢ ውሳኔ በተሰጠው በ፭ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፡፡ቦርዱ የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ በ፲ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተሰጠው በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አቤቱታ አቅራቢ ውሳኔ በተሰጠው ፲ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም የቀረበለትን ቅሬታ ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፭/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በንዑስ አንቀጽ (፬) መሰረት ለቀረበለት አቤቱታ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፮/ ከላይ በተጠቀሱት ንዑሳን አንቀጾች መሰረት በድምፅ ቆጠራ ሂደትና በውጤቱ ላይ የቀረበ ቅሬታ ወይም ይግባኝ በሚታይበት ጊዜ እንደአግባብነቱ የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ፣ ቦርዱ ወይም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቅሬታ የቀረበበት የምርጫ ክልል ውጤት እንዳይገለጽ ሊያዝ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል ስምንት</u>
## <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>

**፩፻፶፮. <u>ጠቅላላ</u>**

በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ በህዝባዊ ምርጫ እና በድምጽ አሰጣጥ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ክፍል የተከለከሉ ተግባራትን መፈፀም በሕግ ያስቀጣል፡፡

**155. <u>Complaints Relating to Vote Counting and Results</u>**

1/ Any political organization, independent candidate or agent who has complaints on the vote counting and results may immediately submit its or his complaint to the Polling Station Grievance Hearing Committee and get a decision in accordance with of Article 58 (4) this Proclamation. A party aggrieved by the decision of the committee may apply to the Grievance Hearing Committee of the constituency within two days.

2/ The Constituency Grievance Hearing Committee shall investigate the complaint submitted to it in accordance with Sub-Article (1) of this Article and give decision within two days.

3/ Any complainant dissatisfied by the decision given in accordance with Sub-Article (2) of this Article may file his petition with the Board within five days of receiving the Committee's decision. The Board shall investigate the complaint and give decision within 10 days.

4/ A complainant dissatisfied by the decision of the Board in accordance with Sub-Article (3) of this Article may file complaint to the Federal Supreme Court within 10 days of receiving the Board's decision. The Court shall request and review all necessary evidences and give its decision on the matter.

5/ The Federal Supreme Court shall give its decision on the complaint submitted to it in accordance with Sub-Article (4) of this Article no later than one month.

6/ While the review of complaints and appeals related to vote counting and results submitted in accordance with the Sub-Articles of this Article are ongoing, the Constituency Grievance Hearing Committee, the Board or the Federal Supreme Court may order the announcement of election results of the constituency or constituencies that are subject of on-going disputes.

## <u>PART EIGHT</u>
## <u>PROHIBITED ACTS</u>

**156. <u>General</u>**

With out prejudice to the provisions of Ethiopian Criminal Code pertaining to offenses against public elections and voting, committing acts prohibited under this Section is punishable by law.

**፩፻፶፯. <u>በምርጫ ሂደት የተከለከሉ ተግባራትና ቅጣቶች</u>**

፩/ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ከቦርዱ ፈቃድ ውጭ ማንኛውንም የምርጫ ሰነድና ቁሳቁስ ያተመ፣ ያባዛ፣ የፈበረከ ወይም በዚህ መልኩ የተዘጋጀን ህገወጥ የምርጫ ሰነድ እና ቁሳቁስ ይዞ የተገኘ ወይም ያደለ እንደሆነ በእስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በድምጽ መስጫ ዕለት በድምፅ መስጫ ጣቢያ አካባቢ ድምፅ ከመስጠት ወይም የተሰጠን ህጋዊ ተግባር ከማከናወን ውጭ ሌላ ማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማድረግ፣ መሳተፍ ወይም ባልተገባ ወይም በተከለከለ ጊዜ የምርጫን ውጤት ማተም፣ ማባዛት፣ ወይም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥፋቶች መፈጸም ከብር ፹ ሺ እስከ ብር ፩፻ ሺ የሚደርስ በገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት እስከ ሦስት ዓመት **በሚደርስ ቀላል እስራት ያስቀጣል፡፡**

፫/ ማንኛውም ሰው:-

ሀ) በቦርዱ ወይም በምርጫ አስፈፃሚዎች ገለልተኝነት ጣልቃ ለመግባት ከሞከረ፣ በተለይም መደለያ ወይም የተስፋ ቃል ከሰጠ ወይም ለመስጠት ከሞከረ፤

ለ) ምርጫን ለማወክ ወይም እንዳይካሄድ ለማድረግ ወይም በምርጫው ሂደት ወይም ውጤት ላይ ጫና ለመፍጠር በማሰብ ጥላቻን ወይም ፍርሀትን የሚቀሰቅስ ወይም በምርጫው ሂደት ወይም በምርጫው ውጤት ላይ ጫና የሚፈጥር የሐሰት መረጃ አሳትሞ ያሰራጨ ወይም ለማሰራጨት ሙከራ ካደረገ፤

ሐ)የምርጫ ሚስጢራዊነትን ከጣሰ፤

መ) ከድምጽ እና ከምርጫ ቁሳቁስ ጋር የተያያዙ ክልከላዎችን ከተላለፈ፤

ሠ) የቦርዱን ወይም የምርጫ አስፈፃሚዎችን እንቅስቃሴ ካወከ፤ ወይም

ረ) የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ወይም የምርጫ ውጤት አገላለፅ፣ የመራጮች ወይም የፓርቲዎችን መብት አስመልክቶ የተጣሉ ክልከላዎችን ከጣሰ፤

ከብር ፴ ሺ እስከ ብር ፶ ሺ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማያንስ ከአንድ **አመት በማይበልጥ ቀላል እስራትይቀጣል፡፡**

፬/ ማንኛውምሰው:-

ሀ) ሆን ብሎ የቦርዱ፣ የምርጫ ዋና አስፈፃሚው፣ የቦርዱ ሰራተኛ ስልጣኑን ወይም ተግባሩንና ኃላፊነቱን በሚያከናውንበት ወቅት እንቅፋት የሆነ ወይም ያደናቀፈ እንደሆነ፤ ወይም

**157. <u>Acts Prohibited During the Elections Period</u>**

1/ Any person or organization, without the consent of the Board, found printing, duplicating, forging any election document and material or found to have possessed or distributed such document and material shall be punishable with imprisonment or a fine.

2/ On election day, acts other than voting and carrying out lawful activity, engaging or participating in political activity, publishing or duplicating elections results at prohibited or inappropriate time, or committing offenses provided below is punishable with a fine from Birr 80,000 to Birr 100,000 or a simple imprisonment from one to three years.

3/ Any person who:

a) Attempts to interfere in the impartiality of the Board or election officials, particularly if he gives or attempts to give bribe or makes a promise;

b) With the intention of disrupting or interrupting the election or exerting undue influence on the election process or the result outcome and distributes or attempts to distribute false information which incites hatred or fear or affects the election result;

c) Violates secrecy of the ballot.

d) Violates prohibitions with regard to voting and elections material

e) Disrupts the undertaking of the Board and election officials; or

f) Violates prohibitions pertaining to political activities or elections result announcement; or the right of voters or parties.

is punishable with fine from Birr 30,000 to Birr 50,000 or simple imprisonment of not less than six months or not exceeding one year.

4/ Any person who intentionally:

a) impedes or obstructs the Board, the chief election official, Board staff when he is exercising his authority or carrying out his duties; or

ለ) የቦርዱን የስብሰባ ሂደት ሆን ብሎ ያቋረጠ ወይም በነዚሁ ቦታዎች በማንኛውም ሁኔታ ያልተገባ ተግባር የፈፀመ እንደሆነ ወይም

ሐ) ሆን ብሎ በቦርዱ የስራ ቦታ ወይም በመታየት ላይ ባለጉዳይ ላይ በሚሰጠው ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ላይ ተገቢ ያለሆነ ተጽእኖ ለማሳደር ሲባል ማንኛውም የሀይል ተግባር የፈፀመ እንደሆነ፣

በ፴ሺ ብር የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል፡፡

**፻፶፰. <u>የምርጫ ማስታወቂያን ስለማጥፋት</u>**

ማንኛውም ሰው ምርጫ ከተጀመረበት ቀን አንስቶ ውጤት እስከሚገለፅበት ቀን ድረስ የማንኛውንም እጩ ተወዳዳሪ ፖስተርን ወይም የምርጫ ማስታወቂያን ያበላሸ፣ ያስወገደ ወይም የቀደደ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል፡፡

**፻፶፱. <u>ዓላማን በህገወጥ መንገድ ማስፋፋት የተከለከለ ስለመሆኑ</u>**

፩/ የአንድን የፖለቲካ ፓርቲ ዓላማ በኃይል ወይም በማስፈራራት ለማስረጽ ማንኛውንም ሰው ወይም ቡድን ማደራጀት ወይም ማሰልጠን ወይም ሰዎችን በግድ መመልመል በህግ ያስቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለፀውን ተግባር ሲፈጸም የረዳ ወይም የተባበረ ማንኛውም ሰው ወይም ቡድን አግባብ ባለው ሕግ ይቀጣል፡፡

## <u>ክፍል ዘጠኝ</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**፻፷. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻ (፪)(ሀ) ያሉት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ መሆን የሚጀምሩት የዚህን አዋጅ መጽደቅ ተከትሎ ከሚደረገው የፌደራልና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫን ቀጥሎ ካለው የበጀት ዓመት ጀምሮ ነው፡፡

፪/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተመዘገበ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ የተቀመጡትን መስፈርቶች ቦርዱ በሚያስቀምጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እንዲያሟላ ይደረጋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚቀመጡትን መስፈርቶች ቦርዱ በሚሰጠው የጊዜ ሰሌዳ ያላሟላ ፓርቲ ቦርዱ ከምዝገባ እስከመሰረዝ የሚደርስ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፡፡

b) interrupts the Board's meeting; or in any condition commits inappropriate act in these places; or

c) commits an act of violence with a view of exerting undue influence on the duty place of the Board or decision or order to be given on a pending case.

is punishable with fine not exceeding Birr 30,000 or simple imprisonment not exceeding one year.

**158. <u>Removing of Election Advertisement</u>**

Whosoever has, from the commencement of the election up to the official announcement of results, damaged, removed or torn apart a candidate's poster or election advertisement shall be punishable with fine or imprisonment not exceeding one year.

**159/ <u>Prohibition of Promoting Agenda through Illegal Means</u>**

1/ Organizing, training, or forcibly recruiting people or group with a view of instilling agenda of a political party through force or intimidation is punishable by law.

2/ Any person or group who assisted or cooperated in the acts in Sub-Article (1) of this Article shall be punished by the appropriate law.

## <u>PART NINE</u>
## <u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

**160. <u>Transitory Provisions</u>**

1/ The Provisions of of Article 100 2(a) of this Proclamation shall come into effect during the budget year following the federal and regional parliamentary elections that will take place after the entry into force of this Proclamation.

2/ Any political party registered before the coming into effect of this Proclamation shall be required to fulfil the requirements set out in this Proclamation according to the timetable established by the Board.

3/ A political party that fails to comply with the requirements stated in Sub-Article (2) of this Article within the timeline set by the Board may face the Board's measures, including cancellation of registration.

**፩፻፷፩. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፩፻፷፪. <u>የተሻሩ ሕጎች</u>**

፩/ የሚከተሉት ሕጎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል:-

ሀ) የተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፪/፲፱፻፺፱፤

ለ) የተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር ፭፻፸፫/፪ሺ፤

ሐ) የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር ፮፻፷፪/፪ሺ፪፤

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

**፩፻፷፫ <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>**

፩/ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይህንን አዋጁ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ቦርዱ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዳ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፩፻፷፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከጸደቀበት ነሐሴ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፩ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት ፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክፕሬዚዳንት**



**161. <u>Duty to Cooperate</u>**

Everyone has the duty to cooperate to implement this Proclamation.

162. <u>Repealed Laws</u>

1/ The following laws are hereby repealed by this Proclamation:

a) The Amended Electoral Law of Ethiopia Proclamation No. 532/2007

b) The Amended Political Parties Registration Proclamation No. 573/2008

c) The Electoral Code of Conduct for Political Parties Proclamation No. 662/2009

2/ Any law which contradicts this Proclamation shall not be applicable on matters covered by this Proclamation.

**163. <u>Power to Issue Regulation and Directive</u>**

1/ The House of Peoples' Representatives may issue regulations to implement this Proclamation.

2/ The Board may issue directives to implement this Proclamation.

164. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force from the date of its adoption by the House of Peoples' Representatives the 24th day of August 2019.

**Done at Addis Ababa, this 16th day of October,2019**

**SAHLE-WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

## የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011

- **ምዕራፍ አንድ-ጠቅላላ**
    - (አንቀጽ 1-2)
- **ምዕራፍ ሁለት-ስለ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ**
    - (አንቀጽ 3-18)
- **ምዕራፍ ሶስት-የቦርዱ ዋና ጽህፈት ቤት**
    - (አንቀጽ 19-24)
- **ምዕራፍ አራት-ስለ ቦርዱ በጀት**
    - (አንቀጽ 25-26)
- **ምዕራፍ አምስት-ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**
    - (አንቀጽ 27-32)

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፩
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 71
ADDIS ABABA 6th June, 2019

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፫/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ...........................................ገጽ ፲፩ሺ፪፻፺፫

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፫/፪ሺ፲፩

## የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ

ዜጎች በየደረጃው በሚካሄድ ነፃ፣ ፍትሃዊና ሰላማዊ ምርጫ በመረጧቸው ተወካዮች አማካኝነት ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ሥልጣናቸውን በተግባር እንዲያውሉ ለማድረግ ነፃ የምርጫ አስፈፃሚ አካል አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ዲሞክራሲን ለማጠናከር ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ከማንኛውም አካል ነፃ አድርጎ በማደራጀት ፍትሃዊ፣ ተዓማኒና ሰላማዊ ምርጫ ለማስፈፀም የሚያስችለው መዋቅር እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አባላትን አመላመልና አሿሿም አሳታፊና ግልጽ በማድረግና የቦርዱን የመዋቅር፤ የሰራተኛ ቅጥርና ምደባ እንዲሁም የበጀት ነፃነት በማረጋገጥ በተፎካካሪ የፖለቲካ ድርጅቶችና በመራጩ ዘንድ ያለውን ተዓማኒነትና የማስፈፀም አቅሙን ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፩፻፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## Content

Proclamation No.1133/2019

National Electoral Board of Ethiopia Establishment Proclamation ............................Page 11293

## PROCLAMATION No. 1133/2019

## A PROCLAMATION TO ESTABLISH THE NATIONAL ELECTORAL BOARD

WHEREAS, it has become important to establish an independent electoral Implementation body in order to enable citizens to exercise their right to self-government through representatives that they elect by way of free, fair and peaceful elections conducted at various levels;

WHEREAS, to strengthen the Ethiopian democracy it has become necessary to organize the National Electoral Board in a manner that is independent from the influence of any other body and which enables it to conduct fair, trust-worthy and peaceful election;

WHEREAS, it has become necessary to improve the credibility and implementing capacity of the National Electoral Board among competing political organizations and the voting public, by making the selection and appointment of the members of the national electoral board participatory and transparent and ensuring the board's independence in regards to its organizational structure, staff employment and deployment and budget;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and 102 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፫/፪ሺ፲፩” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጉም

በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **“ሕገ መንግስት”** ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ሲሆን፤ **“ህገ መንግስታት”** ማለት ደግሞ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና የክልል ህገ መንግስታት ማለት ነው፤

፪/ **" ቦርድ"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፫ መሰረት የተቋቋመው የስራ አመራር ቦርዱን ሙሉ አባላት ያቀፈ ጽህፈት ቤትና በየደረጃው ያሉ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቶችን ያካተተ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፤

፫/ **"የስራ አመራር ቦርድ"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፭ (፩) መሠረት የተሰየመው መልማይ ኮሚቴ የሚመለምላቸውና በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበው የሚሾሙት ናቸው፤

፬/ **“ምርጫ”** ማለት በሕገ መንግስታት እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት የሚካሄድ የጠቅላላ፣ የአካባቢ፣ የማሟያ ወይም የድጋሚ ምርጫ ነው፤

፭/ **“የፖለቲካ ድርጅት”** ወይም **“የፖለቲካ ፓርቲ”** ማለት የፖለቲካ ፕሮግራም ነድፎ ዓላማውን በሕጋዊ መንገድ ለማራመድ የሚንቀሳቀስ ቡድን ነው፤

፮/ **“የምርጫ ክልል”** ማለት ለምርጫ አፈፃፀም እንዲያመች እና ህዝቡ ወኪሎቹን እንዲመርጥ በህግ መሰረት የሀገሪቱ ግዛት ተከፋፍሎ የሚደራጅ የምርጫ አካባቢ ነው፤

፯/ **“የምርጫ ጣቢያ”** ማለት በየደረጃው የሚካሄዱ ምርጫዎች ምዝገባ የሚካሄድበት፤መራጮች ድምፅ የሚሰጡበት እና ቆጠራ የሚካሄድበት ቦታ ነው፤

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the “National Electoral Board of Ethiopia Establishment Proclamation No. 1133/2019”.

### 2. Definitions

In this Proclamation:

1/ **“Constitution”** means the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia; **“Constitutions”** means the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and that of the Regional States;

2/ **“Board”** means the National Electoral Board that is established under Article 3 of this Proclamation which includes all the members of the management board, the office of the board, and coordination offices at different levels;

3/ **“Management Board”** means a board that is comprised of members recruited by committee appointed by the House of People’s Representatives upon recommendation by the Prime Minister in accordance to Article 5 (1) of this Proclamation.;

4/ **“Election”** means general elections, local elections, by-elections and re-elections conducted in accordance with Constitutions and other relevant laws;

5/ “**Political Organization or Political Party**” means a grouping which, having formulated a political program, pursues its aims in a lawful manner;

6 /**“Constituency”** means an electoral district established by dividing the nation's territories in accordance with the law and in a manner conducive for the execution of elections and for the people to elect their representatives;

7/ **“Polling Station”** means a location where voter registration, voting and counting is carried out for elections conducted at every level;

፰/ **“ጽህፈት ቤት”** ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽህፈት ቤት ነው፤

፱/ **“ከፍተኛ የመንግስት ሹመት”** ማለት በሚኒስትር፣ ሚኒስትር ዲኤታ፣ አምባሳደር፣ ኮሚሽነር፤ ምክትል ኮሚሽነር፣ ዋና ዳይሬክተር ወይም ተመሳሳይ ደረጃ ያላቸው ሹመቶችን ያካትታል፤

፲/ **“የስነ ምግባር ጉድለት”** ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙሃኑ የሚስማማባቸው የግብረገብ እሴቶች እና በህጎችና በሙያ ሥነ-ምግባሮች ላይ የተመሰረቱ፡ መርሆችን የሚጥሱ ተግባራት ፈጽሞ መገኘት ነው፤

፲፩/ **"ሰው"** ማለት በህግ የሰውነት መበት የተሰጠው ወይም የተፈጥሮ ሰው ነው፤

፲፪/ በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## ስለ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

### ፫. መቋቋም

፩/ በፌደራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነፃና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲያካሂድ ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ የሆነ ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ተቋቁሟል።

፪/ የቦርዱ ተጠሪነት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል፡፡

፫/ ቦርዱ በአዲስ አበባ ዋና ጽህፈት ቤት የሚኖረው ሲሆን፣ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም የአገሪቱ ክፍሎች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ለመክፈት አጥንቶ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥያቄውን አቅርቦ ሲፈቀድለት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

### ፬. የቦርዱ አቋም

፩/ ቦርዱ ሙሉ ጊዜ የሚያገለግሉ አምስት አባላት ያሉት የስራ አመራር ቦርድ ይኖረዋል፡፡

፪/ የስራ አመራር ቦርድ አባላት በቦርዱ ሰብሳቢ ውሳኔ መሰረት የተለያዩ የቦርዱን ዓላማ ፈፃሚ የስራ ዘርፎችን በኃላፊነት ይመራሉ።

8/ **“Office”** means Office of the National Electoral Board of Ethiopia;

9/ **“High-level Appointment”** means appointment to the rank of Minister, State Minister, Ambassador, Commissioner, Deputy Commissioner, Main Director or appointment of a similar rank;

10/ **“Ethical Misconduct”** means committing actions that are contrary to the moral values that the majority of Ethiopians abide by as well as to principles grounded in legal and professional ethics;

11/ **“Person”** means natural or Juridical person.

12/ Any expression in this proclamation in the masculine gender includes the feminine gender.

## PART TWO
## THE NATIONAL ELECTORAL BOARD

### 3. Establishment

1/ The National Electoral Board is hereby established having its own legal personality as an autonomous organ independent from any influence, in order to conduct free and proper election in the Federal and State constituencies.

2/ The Board shall be accountable to the House of Peoples' Representatives.

3/ The Board shall have head office in Addis Ababa; and as may be necessary, may open branch offices at any part of the country, when submit request to the House of People's Representatives based on study, and approved same by the House of People's Representatives.

### 4. The Organization of the Board

1/ The board shall have a management board consisting of 5 members that serve full-time.

2/ Members of the management board, based on the decision of the board chairman shall be responsible to lead work departments of the board.

፫/ የስራ አመራር ቦርዱ ለስራው አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ንዑስ ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

፬/ ቦርዱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል።

## ፭. የስራ አመራር ቦርዱ አባላት አሰያየም

የስራ አመራር ቦርዱ አባላት በህገ መንግስቱ አንቀጽ ፩፻፪ መሰረት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሚከተለው ሥነ-ሥርዓት መሰረት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ፡-

፩/ ጠቅላይ ሚኒሰትሩ እጩ የስራ አመራር ቦርድ አባላትን የሚመለምል የሚከተሉትን አባላት ያካተተ ገለልተኛ ኮሚቴ ያቋቁማል፡-

ሀ) ከኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ..፩ ሰው፤

ለ) ከኢትዮጵያ የሳይንስ አካዳሚ ............፩ ሰው፤

ሐ) ከኢትዮጵያ ሰራተኞች ኮንፌደሬሽን…፩ ሰው፤

መ) ከኢትዮጵያ ንግድና ማህበራት ምክር ቤት ……………………………………... ፩ ሰው፤

ሠ) ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን….፩ ሰው፤

ረ) ከሲቪል ማህበራትና ከሃገር ሽማግሌዎች የሚመረጡ………………………. ፫ ሰዎች፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስር ከተዘረዘሩት ተቋማት የሚወከሉት ወይም የሚመረጡት የኮሚቴ አባላት ገለልተኛነታቸውና ብቃታቸው የተረጋገጠ፣ እንደ አግባብነቱ በአንቀጽ ፮ ስር የተዘረዘሩትን የስራ አመራር ቦርድ አባልነት መስፈርቶች የሚያሟሉ እና የኮሚቴው ስብጥር ተመጣጣኝ የፆታ ተዋፅኦ ያለበት ሊሆን ይገባል፤

፫/ ኮሚቴው ከህዝብ፣ ከፖለቲካ ድርጅቶችና ከሲቪል ማህበራት የስራ አመራር ቦርድ አባል ሊሆኑ የሚችሉ ግለሰቦችን ጥቆማ ይቀበላል፤

3/ The Management board may establish sub-committees that may be necessary for the execution of its duties.

4/ The Board shall have the staffs necessary for the execution of its duties.

## 5. Appointment of Members of the Management Board

The members of the management board shall be appointed by the House of People's Representatives In accordance with Article 102 of the Constitution, upon nomination by the Prime Minister through the following procedure:

1/ The Prime Minister shall establish an independent committee that will engage in the recruitment of nominees to membership of the management board. The committee shall Composed of the following members:

a) Inter-Religious Council of Ethiopia….. ……………………………..1 person;

b) Ethiopian Academy of Sciences………... ……………………………..1 person;

c) Ethiopian Confederation of Employees …………………..………. 1 person;

d) Ethiopian Chamber of Commerce…… ……………………………..1 person;

e) Ethiopian Human Rights Commission ……………………….…… 1 person;

f) Representatives from civil societies and elders..…………………..….3 persons.

2/ The members of the committee that shall be selected from the institutions under Sub-Article (1) of this Article shall have proportional gender balance and persons whose neutrality and capability are ensured and when appropriate fulfill the criteria to become management board members under Article 6 of this Proclamation;

3/ The Committee shall receive nominations from the public, political organizations and civil societies as to persons fit to be members of the management board;

፬/ ኮሚቴው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ስር በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት ግልፅና አወዳዳሪ በሆነ አካሄድ ከተጠቆሙት ሰዎች ውስጥ የስራ አመራር ቦርድ አባላት ሊሆኑ የሚችሉ እጩዎችን በመለየትና ፈቃደኝነታቸውን በማረጋገጥ የእጩዎቹን ዝርዝር ለሕዝብ ይፋ በማድረግ፣ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይልካል፤

፭/ ኮሚቴው የሚያዘጋጀው የእጩዎች ዝርዝር ምልመላው በሚካሄድበት ወቅት በስራ አመራር ቦርዱ ካሉት ክፍት ቦታዎች ቁጥር እጥፍ መሆን ይኖርበታል፤

፮/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እጩ የስራ አመራር ቦርድ አባላት ስም ዝርዝር ከኮሚቴው ከተቀበለ በኋላ ከተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች ጋር በቀረቡት እጩዎች ላይ ምክክር ያደርጋል፤

፯/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ ፮ ስር የተገለጸውን ምክክር ካደረገ በኋላ ከቀረቡት እጩዎች መካከል በስራ አመራር ቦርዱ ውስጥ ባሉት ክፍት ቦታዎች እጩዎችን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሾሙ ያቀርባል፤

፰/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፯ መሠረት ጠቅላይ ሚኒስትሩ እጩዎችን ሲያቀርብ የሥራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ቦታ ክፍት ከሆነ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ የሚሆኑትን እጩዎች በመለየት ያቀርባል፤

፱/ አንድ እጩ በስራ አመራር ቦርድ አባልነት የሚሾመው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአብላጫ ድምፅ ሹመቱን ሲያፀድቀው ነው፡፡

**፮. <u>የስራ አመራር ቦርድ አባልነት መስፈርቶች</u>**

፩/ አንድ ሰው የስራ አመራር ቦርድ አባል ለመሆን የሚችለው የሚከተሉትን መስፈርቶች ሲያሟላ ነው፡-

ሀ) ትውልደ ኢትዮጲያዊ የሆነ ኢትዮጲያዊ ዜጋ፤

ለ) የማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆነ፤

ሐ) ከምርጫ ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ባላቸው በተለይም በሕግ፣ በፖለቲካል ሳይንስ፣ በሕዝብ አስተዳደር፣ በስታቲስቲክስ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ሌሎች ተዛማጅነት ባላቸው ዘርፎች ከፍተኛ ሙያዊ ብቃት ያለው፤

4/ In accordance with the criteria listed under Article 6 of this Proclamation, the Committee shall select nominees fit to be management board members from the suggestions made in a transparent and competitive process after securing the consent of the nominees. It shall make the list of nominees open to the public and send it to the Prime Minister;

5/ The list of nominees prepared by the committee must be twice the number of available place in the board during the selection process;

6/ The Prime Minister after receiving the list of nominees shall have consultation with representatives of competing political parties on the nominees presented;

7/ The Prime Minister after having the consultation as per Sub-Article 6 of this Article recommend from nominees submitted to it for appointment to the House of People's Representatives, to the available place in the Board;

8/ The Prime Minister when recommend nominees as per Sub-Article (7) of this Article shall identify the Chairman and Deputy Chairman of the management board, if their place is remained vacuum;

9/ A nominee to become a management board member will become a member only when approved by a majority Vote of the House of People's Representatives.

**6. <u>Criteria to be a Management Board Member</u>**

1/ A person shall become a management board member only if he fulfills the following criteria:

a) Ethiopian by birth and Ethiopian national;

b) Not a member of any political party;

c) Has advanced professional qualification on matters related to election; especially law, political science, public administration, statistics, information technology and other related fields;

መ) መልካም ሥነ-ምግባር እና ስብዕና ያለው፤

ሠ) የተሰጠውን ኃላፊነት ለመሸከም የሚያስችል ከፍተኛ የአመራር ብቃት ያለው፡፡

፪/ የቦርዱ አባላት ስብስብ በተቻለ መጠን የብሔርና የፆታዊ ተዋፅኦን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል።

## ፯. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤-

፩/ በሕገ መንግስቱ እና በምርጫ ሕግ መሰረት የሚካሄድ ማንኛውንም ምርጫ እና ህዝበ ውሳኔ በገለልተኝነት ማስፈጸም፤

፪/ የመራጮችን ትምህርት ለሚሰጡ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ፈቃድ መስጠት፣ መከታተልና መቆጣጠር፤

፫/ የፖለቲካ ድርጅቶችን መመዝገብ፣ በህጉ መሰረት መከታተልና መቆጣጠር፤

፬/ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግበትን መስፈርት ማውጣትና በመስፈርቱ መሰረት ድጎማውን ማከፋፈል፤

፭/ በምርጫ ወቅት የፖለቲካ ፓርቲዎችን የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም መወሰን፤

፮/ የምርጫ ክልሎችን አከላለል በተመለከተ ጥናት አድርጎ ለፌደሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ፤

፯/ ለምርጫ ታዛቢዎች ፈቃድ መስጠት፣ መከታተልና መቆጣጠር፤

፰/ የቦርዱን ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በሁሉም ክልሎችና ከዚያ በታች ባሉ የአስተዳደር እርከኖች ማደራጀት፤

፱/ በየደረጃው እና በየጊዜው የሚካሄዱ ምርጫዎች ነፃና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የሚካሄዱበትን ሁኔታ የማመቻቸትና የማረጋገጥ፤

፲/ ምርጫን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሰነዶችና ቁሳቁሶችን የማዘጋጀትና የማሰራጨት፤

፲፩/ በዚህ ህግና በሌሎች ህጎች የተሰጡትን ኃላፊነቶች ለመወጣት አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ማውጣት፤

d) of good ethics and character;

e) High leadership capacity that enables him to hold the responsibility assigned to him.

2/ The composition of management board members to the possible extent shall take into account the ethnic and sex composition.

## 7. Powers and Duties of the Board

The Board shall have the following powers and duties:

1/ execute impartially any election and referendum conducted in accordance with the Constitution and with Election Law;

2/ grant permission, follow up and supervise civil society organizations providing voter education;

3/ register political parties, follow-up and supervise them in accordance with the law;

4/ provide guidelines for the manner in which monetary funds may be contributed to political parties and in accordance with these guidelines allocate the funds;

5/ determine the manner in which political parties may use media during elections;

6/ undertake studies on how to divide electoral regions and present a recommendation to the House of Federation on the basis of those studies;

7/ issue licenses to election observers and follow up and supervise their activities;

8/ establish branch offices of the board at all regional and sub-regional levels;

9/ facilitate and ascertain that elections held periodically and at every level are conducted in a free and fair manner;

10/ prepare and distribute documents and materials necessary to conduct elections;

11/ issue directives necessary to perform its duties given by this Proclamation and other laws;

፲፪/ የምርጫ አስፈፃሚዎችን ገለልተኝነትና ነፃነት የማረጋገጥ እንዲሁም በምርጫ አስፈፃሚነታቸው ምክንያት ከሚደርስባቸው ተፅዕኖ የመከላከል፤

፲፫/ ምርጫን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ የምርጫ ጣቢያዎችን ቁጥር መወሰን፤

፲፬/ ምርጫን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ የምርጫ ክልልና የምርጫ ጣቢያዎችን በመላ ሃገሪቱ ማደራጀት፤

፲፭/ ገለልተኛ፣ ብቃትና የህዝብ ተዓማኒነት ያላቸው የምርጫ አስፈጻሚዎችን መመልመልና ማሰልጠን፤

፲፮/ ከምርጫና ከፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ ማጠናቀር፣ የምርጫ ህጎችንና አፈፃፀምን በመገምገም ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ለይቶ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ፤

፲፯/ የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረክን ማስተባበር፤

፲፰/ የምርጫ ውጤቶችን ማረጋገጥና ይፋ ማድረግ፤

፲፱/ በምርጫ ሂደት ለሚቀርቡ ቅሬታዎች አስተዳደራዊ መፍትሄ መስጠት፤

፳/ በምርጫ ሂደት የምርጫ ውጤትን የሚያዛንፍ የህግ ጥሰት ተከስቷል ብሎ ሲያምን ውጤቱን መሰረዝና ድጋሚ ምርጫ ማካሄድ፣ እንዲሁም በምርጫ ሂደት የተፈጸመ የህግ መጣስ፣ ማጭበርበር ወይም የሰላምና ፀጥታ ማደፍረስ ድርጊት የፈፀሙ ግለሰቦችን በህግ እንዲጠየቁ ማድረግ፤

፳፩/ በጀት አዘጋጅቶ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማቅረብ፣ ማፀደቅና በስራ ላይ ማዋል፤

፳፪/ በየደረጃው የሚካሄዱ ምርጫዎችን መርሃ ግብር ሰሌዳ እንዲዘጋጅ ማድረግ ማጽደቅ እንደ አስፈላጊነቱ ማሻሻልና መፈጸሙን መከታተል፤

፳፫/ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ማቅረብ፤

፳፬/ በዚህ ሕግና በሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ኃላፊነቶች ለመወጣት አስፈላጊ የሆኑ ማንኛውም ተግባራትን ማከናወን፡፡

## ፰. <u>የስራ አመራር ቦርድ ስልጣንና ተግባር</u>

የስራ አመራር ቦርድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ለቦርዱ በአጠቃላይ ከተሰጠው ስልጣንና ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

12/ certify neutrality and freedom of electoral officers and also protect them from any influence that they may come under in relation to their work;

13/ determine the number of polling stations necessary to carry out an election;

14/ establish nation wide the electoral regions and polling stations necessary to carry out an election;

15/ ensure that competent and non-partisan electoral officers who enjoy public trust are recruited and trained;

16/ collect and organaize data relating to elections and political parties, by reviewing election laws and their implementation, submit issues that need revision to the concerned body;

17/ coordinate political parties' joint forum;

18/ certify and officially announce election results;

19/ provide administrative relief for complaints raised in the course of election

20/ cancel election results and order re-election where it has been convinced that violation of law has occurred which would undermine the outcome of the election. In addition, hold individuals accountable for violations of law, fraudulent acts or disturbance of peace in relation to an election;

21/ prepare and submit its Budget to the House of Peoples' Representatives for approval and implement the same;

22/ impose to prepare election schedules taking place at all levels, approve, and as needed amend and follow up the implementation of the same;

23/ submit to the House of Peoples' Representatives reports on its work;

24/ carry out any other activities necessary to fulfill its responsibilities as defined in this Proclamation and other laws.

## 8. <u>Powers and Duties of the Management Board</u>

In addition to the powers and duties given to the board through Article 7 of this Proclamation, the Management Board shall also have the following powers and duties:

፩/ መመሪያዎችን ያወጣል፤

፪/ ለቦርዱ የተሰጡ ዝርዝር ስልጣኖችን የሚመለከቱ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፤

፫/ የቦርዱ የመጨረሻው ቅሬታ ሰሚ አካል ሆኖ ያገለግላል፣ የምርጫ ውጤቶችን ይፋ ከመደረጋቸው በፊት ያፀድቃል፤

፬/ የምርጫ ውጤትን የሚያዛንፍ የህግ ጥሰት በተከሰተ ጊዜ የምርጫ ወጤቶችን ይሰርዛል፣ ድጋሚ ምርጫ ያካሂዳል፤

፭/ የስራ አመራር ቦርዱ፣ የቦርዱ ጽ/ቤት፣ የቦርዱ ሰራተኞች የስራ ሂደት እንዲሁም ቦርዱ ከሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች የሚመሩበትን ፖሊሲ ያዘጋጃል፤ በስራ ላይ ያውላል፤

፮/ የቦርዱን ጽህፈት ቤት ኃላፊና ምክትል ኃላፊ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳ (፩) መሰረት ይሾማል፤

፯/ የስራ አመራር ቦርዱ አባላት የሚመሩበትን የሥነ-ምግባር መመሪያ ያወጣል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡

## ፱. <u>የስራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር</u>

የስራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የስራ አመራር ቦርዱ የበላይ ሃላፊና ዋና ስራ አስፈፃሚ ሆኖ ያገለግላል፤

፪/ ቦርዱን ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ባለው ግንኙነት ይወክላል፤

፫/ የስራ አመራር ቦርዱን ስብሰባ ይጠራል፣ ይመራል፤

፬/ የስራ አመራር ቦርዱ ውሳኔዎች በአግባቡ መፈፀማቸውን ይከታተላል፤

፭/ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በልዩ ሁኔታ በሚፀድቅ ደንብ መሠረት ሰራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

፮/ የቦርዱን የውስጥ አደረጃጀትና በስራ አመራር ቦርዱ አባላት መካከል ያለውን የስራ ክፍፍል ከስራ አመራር ቦርድ አባላት ጋር በመመካከር ይወስናል፤

1/ issue directives;

2/ outline policy directions relating to the powers of the management board as listed above, and follow up their implementation;

3/ serve as the final appeal body of the board for complaints; approve election results before officially announced;

4/ cancel election results and conduct re election when violation of law which would undermine the outcome of the election has occurred.

5/ outline policies to govern liaisons between the management board, the office or staffs of the board and governmental or non-governmental institutions; implement the same;

6/ appoint the Chief Executive and the Deputy Chief Executive of the secretariat as per Article 20 (1) of this Proclamation;

7/ issue Directive on ethics governing the Management Board Members; supervise the implementation of the same;

## 9. <u>Powers and Duties of the Chairman of the Management Board</u>

The Chairman of the Management Board shall have the following powers and duties:

1/ serve as the Main Superior and Chief Executive Officer of the Management Board;

2/ represent the Board in its dealings with third parties;

3/ call and preside over the meetings of the Management Board;

4/ supervise the proper implementation of decisions of the Management Board;

5/ Hire and Administer staffs in accordance with a regulation having basic principles of the civil service law, that will be exclusively passed by the government ;

6/ determine the internal organization of the Board as well as the division of work among the management board member in consultation with the management board members;

፯/ የጽህፈት ቤቱን የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፤

፰/ የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ሰራተኞችን የሙያ ብቃት ካላቸውና ገለልተኛ ከሆኑ የክልሉ ነዋሪዎች መካከል ግልጽ፣ አሳታፊና አወዳዳሪ በሆነ መንገድ መቀጠራቸውን ያረጋግጣል፤

፱/ የፌደራልና የክልል ህገ መንግስቶችን ማዕቀፍ መሰረት በማድረግ የምርጫ አፈፃፀም የጊዜ ሰሌዳ አዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፲/ የቦርዱ በጀት አግባብነት ባላቸው የፋይናንስ ህጎችና መርሆች መሰረት ስራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

፲፩/ የፖለቲካ ድርጅቶችን የጋራ መድረክ ያስተባብራል፤

፲፪/ ማንኛውንም የቦርዱንና የጽህፈት ቤቱን የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ለስራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል፡፡

**፲. የስራ አመራር ቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር**

የስራ አመራር ቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራትይኖሩታል፦

፩/ ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

፪/ በሰብሳቢው የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

**፲፩. የስራ አመራር ቦርዱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት**

፩/ ከስራ አመራር ቦርዱ አባላት ሶስቱ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

፪/ የስራ አመራር ቦርዱ ጉባኤ ውሳኔ በአባላት ድምፅ ብልጫ ይወሰናል፤ ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የሚከፈል ከሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ የስራ አመራር ቦርዱ ውሳኔ ይሆናል፡፡

፫/ የስራ አመራር ቦርዱ የራሱን ዝርዝር የአሰራርና የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፡፡

7/ prepare and submit to the board the short and long-term work plan and budget of the office of the board and supervise its implementation upon approval;

8/ ensure that employees for branch offices of the office were hired from among the region's qualified and impartial residents and in a manner that was transparent, inclusive and competitive;

9/ on the basis of the Federal and State Constitutions, frame work prepare and submit election time tables to the Management Board and supervise its implementation upon approval;

10/ ensure that the Board's budget is used in line with the appropriate rules and regulations of finance;

11/ Coordinate the joint political parties' forum;

12/ present any report on the activities of the Board and the office to the Management Board.

**10. Powers and Duties of the Deputy Chairman of the Management Board**

The Deputy Chairman of the Management Board shall have the following powers and duties:

1/ carry out the duties of the Chairman in the absence of the latter;

2/ perform other duties specifically assigned to him by the Chairman.

**11. Rules of Procedure of the Management Board**

1/ There shall be a quorum where at least 3 members of the Management Board are present.

2/ Decisions of the Management Board shall be made by a majority vote; however, in case of a tie, the Chairman shall have a casting vote.

3/ The Management Board shall issue its own detailed rules of procedure.

## ፲፪. የስራ አመራር ቦርዱ አባላት የስራ ዘመን

፩/ የስራ አመራር ቦርድ አባላት የስራ ዘመን ስድስት ዓመት ይሆናል።

፪/ የስራ አመራር ቦርድ አባላት ለአንድ ተጨማሪ የስራ ዘመን በድጋሚ ሊሾሙ ይችላሉ፤ የመጀመሪያ የስራ ዘመኑ ባለቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የትኛውንም የስራ አመራር ቦርድ አባል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቀጥታ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማቅረብ በአንቀፅ ፭ (፰) መሠረት በድጋሚ ሊያሾም ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አባሉ በራሱ ፍቃድ ስራውን ከለቀቀ ወይም በህዝብ ተወካዮች ምክርቤት፡-

ሀ) በህመም ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን ባለመቻል ፤

ለ) ግልጽ በሆነ የስራ ችሎታ ወይም ብቃት ማነስ፤

ሐ) ከባድ የሥነ-ምግባር ጉድለት መኖር፤ወይም

መ) ለተከታታይ ፮ ወራት በስራ ገበታ ላይ ባለመገኘት፤

ምክንያት ካልተሰናበተ በቀር ከኃላፊነቱ አይነሳም።

፬/ የቦርድ አባል ከቦርድ ኃላፊነቱ በፈቃዱ ከለቀቀ ወይም ጊዜውን ጨርሶ ከተሰናበተ በኋላ ባሉት ሁለት አመታት ውስጥ በማንኛውም ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊነት ሊሾም አይችልም።

## ፲፫. ስራ ስለ መልቀቅና ስለመሰናበት

፩/ አንድ የስራ አመራር ቦርድ አባል በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ (፫) ፣ (ሀ) ፣ (ለ) እና (ሐ) በተቀመጡት ምክንያቶች ከኃላፊነቱ ሊነሳ ይገባል ብሎ ያሰበ አካል ወይም ግለሰብ ጥቆማውን ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ማቅረብ ይችላል።

፪/ አፈ ጉባኤው የቀረበውን ጥቆማ መርምሮ በቂ ምክንያት የሌለው መሆኑን ካመነ ጥቆማውን ውድቅ ያደርጋል፡፡ ጥቆማው ምክንያታዊና መመርመር የሚገባው ነው ብሎ ካመነ፡-

## 12. Membership Term of the Management Board

1/ The term of office of management board members shall be six years.

2/ Management Board members may re-appoint for additional one term; The Prime Minister may directly recommend members for re appointment to the House of People's Representatives after one month of the termination as per Article 5(8).

3/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) and (2) of this Article, unless a management board member leaves his membership on his own consent or is relieved by the House of Peoples' Representatives because of:

a) Inability to carry out his functions due to health reasons;

b) Evident lack of capacity or competence to work;

c) Serious ethical misconduct; or

d) Absence from work for a consecutive period of six months ;

He shall not be relieved of his responsibilities.

4/ For a period of 2 years after leaving his position on his own consent or is relieved by the House of Peoples' Representatives, member of the management board may not be appointed to any high government office.

## 13. Leaving Office and Being Relieved of Office

1/ Any person or anybody who is convinced that a management board member should be relieved of office for the reasons stated in Article 12 /3/ (a), (b) and (c) may inform to the Speaker of the House of People's Representatives to that effect.

2/ If the Speaker of the House of People's Representatives, upon assessing the claim, is convinced that there are no sufficient reasons, it shall reject the claim. If, on the other hand, it is convinced that the claim has sufficient reasons and requires further

ሀ) ከጠቅላይ ፍርድ ቤት አንድ ዳኛ፣

ለ) ከተያዘው ጉዳይ ጋር በቀጥታ የተገናኘ ሙያዊ ብቃት ያለው አንድ ባለሙያ፣ እና

ሐ) ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የተወከለ አንድ ሰው፣

ያሉበት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚሰየም አጣሪ ኮሚቴ ጥቆማውን በተገቢ ሁኔታ እንዲጣራ ያደርጋል፡፡

፫/ ጉዳዩ በመጣራት ላይ ሳለ አፈ ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ክስ የቀረበበት የቦርድ አባል በጊዜያዊነት በቦርዱ ስራ እንዳይሳተፍ ሊያግደው ይችላል፡፡

፬/ አጣሪ ኮሚቴው በሚያጣራበት ሂደት ጥቆማ የቀረበበት የቦርድ አባል እራሱን የመከላከልና መከላከያ ማስረጃ የማቅረብ መብቱ ይጠበቅለታል፡፡

፭/ አጣሪ ኮሚቴው በሚያደርገው ማጣራት ጥቆማው ትክክል መሆኑን ካረጋገጠና ይሄም ከኃላፊነት ሊያስነሳ የሚችል ነው ብሎ ካመነ ፣ የውሳኔ ሃሳቡን ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ያቀርባል፣ አፈ ጉባኤው የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

፮/ የቀረበው የውሳኔ ሃሳብ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በአብላጫ ድምጽ ከፀደቀ ጥቆማው የቀረበበት የቦርድ አባል ከኃላፊነቱ ይነሳል።

## ፲፬. <u>የስራ አመራር ቦርድ አባላት ሥነ-ምግባር</u>

ዝርዝሩ የስራ አመራር ቦርዱ በሚያወጣው የአባላት ሥነ-ምግባር መመሪያ የሚወሰን ሆኖ ማንኛውም የስራ አመራር ቦርዱ አባል፦

፩/ የተሰጠውን ኃላፊነት በገለልተኝነት፣ በነፃነትና በቅን ልቦና ማከናወን አለበት፣

፪/ ማንኛውንም በምርጫ የሚሳተፍ የፖለቲካ ድርጅትም ሆነ የግል ዕጩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በመደገፍም ሆነ በመቃወም መንቀሳቀስ የለበትም፣

investigation, the House of People's Representatives appoint an investigative committee to investigate the matter, and this committee should consist of:

a) One Federal Supreme Court judge;

b) One technical expert whose area of expertise is directly related to the matter at hand;

c) One person representing the Ethiopian Human Rights Commission.

3/ The Speaker of the House If he meets necessary may temporarily suspend the powers and duties of a management board member whose case is still being investigated.

4/ the board member shall have the right to defend himself and present evidence during the process of committee's investigation.

5/ if the investigative committee in its investigation find the complaint lodged to be accurate and that the management board member should be removed, the committee shall present its findings to the Speaker of the House who shall in turn present it to the House of People's Representatives.

6/ the management board member regarding whom the complaint is lodged shall be removed from his position if the decision is approved by majority vote of the House of People's Representatives.

## 14. <u>Ethics of Management Board Members</u>

While the specifics will be determined by directives to be issued by the management board any member of the management board shall:

1/ discharge his responsibility impartially, freely and in good faith;

2/ not directly or indirectly support or oppose any political organization or private candidate participating in the election;

፫/ በስራ አመራር ቦርድ አባልነቱ ምክንያት ባገኘው ሚስጥራዊ መረጃ ጥቅም ማግኘት ወይም ለማግኘት መሞከር የለበትም፤

፬/ የቦርዱን ሚስጥር ለ ፫ኛ ወገን አሳልፎ መስጠት ወይም ማባከን የለበትም፤

፭/ በማንኛውም ሁኔታ የቦርዱን ወይም የአባላቱን ተዓማኒነት፣ገለልተኝነትና ነፃነት ከሚጎዳ ወይም ከሚያጎድፍ ማንኛውም ተግባር መቆጠብ አለበት፡፡

**፲፭. <u>የስራ አመራር ቦርዱ አባላት መብት</u>**

ማንኛውም የስራ አመራር ቦርድ አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፦

፩/ ማንኛውንም የስራ አመራር ቦርዱን ስብሰባ የመሳተፍና ድምፅ የመስጠት፤

፪/ የቦርዱን ሰነዶች የመመልከት፤

፫/ የስራ አመራር ቦርዱን ስብስባ ጥሪ እና አጀንዳ በወቅቱ የማግኘት፤

፬/ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ የመጠየቅ፤

፭/ በስራ አመራር ቦርድ አባልነቱ ሊያገኝ የሚገባውን ክፍያ የማግኘት፤

፮/ ከባድ ወንጀል ሲፈፅሙ እጅ ከፍንጅ ካልተያዙ በቀር በኃላፊነት ላይ እስካሉ ድረስ ያለ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፈቃድ ያለመያዝና በወንጀል ያለመከሰስ መብት።

**፲፮. <u>የስራ አመራር ቦርዱ አባላት የጥቅም ግጭት</u>**

፩/ ማንኛውም የስራ አመራር ቦርድ አባል የተሰጠውን ኃላፊነት በፍትሃዊነትና በገለልተኛነት ለመወጣት እንዳይችል የሚያደርግ ማንኛውም ዓይነት የጥቅም ግጭት ያለበት ጉዳይ ሲገጥመው ወዲያውኑ ለስራ አመራር ቦርዱ በማሳወቅ እራሱን ማግለል ይኖርበታል።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተጠቀሰው ሁኔታ ሲከሰት ጉዳዩ በቃለጉባኤ ተይዞ ጉዳዩ በቀሪዎቹ የስራ አመራር ቦርድ አባላት ይወሰናል።

፫/ ከጉዳዩ ጋር የጥቅም ግጭት ያለው የስራ አመራር ቦርድ አባል ሁኔታውን ሳይገልፅ በማናቸውም መንገድ ተሳትፎ ውሳኔ የተላለፈ ከሆነ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ይደረጋል፡፡

3/ not seek any benefit out of confidential information that he obtained by virtue of being a management board member;

4/ not disclose to a third party any confidential information of the board;

5/ refrain from any acts that in any way damages the credibility, impartiality and independence of the board or its members.

**15. <u>Rights of Management Board Members</u>**

Any member of the management board shall have the following rights:

1/ to participate and vote in any meetings of management board;

2/ to refer and get access to documents of the board;

3/ to be called by the board for meeting and know the agenda in a timely manner;

4/ to request for an extraordinary meeting to be held;

5/ to receive payment appropriate for his management board membership;

6/ not to be arrested or prosecuted without permission of the House of People's Representatives except in the case of flagrante delicto.

**16. <u>Conflict of Interests of Management Board Members</u>**

1/ A management board member shall immediately inform the management board and remove himself from duty when any situation of conflict of interest occurs which prevent him from carrying out his duties in a fair and impartial manner.

2/ Where the situation provided in Sub-Article (1) above occurs, it shall be recorded in the minutes and decided upon by the rest of the management board members.

3/ A decision or action shall be re-considered where management board member that has a conflict of interest with the matter participates in the decision or action in any capacity without notifying the management board about the situation.

፬/ ማንኛውም ሰው የስራ አመራር ቦርድ አባላት ከሚያዩት ጉዳይ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት አለ ብሎ ካመነ ማስረጃውን ወዲያውኑ በቦርዱ ጽህፈት ቤት በኩል ለስራ አመራር ቦርድ ማቅረብ ይችላል፡፡

4/ Any person claiming that a management board member has conflict of interest regarding a matter that he is involved in or with a matter being considered in a meeting he participated may immediately submit his evidence to the management board through the office.

**፲፯. ስለ ይግባኝ**

፩/ የስራ አመራር ቦርዱ የሚሰጣቸው የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የምርጫ ሂደትና ውጤትን በተመለከተ የሚሰጣቸው የመጨረሻ ውሳኔዎች በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሊታዩ ይችላሉ፡፡

፪/ ፍርድ ቤቱ ይግባኙን በተቀበለ በአንድ ወር ጊዜ ውሰጥ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፤ ሆኖም ጉዳዩ አጣዳፊ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የጉዳዩ ባህሪ በሚጠይቀው ፍጥነት ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

**17. Appeal**

1/ Final administrative decisions of the management board may be appealed to the Federal High Court, and final decisions with regard to electoral process and results may be appealed to the Federal Supreme Court.

2/ Courts shall decide cases within one month since an appeal is lodged, however if the matter is of urgent nature, the court may be required to issue a decision that takes into account its urgency.

**፲፰. የስራ አመራር ቦርድ አባላት ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም**

የቦርዱ ሰብሳቢ እና የተቀሩት የቦርዱ አባላት ደመወዝና ጥቅማጥቅም እንዲሁም ከኃላፊነታቸው ከተነሱ በኋላ ስለሚያገኙት መብትና ጥቅሞች በተመለከተ ራሱን አስችሎ የሚወሰን ይሆናል

**18. Salary and Benefits of Management Board Members**

The salary and benefits of the Chairman of the management board and the rest of the members, and also the rights and benefits they receive when outgoing shall be decided next independently.

## ምዕራፍ ሶስት
## የቦርዱ ዋና ጽህፈት ቤት

**፲፱. የቦርዱ ጽህፈት ቤት**

ቦርዱ በአንድ ዋና ኃላፊና በአንድ ምክትል ዋና ኃላፊ የሚመራ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል፡፡

## PART THREE
## THE OFFICE OF THE BOARD

**19. The Office of the Board**

The Board shall have office headed by one chief executive and one deputy chief executive.

**፳. የጽህፈት ቤቱ ኃላፊና ምክትል ኃላፊ አሰያየምና ተጠሪነት**

፩/ የጽህፈት ቤቱ ኃላፊና ምክትል ኃላፊ ግልፅና አሳታፊ በሆነ የምልመላ ሂደት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ለስራ አመራር ቦርድ አባላት ሹመት የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸው መስፈርቶች ማሟላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ተመርጠው በስራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢ አቅራቢነት በቦርዱ ይሰየማሉ፡፡

፪/ የጽህፈት ቤቱ ዋና ኃላፊ ተጠሪነቱ ለስራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢ ሲሆን የምክትል ኃላፊው ተጠሪነት ለጽህፈት ቤቱ ዋና ኃላፊ ይሆናል፡፡

**20. Appointment and Accountability of Chief Executive and Deputy Chief Executive of the the Office of the Board**

1/ Chief Executive and Deputy Chief Executive of the office shall be appointed by the management board through the nomination of the chairman after assessed the fulfillment of necessary requirements indicated in Article 5 of this Proclamation.

2/ The Chief Executive of the office shall be accountable to the management board and the Deputy Chief Executive of the office shall be accountable to the chief executive of the management board.

## ፳፩. <u>የጽህፈት ቤቱ ዋና ኃላፊ ስልጣንና ተግባር</u>

የጽህፈት ቤቱ ዋና ኃላፊ በስራ አመራር ቦርዱ እና በስራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያና አቅጣጫ መሰረት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

፩/ የቦርዱን የድጋፍ ሰጪ የስራ ዘርፍ በበላይ ኃላፊነት ይመራል፤

፪/ የቦርዱን ስልጣንና ተግባር አፈፃፀም ያሳልጣል፣ ያስተባብራል እንዲሁም ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል፤

፫/ ከቦርዱ ሰብሳቢ ጋር በመመካከር የቦርዱን የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፤

፬/ የቦርዱን ቃለጉባኤና ሌሎች ሰነዶች በአግባቡ ይይዛል፤

፭/ የቦርዱ ውሳኔዎች ለሚመለከታቸው ወገኖች እንዲተላለፉ ያደርጋል፤

፮/ በቦርዱ ጉባኤ ስብሰባ ላይ ያለድምፅ በመሳተፍ ቃለ ጉባኤ ይይዛል፤

፯/ ስለጽህፈት ቤቱ የስራ እንቅስቃሴ በየጊዜው ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ሰብሳቢ ያቀርባል፤

፰/ በቦርዱ ሰብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፳፪. <u>የጽህፈት ቤቱ ምክትል ኃላፊ ስልጣንና ተግባር</u>

የጽህፈት ቤቱ ምክትል ኃላፊ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በዋና ኃላፊው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

፪/ የጽህፈት ቤቱ ዋና ኃላፊ በሌለበት ጊዜ ኃላፊውን ተክቶ ይሰራል፡፡

## ፳፫. <u>የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት</u>

፩/ በሁሉም ክልሎች ምርጫ የሚያስተባብር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይቋቋማል፡፡

፪/ የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ገለልተኛነታቸውና ሙያዊ ብቃታቸው ከተረጋገጠ የክልሉ ነዋሪዎች መካከል በቦርዱ ሰብሳቢ አቅራቢነት በቦርዱ ይሰየማሉ፡፡

## 21. <u>Powers and Duties of the Chief Executive of the Office</u>

The Chief Executive of the office shall perform the following powers and duties according to the order and direction given to him by the management board and the chairman of the management board:

1/ direct the supporting activities of the board as its head;

2/ facilitate, coordinate and create suitable conditions for the performance of the board's power and responsibility;

3/ prepare agenda for the meetings of the board in consultation with the management board chairman;

4/ properly keep the minutes and other documents of the board;

5/ cause the decisions of the board to be transmitted to the parties concerne;

6/ keep minutes of management board meetings by participating in meetings without voting rights;

7/ prepare and present periodic reports to the chairman of the management board about the activities of the office;

8/ perform other duties assigned to him by the chairman of the board.

## 22. <u>Powers and Duties of the Deputy Chief Executive of the Office</u>

The Deputy Chief Executive of the office shall have the following powers and duties:

1/ perform activities assigned to him by the chief executive of the office;

2/ act on behalf of the chief executive in his absence.

## 23. <u>Regional Branch Offices of the Board</u>

1/ A regional branch office of the board shall be established in all regions.

2/ The regional office heads shall be appointed by the management board, after recruited and nominated by the chairman of the board, among residents of the regional state who are competent and non-partisan through directive to be issued by the management board.

፫/ ቦርዱ የክልሎችን የቆዳ ስፋት፣ የህዝቡን አሰፋፈርና የመራጮችን ብዛት መሰረት በማድረግ ለክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ተጠሪ የሆኑ እንደ አግባብነቱ የዞን እና የምርጫ ክልል ማስተባበሪያ በቋሚነት ሊያቋቁም ይችላል።

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) የተገለጹት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቶች ገለልተኝነታቸውና ሙያዊ ብቃታቸው የተረጋገጠ ሊሆን ይገባል፡፡ ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነታቸው ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፳፬. የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

እያንዳንዱ የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት በስራ አመራር ቦርዱ እና በስራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢ እንዲሁም እንደ አግባብነቱ በቦርዱ ጽህፈት ቤት ኃላፊ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያና አቅጣጫ መሰረት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡

፩/ በክልል ደረጃ የሚካሄደውን ምርጫ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ይቆጣጠራል፣

፪/ በስሩ የሚቋቋሙት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቶች ስለሚደራጁበት ሁኔታ ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሀሳብ ያቀርባል፣

፫/ ለምርጫ የሚያስፈልጉ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ለሚመለከታቸው ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቶችና የምርጫ ክልልና ጣቢያዎች በወቅቱ መድረሳቸውን ይከታተላል፣ያረጋግጣል፣

፬/ ከቦርዱና የስራ ሂደቱ ኃላፊነት ያለው የስራ አመራር ቦርድ አባል በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስነ-ዜጋና የመራጮች ትምህርት ይሰጣል፣ያስተባብራል፣

፭/ የመራጮች አመዘጋገብ፣ የእጩዎች አቀራረብና የድምፅ አሰጣጥ ስርዓት ህጉ በሚፈቅደው መሰረት እየተካሄደ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ የሚነሱትን ቅሬታዎችና ተቃውሞዎች በክልል ደረጃ እየመረመረ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወስናል፣

፯/ የክልሉን የምርጫ ሂደትና ውጤት በሚመለከት ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባል፣

3/ The management board, taking into account the size of the regional states, settlement of peoples and the number of voters may establish permanent or temporary coordinating offices that are accountable to regional state branch offices.

4/ The impartiality and professional efficiency of the coordinating offices referred in Sub-Article (3) of this Article shall be certified. details of their responsibilities and duties shall be determined in accordance with directive to be issued by the board.

## 24. Powers and Duties of Regional Branch Offices of the Board

Each regional branch office of the board, in accordance with regulation and guidance from the management Board and the chairman of the management Board, and as may be necessary by the chief executive of the office, shall have the following powers and duties:

1/ direct, coordinate and control election at the state level;

2/ submit recommendation to the office of the Board about ways of organizing electoral coordinating offices to be established under it;

3/ follow up and ensure that documents and materials required for the election reach to the concerned electoral coordinating offices, constituency and polling stations on time;

4/ based on the direction of the management board and the management board member responsible for this work stream, offer and coordinate voter and civic education with other concerned bodies;

5/ follow up and control the voter registration, nomination of candidates and voting procedures to make sure that they are conducted in accordance with the law;

6/ investigate and decide on grievances and complaints lodged at regional state levels submitted on matters provided in Sub-Article (5) of this Article in accordance with a directive to be issued by the board;

7/ submit to the office of the board report on the election process and results of the regional state;

፰/ ለምርጫ አፈጻጸም በሚያመች መልኩ አግባብ ያላቸውን መረጃዎች እየሰበሰበና እያጠና በየጊዜው ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባል፤

፱/ ስለስራ እንቅስቃሴው በየወቅቱ ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባል፤

፲/ የስራ አመራር ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በክልል እና በምርጫ ጣቢያ ደረጃ የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረክ እንዲዋቀር ያደርጋል፣ በክልል የሚቋቋሙ የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረክ ያስተባብራል፤

፲፩/ የክልሉን ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ያቋቁማል፤

፲፪/ የስራ አመራር ቦርዱ ሰብሳቢና የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ምዕራፍ አራት
## ስለ ቦርዱ በጀት

### ፳፭. በጀት

፩/ ቦርዱ ራሱ የሚያዘጋጀዉ ዓመታዊ በጀት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ይፀድቃል፡፡

፪/ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ለቦርዱ የተመደበለትን በጀት በፀደቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሙሉ በጀቱን ወደ ቦርዱ የባንክ ሂሳብ ያስገባል፡፡

፫/ ቦርዱ የሶሰት ዓመት በጀት ግምት እንዲወስንለት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላል።

፬/ ቦርዱ አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት ስጦታና የገንዘብ እርዳታን ከሶስተኛ ወገኖች ሊቀበል ይችላል።

### ፳፮. የሂሳብ መዛግብት

፩/ ቦርዱ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የቦርዱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክለው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

8/ collect and analyze data that help the execution of elections and periodically report them to the office of the board;

9/ submit periodic reports about its work activities to the office of the board;

10/ cause the establishment of political parties' joint forum at regional state, and polling station levels in accordance with a directive to be issued by the management board, coordinate political parties joint forum established at the regional state level;

11/ establish the Grievance Hearing Committee of the regional state office in accordance with the directive to be issued by the Board;

12/ perform other duties assigned to it by the chairman of the management board and the chief executive of the office of the board.

## PART FOUR
## BUDGET OF THE BOARD

### 25. Budget

1/ The Annual Budget of the board prepared by it shall be approved by the House of People’s Representatives.

2/ The Ministry of Finance shall credit the whole Board’s Budget to the Boards’ bank account within one month, that approved inaccordance to Sub-Article (1) of this Article

3/ the Board may request the House of People’s Representatives for the allocation of a three years budget plan.

4/ The Board may accept gifts and monetary aids from third parties in accordance with relevant laws.

### 26. Books of Accounts

1/ The Board shall keep complete and accurate books of account.

2/ The books of accounts and financial documents of the Board shall be Audited annually by the Federal Auditor General or by an Auditor designated by him.

## ምዕራፍ አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፯. የመተባበርና የማስፈፀም ግዴታ**

፩/ ማንኛውም የፌደራልም ሆነ የክልል የመንግስት አካል ከቦርዱ ለሚቀርብለት ህጋዊ ጥያቄ ትብብር የማድረግና የማስፈፀም ግዴታ አለበት።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገውን ግዴታ በመጣስ የምርጫ ሂደት እንዲስተጓጎል ያደረገ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባላቸው ህጎችና መርሆች መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፣ እንዲሁም የምርጫ ሕጉ በሚደነግገው መሰረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፳፰. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በአዋጅ ቁጥር ፭፻፴፪/፩ሺ፱፻፺፱ መሰረት ተሹመው በስራ ላይ ካሉ የቦርድ አባላት መካከል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠያቂነት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በስራ አመራር ቦርድ አባልነት እንዲቆዩ ሊወስን ይችላል፡፡

**፳፱. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ**

በአዋጅ ቁጥር ፭፻፴፪/፩ሺ፱፻፺፱ መሰረት ተቋቁሞ ለነበረው ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተሰጥተው የነበሩ መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሰረት ለተቋቋመው ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተላልፈዋል፡፡

**፴. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

፩/ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስችል ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፪/ የስራ አመራር ቦርዱ ይህንን አዋጅ ተከትሎ የሚወጣ ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፴፩. የተሻሩ ህጎች**

፩/ የተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፪/፩ሺ፱፻፺፱ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡

## PART FIVE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**27. Duty to Cooperate and Execute**

1/ Any federal or regional government body presented with a lawful request from the board has an obligation to cooperate with the board and act upon the request of the board.

2/ Any person who by violating the provision of Sub-Article (1) of this Article impedes the election process will face administrative measures on the basis of relevant laws and principles. Additionally, such person shall be criminally liable on the basis of the Electoral Law.

**28. Transitory Provision**

The House of People's Representatives may decide from among the board members appointed before the enactment of this Proclamation based on Proclamation No.532/2007 to stay in a position until their term of office is lapsed up on the request of the Prime Minister.

**29. Transfer of Rights and Duties**

The Rights and Duties given to the National Electoral Board which was established through Proclamation No.532/2007 are hereby transferred to the National Electoral Board established through this Proclamation.

**30. Power to Issue Regulations and Directives**

1/ The House of People's Representatives may issue Regulation for the proper implementation of this Proclamation.

2/ The management board may issue Directives necessary for the implementation of the Regulation to be issued under this Proclamation

**31. Repealed Laws**

1/ Provisions of the amended electoral law Proclamation No. 532/1999 shall not be applicable to matters covered by this proclamation.

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ህጎችና ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ አዋጅ ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

2/ Law and Customary practices inconsistent with this proclamation shall not be applicable on this proclamation.

**፴፪. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት መጋቢት ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**32. <u>Effective date</u>**

This Proclamation shall come into force on this 5th day of April, 2019 upon approval by the House of People's Representatives.

**አዲስ አበባ ግንቦት ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**Done at Addis Ababa, on this 6th day of June, 2019.**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**SAHLEWORKZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATICREPUBLIC OF ETHIOPIA,**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# የእጩ ተወዳዳሪዎች ምዝገባ፣ የድጋፍ ፊርማ አሰባሰብ እና መለያ ምልክት አመራረጥ መመሪያ ቁጥር 7/2013

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1. አውጪው ባለስልጣን

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (1) እና የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ (7) እና አንቀፅ 163 ንኡስ አንቀፅ (2) ላይ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል::

### አንቀፅ 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «**የእጩዎች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 7/2013 ዓ.ም**» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀፅ 3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. **"አዋጅ"** ማለት የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ነው::
2. **"ቦርድ"** ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፡፡
3. **"እጩ ተወዳዳሪ"** ማለት በምርጫ ለመወዳደር በፖለቲካ ድርጅት ወይም በግሉ የተመዘገበ ሰው ነው፡፡
4. **"የእጩ መታወቂያ ካርድ"** ማለት አንድ ሰው በአዋጁ መሰረት መስፈርቶችን አሟልቶ በእጩነት ከተመዘገበ በኋላ በምርጫ ክልሉ ለመወዳደር የሚሰጠው የእጩነት መታወቂያ ካርድ ነው፡፡
5. **"የአካል ጉዳተኛ"** ማለት በዘላቂ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ምክንያት ለጉዳት ተጋላጭ የሆነና የእኩል እድል ተጠቃሚ ያልሆነ ሰው ነው፡፡
6. በአዋጁ ላይ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም አግባብነት ያላቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀፅ 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በጠቅላላ ምርጫ፣ በሚሚያ እና በአከባቢ ምርጫ የእጩዎች ምዝገባ፣ ድጋፍ ፊርማ አሰባሰብ እና መለያ ምልክት አመራረጥ እና አጠቃቀም ሂደት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 5. የጾታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ውስጥ በአንድ ጾታ የተደነገገው አገላለጽ ሌላውንም ጾታ ያካትታል፡፡

## አንቀፅ 6. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ ለምርጫ ውድድር በእጩነት ለመወዳደር የሚያበቁ መስፈርቶችን፣ የጥያቄ አቀራረብ ሂደትና አሠራርን እንዲሁም የምልክት አመራረጥ እና አጠቃቀምን በዝርዝር መደንገግ ነው::

# ምዕራፍ ሁለት

# የዕጩነት ምዝገባ ጥያቄ አቀራረብ እና የምዝገባ ስነ-ስርዓት

## አንቀፅ 7. የእጩነት መመዘኛዎች

1. ማንኛውም ሰው፤

   ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው እና ለመመረጥ የተመዘገበ፣

   ለ) ለእጩነት በሚመዘገብበት እለት እድሜው 21 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ፣

   ሐ) በእጩነት ለመመዝገብ የፈለገበት የምርጫ ክልል ውስጥ ከምርጫ ቀን ወደኋላ ሲቆጠር ቢያንስ ለአንድ አመት በመደበኛነት የኖረ ወይም በሚመዘገብበት የምርጫ ክልል ውስጥ የተወለደ፣

   መ) በህግ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብቱ ያልተገፈፈ፣

   ሠ) በአእምሮ ህመም ምክንያት ለመወሰን ብቃት የሌለው መሆኑን ስልጣን ባለው አካል ወይም በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠበት እና

   ረ) በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን ያሟላ ከሆነ በፖለቲካ ፓርቲ እጩነት ወይም በግል እጩነት መመዝገብ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) (ሐ) ስር የተደነገገው ቢኖርም፡

ሀ) በትምህርት ወይም በመፈናቀል ምክንያት ከመደበኛ መኖሪያው ርቆ የነበረ ሰው ለትምህርት ወይንም በመፈናቀሉ ምክንያት ሌላ ቦታ ከመሄዱ ወይንም የተፈናቀሉ ሰዎች የሚኖሩበት ማዕከል ከመግባቱ በፊት ይኖርበት የነበረው መደበኛ መኖሪያው በሚገኝበት የምርጫ ክልል በእጩነት መቅረብ ይችላል፡፡

ለ) በስራ ምክንያት ከመደበኛ መኖሪያው ሌላ ቦታ የሚኖር እና የቀድሞ መደበኛ መኖሪያውን ያልለቀቀ ሰው ለስራ ሌላ ቦታ ከመሄዱ በፊት ይኖርበት በነበረው መደበኛ መኖሪያው በሚገኝበት የምርጫ ክልል በእጩነት መቅረብ ይችላል፡፡

3. ማንኛውም ሰው መወዳደር የሚፈልግበት ከተማ ወይም ወረዳ ከአንድ በላይ የምርጫ ክልሎችን የሚያቅፍ ከሆነ እና በወረዳው ወይም በከተማው በመደበኛነት ለተከታታይ ሁለት አመታት የሰራ ከሆነ በዚያው ወረዳ ወይም ከተማ ውስጥ ካሉ የምርጫ ክልሎች መካከል በመረጠው በአንዱ የምርጫ ክልል በእጩነት ለመቅረብ ይችላል፡፡ የድጋፍ ፊርማ ማስባሰብ የሚችለው ሊወዳደርበት ከመረጠው የምርጫ ክልል ብቻ ነው፡፡
4. አንድ ሰው በእጩነት ለመቅረብ የሚችለው በግል የቀረበ ከሆነ እራሱ፣ በፖለቲካ ድርጅት የቀረበ ከሆነ ደግሞ እራሱ እና በእጩነት ያቀረበው የፖለቲካ ፓርቲ ቦርዱ ያወጣውን የሥነ ምግባር ደንብ መቀበሉን በፊርማው ካረጋገጠ ነው፡፡
5. አንድ እጩ በአንድ ጊዜ መወዳደር የሚችለው በአንድ የምርጫ ክልል እና ለአንድ ምርጫ አይነት ብቻ ይሆናል፡፡

**አንቀፅ 8. የማንነት እና ሌሎች የነዋሪነት ማረጋገጫ**

1. ማንኛውም የግል ወይም የፖለቲካ ድርጅት ተወዳዳሪ በዕጩነት ለመመዝገብ በሚቀርብበት ወቅት ማንነቱን ለማረጋገጥ የሚያገለግል የአገልግሎት ጊዜው ያላበቃ እና ፎቶግራፍ ያለው የነዋሪነት መታወቂያ፣ ፓስፖርት፣ የመንጃ ፍቃድ፣ የወታደራዊ አገልግሎት መታወቂያ ወይም የመንግስት ወይም በህግ የታወቀ የግል መስሪያ ቤት መታወቂያ፣ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋም ወይም ትምህርት ቤት የተሰጠው መታወቂያ ወይም ተመሳሳይ መታወቂያ ማቅረብ አለበት፡፡
2. ማንኛውም በእጩነት ለመመዝገብ የሚቀርብ የግል ወይም የፖለቲካ ድርጅት ተወዳዳሪ ለመመዝገብ በሚቀርብበት ወቅት፡

ሀ) የሚመዘገበው በትውልድ ቦታው ከሆነ በስፍራው መወለዱን የሚያሳይ የልደት ምስክር ወረቀት፣ እንደሁኔታው በሀይማኖት ተቋም የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ወይም የተወለደበት የህክምና ማዕከል የፃፈው እና ማህተም ያደረገበት የልደት ምስክር ወረቀት

በማቅረብ፤ የተጠቀሱትን ሰነዶች ማቅረብ ካልቻለ ደግሞ በተመዝጋቢው የትውልድ ዘመን በቦታው ነዋሪ የነበሩ መሆናቸው የተረጋገጠ ሦስት ምስክሮች፤

ለ) የሚመዘገበው በመደበኛ መኖሪያው ከሆነ የነዋሪነት መታወቂያ፣

ሐ) የሚመዘገበው ቀድሞ በእንደራሴነት በተመረጠበት ወይንም ለእጩነት በቀረበበት ቦታ ከሆነ የተመራጭነት ወይም የእጩነት ማስረጃ ወይም

መ) የሚመዘገበው በስራ ወይም በትምህርት ለሁለት አመት እና ከዚያ በላይ በሰራበት ወይም በተማረበት ቦታ ላይ ከሆነ ከህጋዊ ቀጣሪው ወይም ከትምህርት ቤቱ የተሰጠው የስራ ቅጥር ወይም የተማሪነት እና የቆይታ ጊዜ ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 መሰረት የቀረቡ ማስረጃዎች የእጩውን ዕድሜ የማይገልጹ በሚሆንበት ጊዜ እንዲሁም እጩው ነዋሪነቱን የሰነድ ማስረጃዎች በማቅረብ ማስረዳት ካልቻለ የምርጫ ክልሉ በሚያካልለው ቦታ ቢያንስ ለአምስት ዓመት መኖራቸው በሰነድ ማስረጃ በተረጋገጠ ሦስት ምስክሮች እድሜው ወይም ነዋሪነቱ ተረጋግጦ በቃለ ጉባዔ ላይ ከሰፈረ በኋላ እጩ ሆኖ ሊመዘገብ ይችላል፡፡

4. በእጩነት ለመመዝገብ በሚል ሆነ ብሎ ሀሰተኛ ሰነድ የተጠቀመ፣ ሀሰተኛ ምስክር ያቀረበ ወይም ሀሰተኛ መረጃ የሰጠ መሆኑ በማናቸውም ሰው በሚቀርብ ጥቆማ ወይም ቦርዱ በራሱ በሚያደርገው ማጣራት የተረጋገጠበት ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት የሚወሰደው እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የእጩነት ምዝገባ ማመልከቻው ውድቅ ሆኖ ወይም ምዝገባው ተሰርዞ ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በግል እጩነትም ሆነ በፖለቲካ ፓርቲ አመራር ወይም አባልነት እንዳይሳተፍ ቦርዱ ውሳኔ መስጠት አለበት።

## አንቀፅ 9. በግል እጩ ተወዳዳሪነት ስለመቅረብ

1. ማንኛውም በግል እጩ ተወዳዳሪነት መመዝገብ የሚፈልግ ሰው በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ላይ ከተዘረዘሩት መመዘኛዎች በተጨማሪ የሚወዳደረው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከሆነ፡

ሀ) በተወዳዳሪነት ሊቀርብበት በሚፈልግበት የምርጫ ክልል ውስጥ የመምረጥ መብት ያላቸው ቢያንስ 5000 ሰዎች ለእጩነት እንዲቀርብ የሰጡትን የድጋፍ ፊርማ፤

ለ) የግል እጩ ተወዳዳሪው የአካል ጉዳተኛ የሆነ እንደሆነ በተወዳዳሪነት ሊቀርብበት በሚፈልግበት የምርጫ ክልል ውስጥ የመምረጥ መብት ያላቸው ቢያንስ 3000 ሰዎች

ለእጩነት እንዲቀርብ የሰጡትን የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ አለበት፡፡

2. የቀረበው እጩ የሚወዳደረው ለክልል ምክር ቤት ከሆነ፡

ሀ) በተወዳዳሪነት ሊቀርብበት በሚፈልግበት የምርጫ ክልል ውስጥ የመምረጥ መብት ያላቸው ቢያንስ 2500 ሰዎች ለእጩነት እንዲቀርብ የሰጡትን የድጋፍ ፊርማ፣

ለ) የአካል ጉዳተኛ ከሆነ በተወዳዳሪነት ሊቀርብበት በሚፈልግበት የምርጫ ክልል ውስጥ የመምረጥ መብት ያላቸው ቢያንስ 1500 ሰዎች ለእጩነት እንዲቀርብ የሰጡትን የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ አለበት፡፡

3. የቀረበው እጩ የሚወዳደረው ለልዩ ዞን፣ ለወረዳ፣ ለከተማ አስተዳደር ወይም ለቀበሌ ምክር ቤት ምርጫ ከሆነ፤

ሀ) ለልዩ ዞን ወይም ብሄረሰብ ዞን፣ ለወረዳ ምክር ቤት ወይም ለከተማ አስተዳደር ምክር ቤት የመምረጥ መብት ያላቸው ቢያንስ 500 ሰዎች ለዕጩነት እንዲቀርብ የሰጡትን የድጋፍ ፊርማ፣

ለ) ለልዩ ዞን ወይም ብሄረሰብ ዞን፣ ለወረዳ ምክር ቤት ወይም ለከተማ አስተዳደር ምክር ቤት የሚወዳደር የአካል ጉዳተኛ ከሆነ የመምረጥ መብት ያላቸው ቢያንስ 300 ሰዎች ለዕጩነት እንዲቀርብ የሰጡትን የድጋፍ ፊርማ፣

ሐ) ለቀበሌ ምክር ቤት ከሆነ የመምረጥ መብት ያላቸው ቢያንስ 100 ሰዎች ለዕጩነት እንዲቀርብ የሰጡትን የድጋፍ ፊርማ፣

መ) ለቀበሌ ምክር ቤት የሚወዳደረው ዕጩ የአካል ጉዳተኛ ከሆነ የመምረጥ መብት ያላቸው ቢያንስ 50 ሰዎች ለዕጩነት እንዲቀርብ የሰጡትን የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ አለበት፡፡

4. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገው ቢኖርም ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለልዩ ዞን፣ ለወረዳ፣ ቀበሌ ወይም ለከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ለሚደረጉ ምርጫዎች በአንዳንድ የምርጫ ክልሎች ላይ በግል የሚወዳደሩ እጩዎች ሊያቀርቡት የሚገባውን የድጋፍ ፊርማ ቁጥር ዝቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

5. ቦርዱ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ፣ በዚህ አንቀጽ ስር የተጠቀሱ የግል እጩ ሊያቀርብ የሚገባቸው የድጋፍ ፊርማ መስፈርቶች

በክፊል በ6ኛው ብሔራዊ ምርጫ ተፈጻሚ አይሆኑም::

## አንቀፅ 10. የፖለቲካ ድርጅት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ግንባር ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች ቅንጅት እጩ ስለማቅረብ

1. አንድ የፖለቲካ ድርጅት፣ ግንባር ወይም ቅንጅት በአንድ የምርጫ ክልል ለአንድ የምክር ቤት መቀመጫ ማቅረብ የሚችለው አንድ እጩ ብቻ ነው፡፡
2. የሚቀርበው እጩ፡-

   ሀ) በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን የሚያሟላ እና

   ለ) የፖለቲካ ድርጅቱ አባል መሆን አለበት፡፡
3. ዕጩው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚወዳደር ከሆነ በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ከሚኖሩ መራጮች ቢያንስ የ2000 ሰዎች የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ አለበት፡፡ ነገር ግን የሚቀርበው እጩ የአካል ጉዳተኛ ከሆነ ቢያንስ 1500 መሆን አለበት፡፡
4. እጩው ለክልል ምክር ቤት የሚወዳዳር ከሆነ በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ከሚኖሩ መራጮች ቢያንስ የ1000 ሰዎች የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ አለበት፡፡ ነገር ግን እጩው የአካል ጉዳተኛ ከሆነ የድጋፍ ፊርማው ቢያንስ 750 መሆን አለበት፡፡
5. ምርጫው የሚካሄደው ለዞን ወይም ልዩ ወረዳ፣ ለወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ሲሆን በፖለቲካ ድርጅት የሚቀርብ እጩ በምርጫ ክልሉ ከሚኖሩ መራጮች ቢያንስ የ300 ሰዎች የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ አለበት፡፡ ነገር ግን እጩው የአካል ጉዳተኛ ከሆነ የሚያቀርበው የድጋፍ ፊርማ ብዛት ከ200 ያላነሰ መሆን አለበት፡፡
6. ለቀበሌ ምክር ቤት የሚወዳደር በፖለቲካ ድርጅት የሚቀርብ ዕጩ በቀበሌው ውስጥ የመምረጥ መብት ያላቸው የ100 ሰዎች የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ አለበት፡፡ ነገር ግን እጩው የአካል ጉዳተኛ ከሆነ የሚያቀርበው የድጋፍ ፊርማ ብዛት ከ50 ያላነሰ መሆን አለበት፡፡
7. ቦርዱ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ፣ በዚህ አንቀጽ ስር የተጠቀሱ የፖለቲካ ፓርቲ እጩ ሊያቀርብ የሚገባቸው የድጋፍ ፊርማ መስፈርቶች በ6ኛው ብሔራዊ ምርጫ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

## አንቀፅ 11. የድጋፍ ፊርማ መስጠት ስለሚችል ሰው

ለእጩ ተወዳዳሪ የድጋፍ ፊርማ የሚሰጠው ሰው፡

1. ኢትዮጵያዊ ዜጋ ፣
2. በምርጫ ክልሉ ለስድስት ወራት በነዋሪነት የቆየ፣

3. እድሜው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ፣
4. የመምረጥ መብቱ በህግ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ያልተከለከለ እና
5. በአዕምሮ ህመም ምክንያት የመምረጥ መብቱ ያልተገደበበት መሆን አለበት፡፡

**አንቀፅ 12. መስጠት የሚቻለው የድጋፍ ፊርማ ቁጥር**

1. አንድ ሰው በአንድ ምርጫ ክልል ውስጥ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውድድር ከቀረቡት እጩዎች መካከል ከሁለት እጩዎች በላይ የድጋፍ ፊርማ መስጠት አይችልም፡፡
2. አንድ ሰው ለክልል ምክር ቤት እና በአካባቢ ምርጫ ለሚመሰረቱ ምክር ቤቶች ከሚቀርቡ መቀመጫዎች ውስጥ የድጋፍ ፊርማ መስጠት የሚችለው ለወድድር ከቀረቡት መቀመጫዎች ቁጥር እጥፍ ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 13. የድጋፍ ፊርማ የሚቀርብበት እና የሚረጋገጥበት አሠራር**

1. ማንኛውም በግል ወይም በፖለቲካ ድርጅት እጩነት የሚቀርብ ሰው ራሱ ወይም ድርጅቱ የእጩ ድጋፍ ማሰባሰቢያ ቅፅ ከምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት አንድ ቅጂ በመውሰድ እና ቅፁን በማባዛት የድጋፍ ፊርማ በራሱ ወይም በሌላ በወከለው ሰው አማካኝነት ማሰባሰብ ይችላል፡፡
2. የምርጫ ክልሉም እጩ ተወዳዳሪው ያቀረበውን የድጋፍ ፊርማ ተቀብሎ ይመረምራል፡፡ አስፈላጊውን መመዘኛ አሟልቶ ሲገኝም በእጩ ተወዳዳሪነት ቅፅ ላይ ይመዘግበዋል፡፡
3. የቀረበው የድጋፍ ፊርማ ጉድለት ያለው ከሆነ የግል እጩው ወይም እጩውን ያቀረበው የፖለቲካ ድርጅት በጊዜ ሰሌዳው መሠረት አስተካክሎ እንዲያቀርብ በወቅቱ ሊገለጽለት ይገባል፡፡
4. እጩው ያቀረበው የድጋፍ ፊርማ ትክክለኛነት በቃለ መሃላ የተደገፈ መሆን አለበት፡፡ ነገር ግን የምርጫ ክልሉ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ የቀረበው የድጋፍ ፊርማ ትክክለኛ ስለመሆኑ ጥርጣሬ ሲያድርበት ወይም ጥቆማ ሲደርሰው የድጋፍ ፊርማ የሰጡ ሰዎች በሚኖሩበት አካባቢ የነዋሪነት ማረጋገጫ የመስጠት ስልጣን ካለው አካል ጋር በመተባበር ሊያጣራ ይችላል፡፡

**አንቀፅ 14. የድጋፍ ፊርማ አሰባሰብ**

1. ማንኛውም የድጋፍ ፊርማ የሚሰበስብ እጩ ወይንም ወኪሉ ፊርማውን በሚያሰባስብበት ጊዜ የፆታን እና የተለያዩ በአካባቢው ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተዋፅኦ ለማካተት ጥረት ማድረግ አለበት፡፡

2. እጩ ወይም ወኪሉ የድጋፍ ፊርማ በሚያሰባስብበት ወቅት ፆታን፣ የኑሮ ደረጃን፣ የአካል ጉዳተኝነት ወይም ሌላ ማህበራዊ መለያን መሰረት በማድረግ ልዩነት መፍጠር የለበትም፡፡
3. የድጋፍ ፊርማ የሚቀርብበት ቅፅ የፈራሚውን፡

ሀ) ሙሉ ስም ከነአያት፣

ለ) ፆታ፣

ሐ) እድሜ፣

መ) መኖሪያ አድራሻ (ክልል፣ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ የመኖሪያ አካባቢው ልዩ መጠሪያ እና የቤት ቁጥር) ፣

ሠ) ያቀረበው የነዋሪነት ማረጋገጫ አይነት እና ቁጥር (ካለው) ወይም የመራጭነት ካርድ ቁጥር እና

ረ) የድጋፍ ፊርማ ሰጪው የድጋፍ ፊርማ እንዲሁም የመረጃ ሰብሳቢውን ስም እና ፊርማ የያዘ መሆን አለበት፡፡

4. ድጋፍ ሰጪው የሚፈርመው በፅሁፍ ወይም በጣት አሻራ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ድጋፉን መስጠት የሚፈልግ ማንኛውም ሁለት እጅ የሌለው እና በምልክትም ሆነ በጣት አሻራ ድጋፉን መግለጽ የማይችል ሰው ሲሆን ይህንኑ የሚገልጽ ማረጋገጫ ለእጩ ተወዳዳሪው ይሰጣል፡፡
5. ማንኛውም የድጋፍ ፊርማ የሚያሰባስብ ሰው የድጋፍ ፊርማውን ለማግኘት ሰዎችን ማስፈራራት፣ ማስገደድ እና በማንኛውም መንገድ መደለል የለበትም፡፡
6. የምርጫ ክልሉ የድጋፍ ፊርማው የተገኘው በማስፈራራት፣ በማታለል እና በመደለል መሆኑን ሲያረጋግጥ ይህንኑ ለቦርዱ ሪፖርት ያደርጋል፡፡ ቦርዱ እጩው ያቀረበው የድጋፍ ፊርማ እንዳይቆጠር እና እጩውም እንዳይመዘገብ ወይም ምዝገባው እንዲሰረዝ ያደርጋል፡፡
7. እጩው ድጋፉን ያልሰጠ ሰው የሰጠ በማስመሰል፣ በሃሰት ስምና ፊርማ በማዘጋጀት፣ የሌለ ሰው እንዳለ በማስመሰል ወይም በሌላ የተጭበረበረ መንገድ የድጋፍ ፊርማ ማቅረቡ በማናቸውም ሰው በሚቀርብ ጥቆማ ወይም ቦርዱ በራሱ በሚያደርገው ማጣራት

9

ከተረጋገጠበት አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት የሚወሰደው እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የእጩነት ምዝገባ ማመልከቻው ውድቅ ሆኖ ወይም ምዝገባው ተሰርዞ ለሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት በግል እጩነትም ሆነ በፖለቲካ ፓርቲ አመራር ወይም አባልነት እንዳይሳተፍ መደረግ አለበት፡፡

**አንቀፅ 15. በእጩነት መቅረብ ስለማይችሉ ሰዎች**

1. በፌዴራለም ሆነ በክልል መንግስት ተቀጥረው የሚሰሩ ዳኞች፣ ዓቃቤ ህጎች፣ ወታደሮች፣ ፖሊሶች፣ ደህንነቶች ወይም ሌላ የፀጥታ አካል ሰራተኞች እና የምርጫ ቦርድ ሰራተኛ በመሆን የሚሰሩ ሰራተኞች እጩ ተወዳዳሪ ሆነው መቅረብ አይችሉም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር (1) ስር የተዘረዘሩት ሰዎች የምርጫ እጩ ተወዳዳሪ ሆነው መቅረብ የፈለጉ እንደሆነ ለመመዝገብ ጥያቄ ሲያቀርቡ ከሚሰሩበት መስሪያ ቤት የተጻፈ ስራ መልቀቃቸውን የሚገልፅ እና የመስሪያ ቤቱ ማህተም ያረፈበት ደብዳቤ አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡

**አንቀፅ 16. በእጩነት መቅረብ ስለሚፈልግ የመንግስት ሰራተኛ**

1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀጽ (1) ስር ከተዘረዘሩት በስተቀር ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ስራውን መልቀቅ ሳያስፈልገው በምርጫ ለመወዳደር በእጩነት መቅረብ ይችላል፡፡

2. የመንግሥት ሰራተኛ ለምርጫ ተወዳዳሪ ሆኖ ሲቀርብ የእጩነት ምዝገባ ጥያቄ ተቀባይነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ የመጨረሻ የምርጫ ውጤት በቦርዱ እስከሚነገር ባለው ጊዜ ፈቃድ ያለደመወዝ የማግኘት መብት ያለው ሲሆን ፈቃዱን ማግኘቱን የሚያጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

**አንቀፅ 17. የእጩዎች የመመዝገቢያ ቦታ**

1. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የክልል ምክር ቤት የተወዳዳሪ እጩዎች ምዝገባ የሚከናወነው በምርጫ ክልሎች ይሆናል፡፡

2. ለልዩ ዞን፣ ብሔረሰብ ዞን፣ ዞን፣ ለከ/ከተማ፣ ለወረዳ ወይም ለቀበሌ ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ የእጩዎች ምዝገባ የሚካሄደው ቦርዱ በሚወስነው ቦታ ወይም አግባብነት ያላቸው

የምርጫ ክልል ፅ/ቤቶች በሚወስኑት በወረዳው ወይም በቀበሌው ምርጫ አስፈፃሚ ጽ/ቤት ሊሆን ይችላል፡፡

**አንቀፅ 18. የእጩዎች መመዝገቢያ ጊዜ**

1. የእጩዎች ምዝገባ የሚካሄደው አዋጁን መሰረት በማድረግ ከምርጫው እለት ከዘጠና ቀናት በፊት ሆኖ ቦርዱ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ቅዳሜ እና እሁድን ጨምሮ በፌደራል መንግስት ሕጎች የተደነገጉ የሕዝብ በዓላትን ሳይጨምር ዘወትር ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት እስከ ቀኑ 11፡30 ሰዓት ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው ቢኖርም ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተጨማሪ የእጩዎች የመመዝገቢያ ጊዜ ወይም ልዩ የመመዝገቢያ ሰዓት ሊወስን ይችላል፡፡

**አንቀፅ 19. የፖለቲካ ድርጅት እጩ አቀራረብ**

1. በፖለቲካ ድርጅት ታጭተው የሚወዳደሩ እጩዎችን ዝርዝር በሚወዳደሩበት የምክር ቤት ምርጫ አይነት በመለየት እያንዳንዱ እጩ የሚወዳደርበትን የምርጫ ክልል በመግለጽ ለቦርዱ የሚያቀርበው የድርጅቱ፣ የግንባሩ ወይም የቅንጅቱ ሃላፊ ወይም ለዚህ አላማ የተወከለ ሌላ ሰው ይሆናል፡፡

2. ለአካባቢ ምርጫ በፖለቲካ ድርጅት ተወክለው የሚወዳደሩ እጩዎች ዝርዝር ለምርጫ ክልሉ የሚቀርበው በፖለቲካ ድርጅቱ ሃላፊ ወይም በዞኑ ወይም በወረዳው የድርጅቱ ሃላፊ ወይም ተወካይ ፊርማ እና በድርጅቱ ማህተም ተረጋግጦ ይሆናል፡፡
3. እያንዳንዱ የፖለቲካ ድርጅት፣ ግንባር ወይም ቅንጅት ፓርቲውን ወክለው የሚወዳደሩ እጩዎች ዝርዝር ቦርዱ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት አጠቃላይ ዝርዝሩን ለቦርዱ እና እያንዳንዱ እጩ ደግሞ ለሚወዳደርበት ምርጫ ክልል ጽሕፈት ቤት ማቅረብ አለበት።
4. በፖለቲካ ድርጅት ተወክሎ የሚቀርብ እጩ በፓርቲው መወከሉን እና በእጩነት ለመቅረብ መስማማቱን የሚገልጽ ማስረጃ ከእጩነት ማመልከቻ ቅጽ እና ሌሎች በዚህ መመሪያ ከሚጠየቁ ማስረጃዎች ጋር አያይዞ ለሚወዳደርበት የምርጫ ክልል በአካል በመቅረብ ይመዘገባል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (4) የተደነገገው ቢኖርም በፓለቲካ ድርጅት የቀረበ እጩ እንደ ጽኑ ህመም፣ ከባድ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋ ወይም በሌሎች ከተመዝጋቢው ቁጥጥር እና አቅም በላይ የሆኑ አስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት በግንባር ቀርቦ መመዝገብ ካልቻለ ለእጩነት የሚያበቁ መስፈርቶችን ማሟላቱን የሚያረጋግጥ የሠነድ እና እንደአግባብነቱ የሰው ማስረጃ እጩውን ባቀረበው የፖለቲካ ድርጅት ወይም በወኪሉ አማካኝነት በማቅረብ ሊመዘገብ ይችላል፡፡

6. የምርጫ ክልሉ የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (4) መሰረት የእጩነት ምዝገባ ጥያቄ ሲቀርብለት የእጩ ተወዳዳሪው ስም በፖለቲካ ድርጅቱ እጩ ተወዳዳሪዎች ዝርዝር ውስጥ ያለ መሆኑን እና መመዘኛ መስፈርቶቹን የሚያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ ምዝገባውን ያካሂዳል፡፡

**አንቀፅ 20. የግል ተወዳዳሪ እጩነት ጥያቄ አቀራረብ**

1. በግል እጩ ተወዳዳሪነት መቅረብ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ቦርዱ ለዚሁ አላማ በሚያዘጋጀው ቅጽ ላይ የሚወዳደርበትን ምክር ቤት በመጥቀስ በአዋጁ አንቀፅ 31 እና በዚህ መመሪያ ለግል እጩ ተወዳዳሪነት ለመቅረብ መሟላት ካለባቸው ማስረጃዎች ጋር በማያያዝ በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል በአካል ቀርቦ ይመዘገባል፡፡

2. በእጩ ምዝገባ ወቅት ባጋጠመው እንደ ጽኑ ህመም፣ ከባድ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋ ወይም በሌሎች ከተመዝጋቢው ቁጥጥር እና አቅም በላይ የሆኑ አስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት በአካል ቀርቦ ለመመዝገብ ያልቻለ በግል እጩነት ለመመዝገብ የሚፈልግ ሰው በህጋዊ ተወካዩ አማካኝነት መመዝገብ ይችላል፡፡
3. በምዝገባው ወቅት በሌላ ወገን ሆን ተብሎ በተፈጠረበት መሰናክል በአካል ተገኝቶ በእጩ ተወዳዳሪነት መመዝገብ ያልቻለ ሰው ቅሬታውን ለምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በማቅረብ ውሳኔ ማግኘት ይችላል፡፡ ነገር ግን በማንኛውም ሁኔታ ለምርጫ ቀን አንድ ወር ሲቀረው የሚቀርብ የእጩ ተወዳዳሪነት ምዝገባ ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

**አንቀፅ 21 እጩዎች ስለሚያቀርቡት ፎቶግራፍ**

1. በእጩነት ለመመዝገብ የሚያመለክት እጩ የእጩነት መታወቂያው ላይ እና የድምፅ መስጫ ወረቀት ላይ የሚታተም ፎቶግራፍ በሚመዘገብበት የምርጫ ክልል ለምዝገባ ሲያመለክት ይነሳል፡፡
2. ለእጩነት የሚመዘገበው ሰው ምዝገባውን የሚያካሂደው በተወካዩ አማካኝነት ከሆነ ወይም ቀድሞ የተነሳውን ፎቶግራፍ ማቅረብ ከፈለገ ፎቶግራፉ፡-

    ሀ) ባለቀለም የሆነ፣

    ለ) ከኋላ ነጭ በሆነ ቦታ ላይ የተነሳው፣

    ሐ) ቁመቱ 45 ሚ.ሊ ሜትር ስፋቱ 35 ሚ.ሊ ሜትር የሆነ፣

    መ) ከስድስት ወር ወዲህ የተነሳውና የተነሺውን የፊት ገጽታ በትክክል የሚያሳይ፣

2. ዕጩ ተመዝጋቢው ወይም ወኪሉ መታወቂያ ካርዱን ከመውሰዱ በፊት የእጩነት መታወቂያ ካርድ ላይ ያለው መረጃ እንዲሁም የፎቶግራፉን ትክክለኛነት እና ጥራት በማረጋገጥ ይህ መረጃ እና ፎቶግራፍ በድምፅ መስጫ ወረቀት ላይ የሚታተም መሆኑን መስማማቱን በመግለፅ ይፈርማል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (1) መሰረት የሚዘጋጀው የእጩነት መታወቂያ ካርድ በሁለት ቅጂ የሚዘጋጅ ሆኖ አንደኛው ቅጂ ለዕጩ ተመዝጋቢው ወይም ወኪሉ የሚሰጠው ሲሆን ቀሪው በምርጫ ክልሉ ፅ/ቤት የሚቀመጥ ይሆናል፡፡
4. ለህዝብ ተወካዮች፣ ለክልልና በዞን ለሚመሰረቱ ምክር ቤቶች ምርጫ የሚሰጥ የእጩነት መታወቂያ ካርድ እንደአግባብነቱ በቦርዱ ወይም በምርጫ ክልሉ ማህተም እና በምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ፊርማ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
5. ለወረዳ፣ ለከተማ እና ለክፍለ ከተማ እና ለቀበሌ ምክር ቤት ምርጫ የሚሰጥ የእጩነት መታወቂያ ካርድ በቀበሌው ምርጫ ጽሕፈት ቤት ሃላፊ ፊርማ ብቻ ይረጋገጣል፡፡
6. ለፖለቲካ ድርጅቶች እጩ የእጩነት መታወቂያ ካርድ ለእጩ ለራሱ ወይም ላስመዘገባው የፖለቲካ ድርጅት ሊሰጥ ይችላል፡፡
7. እጩ ወይም የፖለቲካ ድርጅቱ ተወካይ የእጩ መታወቂያ ካርዱን በወቅቱ መረከቡን በማረጋገጥ የፈረመበትን መተማመኛ በምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት በማስረጃነት እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡
8. የዕጩነት መታወቂያ ካርድ የሚያገለግለው የምርጫ ውጤት በቦርዱ ይፋ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ ብቻ ይሆናል፡፡
9. የዕጩነት መታወቂያ ካርድ የሚያገለግልበት ጊዜ እንዳለቀ እጩዎች ካርዱን ወዲያውኑ ለተመዘገቡበት ምርጫ ክልል ጽ/ቤት ማስረከብ አለባቸው፡፡

**አንቀፅ 23. የእጩ መታወቂያ ካርድ ይዘት**

1. የእጩዎች መታወቂያ ካርድ፤

ሀ) እጩው የሚወዳደርበት የምርጫ ክልሉ ስም እና/ወይም ቁጥር፣

ለ) እጩው ለምርጫ የሚወዳደርበት ምክር ቤት ስም፣

ሐ) ምርጫው የሚደረግበት ዓመተ ምህረት፣

መ) የእጩ ሙሉ ስም (የአያት ስምን ጨምሮ)፣ እድሜ እና ፆታ፣

ሠ) የእጩ ሙሉ አድራሻ ስልክ ቁጥርን ጨምሮ፣

ረ) እጩው የሚወዳደረው በግል ከሆነ የግል እጩ የሚል ፅሁፍ፣ የሚወዳደረው የፖለቲካ ድርጅትን ወክሎ ከሆነ የፖለቲካ ድርጅቱ ስም እና የፖለቲካ ድርጅት እጩ እንደሆነ የሚገልፅ ጽሁፍ፣

ሰ) የእጩው ፎቶ ግራፍ፣

ሸ) የእጩው ፊርማ እና ቀን፣

ቀ) እንደአግባብነቱ የምርጫ ቦርድ ወይም የምርጫ ክልሉ ማህተም እና የምርጫ ክልሉ ሃላፊ ፊርማ እና ቀንመያዝ አለበት፡፡

2. በእጩነት መታወቂያ ካርድ ግርጌ ወይም ጀርባ ላይ ካርዱ ወድቆ ቢገኝ አቅራቢያው ወዳለው ምርጫ ክልል ፅ/ቤት ወይም ቦርድ ወይም ፖሊስ ጣቢያ እንዲመለስ የሚያስገነዝብ ማስታወሻ መኖር አለበት፡፡

## አንቀፅ 24. የመታወቂያ መቀደድ፣ መበላሸት እና መጥፋት

1. የእጩነት መታወቂያ ካርዱ የጠፋበት፣ የተቀደደበት ወይም የተበላሸበት እጩ ተወዳዳሪ የካርዱን መጥፋት፣ መቀደድ ወይም መበላሸት ካወቀበት ቀን ጀምሮ የምርጫ ድምጽ የሚሰጥበት ቀን ከመድረሱ በፊት ባለው ማንኛውም ጊዜ ሁኔታውን ለተመዘገበበት የምርጫ ክልል በማመልከት ምትክ የእጩነት መታወቂያ ካርድ ማግኘት ይችላል፡፡

2. የምርጫ ክልሉም የእጩውን ማመልከቻ በመቀበል እና ማንነቱን ካረጋገጠ በኋላ እና ይህንኑ የሚገልፅ ማስታወሻ እጩው በተመዘገበበት ቅፅ ላይ በማስፈር ምትክ ካርድ ይሰጠዋል፡፡

3. ምትክ ካርዱ ላይ የሚፃፈው ቀን እጩው በመጀመሪያ የተመዘገበበት ቀን ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 25. የእጩነት ካርድ ወይም መዝገብ ላይ ስለተፈጠረ ስህተት

1. በእጩው ካርድ ወይም መዝገብ ላይ የሰፈረው እጩውን የሚመለከተው መረጃ ላይ ስህተት አለ የሚል እጩ ወይም እጩውን ያቀረበው የፖለቲካ ድርጅት ጊዜያዊ የእጩዎች ዝርዝር

ይፋ በተደረገ በ 7 ቀናት ውስጥ እጩው ለተመዘገበበት የምርጫ ክልል እንዲስተካከልለት ማመልከት ይችላል፡፡

2. የይስተካከልልኝ ጥያቄ የቀረበለት የምርጫ ክልል ጥያቄውን ከሚቀርበው የማንነት እና ሌሎች መመዘኛ መስፈርት ማረጋገጫ ሰነዶች ጋር በማመሳከር፡-

ሀ) ስህተቱ የተፈጠረው መዝገቡ ላይ ከሆነ መዝገቡን በማስተካከል ማስተካከያውን መዝገቡ ላይ በማስፈር ማስተካከያ መደረጉን በቃለጉባኤ ላይ ያሰፍራል፡፡

ለ) ስህተቱ የተፈጠረው በተሰጠው የእጩነት መታወቂያ ካርድ ላይ ከሆነ ደግሞ ማስተካከያ የተደረገበትን ምትክ መታወቀያ ካርድ በመስጠት የተሳሳተውን የመታወቂያ ካርድ ተቀብሎ የተበላሸ ከሚል ማስታወሻ ጋር መዝገቡ ላይ ያያይዛል፡፡ ይንንም የሚመለከት ቃለጉባኤ ይይዛል፡፡

**አንቀፅ 26. እጩዎችን ለሕዝብ ይፋ ስለማድረግ**

1. ቦርዱ ባወጣው የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የእጩዎችን ስም ዝርዝር በቀረቡበት የምክር ቤት የምርጫ አይነት በመለየት ለሚወዳደሩበት የምርጫ ክልል ሕዝብ ይፋ ይደረጋል፡፡
2. የምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት የእጩነት መታወቂያ ያገኙ እጩዎችን፤

ሀ) ሙሉ ስም ከነአያት፣

ለ) እድሜ፣

ሐ) ፆታ፣

መ) የትምሕርት ደረጃ፣

ሠ) የሥራ አይነት ወይም የሙያ ዘርፍ፣

ረ) የተወከሉበት የፖለቲካ ድርጅት ስም ወይም በግል የቀረቡ መሆናቸውን፣

ሰ) የመወዳደሪያ ምልክት ወይም መጠሪያ እና

ሸ) ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ከቦርዱ ዋና ጽሕፈት ቤት በተላከለት ዕጩዎቹን ለሕዝብ ማሳወቂያ ቅፅ ላይ በመሙላት መራጩ ሕዝብ እንዲያውቀው ሕዝብ በሚበዛበት እና በሚዘዋወርበት እንደዚሁም በምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት ቅጥር ግቢ

እና በምርጫው እለት በየምርጫ ጣቢያው መለጠፍ አለበት፡፡

3. ለህዝብ ተወካዮች፣ ለክልል፣ ለዞንና ለብሔረሰብ ዞን ምክር ቤቶች ለሚደረግ ምርጫ የምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በእያንዳንዱ የእጩ ማሳወቂያ ፖስተር ላይ ስሙን ሞልቶ መፈረም እና የምርጫ ክልሉን ማሕተም በፖስተሮቹ ግርጌ ላይ በግልፅ በሚታይ ሁኔታ ማተም ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (3) የተደነገገው ቢኖርም የወረዳ፣ የከተማ፣ የክፍለ ከተማና የቀበሌ ምክር ቤቶች ምርጫ የእጩ ማስታወቂያ ፖስተር በየደረጃው ባሉ የአስተዳደር እርከኖች የምርጫ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ፊርማ ብቻ ተረጋግጦ ሊለጠፍ ይችላል፡፡
5. የእጩ ዝርዝሮችን ለህዝብ ይፋ የማድረግ ሃላፊነት ያለበት ሃላፊ የእጩ መተካት ወይም መሰረዝ ሲኖር ተከታትሎ መተካቱ ወይም መሰረዙ ወይም እጩው ራሱን ማግለሉን በተመለከተ ትክክለኛ መረጃ እንዳገኘ በተቻለ ፍጥነት ዝርዝሩን ቀድሞ በተለጠፈበት ቦታ ላይ በመለጠፍ ህዝቡ እንዲያውቀው ማድረግ አለበት፡፡

**አንቀፅ 27. የእጩዎች ከውድድር ራስን ማግለል**

1. አንድ የፖለቲካ ድርጅት እጩ ወይም የግል ዕጩ ራሱን ከዕጩነት ሊያገል ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ራሱን ከእጩነት ያገለለ የግል እጩ የእጩነት መታወቂያ ካርዱን ዋና ቅጂ እና ራስን ከእጩነት የማግለል ውሳኔውን የሚገልጽ ማመልከቻ አያይዞ በእጩነት ለተመዘገበበት የምርጫ ክልል ማቅረብ አለበት፡፡
3. ከውድድር ራሱን ያገለለ የፖለቲካ ድርጅት ዕጩ ለወከለው የፖለቲካ ድርጅት በጽሑፍ እና በፊርማው በማረጋገጥ ማሳወቁን የሚገልፅ ማስረጃ ለተመዘገበበት የምርጫ ክልል ማቅረብ አለበት፡፡
4. ራሱን ከእጩነት ያገለለ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል ዕጩ ያገለለበትን ምክንያት እንዲገልፅ አይገደድም፡፡

**አንቀፅ 28. ስለ እጩ መሞት**

1. እጩ የሞተበት የፖለቲካ ድርጅት የእጩ ምዝገባ የጊዜ ሠሌዳ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ሌላ እጩ ሊተካ ይችላል፡፡

2. ማንኛውም እጩ ሆኖ የተመዘገበ ሰው ከድምፅ መስጫ ቀን አንድ ወር በፊት ወይም የድምፅ መስጫ ወረቀት ከመታተሙ በፊት የሞተ እንደሆነ የምርጫ ክልሉ እጩ ተወዳዳሪዎች ዝርዝር ውስጥ ሳይካተት የሌሎች ተወዳዳሪዎች ዝርዝር ብቻ ለህዝብ ይፋ ይደረጋል፡፡

3. እጩ ተወዳዳሪው የሞተው ዝርዝሩ ለህዝብ ይፋ ከተደረገ በኋላ ከሆነ ሟቹ ተመዝግቦበት የነበረው የምርጫ ክልል ይህንኑ መረጃ በምርጫ ክልሉ ፅ/ቤት በመለጠፍ ለህዝቡ ማሳወቅ አለበት፡፡

**አንቀፅ 29. ስለ እጩ መተካት**

1. አንድ የፖለቲካ ድርጅት ያቀረበው እጩ የሞተበት ወይም ራሱን ከውድድር ያገለለበት እንደሆነ የዕጩ ምዝገባ የጊዜ ሠሌዳ እስከሚያልቅ ድረስ ሌላ ዕጩ ሊተካ ይችላል፡፡
2. ምትክ እጩ ለማቅረብ የሚፈልግ የፖለቲካ ድርጅት ጉዳዩን በሚመለከተው ኃላፊ ፊርማ እና በድርጅቱ ማሕተም በማረጋገጥ እንደዚሁም እጩው ራሱን ከውድድር ያገለለበትን ሰነድ ወይም ያቀረበው እጩ የሞተበት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ፣ የተመለሰውን የእጩ መታወቂያ ካርድ፣ የተተኪውን እጩ ስም እና ሌሎች ለእጩነት የሚያበቁ ማስረጃዎችን በማያያዝ ወዲያውኑ ለምርጫ ክልሉ ማቅረብ አለበት፡፡
3. የምርጫ ክልሉ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ጉዳይ በመመርመር ተተኪውን እጩ በወቅቱ ይመዘግባል፣ የእጩነት መታወቂያ ካርድም ይሰጣል፡፡
4. የመጀመሪያው እጩ ራሱን ያገለለው ወይም የሞተው በእጩ ምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ከሆነ የፖለቲካ ድርጅቱ የመጀመሪያው እጩ ራሱን ማግለሉን ወይም እጩው መሞቱን ፓርቲው ካወቀበት ቀን ጀምሮ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ሌላ ዕጩ መተካት ይችላል፡፡
5. እጩው ራሱን ያገለለው ወይም የሞተው የእጩዎች ምዝገባ ጊዜ ካለቀ በኋላ ከሆነ የፖለቲካ ድርጀቱ ተተኪ እጩዉን ማቅረብ የሚችለው ለድምፅ መስጫ ቀን የቀረው ጊዜ አንድ ወር ከሆነ ብቻ ነው፡፡
6. እጩው እራሱን ያገለለበት ወይም የሞተበት የፖለቲካ ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (5) በተሰጠው ጊዜ ሌላ እጩ ካልተካ ምርጫው በተያዘለት ጊዜ በቀሩት እጩዎች መካከል ይካሄዳል፡፡
7. የሞተው ወይም ራሱን ከምርጫ ያገለለው እጩ በምርጫ ክልሉ የነበረ ብቸኛው እጩ ከሆነ ቦርዱ በሚያወጣው ጊዜ ሰሌዳ መሰረት አዲስ እጩዎች እንዲመዘገቡ ተደርጎ ምርጫው ይከናወናል፡፡
8. አንድ እጩ በሌላ እንዲተካለት የሚቀርብ ማመልከቻ እጩ ለማቅረብ ከሚቀርበው ማመልከቻ እና ማስረጃዎች ጋር አንድ አይነት ሆኖ የማመልከቻው አርእስት ብቻ ለመተካት እንዲሆን ተደርጎ ይቀርባል፡፡

**አንቀፅ 30. ከእጩነት ስለመሰረዝ**

1. የእጩነት መታወቂያ ካርድ የተሰጠው ሰው፡-

   ሀ) ለእጩነት የሚያበቁ መስፈርቶችን የማያሟላ መሆኑ ከተረጋገጠ፣

   ለ) እጩ ሆኖ በመቅረቡ ላይ ቅሬታ ቀርቦበት ቅሬታው ተቀባይነት ካገኘ፣

   ሐ) በፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ወይም ከባድ ወንጀል ሲፈፅም እጅ ከፍንጅ ተይዞ በፍርድ ቤት የጥፋተኛ ውሳኔ ተላልፎበት የመመረጥና የመመረጥ መብቱ በውሳኔው ከተገፈፈ፣

   መ) እጩው ሆን ብሎ ከአንድ በላይ የምርጫ ክልሎች የተመዘገበ እንደሆነ፣

   ሠ) ራሱን ከምርጫ ማግለሉን የገለፀ እንደሆነ እና

   ረ) ለምዝገባ ያስገባው የድጋፍ ፊርማ ላይ ያልፈረመን ሰው በሀሰት የፈረመ በማስመሰል ወይም መፈረም የማይገባው ሰው እንዲፈርም አድርጎ ከተገኘ ከእጩነት ይሰረዛል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (1)(ረ) መሰረት ያልፈረመን ሰው በሀሰት የፈረመ ማስመሰሉ ወይም መፈረም የማይገባውን ሰው እንዲፈርም መደረጉ የታወቀው ምርጫው ከተደረገ በኋላ ከሆነ ቦርዱ፡-

   ሀ) እጩው በምርጫ ክልሉ ላይ ያሸነፈ ከሆነ ለተመረጠበት ምክር ቤት፣

   ለ) እጩው አሸናፊ ካልሆነ ደግሞ ለሚመለከተው ወንጀል አጣሪ አካል ካሉት ማስረጃዎች ጋር አያይዞ በማቅረብ ያመለክታል፡፡

3. የፖለቲካ ድርጅትን ወክሎ የቀረበ እጩ ከእጩነት የተሰረዘው የፖለቲካ ድርጅቱ ባልተሳተፈበት ወይም ማወቅ በማይችልበት ሁኔታ በራሱ ጥፋት ከሆነ እና መሰረዙ የተደረገው ከድምፅ መስጫው ቀን ከአንድ ወር በፊት ከሆነ ብቻ የፖለቲካ ፓርቲው በተሰረዘው እጩ ምትክ ሌላ ሰው ማቅረብ ይፈቀድለታል፡፡

**አንቀፅ 31. ከአንድ የምርጫ ክልል በላይ ስላለመወዳደር**

1. ማንኛውም ሰው ለአንድ ምርጫ እጩ ሆኖ መቅረብ የሚችለው በአንድ የምርጫ ክልል ብቻ ነው፡፡

2. ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ ከአንድ በላይ በሆኑ የምርጫ ክልሎች በእጩነት ተመዝግቦ የተገኘ እንደሆነ ከሁሉም የምርጫ ክልሎች እጩነት ይሰረዛል፡፡

3. አንድ በምርጫ ያሸነፈ እጩ ከአንድ የምርጫ ክልል በላይ በእጩነት መመዝገቡ ከምርጫው ውጤት በኋላ የታወቀ እንደሆነ እጩው ያገኘው ድምፅ ተሰርዞ ከተሰረዘው አሸናፊው ቀጥሎ ከፍተኛውን ድምፅ ያገኘው ተወዳዳሪ አሸናፊ ይደረጋል፡፡

## አንቀፅ 32. ወደ ሌላ ምርጫ ክልል ተዛውሮ ስለመወዳደር

1. አንድ እጩ በእፅጩ ምዝገባ የጊዜ ሠሌዳ ውስጥ በአዋጁ መሠረት ሊወዳደርበት ካለው የምርጫ ክልል ሊወዳደርበት በሕግ ወደተፈቀደለት ሌላ የምርጫ ክልል ተዛውሮ መወዳደር ይችላል፡፡
2. የዝውውሩን ጥያቄ ያቀረበው የፖለቲካ ድርጅት ከሆነ የዝውውሩን ጥያቄ በድርጅቱ ማህተምና የሃላፊ ፊርማ በተረጋገጠ ደብዳቤ እጩ ተመዝግቦበት ለነበረው የምርጫ ክልል ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
3. የዝውውሩን ጥያቄ ያቀረበው የግል እጩ ተወዳዳሪ ከሆነ የዝውውር ጥያቄውን በፊርማው በማረጋገጥ ተመዝግቦበት ለነበረው የምርጫ ክልል በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡
4. እጩው የቀድሞውን የምዝገባ ሰነድ እና የእጩነት መታወቂያ በተመዘገበበት የምርጫ ክልል መልሶ እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡ ይህንኑ የሚያረጋግጥ የጽሁፍ ማስረጃም ከተሰረዘበት የምርጫ ክልል ጽሕፈት ቤት ይሰጠዋል፡፡
5. የሚዛወረው እጩ ቀድሞ ተመዝግቦበት ከነበረው የምርጫ ክልል የተሰጠውን የጽሑፍ ማስረጃ ተዛውሮ መወዳደር ወደፈለገበት የምርጫ ክልል ጽሕፈት ቤት ያቀርባል፡፡ የምርጫ ክልል ጽሕፈት ቤቱም መስፈርቱን ማሟላቱን በማረጋገጥ ይመዘግባል፡፡ የእጩነት መታወቂያና ሌሎች የምዝገባ ሰነዶች ይሰጠዋል፡፡
6. ይህ የእጩ ዝውውር ማመልከቻ የሚቀርበው እና ዝውውሩ የሚካሄደው የእጩዎች ምዝገባ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ነው፡፡

## አንቀፅ 33. የእጩነት ምዝገባ ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ

1. የእጩ ምዝገባን በመቃወም ወይም በእጩነት ለመመዝገብ ተከለከልኩ የሚል አቤቱታ ያለው ሰው ቅሬታውን ካሉት ማስረጃዎች ጋር አያይዞ ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቦርዱ ባወጣው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አደረጃጀት እና አሰራር መመሪያ መሰረት ቅሬታውን በማስተናገድ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት
## ስለእጩ መወዳደሪያ እና መለያ ምልክት

### አንቀፅ 34. ስለዕጩዎች መለያ ምልክት አመራረጥ

1. በድምፅ መስጫ ወረቀት ላይ የሚኖረው የእጩዎች የመለያ ምልክት አደራደር በቦርዱ በእጣ የሚወሰን ይሆናል፡፡
2. ቦርዱ የተለያዩ አማራጭ የእጩ መለያ ምልክቶችን በአልበም መልክ ያዘጋጃል፡፡
3. ማንኛውም እጩ መለያ ምልክቱን እራሱ ሊያቀርብ ወይም ቦርዱ ካዘጋጀው አልበም ሊመርጥ ይችላል፡፡ እጩው መለያ ምልክቱን እራሱ የሚያቀርብ ከሆነ ምልክቱ ቦርዱ ከሚያወጣቸው የቴክኒክ መስፈርት ጋር መጣጣም አለበት፡፡
4. ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት መወዳደሪያ ምልክቱን ቦርዱ ባወጣው የምርጫ አፈፃፀም የጊዜ ሠሌዳ መሠረት በቦርዱ ዋና ጽሕፈት ቤት ተገኝቶ እንዲመርጥ ወይም የራሱን መለያ ምልክት እንዲያቀርብ ይደረጋል፡፡
5. የቦርዱ ጽሕፈት ቤት በማዕከል የተመረጡና ያልተመረጡ የመወዳደሪያ ምልክቶችን በመዘርዘር ለምርጫ ክልሎች ያሳውቃል፡፡
6. የግል ዕጩዎች የመወዳደሪያ ምልክታቸውን፡-

   ሀ) ቦርዱ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሊወዳደሩበት ባሰቡት የምርጫ ክልል ጽህፈት ቤት በመገኘት ይመርጣሉ፡፡

   ለ) እራሳቸው ሊያቀርቡ ወይም በሚወዳደሩበት የምርጫ ክልል ጽህፈት ቤት ቦርዱ በየምርጫው ዓይነት ለይቶ ካዘጋጀው የምልክት መምረጫ አልበም ውስጥ ሊመርጡ ይችላሉ፡፡

7. እጩዎች በመረጧቸው ምልክቶች ተጠቃሚ የሚሆኑት በቦርዱ ጽሕፈት ቤት ወይም በቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሲሰጣቸው ነው፡፡
8. የአንድ የፖለቲካ ድርጅት ዕጩዎች በሁሉም የምርጫ ደረጃዎች አንድ አይነት መለያ ምልክት መጠቀም አለባቸው፡፡
9. የአንድ የፖለቲካ ድርጅት ዕጩዎች ለየምክር ቤቱ ምርጫ በሁሉም የምርጫ ክልሎች አንድ ዓይነት መለያ ምልክት መጠቀም አለባቸው፡፡
10. አንድ የፖለቲካ ድርጅትም ሆነ የግል እጩ ባለፈው ምርጫ የተጠቀመበትን የምርጫ ምልክት ቅድሚያ ተሰጥቶት እንዲመርጥ መደረግ ያለበት ሲሆን ካስፈለገ ምልክቱ ቦርዱ የሚያወጣቸውን የቴክኒክ መስፈርት ተከትሎ መስተካከል አለበት፡፡

11. በምርጫ ምልክት ላይ ለሚነሱ አለመግባባቶች በዚህ መመሪያ አንቀፅ 37 መሰረት ቦርዱ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡
12. ቦርዱ የአዋጁን እና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎችን የሚጥስ ነው ብሎ ሲያምን የአንድን የግል እጩ ተወዳዳሪ ወይም የፖለቲካ ድርጅት መለያ ምልክት እንዲቀየር ሊያዝ ይችላል።

## አንቀፅ 35. የእጩ መለያ ምልክት ይዘት

ማንኛውም የእጩ መለያ ምልክት፡-

1. ቦርዱ የሚያወጣቸውን የጥራት መስፈርቶችን ያሟላ፣
2. ከሌሎች ቀድመው ያስመዘገቡ የግል ዕጩዎች ወይም ፖለቲካ ፓርቲዎች መለያ ምልክት ጋር የማይመሳሰል፣
3. በብሔር ብሔረሰብ፣ በዘር፣ በሃይማኖት መካከል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጥላቻና ግጭት ሊቀሰቅስ ከሚችል ነገር ወይም ሁኔታ ጋር ግንኙነት የሌለው፣
4. ሀይማኖትን፣ የተለየ ቡድንን ወይም የማህበረሰብ ክፍልን፣ ጾታን፣ ብሔር ብሔረሰቦችን እና ዘርን የሚመለከት አሉታዊ አመለካከትን የማያንፀባርቅ፣
5. የጦርነት ወይም ሌላ ሕገወጥ ድርጊት መልዕክት የማያስተላልፍ፣
6. ከፌደራልም ሆነ ከክልል መንግሥታት ሰንደቅ ዓላማ፣ አርማ ወይም ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች አርማ ወይም ከልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዓርማና ሰንደቅ አላማ ወይም ከሃይማኖት ድርጅቶች ምልክቶች ጋር የማይመሳሰል፣
7. በምልክት ቋንቋ የታወቀ የተለየ ትርጉም የሌለው እና፣
8. በህግ የተመዘገበ ወይም የተቋቋመ የግል ድርጅት፣ የመንግስት ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም አርማ ጋር የማይመሳሰል እና
9. የሕዝብን ሞራል፣ መልካም ስነምግባር እና የመሳሰሉትን የማይጥስ መሆን ይኖርበታል፡፡

## አንቀፅ 36. የእጩ ምልክቶችን መለወጥና መተካት

1. ቦርዱ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀፅ (12) መሠረት የአንድ ፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ መለያ ምልክትን እንዲለወጥ ሊያዝ ይችላል፡፡
2. የእጩ ምልክት እንዲለወጥ በቦርዱ ሲወሰን የእጩዎች ምዝገባ ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ ውሳኔውን የፖለቲካ ድርጅቱ ወይም የግል እጩው እንዲያውቀውና ተለዋጭ ምልክት እንዲያቀርብ ወይም እንዲመርጥ ይደረጋል፡፡
3. የፖለቲካ ድርጅትም ሆነ የግል እጩ ቀደም ሲል የመረጠውን ምልክት በሌላ ለመለወጥ ሲፈልግ የእጩዎች ምዝገባ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ በአስር ቀናት ውስጥ ቀድሞ

የነበረውን እና አዲስ የሚተካውን ምልክት አያይዞ ለውጡን ለቦርዱ ወይም ለምርጫ ክልሉ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

**አንቀፅ 37. መለያ ምልክት ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ**

1. ማንኛውም የግል እጩ ወይም የፓለቲካ ፓርቲ መለያ ምልክት ያለአግባብ በሌላ ተወዳዳሪ ተወሰደብኝ፣ ተከለከልኩ ወይም እንድቀይር ታዘዝኩ የሚል ቅሬታ ያለው እንደሆነ ለቅሬታው መንስኤ የሆነው ጉዳይ ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ አምስት ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ በማቅረብ ውሳኔ ማግኘት ይችላል፡፡
2. ቦርዱ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ቅሬታው በቀረበለት በአምስት ቀናት ጊዜ ውስጥ ቅሬታ ላቀረበ ሰው ውሳኔውን በፅሁፍ ይሰጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር (2) መሰረት የሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታውን ውድቅ የሚያደርግ፣ ጥያቄውን የሚቀበል ወይም ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ትእዛዝ የሚሰጥ ሊሆን ይችላል፡፡
4. በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ቅሬታውን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀፅ 38. የእጩዎች ልዩ መብት**

1. እጩዎች ከባድ ወንጀል ሲፈፅሙ እጅ ከፍንጅ ካልተያዙ በስተቀር ምርጫው እስከሚጠናቀቅ ድረስ አይያዙም፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተጠቀሰው በተለየ ሁኔታ እጩዎች ሕገወጥ ድርጊት የፈፀሙ ከሆነ ሕጋዊ እርምጃ የሚወሰድባቸው የምርጫ ውጤት በቦርዱ አማካይነት በይፋ ለሕዝብ ከተገለፀ በኋላ ብቻ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (2) የተጠቀሰው ቢኖርም ወንጀል አድራጊው ሰው አሸናፊ ከሆነ በምርጫ ወቅት ለፈፀመው ወንጀል የሚጠየቀው በሚመለከተው ምክር ቤት የሕግ ከለላው ሲነሳ ነው፡፡

**አንቀፅ 39. የቦርዱ ሃላፊነት**

1. ቦርዱ በእጩነት ለመመዝገብ የሚፈልግ ሰው በአዋጁና በዚህ መመሪያ ላይ የተደነገጉ መስፈርቶች አሟልቶ የእጩዎች የምዝገባ ሰሌዳ ጊዜ ውስጥ ማመልከቻውን እንዲያቀርብ ለህብረተሰቡ ተደራሽ በሆኑ የመገናኛ ዘዴዎች አስቀድሞ ያሳውቃል፡፡

2. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀፅ (1) ላይ የተደነገገውን ሃላፊነቱን ሲወጣ የሚያሰራጨው መረጃ ሴቶችን እንዲሁም በተለየ ሁኔታ ለመረጃ ቅርብ ያልሆኑ እና ልዩ ድጋፍ የሚሹ ዜጎችን፣ አካል ጉዳተኞች እና የመሳሰሉትን የህብረተሰብ ክፍሎች የሚደርስበትን ዘዴ ግምት ውስጥ ያስገባል፡፡

**አንቀፅ 40. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ወይም አካል የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀፅ 41. የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የሌላቸው አሠራሮች እና መመሪያዎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም፡፡

**አንቀፅ 42. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በቦርዱ ከፀደቀበት ታህሳስ 28 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ብርቱካን ሚደቅሳ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# የመራጮች ምዝገባ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 6/2013 ዓ.ም.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### አንቀፅ 1. አውጪው ባለሥልጣን

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ዓ.ም. አንቀፅ 163 ንዑስ አንቀፅ (2) እንዲሁም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ (11) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### አንቀፅ 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመራጮች ምዝገባ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 6 /2013 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀፅ 3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ፤

1. **"ኢ.ፌ.ዲ.ሪ"** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ነው፡፡
2. **"ቦርድ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፡፡
3. **"የፖለቲካ ፓርቲ"** ማለት ዜጎች ተደራጅተው የሚመሠርቱት የፖለቲካ ፕሮግራም በማውጣት በሀገር አቀፍ፣ በክልል ወይም ከክልል በታች ባለ ደረጃ የፖለቲካ ሥልጣን በምርጫ ለመያዝ በምርጫ ሕጉ መሠረት ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ ተቋም ነው፡፡
4. **"ጠቅላላ ምርጫ"** ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት የሚካሄድ የህዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው፡፡
5. **"የአካባቢ ምርጫ"** ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት የሚካሄድ የብሔረሰብ ዞን፣ የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማ፣ የክፍለ ከተማ ወይም የቀበሌ ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው፡፡
6. **"ድጋሚ ምርጫ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀፅ (16) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ቦርዱ የምርጫ ውጤቱ እንዲሰረዝ ሲወስን፣ በምርጫ ሕጉ አንቀጽ 154 መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ሲወስን፤ ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምፅ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን ለመለየት የሚካሄድ ምርጫ ነው፡፡
7. **"ማሟያ ምርጫ"** ማለት በመራጮች ውሳኔ ከምክር ቤት መነሳትን ጨምሮ በማንኛውም ምክንያት በየደረጃው የሚገኙ የተጓደሉ የምክር ቤት አባላት መቀመጫዎችን ለመሙላት

የሚካሄድ ምርጫ ነው::

8. **"ህዝበ ውሳኔ"** ማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግሥት ወይም አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ሲወሰን የህዝብ ፍላጎትን ለመለካት እና የህዝብን ውሳኔ ለማወቅ ድምፅ የሚሰጥበት ስርዓት ነው::
9. **"የምርጫ ጣቢያ"** ማለት በየደረጃው ለሚካሄዱ ምርጫዎች የመራጭ ምዝገባ የሚካሄድበት፣ መራጮች ድምፅ የሚሰጡበት እና የድምጽ ቆጠራ የሚካሄድበት ቦታ ነው::
10. **"የመራጮች መዝገብ"** ማለት በየደረጃው ለሚካሄድ ምርጫ መራጩ ሕዝብ በምርጫ ጣቢያው በመራጭነት የሚመዘገብበት መዝገብ ነው::
11. **"የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ"** ማለት አንድ ሰው በመራጭነት ስትመዘገብ ከመዘገባት የምርጫ ጣቢያ የሚሰጣት የመራጭነት ማረጋገጫ ነው::
12. **"የምርጫ አስፈፃሚ"** ማለት በየደረጃው ምርጫን ለማስፈጸም በቦርዱ የምትመደብ ሰው ናት፡፡
13. **"የምርጫ ጣቢያ ኃላፊ"** ማለት የምርጫ ጣቢያውን በሰብሳቢነት የምትመራ በቦርዱ የምትመደብ የምርጫ አስፈጻሚ ናት፡፡
14. **"የመዝገብ ሹም"** ማለት መራጮችን እንድትመዘግብ በምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የተመደበች የምርጫ ጣቢያ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ናት፡፡
15. **"ሰልፍ አስከባሪ"** ማለት በምርጫ ጣቢያው መግቢያ ላይ በመቆም መራጮች ለምዝገባ ሲመጡ በቅደም ተከተል የምታስተናግድ የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ናት፡
16. **"የፀጥታ አስከባሪ"፣ "የፀጥታ ኃይል" ወይም "የፀጥታ አካል"** ማለት የምርጫ ጣቢያን ደህንነት ለማስከበር በምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ጥያቄ አማካኝነት የሚመደብ የፖሊስ ኃይል ነው፡፡
17. **"ልዩ የምዝገባ ቀን"** ማለት ቦርዱ ለመራጮች ምዝገባ ባወጣው መደበኛ ጊዜ ውስጥ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሳይመዘገብ የቀረ ሰው እንዲመዘገብበት ቦርዱ የሚወስነው ቀን ነው።
18. **"የምርጫ ህግ"** ማለት የኢትዮጵያ የምርጫ፥ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ዓ.ም. ነው::
19. **"ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ"** ማለት በክልል ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት፤ በምርጫ ክልል እና በምርጫ ጣቢያ ደረጃ ለሚነሱ ቅሬታዎች አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጥ በአዋጁ መሰረት ለምርጫ ወቅት የሚቋቋም ኮሚቴ ነው፡፡
20. **"ሰው"** ማለት ሕጋዊ ወይም የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡
21. በአዋጁ ላይ የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደአግባብነታቸው ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**አንቀፅ 4. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ ለጠቅላላ ፣ ለአካባቢ፣ ለማሟያ፣ ለድጋሚ ምርጫ እና በህገ መንግሥቱ መሠረት ለሚካሄድ ህዝበ ውሳኔ እንዲሁም አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች መሰረት በልዩ ሁኔታ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በመደበኛ፣ በተንቀሳቃሽና በልዩ ሁኔታ በሚቋቋሙ የምርጫ ጣቢያዎች በሚደረግ የመራጮች ምዝገባ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አንቀፅ 5. አላማ**

የዚህ መመሪያ አላማ ዜጎች የመምረጥ መብታቸውን በመጠቀም ተወካዮቻቸውን በእኩልነት የሚመርጡበት ትክክለኛ፣ አሳታፊ እና ግልጽ የመራጮች ምዝገባ የአሰራር ስርአት መዘርጋት ነው::

**አንቀፅ 6. የፆታ አገላለፅ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በአንዱ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሌላኛውን ጾታም ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የመራጮች ምዝገባ አደረጃጀት

**አንቀፅ 7. የምርጫ ጣቢያ አካላት አደረጃጀት**

1. እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ በምርጫ ህጉ እንዲሁም አግባብ ባለው የቦርዱ መመሪያ መሠረት በቦርዱ የሚመለመሉ ቢያንስ አንድ ሴት የያዘ የምርጫ አስፈፃሚዎች ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡
2. የመራጮች ምዝገባ የሚከናወነው ከምርጫ አስፈጻሚዎች ቢያንስ ሦስቱ በጣቢያው ሲገኙ ነው፡፡
3. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ከምርጫ አስፈፃሚ አባላት መካከል አንዷን የመዝገብ ሹም አድርጋ ትመድባለች፡፡
4. የመራጮች ምዝገባ የሚከናወነው በተመደበችው የመዝገብ ሹም ይሆናል፡፡
5. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ  በየሳምንቱ የምርጫ ጣቢያውን ምርጫ አስፈጻሚዎች በመዝገብ ሹምነት በየተራ ትመድባለች፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (3) የተደነገገው ቢኖርም አንድ በመዝገብ ሹምነት የተመደበች የምርጫ ጣቢያ የምርጫ አስፈፃሚ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር በሥራዋ ላይ መገኘት ካልቻለች የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዋ በምትሰጠው መመሪያ መሠረት ምዝገባው በሌላ የምርጫ ጣቢያው አስፈፃሚ አባል በጊዜያዊነት እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡
7. አንድ የመዝገብ ሹም በቋሚነት በሥራዋ ላይ መገኘት ካልቻለች የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ወዲያውኑ በተጠባባቂነት ከተያዙት የምርጫ አስፈፃሚዎች መካከል በቋሚነት እንድትተካ ታደርጋለች፡፡
8. በምርጫ ጣቢያው በተጠባባቂነት የተያዘች አስፈፃሚ ከሌለች በፍጥነት ለምርጫ ክልሉ በማሳወቅ እንድትተካ ታደርጋለች፡፡
9. እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ በምርጫ ጣቢያ ኃላፊዋ በምትመደብ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ሰብሳቢነት የሚመራና በምርጫ ክልሉ ከተመዘገቡ መራጮች መካከል የሚመረጡ አንድ ወንድ እና አንድ ሴት አባል የሆኑበት የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡
10. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባል የሆኑ ሰዎች የማንም ፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆኑና በመልካም ሥነ ምግባራቸውና ስብእናቸው የታወቁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ዝርዝር አሰራራቸውም ቦርዱ ባወጣው የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ መመሪያ መሰረት የሚገዛ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 8. የምርጫ ጣቢያው አስፈጻሚዎች ስልጣንና ኃላፊነት**

በምርጫ ሕጉ፤ በዚህ መመሪያ እና ቦርዱ በሚያወጣው የመራጮች ምዝገባ አፈፃፀም ማንዋል መሠረት የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዎች የሚከተሉት ዋና ዋና ኃላፊነትና ስልጣኖች አሏቸው፡

1. የምርጫ ጣቢያ ኃላፊ

   ሀ) የምርጫ ጣቢያውን አስፈጻሚ ኮሚቴ በሰብሳቢነት መምራት፤

   ለ) በምርጫ ሕጉ እና በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን ጨምሮ በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን ሥልጣንና ኃላፊነቶች እንዲያከናውኑ የምርጫ ጣቢያው አስፈጻሚዎችን መመደብ፣

ማቀያየር፣ እንዲሁም ሲጓደሉ ቦርዱ በምርጫ ክልሎች ካስቀመጣቸው ተጠባባቂ አስፈጻሚዎች ጠይቆ መተካት፤

ሐ) የመራጮች ምዝገባ ሰነድና ቁሳቁስ ከምርጫ ክልል ጽሕፈት ቤት ወደ ምርጫ ጣቢያው መድረሳቸውን ማረጋገጥ፤ የምርጫ ጣቢያው በቂ የመራጮች ምዝገባ ሰነዶች እንዳሉት ማረጋገጥ እንዲሁም ሰነዶቹ በቀጣዮቹ ሁለት ወይም ሦስት ቀናት የሚያልቁ ከሆነ ለምርጫ ክልሉ ፅሕፈት ቤት ማሳወቅ፤

መ) ሁሉም ሰነድና ቁሳቁስ ለመራጮች ምዝገባ በማይውሉበት ጊዜ ሁሉ በአግባቡ ተጠብቀው መቀመጣቸውን ማረጋገጥ፤

ሠ) የምርጫ ጣቢያው ለሥራ ምቹ የሆነ ክፍል እንዳለው እንዲሁም በአግባቡ መሰናዳቱን ማረጋገጥ፤

ረ) በምርጫ ህጉ መሰረት በምርጫ ጣቢያው ውስጥ መገኘት ያለባቸው ሰዎች ብቻ መገኘታቸውን ማረጋገጥ፤

ሰ) የምርጫ ቁሳቁስ በምርጫ ቁሳቁስ አስተዳደር መመሪያ መሰረት በአግባቡ መያዛቸውን መከታተል ስለአፈፃፀሙም በየእለቱ ለምርጫ ክልሉ ሪፖርት ማድረግ፤

ሸ) የምርጫ ጣቢያው ደህንነትና ሥርዓት መጠበቁን ማረጋገጥና ይህም እንዲከበር ማድረግ፤

ቀ) የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ደህንነትን የማስከበር ጥያቄ ካላቀረበች በስተቀር የፖሊስ ወይም የፀጥታ አካል ከምርጫ ጣቢያው ውጪ በተገቢው ርቀት ላይ መቆየታቸውን ማረጋገጥ፤

በ) በእያንዳንዱ የምዝገባ ቀን መጨረሻ ላይ የምዝገባ መረጃዎች ለምርጫ ክልል ጽ/ቤቱ ሪፖርት መደረጋቸውን ማረጋገጥ፤

ተ) በቦርዱ በሚቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት፣ በ"የምርጫ ማስፈጸሚያና የድምጽ መስጫ መሳሪያዎች፣ ሰነዶች እና ቁሳቁስ ድልድል፣ ሥርጭት፣ አጠቃቀም፣ ርክክብና አወጋገድ መመሪያ"፣ በ"የምርጫ አስፈፃሚዎች የአሰራርና የስነምግባር መመሪያ"እና በአፈፃፀም መመሪያዎች መሰረት አስፈላጊ ቁሳቁሶች እና ሰነዶች ወደ የምርጫ ክልል ጽ/ቤት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መላካቸውን ማረጋገጥ፤

ቸ) እያንዳንዱ የመራጮች ካርድ መዝገብ ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ ወደ ምርጫ ክልሉ በፍጥነት መላኩን ማረጋገጥ፤

ነ) በቦርዱ ወይም በምርጫ ቦርዱ ስልጣን የተሰጣት ሰው የምትሰጣትን ተጨማሪ ተግባራት ማከናወን።

2. የመዝገብ ሹም

የመዝገብ ሹም ሆና የተመደበች የምርጫ አስፈፃሚ፥

ሀ) የምዝገባ ቅጹን በመሙላት የመራጮች ምዝገባ ታካሂዳለች፤

ለ) ተመዝጋቢዋ የመታወቂያ ካርድ ባቀረበችበት ጊዜ ለመዝጋቢዋ ከምትሰጠው መረጃ ጋር በማመሳከር የተመዝጋቢዋ መረጃ በትክክል መስፈሩን ታረጋግጣለች፤

ሐ) ለመራጭነት ብቁ የሆነችን ሰው በተዘጋጀው የመራጮች መዝገብ ላይ በመመዝገብ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ ወዲያውኑ ለተመዝጋቢዋ ትሰጣለች፤

መ) በእስክሪቢቶ ወይም በጭቃ ቀለም ብቻ ሆኖ በግልፅ ሊነበብ በሚችል የእጅ ጽሑፍ እና ስርዝ ድልዝ በሌለበት ሁኔታ መራጮችን ትመዘግባለች፤

ሠ) የመራጮችን መዝገብና ቅጾች ምዝገባው እንዲከናወን በተወሰነበት የጊዜ ገደብ ሁሉ በሚገባ ትጠብቃለች፤

ረ) የመራጮች መዝገብን ጨምሮ ሌሎች የምዝገባ ሰነድና ቁሳቁስ በአግባቡ ተሰናድተው ያልተፈቀደላቸው ሰዎች በማይደርሱበት ቦታ መቀመጣቸውን ታረጋግጣለች፤

ሰ) በምርጫ ጣቢያ ሃላፊዋ ወይም በምርጫ ቦርድ ስልጣን የተሰጣት ሰው የምትሰጣትን ተጨማሪ ተግባራት ታከናውናለች።

3. የሰልፍ አስከባሪ

ሀ) በምርጫ ጣቢያው መግቢያ በር ላይ በመቆም መራጮች ለምዝገባ ሲመጡ የመራጭ ረዳት ከሆኑ ሰዎች በስተቀር በአንድ ወቅት አንድ ሰው ብቻ ወደ መዝገብ ሹሟ መሄዷን ማረጋገጥ፤

ለ) ለመመዝገብ የሚመጡ መራጮችን እየፈተሸች ታስገባለች፡፡ ወደ ምርጫ ጣቢያ ይዞ መግባት የተከለከሉ የጦር መሳሪያና ስለት ያላቸው ነገሮችን መራጮች ይዘው እንዳይገቡ ትከለክላለች፤

ሐ) ለመመዝገብ የሚጠባበቁ መራጮች በምርጫ ጣቢያው መግቢያ ላይ በአግባቡ መሰለፋቸውን እንዲሁም ከተመዘገቡ በኂላ ወዲያውኑ ከጣቢያው መውጣታቸውን ታረጋግጣለች፤ የምርጫ ጣቢያውን ስራ የሚያውክ ሁኔታ ሲፈጠር ለምርጫ ጣቢያ ሃላፊዋ ወዲያውኑ ሪፖርት ታደርጋለች፤

መ) በምርጫ ጣቢያ ሃላፊዋ ወይም በምርጫ ቦርዱ ስልጣን የተሰጣት ሰው የምትሰጣትን ተጨማሪ ተግባራት ታከናውናለች፡፡

**አንቀፅ 9. የምዝገባ የጊዜ ሠሌዳ**

1. የጠቅላላ ምርጫ ምዝገባ በአገር አቀፍ ደረጃ ቦርዱ በሚወስናቸው ቀናት የሚጀመርና

የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡

2. ቦርዱ የሚመለከታቸውን ክልሎች ህገ መንግስት ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ህጎች መነሻ በማድረግ የአካባቢ ምርጫዎችን የምዝገባ ጊዜ ሰሌዳ ያወጣል፡፡
3. ቦርዱ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) እና (2) መሰረት የምዝገባ ቀናቱን ከመወሰኑ በፊት በምርጫው ከሚሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር እንደ አስፈላጊነቱም ከሲቪል ማህበራት፤ መገናኛ ብዙሃን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ይመካከራል፡፡
4. ቦርዱ የመራጮች ምዝገባ የሚጀምርበትን ዕለት በምርጫ የጊዜ ሰሌዳው በማካተት ምዝገባው ከመጀመሩ 15 ቀን በፊት ጀምሮ ባሉት ቀናት በተከታታይ በመገናኛ ብዙሃንና በሌሎች የማስታወቂያ መንገዶች አማካኝነት የምዝገባውን ሰሌዳ ለህዝቡ ይገልፃል፡፡
5. የመራጮች ምዝገባ ቦርዱ ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ቅዳሜ እና እሁድን ጨምሮ በፌደራል መንግስት ሕጎች የተደነገጉ የሕዝብ በዓላትን ሳይጨምር በመደበኛ የመንግሥት የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት መሰረት ይከናወናል፡፡
6. የምርጫ አስፈጻሚዎቹ የየክልሉን መደበኛ የሥራ ሰዓት በመከተል ለአንድ ሰዓት ብቻ ለምሳ ይወጣሉ፡፡
7. ቦርዱ በአንዳንድ ክልሎች ያለውን የመንግስት ስራ ሰአት አፈፃፀም ህጎች ግምት ውስጥ ማስገባት የሚያስፈልግ ሆኖ ሲያገኘው የተለየ የስራ ሰአት ሊወስን ይችላል፡፡

**አንቀፅ 10. ልዩ የምዝገባ ቀን**

1. ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መደበኛው የመራጮች ምዝገባ ቀናት ከመጠናቀቁ አንድ ሳምንት በፊት ተጨማሪ ልዩ የመራጮች ምዝገባ ቀን እንዲኖር ሊወስን ይችላል፡፡
2. በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያስችላትን መስፈርት የምታሟላ ሆና በመመራጭነት ከመመዝገብ የሚያግድ እክል ያጋጠማት መራጭ ቦርዱ በሚወስነው ልዩ የምዝገባ ቀን ለመመዝገብ ልትጠይቅ ትችላለች፡፡
3. መራጯ ከመመዝገብ የሚያግድ እክል ገጥሚታል የሚባለው ከታች የተዘረዘሩት እና መሰል ያልታሰቡ ድንገተኛ ክስተቶች ሲፈጠሩ ነው፡-

   ሀ) መራጯ ኃላፊ የማትሆንበት ያልታሰቡና በሦስተኛ ወገን ድርጊት የተከሰቱ ድንገተኛ ደራሽ ነገሮች፤

   ለ) መራጯ ባልታሰበ ሁኔታ የሚደርስባት ከባድ አደጋ ወይም ጽኑ ሕመም፡፡

4. ማንኛውም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ያጋጠማትና በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያስችላትን መስፈርት የምታሟላ መራጭ ለምርጫ ጣቢያው ሃላፊ አስፈላጊውን የፅሁፍ ወይም የሰው ማስረጃ አቅርባ መመዝገብ ትችላለች፡፡

5. በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚቀርብ አቤቱታ የመራጮች ምዝገባ ከተጠናቀቀ በኋላ ቦርዱ በሚወስነው ቀን የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

6. ቦርዱ በዚህ አንቀፅ መሠረት ልዩ የምዝገባ ቀን ከወሰነ፤

   ሀ) መራጮችን ጨምሮ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት አመቺ በሆነ ማስታወቂያ ይገልፃል፡፡

   ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ውሳኔው ሲደርሳቸው የምርጫ ጣቢያዎች

ቦርዱ ባወጣው መመሪያ መሠረት በልዩ የምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ እንዲመዘገቡ የተፈቀደላቸው መራጮችን ከመራጮች መዝገብ መጨረሻ ላይ የምርጫ አስፈጻሚዎችና ወኪሎች ተፈራርመው ከተዘጋው ገጽ ቀጥሎ ባለው ገጽ ላይ ተመዘግበው የልዩ ምዝገባ ሰሌዳው ሲያልቅ አስፈፃሚዎቹ ተፈራርመውበት ይዘጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የምዝገባ ቀሳቁስ ስርጭትና ጥበቃ

### አንቀፅ 11. ስለሰነዶች ስርጭትና የመራጮች ምዝገባ ቅድመ ዝግጅት

1. ቦርዱ ለመራጮች ምዝገባ የሚያገለግል ሰነድና ቁሳቁስ ከመራጮች ምዝገባ ከሚጀመርበት ዕለት አምስት ቀናት ቀደም ብሎ በየምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤቶች እንዲደርስ ያደርጋል፡፡
2. የምርጫ ክልል ጽ/ቤት የመራጮች ምዝገባ ሰነዶችና ቁሳቁስ ቦርዱ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የመራጮች ምዝገባ ከሚጀመርበት ዕለት ሁለት ቀናት ቀደም ብሎ በየምርጫ ጣቢያ እንዲደርስ ማድረግ አለባቸው::
3. ቦርዱ ስለመራጮች ምዝገባ በየደረጃው ላሉ የምርጫ አስፈፃሚ አካላት በቂ ስልጠና ይሰጣል።

### አንቀፅ 12. ስለምርጫ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ርክክብ

እያንዳንዱ የምርጫ ክልል ለመራጮች ምዝገባ የተላኩ ሰነዶችን እና ሌሎች የምርጫ ቁሳቁሶችን ተረክቦ ቦርዱ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ለየምርጫ ጣቢያዎቹ በጥንቃቄ እና በአግባቡ መድረሱን ያረጋግጣል፤ ርክክቡም በቦርዱ በተዘጋጀ የመረካከቢያ ቅፅ ይፈፀማል፡፡

### አንቀፅ 13. ስለምርጫ ሰነዶችና ቁሳቁስ ጥበቃ

1. የምርጫ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ከቦርዱ ወደ የምርጫ ክልሉም ሆነ ወደ የምርጫ ጣቢያዎች ሲሰራጩ በየደረጃው የሚገኙ የምርጫ አስፈፃሚዎች ተገቢው የጥበቃና የጥንቃቄ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋሉ::
2. የምርጫ ክልል እና የምርጫ ጣቢያ የምርጫ አስፈፃሚዎች የመራጮች መዝገብ እንዲሁም የምርጫ ሰነዶች እና ቁሳቁሶችን ለመረከብ እና ለማስቀመጥ የሚያስችል ምቹ ቦታ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡
3. የምርጫ ክልል እና የምርጫ ጣቢያ ምርጫ አስፈፃሚዎች የመራጮች መዝገብ፣ እንዲሁም የምርጫ ሰነዶች እና ቁሳቁሶችን ያለፈቃድ እና አላግባብ እንዳይነካኩ፣ እንዳይበላሹ፣ እንዳይቃጠሉ፣ እንዳይሰረቁ እና እንዳይከፋፈቱ ጥበቃው አስተማማኝ በሆነ ቦታ በጥንቃቄ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡
4. የመዝገብ ሹሟ በኃላፊነቷ ሥር ያሉ ሁሉንም የምዝገባ ቁሳቁሶች በየቀኑ በአግባቡ በማሸግ እንዲቀመጡ ታደርጋለች፤
5. የመራጮች ምዝገባና የመራጮች መዝገብ ለሕዝብ ግልጽ የማድረጊያ ጊዜ ሲጠናቀቅ የመራጮች ምዝገባ ቁሳቁሶች በቦርዱ በተዘጋጀ መረካከቢያ ቅፅ መሰረት በምርጫ ጣቢያው ሃላፊና የምርጫ ክልል ሃላፊ ርክክብ ተደርጎ በምርጫ ክልል ጽህፈት ቤት እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡
6. የምርጫ ምዝገባ ማስፈሚያ መሳሪያ፣ ቁሳቁስ፣ እንዲሁም ሰነዶች አያያዝ፣ ርክክብና አወጋገድ ዝርዝር ይህንኑ በተለይ በሚመለከተው የቦርዱ መመሪያ መሠረት ይፈጸማል፡፡

## ክፍል አራት
## የምዝገባ ቅድመ ዝግጅት

### አንቀፅ 14. የመራጮች ምዝገባ ቦታ

1. የመራጮች ምዝገባ የሚከናወነው የመራጮችን መደበኛ መኖሪያ መሰረት በማድረግ በምርጫ ህጉ መሠረት በቦርዱ በሚቋቋም የምርጫ ጣቢያ ነው::
2. ከምርጫ ጣቢያ ውጪ ቤት ለቤትም ሆነ በተመሳሳይ ቦታ እየተዘዋወሩ የመራጮች ምዝገባ ማከናወን የተከለከለ ነው::
3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2) የተደነገገው ቢኖርም ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የአርብቶ አደሩን አኗኗር መሰረት ያደረገ ተንቀሳቃሽ የምርጫ ጣቢያ ሊያቋቁም ወይም ቤት ለቤት በመሄድ የመራጮች ምዝገባ እንዲከናወን ሊወስን ይችላል፡፡
4. የምርጫ ጣቢያዎች የአካል ጉዳተኞችን ልዩ ሁኔታ፣ ለመራጮች ምዝገባ እና ለሌሎች የምርጫ ተግባራት ምቹነታቸው፣ አማካይ እና መራጩ በቀላሉ ሊያውቃቸው የሚችሉ መሆናቸውን ጨምሮ የተለያዩ ታሳቢዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ቦርዱ በሚወስነው ስፍራ በምርጫ አስፈጻሚዎች ተመቻችተው የሚቋቋሙ ይሆናል፡፡
5. የመራጮች ምዝገባ የሚከናወንበት ቦታ የመራጮች ምዝገባ ከመጀመሩ 15 ቀናት አስቀድሞ ለመራጩ ህዝብ እና ለተወዳዳሪዎች ይፋ መደረግ አለበት::
6. በማንኛውም ምርጫ አንድ ምርጫ ጣቢያ የሚያስተናግደው የመራጮች ብዛት ከአንድ ሺህ አምስት መቶ መብለጥ የለበትም::
7. ልዩ የምርጫ ጣቢያዎችን እንዲሁም ተንቀሳቃሽ የምርጫ ጣቢያዎችን በተመለከተ በምርጫ ሕጉና እነዚህን በሚመለከቱ መመሪያዎች ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለአንድ የምርጫ ጣቢያ በተከለለ አካባቢ ከአንድ የምርጫ ጣቢያ በላይ ማቋቋም አይቻልም::
8. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (7) ስር የተደነገገው ቢኖርም፣ በአንድ ምርጫ ጣቢያ ከአንድ ሺህ አምስት መቶ በላይ መራጮች የተገኙ እንደሆነ አዲስ የምርጫ ጣቢያ ተቋቁሞ የመራጮች ምዝገባው ይቀጥላል፡፡
9. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (7) ስር የተደነገገው ለልዩ የምርጫ ክልሎች በሚቋቋሙ እና በህግ በተለዩ ተቋማት በሚቋቋሙ ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም::
10. ቦርዱ ለምርጫው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የምርጫ ጣቢያ ቦታዎችን ሊለውጥ ይችላል፤ ለውጡንም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ለመራጩ ህዝብ፣ ለተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ ታዛቢዎች፤ የመራጮች ትምህርት ለሚሰጡ ሲቪክ ማህበራት እና ጋዜጠኞች ይፋ ማድረግ አለበት፡፡ ቦርዱ ይህንን የሚመለከት የአሰራር ስርአት ሊዘረጋ ይችላል ፡፡

### አንቀፅ 15. የመራጮች ምዝገባ ቦታ በመሆን የማያገለግሉ ቦታዎች

በልዩ ሁኔታ የሚቋቋሙ ምርጫ ጣቢያዎች መመሪያ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በሚከተሉት ቦታዎች የመራጮች ምዝገባ ጣቢያ ማቋቋም አይቻልም፤

1. ወታደራዊ ካምፖች፣
2. የፖሊስ ጣቢያዎች፣
3. ቤተክርስቲያናት፣
4. መስጊዶች፣
5. ሌሎች የእምነት ቦታዎች፣
6. ሆስፒታሎችና በየደረጃው ያሉ ሌሎች የሕክምና ተቋማት፣

7. ሆቴሎች፣ ምግብ ቤቶችና መጠጥ ቤቶች፣
8. የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የሃይማኖት ድርጅቶች ህንፃዎች እና
9. የግል መኖሪያ ቤቶች::

## አንቀፅ 16. የምርጫ ጣቢያ ዝግጅት

1. የምርጫ ጣቢያ የምርጫ አስፈፃሚዎች ለምርጫ ጣቢያነት የተመረጠውቦታ ለመራጮች ምዝገባ ምቹ እንዲሆን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ዝግጅት ያደርጋሉ፤

   ሀ) መግቢያና መውጫው የተለያየ የመራጮች መመዝገቢያ ቤት ወይም ድንኳን ወይም ዳስ ያዘጋጃሉ::

   ለ) የመዝገብ ሹም፣ ታዛቢዎች እና የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት አቀማመጥ ፊት ለፊት ሆኖ ተመዝጋቢዎች ወደ መመዝገቢያው ቦታ ሲገቡ እና ከምዝገባ ቦታው ሲወጡ እንዲሁም የምዝገባውን ሂደት በግልፅ በማየትና በመስማት ሊታዘቡ የሚችሉበትን አቀማመጥ ያመቻቻሉ።

   ሐ) መራጮች ለመመዝገብ ሲመጡ ተራ የሚጠብቁበት ከፀሐይና ዝናብ መከለያ ቦታ ያዘጋጃሉ።

2. የምርጫ ክልል አስፈፃሚዎች የመራጮች ምዝገባ ከሚጀመርበት ዕለት 3 ቀናት አስቀድመው፣

   ሀ) የመራጮች ምዝገባ የሚካሄድበትን የምርጫ ጣቢያ በግልፅ ማወቅ ይችሉ ዘንድ አስፈላጊው ማስታወቂያ ለዚሁ በተዘጋጀ ወረቀት ላይ በጉልህ ተጽፎ በምርጫ ጣቢያው እንዲሰቀል ያደርጋሉ፤

   ለ) ከዚህ በተጨማሪ በቦርዱ የመራጮች ትምህርት መርሀግብር አማካይነት ተጨማሪ መረጃ ለመራጮች እንዲደርስ ያደረጋሉ።

3. የምርጫ ጣቢያ አስፈፃሚዎች ለመራጮች ምዝገባ የሚያስፈልጉ የመራጮች መዝገብ፣ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ እንዲሁም የማህተም መርገጫ እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች እና ቁሳቁሶች በበቂ ሀኔታ መኖራቸውን ያረጋግጣሉ፤
4. ያልተሟሉ ቁሳቁሶች ሲኖሩ የምርጫ ጣቢያው ሃላፊ ቁሳቁሶቹ እንዲሟሉ ጥያቄውን ለምርጫ ክልሉ ፅህፈት ቤት ወዲያውኑ ታቀርባለች።

## አንቀፅ 17. የመራጮች መዝገብ ዝግጅት

1. እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ በምርጫ ህጉ መሠረት ለምርጫ አስፈጻሚዎች አያያዝና አጠቃቀም ቀላል የሆነ እንዲሁም ስህተቶች እንዳይፈጠሩ የሚያግዝ የመራጮች መዝገብ ይኖረዋል፤
2. የመራጮች መዝገቡ በምርጫ ሕጉ የተጠየቁ መረጃዎችን ጨምሮ ቦርዱ ለምርጫ ሂደቱ ጠቃሚ የሚላቸውን ተጨማሪ መረጃዎች ያካተቱ ዐምዶች አስቀድሞ የታተሙበት ይሆናል፤
3. የመራጮች መዝገብ ከመራጮች ምዝገባ መጀመሪያ ቀን በፊት መዘጋጀት አለበት፤
4. የመዝገቡ የፊት ሽፋን ገፅ ላይ የክልሉ፣ የምርጫ ክልሉ፣ የወረዳው፣ የቀበሌው፣ የምርጫ ጣቢያው መጠሪያ እና የምርጫ ጣቢያው መለያ ቁጥር ይመዘገባል፤

**አንቀፅ 18. በመራጮች ምዝገባ ቦታ መገኘት የሚችሉ ሰዎች**

1. በመራጮች ምዝገባ ቀናት የሚከተሉት ሰዎች በምርጫ ጣቢያው መገኘት ይችላሉ፤
   ሀ) በቦርዱ እውቅና የተሰጣቸው ተዘዋዋሪ ወይም ተቀማጭ የምርጫ ታዛቢዎች፣

   ለ) በቦርዱ እውቅና የተሰጠቸው የመገናኛ ብዙኃን አባላት፤

   ሐ) የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፤

   መ) በቦርዱ የተመደቡ እና ማረጋገጫ ያላቸው የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰራተኞች፤

   ሠ) በቦርዱ እውቅና የተሰጣቸው የፖለቲካ ፓርቲ እና የግል እጩ ወኪሎች፤

   ረ) በመራጭነት ለመመዝገብ የሚመጡ አካል ጉዳተኞችን የሚያግዙ ረዳቶች፤

2. በንኡስ አንቀፅ አንድ መሰረት በመራጮች ምዝገባ ወቅት መገኘት የሚችሉ ሰዎች ባይገኙም የመራጮች ምዝገባ ሂደት በተያዘው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ይከናወናል::

## ክፍል አምስት
## የመራጮች ምዝገባ አፈጻጸም

**አንቀፅ 19. በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያበቁ መመዘኛዎች**

1. ማንኛዋም ሰው በመራጭነት ለመመዝገብ በምርጫ አዋጁ አንቀጽ 18 መሠረት የሚከተለውን ማሟላት ይኖርባታል፤

   ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሆነች፣

   ለ) በምዝገባው ዕለት እድሜዋ 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ እና

   ሐ) በምርጫ ክልሉ ቢያንስ ለ6 ወር የኖረች።

**አንቀፅ 20. በመራጭነት ለመመዝገብ የሚቀርቡ ማስረጃዎች**

1. አንድ በመራጭነት ለመመዝገብ ብቁ የሆነች ሰው እንደ ሁኔታው ከሚከተለው አንዱን ማስረጃ በምትኖርበት አካባቢ ለሚገኝ ምርጫ ጣቢያ በማቅረብ በመራጭነት መመዝገብ ትችላለች፤
   ሀ) ተመዝጋቢዋ በምትኖርበት የምርጫ ጣቢያ ማንነቷን የሚገልፅ የቀበሌ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ።

   ለ) የቀበሌ መታወቂያ ካርዱ ወይም ፓስፖርቱ ያልታደሰ ቢሆንም እንኳን ለምዝገባ ሊያገለግል ይችላል። ነገር ግን የካርዱ ዕድሳት ጊዜ ከአምስት አመት በላይ ያለፈ ከሆነ ሌላ ማረጋገጫ ማቅረብ ይጠበቅበታል።

ሐ) የቀበሌ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ማቅረብ ካልቻለች የቅርብ ፎቶግራፍ ተደርጎበት የተሰጠ እንደ መንጃ ፈቃድ፣ የመኖሪያ የምስክር ወረቀት፣ ከውትድርና የተገለለችበት ሰነድ፣ የትምህርት ቤት መታወቂያ፣ የሰራተኛነት መታወቂያ የመሳሰሉ የመለያ ማስረጃዎች በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያስችሉ ሰነዶች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

2. ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ማስረጃዎች በማይኖሩበት ወቅት፤

ሀ) ከምርጫ አስፈጻሚዎቹ ሁለቱ መራጯን ለይተው የሚያውቋት ከሆነ በአስፈጻሚዎቹ ምስክርነት ወይም፣

ለ) በገጠር አካባቢ ሲሆን በባሕላዊና በልማዳዊ ዘዴ ተመዝጋቢዋን ለመለየት የሚቻልበት ሁኔታ ካለ ባሕሉን የሚያውቁ ሁለት ሰዎች ለምርጫ ጣቢያው ሰብሳቢ በሚሰጡት ምስክርነት ቃለ ጉባኤ ተይዞ እና በቃለ ጉባዔው ላይ የምርጫ ጣቢያው አስፈጻሚዎች ተፈራርመውበት ምዝገባው ይከናወናል፡፡

ሐ) የተመዝጋቢዋ እድሜ 18 ዓመት ስለመሆኑ የሚቀርብ ማስረጃ ሳይኖርና ወይም ጥርጣሬ ሲኖር በተመዝጋቢዋ ቤተሰብ አንጋፋ አባል ወይም ዘመድ፣ እነሱ ከሌሉ ስለግለሰቧ የሚያውቁ ሁለት ሰዎች ለምርጫ ጣቢያው ሰብሳቢ በሚሰጡት የምስክርነት ቃል በማረጋገጥ ሂደቱ በቃለ ጉባዔ ተይዞ ሊመዘገብ ይችላል፡፡

መ)የሚሰጠውን ምስክርነት የምርጫ ጣቢያው ሃላፊ ትሰማለች፤ በቃለ ጉባዔው ላይ የምርጫ ጣቢያው አስፈጻሚዎች ይፈራረሙበታል፡፡

3. የምርጫ ጣቢያው በተቋቋመበት ቀበሌ ለረዥም ጊዜ በመደበኛነት መኖራቸው በሰነድ የተረጋገጠ ሦስት ግለሰቦች በሚሰጡት ምስክርነት የሰነድ ማስረጃ አልባዋን ተመዝጋቢ ለመለየት ከተቻለ ሂደቱ ቦርዱ በሚያዘጋጀው የቃለ ጉባዔ ላይ የምርጫ ጣቢያው አስፈጻሚዎች ተፈራርመውበት ምዝገባው ሊከናወን ይችላል፡፡
4. ስለመራጭ ማንነት፣ ነዋሪነት ወይም ሌላ ሁኔታ ማንኛውም ዓይነት ምሥክርነት የምትሰጥ ሰው፡-

    ሀ) በመራጭነት የተመዘገበች፣

    ለ) እጩ ተወዳዳሪ  ወይም የእጩ ተወካይ ያልሆነች መሆን ይኖርባታል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ከተመለከቱት ማረጋገጫዎች በአንዱ ብቻ የመራጩን ማንነትና የነዋሪነት ቆይታ ማረጋገጥ ያልተቻለ እንደሆነ መዝጋቢዎች ከአንድ በላይ መስፈርቶችን በመጠቀም ያረጋግጣሉ፡፡

**አንቀፅ 21. በመራጭነት ሊመዘገቡ ስለማይችሉ ሰዎች**

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሰዎች በመራጭነት ሊመዘገቡ አይችሉም፤

1. ኢትዮጵያዊ ዜጋ ያልሆነች፣
2. በምዝገባው ዕለት ዕድሜዋ ከ18 ዓመት በታች የሆነች፣

3. በአዕምሮ ህመም ምክንያት የመወሰን አቅም የሌላት ስለመሆኑ በታወቀ ሕክምና ተቋም ወይም በፍርድ ቤት የተረጋገጠባት ሰው፣
4. የመምረጥ መብቷ በህግ መሠረት በፍርድ ቤት ውሳኔ የተገደበባት ሰው::

**አንቀፅ 22. የአመዘጋገብ ስርዓት**

1. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) ስር ከተጠቀሱት መራጮች በስተቀር ለመራጭነት ብቁ የሆነች ሰው እንደ አመጣጧ ተራዋን ጠብቃ መዝገብ ሹሟ ፊት በመቅረብ በመራጮች መዝገብ ላይ በጥንቃቄ እንድትመዘገብ ይደረጋል::
2. ለምዝገባ የቀረበች ሰው መዝጋቢዎች ግላዊ መረጃዋን በተመለከተ የሚጠይቋትን ጥያቄ በትክክል መመለስ አለባት:: የሰጠችው እያንዳንዱ መረጃም በተዘጋጀው የመራጮች መዝገብ ላይ በጥንቃቄ ይሰፍራል፡፡
3. ለመመዝገብ ብቁ የሆኑና አቅም ደካሞች፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ ነፍሰ ጡሮች፣ የሚያጠቡ እንዲሁም ጨቅላ ሕፃናት የያዙ ወላጆች እራሳቸው በወሰኑት ረዳት አማካኝነት በአካል ተገኝተው ተራ ሳይጠብቁ ለምርጫ ጣቢያው ሀላፊ በማሳወቅ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ይመዘገባሉ::
4. ለአቅመ ደካሞች፣ ለዓይነ ስውራን ወይም ማንበብና መጻፍ ለማይችሉ ሰዎች ረዳት የሆነች ሰው፤

   ሀ) እድሜዋ 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ እና

   ለ) እጩ ተወዳዳሪ፣ የእጩ ተወካይ ወይም የምርጫ ታዛቢ ያልሆነች መሆን ይኖርባታል፡፡

   ሐ) ረዳት የሚፈልጉ ሰዎች የራሳቸውን ረዳት ሳይዙ የመጡ ከሆነ የምርጫ አስፈጻሚዋ ለመመዝገብ ከመጡ መራጮች መካከል ፈቃደኛ የሆነች ሰው ጠይቃ እንድታግዝ ታደርጋለች፡፡

5. የመዝገብ ሹሟ መራጯን ስትመዘግብ በምርጫ ጣቢያው የሚገኙ ታዛቢዎች እና ተመዝጋቢዋ ለመስማት በሚችሉበት ሁኔታ ድምጹዋን ከፍ አድርጋ መረጃዎቹን አንድ በአንድ ደግማ በመናገር ዝርዝሩን በመራጮች መዝገብ ላይ ታሰፍራለች፡፡
6. መራጮች ከተመዘገቡ በኋላ በመራጮች መዝገቡ ላይ በስማቸው ትይዩ እንደ ችሎታቸው በጽሁፍ ወይም በጣት አሻራ እንዲፈርሙ ወይም ጣቶች የሌሏት ሰው ከሆነች መዝጋቢዋ በመራጮች መዝገቡ ልዩ አስተያየት አምድ ላይ ይህንኑ ትጽፋለች፡፡

**አንቀፅ 23. አንድ ጊዜ እና አንድ ቦታ ብቻ በግንባር ስለመመዝገብ**

1. ማንኛዋም መራጭ በአንድ ምርጫ ጣቢያ ከአንድ ጊዜ በላይ ወይም በሌላ የምርጫ ጣቢያ ድጋሚ መመዝገብ የለባትም::
2. የመራጭነት ምዝገባ ልዩ የመራጮች ምዝገባን ጨምሮ የሚካሄደው በግንባር በመቅረብ ብቻ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 24. ስለመራጮች የምዝገባ መታወቂያ ካርድ

በመራጭነት የተመዘገበች ሰው፤

1. የመራጭነት ምዝገባ መታወቂያ ካርድ ይሰጣታል።
2. እያንዳንዱ የመራጭነት ምዝገባ መታወቂያ ካርድ መራጮች በመራጮች በመዝገብ ላይ ከተመዘገቡ በኋላ ከመዝገቡ ጋር እየተገናዘቡ የሚሞሉ የሚከተሉት አምዶች ይኖሩታል፤
   ሀ) የመራጯ ስም ከነአያቷ፣

   ለ) የምትኖርበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ ምርጫ ጣቢያ፣ የቤት ቁጥር፣ መንደር ወይም ጎጥ፤

   ሐ) የመዝገብ ቁጥር፣ የመዝገብ ተራ ቁጥር፣ የመራጭ መለያ ቁጥር እና የመዝገብ ገጽ፤

   መ) የመራጯ ዕድሜ፤

   ሠ) የመራጯ የምልክት ወይም የአውራ ጣት ፊርማ፣ የመዝጋቢዋ ፊርማ እና

   ረ) የተመዘገበችበት ቀን።
3. አንድ መራጭ አንድ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ ብቻ ይኖረዋል።
4. ለምርጫ የተመዘገበች ሰው በድምፅ መስጫው ዕለት የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርዷን ይዛ ወደ ምርጫ ጣቢያ መምጣት አለባት።
5. የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ የጠፋባት መሆኑን በማስረጃ ያረጋገጠች ወይም የተበላሸባት መራጭ የመራጮች ምዝገባ እየተካሄደበት ባለበት ጊዜ፣ የመራጮች መዝገብ ለሕዝብ ግልጽ በሚደረግበት ጊዜ ወይም በምርጫው ቀን በማንኛውም የምርጫ ጣቢያው የሥራ ጊዜ የምርጫ ጣቢያው ምትክ ካርድ እንዲሰጣት ማመልከት ትችላለች።
6. መመዝገቧ ከምርጫ ጣቢያው መዝገብ ከተረጋገጠ በኋላ በቃለ ጉባዔ ተይዞ በምትኩ ሌላ ካርድ ይሰጣታል ወይም አቤቱታው የቀረበው በምርጫው ቀን ሲሆን ድምጽ እንድትሰጥ ይደረጋል። በመራጮች መዝገብ ላይ ቀድሞ የተሰጣት ካርድ ቀሪ ኮፒ ላይ ውድቅ የተደረገ ተብሎ ምልክት ይደረግበታል። የተበላሸውን ካርድ ይዛ ከቀረበችም እንድትመልስ ይደረጋል።

## አንቀፅ 25. የመራጮች መዝገብ ይዘት

1. የመራጮች መዝገብ የሚከተሉትን መረጃዎች ለመሙላት የሚያስችሉ አምዶች ይኖሩታል፤
   ሀ) የመዝገብ ተራ ቁጥር፣

   ለ) የመራጭ መለያ ቁጥር፣

   ሐ) የምዝገባ ቀን፣

   መ) የተመዝጋቢዋ ሙሉ ስም ከነአያት፣

   ሠ) የምስክርነት ቃል የተሰጠ እንደሆነ፣

ረ) የተመዝጋቢዋ ፆታ፣

ሰ) የተመዝጋቢዋ ዕድሜ፣

ሸ) የተመዝጋቢዋ የትውልድ ቀን እና ዓ.ም፣

ቀ) አካል ጉዳተኝነት፣

በ) የአካል ጉዳተኝነት ዓይነት፣

ተ) የቤት ቁጥር፣ መንደር ወይም ጎጥ፣

ቸ) በምርጫ ክልሉ የኖረበት ጊዜ፣

ኀ) የምዝገባው ዕለት የጽሕፈት ወይም የአውራ ጣት ወይም በሌላ ምልክት ፊርማ፣

ነ) የምርጫው ዕለት የጽሕፈት ወይም የአውራ ጣት ወይም በሌላ ምልክት ፊርማ፣ እና

ኘ) ልዩ አስተያየት፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1)(መ)፣ (ረ)፣ (ሰ)፣ (ሸ)፣ (ቀ)፣ (በ)፣ (ተ) እና (ቸ) የተደነገገው በመራጮች ምዝገባ ወቅት ለመመዝገብ የመጣችን ነዋሪ በመጠየቅ እና ማስረጃውን በማየት የሚሞላ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1(ነ) የተደነገገው በድምፅ መስጫው ዕለት መራጯ የምትፈርምበት አምድ ነው፡፡

## አንቀፅ 26. በምርጫ ጣቢያው በየዕለቱ ምዝገባ ማጠናቀቂያ ላይ ስለሚያዝ ቃለ ጉባዔ

1. የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዎች ለምሳ ሲወጡና ሲመለሱ እንዲሁም የቀኑ የመራጮች ምዝገባ ሥራ እንደተጠናቀቀ የመራጮች መዝገብ፤

ሀ) መጨረሻ የተመዘገበው መራጭ መለያ ቁጥር፣

ለ) ቀን፣ ወር እና ዓመተ ምህረት

ሐ) ክልል፣

መ) የምርጫ ክልል፣

ሠ) ወረዳ፣

ረ) ቀበሌ፣

ሰ) የምርጫ ጣቢያ ስም፣

ሸ) የምርጫ ጣቢያ መለያ ቁጥር፣

ቀ) የማሽጊያው ቁጥሮች፣

በ) የመዝጊያ ሰዓት እና

ተ) የመክፈቻ ሰዓት በመመዝገብ ቦርዱ በሚያዘጋጀው የመፈራረሚያ ቅፅ ላይ ይሞላል፡፡

2. በቅፁ ላይ የምርጫ ጣቢያው የምርጫ አስፈጻሚዎች በየቀኑ ይፈራረሙበታል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ መሠረት የተያዘና የተፈረመው ቅፅ በምርጫ ጣቢያው በጥንቃቄ ይያዛል፡፡
4. ምርጫ አስፈፃሚዎች ለምሳ ሲወጡና ከምሳ ሲመለሱ የምርጫ ጣቢያውንና የምርጫ ሰነዶች ባሉበት ሁኔታ አሽገው ይወጣሉ፤ ሲመለሱ እሽጉን ከፍተው ቃለ ጉባኤ ይፈራረማሉ፡፡
5. በዚህ መሰረት የምርጫ አስፈፃሚዎች፤ ታዛቢዎችና የተወዳዳሪዎች ወኪሎች የምርጫ ጣቢያው ሲከፈት፤ ለምሳ ሲወጡ፤ ከምሳ ሲመለሱ እና ምዝገባ ሲጠናቀቅ በቦርዱ በተዘጋጀ የቃለጉባኤ መያዣ ቅፅ ላይ ይፈራረማሉ፡፡ በቃለ ጉባኤው ይዘት የተለየ ሃሳብ ያለው ሰው ልዩነቱን መዝግቦ ፊርማውን ያሰፍራል፡፡

## አንቀፅ 27. የመደበኛው የመራጮች መዝገብ አዘጋግ

1. በመራጮች መደበኛ ምዝገባ ማጠናቀቂያ ዕለት እና የመራጮች ምዝገባ ሰዓት እንዳበቃ፤ በመራጮች መዝገብ ላይ የሚካሄደው ምዝገባ ይቆማል፡፡
2. መዝገቡ ከዚህ ቀጥሎ በቅደም ተከተል የተዘረዘረው ሁኔታ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ይዘጋል፤
3. የመራጮች ምዝገባ ሲጠናቀቅ በመዝገቡ ላይ በመጨረሻ ተራ ቁጥር ከተመዘገበው ስም ቀጥሎ ያሉትን መመዝገቢያ መስመሮች ከግራ ወደቀኝ በዚግዛግ መስመር በማያያዝ ይዘጋል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ፦

ሀ) ጠቅላላ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር፣

ለ) የተመዘገቡ ሴት መራጮች ቁጥር፣

ሐ) የተመዘገቡ ወንድ መራጮች ቁጥር፣

መ) ክልል፣

ሠ) የምርጫ ክልል፣

ረ) ወረዳ፣

ሰ) ቀበሌ፣

ሸ) የምርጫ ጣቢያ ስም፣

ቀ) የምርጫ ጣቢያ መለያ ቁጥር፣

በ) ቀን፥ወር እና ዓመተ ምህረት፣

ተ) መጨረሻ የተመዘገበው መራጭ መለያ ቁጥር፣

ቸ) የተበላሹ የመራጭ መታወቂያ ካርዶች ብዛት፣

ኀ) የምስክርነቶች ቁጥር፣

ነ) የአቤቱታዎች ቁጥርን

በመለየት ቦርዱ በሚያዘጋጀው የመተማመኛ ቅፅ ላይ ይሰፍራል፤ የምርጫ ጣቢያው ሰብሳቢ ስምና ፊርማ ያርፍበታል።

5. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (3)መሠረት የተለየውን መራጭ ብዛት በዚግዛግ ከተዘጋው መዝገብ መጨረሻ ገፅ ጀርባ ላይ "ወንድ_____ ሴት_____ ድምር _____" በሚል በመመዝገብ እና በቃለ ጉባኤው ላይ በመሙላት የምርጫ አስፈፃሚዎች ይፈራረሙበታል።
6. ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነና አመቺ በሆነ ማስታወቂያ ለሚመለከታቸው ምርጫ ጣቢያዎች ካልገለፀላቸው በስተቀር በዚህ አንቀፅ መሠረት ተዘግቶ የምርጫ አስፈፃሚዎች ከፈረሙበት በኋላ በመራጮች መዝገብ ላይ አዲስ መራጮች አይመዘገቡም፣ የሚሰፍር ወይም የሚፃፍ ነገር አይኖርም።
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመራጭ ምዝገባን በተመለከተ በሚነሱ ክርክሮች ላይ የምርጫ ጣቢያ ወይም የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት እንደ አግባብነቱ የምርጫ ጣቢያ ወይም የምርጫ ክልል ፅህፈት ቤት የመሰረዝ ወይም የመመዝገብ ስራውን ያከናውናል።
8. የመራጮች ምዝገባን በተመለከተ የፍርድ ቤት ውሳኔ ቅጂ ይዞ የቀረበ መራጭ የድምፅ አሰጣጥ ቆጠራና ውጤት አፈፃፀም መመሪያ ላይ በተቀመጠው መሰረት በቀጥታ ድምጽ እንዲሰጥ ይደረጋል።
9. የመራጮች ምዝገባ በተጠናቀቀበት ዕለት በአንቀፅ 27 ንኡስ አንቀፅ (4) መሰረት ከሚያዘው መተማመኛ በተጨማሪ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (5) መሠረት በየመዝገቡ ላይ ከተሞላው ማጠቃለያ ድምር ቀጥሎ የምርጫ አስፈፃሚዎች ይፈራረሙበታል።
10. የግል እጩዎች ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች፣ የመገናኛ ብዙሃን ተወካዮች፣ እንዲሁም ታዛቢዎች የመራጮች መዝገብ አዘጋግ ሂደትን ጨምሮ መታዘብ ይችላሉ።

**አንቀፅ 28. የመራጮች ልዩ መዝገብ አዘጋግ**

በዚህ መመሪያ አንቀፅ 11 መሠረት ቦርዱ በወሰነው ልዩ የመራጮች ምዝገባ ቀን መራጮች ከተመዘገቡ በኋላ የመራጮች ልዩ መዝገብ በሚከተለው ሁኔታ ይዘጋል፤

1. ልዩ ምዝገባው የሚጠናቀቀው እና መዝገቡ የሚዘጋው ቦርዱ ባወጣው የጊዜ ሠሌዳ መሠረት በልዩ ምዝገባ ማጠናቀቂያ ዕለትና ሰዓት ይሆናል።
2. የልዩ ምዝገባ መራጮች መዝገብ አዘጋግ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 27 ለመራጮች መደበኛ

መዝገብ አዘጋግ በተደነገገው መሠረት ይሆናል::

## አንቀፅ 29. የመራጮችን መዝገብ ለህዝብ ግልፅ ስለማድረግ

1. የመራጮች ምዝገባ እንደተጠናቀቀ የመራጮች መዝገብ በምርጫ ጣቢያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ለተከታታይ 10 ቀናት ይፋ ሆኖ ህዝብ በግልፅ እንዲያየው ይደረጋል፡፡
2. የመራጮችን መዝገብ ለመመልከት የምትቀርብ ሰው የመራጭነት ምዝገባ ካርዷን እና የማንነት መታወቂያ ካርድ ወይም ማንነቱዋን የሚያውቅ ምስክር ማቅረብ አለባት::
3. የመራጮች መዝገብ ህዝብ በግልፅ እንዲያየው የሚደረገው በሚከተለው አሰራር ይሆናል፤

   ሀ) የመራጮችን መዝገብ ህዝቡ በግልፅ እንዲያይ የሚያደርጉት በምርጫ ጣቢያው የመዝገብ ሹም ሆነው የተመደቡት የምርጫ አስፈፃሚ አባላት ናቸው::

   ለ) የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ መዝገቡን ለመመልከት የሚፈልጉትን ሰዎች እንዳመጣጣቸው ተራ በተራ ወደ መዝገቡ እየቀረቡ እንዲመለከቱ አስፈላጊ ሁኔታዎችን ታመቻቻለች፣ ታስፈፅማለች፡፡

   ሐ) የመራጮችን መዝገብ መመልከት የምትፈልግ ሰው ወደመዝገብ ሹም በመቅረብ የምትፈልገውን መረጃ ከመዝገቡ ለማየት የመዝገብ ሹሚን ትጠይቃለች፡፡ የመዝገብ ሹሚም የተጠየቀውን መረጃ ለሚመለከታት ሰው መዝገቡን በመግለፅ ታሳያለች፡፡

   መ) የመራጮችን መዝገብ የምትመለከት ሰው በመዝገብ ሹሚ አማካኝነት የምትፈልገው መረጃ ያለበትን ገጽ /ገፆች/ በዓይን ከማየት ወይም መረጃው ሲነበብላት ከማዳመጥና ማስታወሻ ከመያዝ ውጪ በእጇ መንካት፣ መዝገቡ ላይ መፃፍ፣ ምልክት ማድረግ፣ ወይም ፎቶግራፍ ማንሳት የተከለከለ ነው::

4. የመራጮች መዝገብ ህዝብ በግልፅ እንዲያየው ሲደረግ የምርጫ ታዛቢዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የግል እጩ ወኪሎች እና የምርጫ አስፈፃሚዎች ሊገኙ ይችላሉ፡፡
5. የመራጮች መዝገብ ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ይፋ ወጥቶ ቅዳሜ እና እሁድን እንዲሁም በዓላትን ጨምሮ ለ10 ተከታታይ ቀናት ህዝቡ በግልፅ እንዲያየው የሚደረገው በየዕለቱ በመንግሥት የሥራ ሰዓት ይሆናል::
6. የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ግልፅ የሚሆንባቸው ቀናት ሲጠናቀቅ፤

   ሀ) መዝገቡ ለ10 ተከታታይ ቀናት ህዝቡ እንዲያየው ስለመደረጉ፣

   ለ) ህዝቡ መዝገቡን ሲመለከት የጠየቀውን መረጃ ይዘት እና መረጃውን ስለማግኘት እና አለማግኘቱ በአጭሩ፣

   ሐ) የአካባቢው ነዋሪ የሆነች ሰው መዝገቡን አይታ ለአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ያቀረበችው አቤቱታ ካለ እና ስለተሰጠው መልስ በአጭሩ እንዲሁም መዝገቡ ለሕዝብ ግልፅ በሆነባቸው ቀናት የተገኙ ታዛቢዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የግል እጩ ወኪሎችን የሚመለከቱ መረጃዎች መተማመኛ ይዘጋጃል፡፡ የምርጫ አስፈፃሚዎች ከተፈራረሙበት በኂላ በሰነድነት ይያዛል፡፡

## አንቀጽ 30. በመራጭ አመዘጋገብ ሂደት የተፈፀመ ስህተት የሚስተካከልበት አግባብ

1. በመራጭነት የተመዘገበች ሰው የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ይፋ በሆነበት ጊዜ የግል

መረጃዋን በተመለከተ ስህተት አለ የሚል ቅሬታ ካላት እንዲስተካከልላት ለምርጫ ጣቢያው ማመልከት ትችላለች፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ስር የተጠቀሰው ማመልከቻ ለዚሁ አላማ በተዘጋጀ ቅጽ ላይ ተሞልቶ ከመራጪ የምዝገባ መታወቂያ ካርድ እና በመራጮች መዝገብ ላይ የሰፈረው መረጃ ትክክል እንዳልሆነ ከሚያስረዳ ማንኛውም ሰነድ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
3. ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ የምርጫ አስፈጻሚዋ ለምርጫ አስፈጻሚዎች በተዘጋጀው ምዝገባ ማኑዋል ላይ በተገለጸው አግባብ ማስተካከያውን ታደርጋለች፡፡

## አንቀፅ 31. ከምዝገባ ስለመሰረዝ

1. በመራጭነት የተመዘገበች ሰው በአዕምሮ ህመም ምክንያት ለመወሰን ብቃት የሌላት መሆኑ በባለሙያ ካልተረጋገጠ፣ ወይም በማጭበርበር የተመዘገበች፣ በድጋሚ የተመዘገበች፣ የሞተች ወይም አግባብ ባለው ህግ መሠረት በተሰጠ የፍርድ ቤት ውሳኔ የመምረጥ መብቷ የተገደበ መሆኑን የሚመለከት በማስረጃ የተረጋገጠ ተቃውሞ ካልቀረበባት በስተቀር ከመራጮች መዝገብ አትሰረዝም::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ሲከሰት ወይም ሲታወቅ እንደ የአግባብነቱ ፍርድ ቤቶች፣ የወሳኝ ኩነት ቢሮዎች፣ ሆስፒታሎች፣ እድሮች ወይም ሌሎች ስለጉዳዩ ዕውቀት ያላቸው የህብረተሰቡ አባላት ወዲያውኑ ለሚመለከተው፤

   ሀ) የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ወይም

   ለ) የምርጫ ክልል ወይም

   ሐ) የምርጫ ጣቢያ

   መ) መራጪ የተመዘገበችበትን የምርጫ ክልልና ጣቢያ ለይቶ በመግለፅ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለባቸው::

3. የእጩ ስረዛ የሚከናወነው በምርጫ ጣቢያ ሲሆን፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት መረጃ የደረሰው የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ወይም የምርጫ ክልል መረጃውን በተቻለ ፍጥነት ለምርጫ ጣቢያ እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) እና (3) መሰረት መረጃ የደረሰው ምርጫ ጣቢያ፡-

   ሀ) ተመዝጋቢውን ወዲያውኑ ከመራጮች መዝገብ ላይ ይሰርዘዋል፡፡

   ለ) ለተሰረዘው መራጭ ከመራጮች መዝገብ መሰረዙን እና ተቃውሞ ካለው ለምርጫ ጣቢያው የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ እንደሚችል ገልጾ በጽሁፍ ያስታውቀዋል፡፡

   ሐ) ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ “ሀ” መሠረት የተሰረዘው መራጭ ለመሠረዙ የቀረበበትን ማስረጃ በመጥቀስ ቃለ ጉባኤ ይይዛል፡፡

   መ ) ከላይ በዚህ ንዑስ አንቀፅ “ሐ” መሠረት የተያዘ ቃለጉባዔ የምርጫ አስፈፃሚዎች ይፈራረሙበታል፡፡

5. በዚህ አንቀፅ መሠረት አንድ ሰው ከመራጮች መዝገብ የምትሰረዘው የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ይፋ የሚሆንበት ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ ብቻ ነው፡፡

## ክፍል ስድስት

## ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የመራጮች ምዝገባ እና የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ግልፅ የማድረግ ሂደት ስለሚቋረጥበት ሁኔታ

### አንቀፅ 32. የመራጮች ምዝገባ ወይም የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ግልፅ የማድረግ ሂደት መቋረጥ

1. የምርጫ ጣቢያው ሰብሳቢ የምርጫ ጣቢያው በሁከት፣ ግጭት፣ በአውሎ ነፋስ፣ በጎርፍ፣ በእሳት ወይም በማንኛውም አስገዳጅ ምክንያት መደበኛ እንቅስቃሴዎችን ማካሄድ የማይቻልበት ከአቅም በላይ የሆነ አስገዳጅ ሁኔታ ካጋጠመው የመራጮችን ምዝገባ ወይም የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ግልፅ የማድረግ ሂደት ሊያቆም ይችላል።
2. የመራጮች ምዝገባ ወይም የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ግልፅ የማድረግ ሂደት በደህንነት ችግር ምክንያት ከማቋረጡ በፊት የምርጫ ጣቢያው ሰብሳቢ ከሚመለከተው የፀጥታ አስከባሪ ጋር መማከር ይኖርበታል ።
3. በዚህ አንቀጽ በተቀመጠው አግባብ የመራጮች ምዝገባ ወይም የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ይፋ የማድረግ ሂደት ከመቋረጡ በፊት፤ በተቻለ መጠን የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ከምርጫ ክልል ጽ/ቤት ጋር መማከር ይኖርበታል። ነገር ግን ይህን ማድረግ የማይቻል ከሆነ የመራጮች ምዝገባ ወይም የመራጮችን መዝገብ ለህዝብ ግልፅ የማድረግ ሂደቱ እንደተቋረጠ በተቻለ ፍጥነት ለምርጫ ክልል ጽ/ቤት ማሳወቅ አለበት ።
4. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ሂደቱን እንዲያቋርጥ ከምርጫ ክልሉ ጽ/ቤት ወይም ከምርጫ የፀጥታ አስከባሪዎች የቅርብ ኃላፊ ሃሳብ ከተሰጠው የመራጮችን ምዝገባ ወይም የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ይፋ የማድረግን ሂደት ማቋረጥ አለበት።
5. በዚህ አንቀጽ አግባብ የመራጮች ምዝገባ ወይም የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ይፋ የማድረግ ሂደት የተቋረጠ ከሆነ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ልዩ ጥበቃ የሚሹ ቁሳቁሶችን፤

   ሀ) መራጮች ምዝገባ መቋረጥ በተመለከተ ሲሆን የመራጮች መዝገብ እና የመራጮች ካርድ መዝገብ፣ ህጋዊ የምርጫ ጣቢያው ማህተም እና የተጠናቀቁ ቅጾች፣

   ለ) የመራጮችን መዝገብ ለህዝብ ግልፅ ማድረግ ሂደት መቋረጥን በተመለከተ ሲሆን የመራጮች መዝገብ፣ የምርጫ ጣቢያው ህጋዊ ማህተም እና የተጠናቀቁ ቅጾች ደህንነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ መታሸጋቸውን ማረጋገጥ አለበት።

6. የመራጮች ምዝገባ ወይም የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ይፋ የማድረግ ሂደት እስከሚቀጥል ድረስ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ልዩ ጥበቃ የሚሹ ቁሳቁሶች በጊዜያዊነት የሚቀመጡበትን ቦታ ለመወሰን ከምርጫ ክልል ጽ/ቤት ጋር ይመክራል። በጊዜያዊነት የሚቀመጡበት ቦታ

ከተወሰነ በኋላ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ልዩ ጥበቃ የሚሹ ቁሳቁሶች ታሽገውና በተቆለፈ ክፍል ውስጥ ተገቢውን የደህንነት ጥበቃ ተደርጎላቸው መቀመጣቸውን ያረጋግጣል፡፡

7. በምርጫ ጣቢያው የተገኙ ፈቃድ ያላቸው ወኪሎች፣ ታዛቢዎች እና ጋዜጠኞች ልዩ ጥበቃ የሚሹ ቁሳቁሶች ሲታሸጉና ወደ ጊዜያዊ ማስቀመጫ ቦታ በሚሄድበት ጊዜ ሂደቱን እንዲመለከቱ ይደረጋል፡፡
8. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ሂደቱ የተቋረጠበትን ጊዜ እና ምክንያት በምርጫ ጣቢያው ቃለጉባዔ ላይ መያዙን አስፈፃሚዎቹም እንደፈረሙበት ያረጋግጣል፡፡

**አንቀፅ 33. የተቋረጠ የመራጮች ምዝገባ ወይም የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ይፋ ማድረግ ሂደት ዳግም ስለመጀመር**

1. የተቋረጠው እንቅስቃሴ በምርጫ ጣቢያው እንደገና ሊጀመር ይችል እንደሆነ ለመወሰን የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ከምርጫ ክልል ጽ/ቤት እና በፀጥታ ምክንያት ከተቋረጠ ደግሞ ከምርጫ ጣቢያው የጸጥታ አስከባሪዎች ሀላፊ ጋር ምክክር ማድረግ አለበት፡፡
2. በተፈጠረው ችግር ምክንያት የምርጫ ጣቢያውን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል የማይቻል ከሆነ፣ ሌላ የምርጫ ጣቢያ ቦታ በአቅራቢያው እንዲቋቋም ለመወሰን ወይም በአቅራቢያው ባለ ሌላ የምርጫ ጣቢያ ሂደቱን ለማስቀጠል የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ከምርጫ ክልል ጽ/ቤት ጋር ወይም ከሚመለከተው የቦርዱ ጽ/ቤት ጋር መማከር አለበት፡፡
3. በምርጫ ጣቢያው የተቋረጠው እንቅስቃሴ በተቻለ ፍጥነት መጀመር አለበት፣ ሂደቱ ተቋርጦ ለቆየበት ጊዜ ያህል ይራዘማል፡፡
4. እንቅስቃሴው የሚጀመርበት ቦታ እና ጊዜ ከተወሰነ በኋላ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊና የምርጫ ክልሉ ጽ/ቤት ይህንን መረጃ ለህዝብ ይፋ ማድረግ አለባቸው፡፡
5. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ እንቅስቃሴው የሚጀመርበትን ቦታና ሰዓት ፈቃድ ለተሰጣቸው ወኪሎች፣ ታዛቢዎች እና ጋዜጠኞች ያሳውቃል፡፡
6. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ እንቅስቃሴው እንደገና የሚጀመርበትን ቦታ እና ሰዓት በምርጫ ጣቢያው ቃለጉባኤ ላይ ያሰፍራል፡፡

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀፅ 34. በመራጮች ምዝገባ ሂደት የተከለከሉ ተግባራት**

1. በመራጮች ምዝገባ ሂደት የሚከተሉትን የተከለከሉ ተግባራት ፈፅማ የተገኘች በህግ ተጠያቂ ትሆናለች፤

   ሀ) ተመዝጋቢዋ መመዘኛውን አለማሟላቷን እያወቀች በመራጭነት መዝግባ የተገኘች የመዝገብ ሹም፣

ለ) በምርጫ አፈፃፀም የጊዜ ሠሌዳ መሠረት እና ለመራጮች ምዝገባ ከተወሰኑት ቦታ፣ ቀን እና ሰዓት ውጪ ማንኛውንም ዓይነት ምዝገባ ስታከናውን የተገኘች የመዝገብ ሹም፣

ሐ) ለመራጭነት ከአንድ ጊዜ በላይ ወይም ከአንድ ምርጫ ጣቢያ በላይ ተመዝግባ የተገኘች እንደሆነ ወይም ከአንድ በላይ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ ይዛ የተገኘች፣

መ) በመራጭነት ለመመዝገብ ስትል የሀሰት መግለጫ፣ ወይም ማስረጃ የሰጠች ወይም የሀሰት ሰነድ ለሚመለከተው አካል አቅርባ የተገኘች፣

ሠ) መራጮች እንዳይመዘገቡ ወይም እንዲመዘገቡ በማንኛውም መንገድ ያስፈራራች ወይም የሀሰት መረጃ ወይም ማስረጃ የሰጠች፣

ረ) የሌላውን በመራጭነት የመመዝገብ ወይም አቤቱታ የማቅረብ መብት እንዳይጠቀምበት የከለከለች፥ የገደበች ወይም ያወከች፣

ሰ) የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ የለወጠች፣ የሠረዘች፣ የደለዘች፣ ወይም አስመስላ የሰራች፣

ሸ) በህጋዊ መንገድ የተመዘገበን መራጭ ከማንኛውም የምርጫ ሰነድ የሠረዘች ወይም የደለዘች።

ቀ) ከመዝገብ ሹሟ ውጪ የመራጮች ምዝገባ አከናውና የተገኘች።

2. የምርጫ ጣቢያ ሃላፊዋ በዚህ አንቀጽ የተከለከሉ ሌሎች ተግባራት በምርጫ ሕጉ አንቀጽ 157 እንዲሁም አግባብነት ባለው የወንጀል ህግ መሠረት የተፈፀሙ ጥሰቶች ሲኖሩ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ጉዳዮቹን ለፖሊስ ትመራለች፣ ትከታተላለች።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተደነገገው እደተጠበቀ ሆኖ፤

ሀ) የተመዘገበች መራጭ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ወኪል በመራጮች ምዝገባ ላይ ተቃውሞ ካላት ተቃውሞውን ከነምክንያቱ በቦርዱ በተዘጋጀ ቅጽ አማካኝነት ለምርጫ ጣቢያው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ታቀርባለች።

ለ) በምርጫ ሕጉ በተፈቀደላቸው የአምስት ቀን ጊዜ ገደብ ውሳኔ ካልተሰጠ ወይም በተሰጠው ውሳኔ ያልተስማማች እንደሆነ በአምስት ቀን ገደብ ውስጥ በየደረጃው ላሉ የቦርዱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ኮሚቴዎች አልፎም ስልጣን ላላቸው በየደረጃው ላሉ የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት አቅርባ ውሳኔውን በጽሑፍ የማግኘት መብት አላት።

ሐ) የምርጫ ጣቢያው የጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፥ የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ስራውን ያከናውናል።

4. የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዋ አንድ መራጭ በዚህ መመሪያ መሰረት ከአንድ ጊዜ በላይ

ወይም በሌላ የምርጫ ጣቢያ ድጋሚ መመዝገቧን ወይም እየተመዘገበች መሆኑን አልያም ከአንድ በላይ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ ይዛ እንደተገኘች ስታውቅ ወይም በመረጃ የተደገፈ አቤቱታ ሲደርሳት በምርጫ ሕጉ እና በዚህ መመሪያ መሰረት መራጯን ከመራጮች መዝገብ ላይ ወዲያውኑ ትሰርዛለች፡፡

5. በምርጫ ሕጉ አንቀጽ 152 ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት በቀረበ አቤቱታ መነሻነት አግባብ ያለው የቦርዱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ድጋሚ ምዝገባ ተግባሩ የተፈጸመው ሆን ብሎ ለማጭበርበር እንዳልሆነ ከወሰነ የመራጯ ድጋሚ ምዝገባ እንዲሰረዝ ሁለተኛው የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድም እንዲወገድ ውሳኔውን ለምርጫ ጣቢያው ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ያስተላልፋል፡፡ የምርጫ ጣቢያው ፅሕፈት ቤትም በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ስራውን ያከናውናል፡፡

## አንቀፅ 35. በመራጮች ምዝገባ ሂደት ሥራ ላይ ስለሚውሉ ቅፆች እና ስለ ሪፖርት አቀራረብ

1. በየደረጃው የተቋቋሙ የምርጫ አስፈፃሚ አካላት የመራጮች ምዝገባ እንቅስቃሴን አስመልክቶ ለበላይ የምርጫ አስፈፃሚ አካል ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው::
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የሚቀርብ ሪፖርት ቦርዱ ባወጣው የጊዜ ሠሌዳ እና መመሪያዎች መሰረት ይከናወናል፡፡

## አንቀፅ 36. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ወይም አካል የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ በምርጫ ክልል ኃላፊ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት የመተባበር ግዴታ አለበት::

## አንቀፅ 37. ስለቅጣት

ይህን መመሪያ የጣሰች ወይም ሆን ብላ የምርጫውን ሂደት የሚያሰናክል ጥፋት ፈፅማ ከተገኘች አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ትጠየቃለች፡፡

## አንቀፅ 38. የተሻሩ መመሪያዎችና አሰራሮች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም::

## አንቀፅ 39. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከታህሳስ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ብርቱካን ሚደቅሳ**

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ**

**ሰብሳቢ**

# የምርጫ ጉዳዮች በፍርድ ቤት የሚስተናገዱበት የሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ

## (ረቂቅ) ደንብ

ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ አቤቱታዎች እና ክርክሮችን ለመምራት እና ለማስተናገድ የሚያስፈልግ ሥነ ሥርዓት መደንገግ በማስፈለጉ ፤

የምርጫ ጉዳዮችን የሚያስተናግዱ ፍርድ ቤቶች ጉዳዮችን ፈጣን ፣ ግልጽ እና ተአማኒ በሆነ መልኩ ማስተናገዳቸው የምርጫውን ፍትሐዊነት የሚያረጋግጥ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አቤቱታዎች ወደ ፍርድ ቤት እንደሚቀርቡ እና እንደሚስተናገዱ የሚደነግግ ቢሆንም አቤቱታዎች የሚቀርቡበትን እና የሚስተናገዱበትን ዝርዝር ሁኔታ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከምርጫ ጋር በተያያዙ የሚነሱ ጉዳዮች በመሠረቱ የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ቢሆኑም የጉዳዮቹ ልዩ ባህሪ ከመደበኛው የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ የተለየ የሥነ ሥርዓት ሕግ ማውጣትን የሚጠይቅ በመሆኑ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ (1) ፣ በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 163 ንዑስ አንቀጽ (1) እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 30 መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የምርጫ ጉዳዮች በፍርድ ቤት የሚስተናገዱበት የሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ደንብ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ ደንብ ውስጥ

1. "አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ነው፡፡
2. "ቦርድ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፡፡
3. "ፍርድ ቤት" ማለት የወረዳ ፍርድ ቤት፣ በወረዳ ፍርድ ቤት ደረጃ ጉዳችን ለማየት ስልጣን ያለው የከተማ ፍርድ ቤት፣ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማለት ነው፡፡
4. "ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 መሰረት በምርጫ ጣቢያ፣ በምርጫ ክልል እና በክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ደረጃ ለሚነሱ ቅሬታዎች አስተዳደራዊ ውሳኔ ለመስጠት የተቋቋሙ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ናቸው፡፡
5. "የምርጫ ሂደት" ማለት የመራጭ ምዝገባ፣ የዕጩ ምዝገባ፣ የዕጩ የምርጫ መለያ ምልክት መረጣ፣ የምረጡኝ ቅስቀሳ፣ የድምፅ አሰጣጥ፣ የድምፅ ቆጠራ፣ ጊዜያዊ ውጤት አደማመር፣ የቅሬታ አፈታት ሥርዓት እና የመጨረሻ የምርጫ ውጤት ማሳወቅን፣ የሥነ ዜጋና መራጮች ትምህርት የሚሰጡ ተቋማት እንዲሁም የምርጫ ታዛቢዎች እና ጋዜጠኞች ፈቃድ አሰጣጥን ያካትታል፡፡
6. "አቤቱታ" ማለት አመልካች በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ወይም በቦርድ የተሰጠ ውሳኔ ላይ ያለውን ቅሬታ ለፍርድ ቤት የሚያቀርብበት ማመልከቻ ነው፡፡
7. "አመልካች" ማለት በአዋጁ መሰረት በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ወይም በቦርዱ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወይም ውሳኔ ሳይሰጠው በመቅረቱ ቅር በመሰኘት በአዋጁ መሰረት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀረበ ሰው ነው፡፡
8. "ቀን" ማለት በቀን መቁጠሪያ ላይ የሚታወቁ ሁሉንም ቀናት ያካትታል፡፡

9. “ተጠሪ” ማለት በአመልካች አቤቱታ ላይ ተጠሪ ተብሎ የተጠቀሰው አካል ነው፡፡
10. “ሰው” ማለት ሕጋዊ ወይም የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡
11. በአዋጁ የተገለጹ የቃላትና ሐረጎች ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ያገለግላሉ፡፡
12. በዚህ ደንብ ውስጥ በአንዱ ፆታ የተገለፀው ሌላውንም ጾታ ያካትታል፡፡

**3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ የምርጫ ሂደትን በተመለከተ ወደ ፍርድ ቤት በሚቀርቡ አቤቱታዎች እና ክርክሮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**4. <u>አላማ</u>**

ይህ ደንብ

1. ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች ካላቸው ባህርያት አንጻር በልዩ ሁኔታ የሚስተናገዱበትን፣
2. ጉዳዮች የምርጫን የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በማድረግ በተፋጠነ እና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ በአጭር ጊዜ ውስጥ እልባት የሚያገኙበትን እና
3. ባለጉዳዮች በእኩልነት የመሰማት ሕገ መንግስታዊ መብታቸው የተከበረ መሆኑን የማረጋገጥ እና ፍትሐዊ የክርክር ሂደት ለማስፈን የሚያስችል ሥነ ሥርዓት የመዘርጋት አላማዎች አሉት፡፡

**<u>ምዕራፍ ሁለት</u>**

**<u>የመራጮች ምዝገባ አቤቱታ አቀራረብና ውሣኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት</u>**

**5. <u>አቤቱታ ስለማቅረብ</u>**

1. ማንኛውም በመራጭነት ከመመዝገብ አላግባብ ተከልክያለሁ በማለት በአዋጁ አንቀፅ 152 ንዑስ አንቀጽ (8) መሠረት ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታ አቅርቦ በአምስት ቀናት ውስጥ ውሣኔ ሳይሰጠው የቀረ ወይም የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሰጠው ውሣኔ ያልተስማማ ሰው

   ሀ. አቤቱታው የተነሳው በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ ከሆነ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ፤

   ለ. አቤቱታው የተነሳው በክልል ከሆነ ለወረዳ ፍ/ቤት

   በአምስት ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለማቅረብ ይችላል፡፡

2. በመራጭነት መመዝገብ የሌለበት ሰው አለአግባብ ተመዝግቧል በማለት በአዋጁ አንቀጽ 152 ንዑስ አንቀጽ (8) መሠረት ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ተቃውሞ አቅርቦ በአምስት ቀን ውስጥ ውሣኔ ሳይሰጠው የቀረ ወይም የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሰጠው ውሣኔ ያልተስማማ ሰው ወይም የፖለቲካ ፓርቲ

   ሀ. አቤቱታው የተነሳው በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ ከሆነ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት

   ለ. አቤቱታው የተነሳው በክልል ከሆነ ለወረዳ ፍ/ቤት

   በአምስት ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለማቅረብ ይችላል፡፡

**6. <u>አቤቱታ ስለሚቀርብባቸው ምክንያቶች</u>**

1. አንድ ሰው በአዋጁ አንቀጽ 18 እና 28 ከተመለከቱት ወይም በአዋጁ ሌሎች ድንጋጌዎች ላይ ከተመለከቱት በመራጭነት ከመመዝገብ ከሚያስከለክሉ ምክንያቶች ውጪ በሆነ ምክንያት እንዳልመዘገብ ተከልክያለሁ የሚል ከሆነ በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የሚቀርበው ተቃውሞ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በአዋጁ አንቀጽ 18 እና 28 የተመለከተቱትን እና በአዋጁ ሌሎች ድንጋጌዎች የተገለጹ ምክንያቶችን የሚያካትት ሆኖ ተመዝጋቢው

ሀ. ኢትዮጲያዊ ዜጋ አይደለም፣

ለ. በመራጭነት በሚመዘገብበት ቀን ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች ነው፣

ሐ. በምርጫ ክልሉ የኖረው ከስድስት ወራት በታች ነው፣

መ. በአእምሮ ህመም ምክንያት ለመወሰን ብቃት የሌለው ለመሆኑ ሥልጣን ባለው አካል ወይም በበቂ ማስረጃ ተረጋግጧል፣

ሠ. በማጭበርበር ወይም በድጋሚ ተመዝግቧል ወይም

ረ. በፍርድ ወይም በሕግ የመምረጥ መብቱ ተገድቧል በማለት መቃወሚያ ሊቀርብ ይችላል፡፡

**7. <u>አቤቱታው በጊዜው የቀረበ ስለመሆኑ ማረጋገጥ</u>**

የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር አመልካቹ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 መሰረት ያቀረበውን አቤቱታ የሚቀበለው አቤቱታው የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ በሰጠ በአምስት ቀናት ውስጥ ወይም ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታ ቀርቦ ኮሚቴው ውሳኔ ሳይሰጥ 5 ቀናት ካለፉ በኋላ ባሉት 5 ቀናት ከቀረበለት ብቻ ነው፡፡

**8. <u>መጥሪያ እንዲደርስ ስለማዘዝ</u>**

አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት አመልካቹ ያቀረበው አቤቱታ ለአቤቱታ መነሻ የሚሆን ምክንያት ያለው መሆኑን ያመነ እንደሆነ አቤቱታው እና መጥሪያ በ48 ሰዓታት ውስጥ ለተጠሪ ደርሶት ተጠሪው መጥሪያ በደረሰው 48 ሰዓታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንደሁኔታው መልሱን በጽሁፍ ይዞ እንዲቀርብ ወይም በቃል ቀርቦ እንዲያስረዳ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

**9. <u>በፍርድ ቤት ስለሚሰጥ ውሳኔ</u>**

1. ፍርድ ቤቱ ተከራካሪዎቹን ከመረመረ በኋላ በአራት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቱ ሁኔታ ቢሆን አመልካቹ አቤቱታውን ካቀረበለት ጊዜ ጀምሮ ባሉት አስር ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
2. ፍርድ ቤቱ የምርጫ ጣቢያው ወይም የምርጫ ክልሉ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሰጠውን ውሳኔ የሻረው እንደሆነ አመልካቹ በመራጭነት እንዲመዘገብ ወይም አላግባብ የተመዘገበው ሰው ከመራጮች መዝገብ እንዲሰረዝ ይወስናል፡፡

<u>**ምዕራፍ ሶስት**</u>

<u>**የዕጩዎች ምዝገባ አቤቱታ አቀራረብና ውሣኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት**</u>

10. **<u>አቤቱታ ስለማቅረብ</u>**

1. ማንኛውም በዕጩነት ከመመዝገብ አላግባብ ተከልክያለሁ የሚል ሰው ወይም ያቀረብኩት ዕጩ አለአግባብ እንዳይመዘገብ ተከልክሎብኛል የሚል የፖለቲካ ፓርቲ በአዋጁ አንቀፅ 153(1) መሠረት ለክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታ አቅርቦ በሰባት ቀናት ውስጥ ውሣኔ ሳይሰጠው የቀረ ወይም በተሰጠው ውሣኔ ያልተስማማ እንደሆነ
   ሀ. አቤቱታው የተነሳው በአዲስ አበባ ወይም በድሬደዋ ከተማ ከሆነ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም
   ለ. አቤቱታው የተነሳው በክልል ከሆነ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት
   በአምስት ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዕጩነት የተመዘገበ ሰው በእጩነት ሊመዘገብ አይገባም የሚል ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት በአዋጁ አንቀጽ 153(2) መሠረት ተቃውሞውን ለክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቅርቦ በሰባት ቀናት ውስጥ ውሣኔ ሳይሰጠው የቀረ እንደሆነ ወይም በተሰጠው ውሣኔ ያልተስማማ እንደሆነ
   ሀ. አቤቱታው የተነሳው በአዲስ አበባ ወይም በድሬደዋ ከተማ ከሆነ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም
   ለ. አቤቱታው የተነሳው በክልል ከሆነ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

በአምስት ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለማቅረብ ይችላል፡፡

## 11. <u>አቤቱታ ስለሚቀርብባቸው ምክንያቶች</u>

1. ማንኛውም በአዋጁ ላይ ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጪ በዕጩነት ከመመዝገብ ተከልክያለሁ የሚል ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የሚቀርበው ተቃውሞ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በአዋጁ አንቀጽ 31፣32፣33 እና በአዋጁ ሌሎች ድንጋጌዎች የተገለጹ ምክንያቶችን የሚያካትት ሆኖ ዕጩው

ሀ. ኢትዮጲያዊ ዜጋ አይደለም፣

ለ. በምዝገባ ወቅት ዕድሜው 21 አልሞላም ነበር፣

ሐ. በምርጫ ክልሉ የኖረው ከአንድ ዓመት ላነሰ ጊዜ ነው ወይም በዕጩነት ሊቀርብበት በፈለገው ቦታ አልተወለደም ፣

መ. ሊወዳደር በፈለገበት ከተማ ወይም ወረዳ በስራ ላይ የቆየው ከሁለት ዓመታት በታች ለሆነ ጊዜ ነው፣

ሠ. በፍርድ ወይም በህግ የመምረጥ እና የመመረጥ መብቱ ተገፍፏል፣

ረ. በአእምሮ ህመም ምክንያት ለመወሰን ብቃት የሌለው ለመሆኑ ሥልጣን ባለው አካል ወይም በበቂ ማስረጃ ተረጋገጧል፣

ሰ. ዕጩው ወይም የፖለቲካ ፓርቲው ቦርዱ ያወጣውን የስነ ምግባር ደንብ መቀበሉን በፊርማው አላረጋገጠም፣

ሸ. በአዋጁ መሰረት አስፈላጊ የሆነውን የድጋፍ ፊርማ አላቀረበም ፣

ቀ. በዕጩነት የተመዘገበዉ በሥራ ላይ የሚገኝ ዳኛ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ ወታደር፣ ፖሊስ፣ የጸጥታ ሰራተኛ፣ የደህንነት ሰራተኛ ወይም የቦርዱ ሰራተኛ ነው በማለት መቃወሚያ ሊቀርብ ይችላል፡፡

## 12. <u>መጥሪያ እንዲደርስ ስለማዘዝ</u>

አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት አመልካቹ ያቀረበው አቤቱታ ለአቤቱታ መነሻ የሚሆን ምክንያት ያለው መሆኑን ያመነ እንደሆነ አቤቱታው እና መጥሪያ በ48 ሰዓታት ውስጥ ለተጠሪ ደርሶት ተጠሪው መጥሪያ በደረሰው 48 ሰዓታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንደሁኔታው መልሱን በጽሁፍ ይዞ እንዲቀርብ ወይም በቃል ቀርቦ እንዲያስረዳ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

## 13. <u>በፍርድ ቤት ስለሚሰጥ ውሳኔ</u>

1. ፍርድ ቤቱ ተከራካሪዎቹን ከመረመረ በኋላ በአራት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ሆኖም በማናቸውም ሁኔታ አመልካቹ አቤቱታውን ካቀረበለት ጊዜ ጀምሮ ባሉት በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
2. ፍርድ ቤቱ የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሰጠውን ውሳኔ የሻረው እንደሆነ አመልካቹ በዕጩነት እንዲመዘገብ ወይም ዕጩው ከመዝገብ እንዲሰረዝ ይወስናል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የዕጩዎች ምርጫ መለያ ምልክትን የሚመለከት አቤቱታ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

### 14. አቤቱታ ስለማቅረብ

ማንኛውም የግል እጩ ወይም የፓለቲካ ፓርቲ የምርጫ መወዳደሪያ ምልክቴ ያለአግባብ በሌላ ተወዳዳሪ ተወሰደብኝ ወይም በመረጥኩት ምልክት እንዳልጠቀም ተከለከልኩ ወይም እንድቀይር ታዘዝኩ በሚል ለቦርዱ አቤቱታ አቅርቦ ቦርዱ በሰጠው ውሣኔ ያልተስማማ ወይም ከቦርዱ መልስ ያላገኘ እንደሆነ በአስር ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታው ለማቅረብ ይችላል፡፡

### 15. አቤቱታ ስለሚቀርብባቸው ምክንያቶች

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 14 መሰረት የሚቀርበው አቤቱታ በአዋጁ አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ (6) የተመለከተቱትን እና በአዋጁ ሌሎች ድንጋጌዎች የተገለጹ ምክንያቶችን መሰረት ያደርጋል፡፡
2. አመልካቹ ቀደም ብዬ ያስመዘገብኩት የምርጫ መወዳዳሪያ ምልክት ለሌላ የግል ዕጩ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ተሰጥቶብኛል ወይም ሌላ ሰው በምልክቴ እየተጠቀመ መሆኑን ለቦርዱ ባመለክትም ምላሽ አላገኘሁም የሚል አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል፡፡
3. አመልካች ለምዝገባ ያቀረብኩት የምርጫ መወዳደሪያ ምልክት

   ሀ. በብሔር ብሔረሰቦች ፣ በዘር፣ በሃይማኖት መካከል ጥላቻና ግጭት ይቀሰቅሳል ወይም

   ለ. የጦርነት ወይም የሌላ ሕገወጥ ድርጊት መልዕክት ያስተላልፋል ወይም

   ሐ. ከፌደራልም ሆነ ከክልል መንግሥታት ሰንደቅ ዓላማ፣ አርማ ወይም ከልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዓርማና ሰንደቅ አላማ ወይም ከሃይማኖት ድርጅቶች ምልክቶች ጋር ይመሳሰላል ወይም

   መ. የሕዝብን ሞራል ወይም መልካም ስነ ምግባር ይጥሳል ወይም

   ሠ. በምልክት ቋንቋ የታወቀ የተለየ ትርጉም አለው በሚል እንዳይመዘገብ ተከልክያለሁ ወይም ምልክቱን እንድቀይር ታዝዣለሁ በማለት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

### 16. መጥሪያ እንዲደርስ ስለማዘዝ

አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት አመልካቹ ያቀረበው አቤቱታ ለአቤቱታ መነሻ የሚሆን ምክንያት ያለው መሆኑን ያመነ እንደሆነ አቤቱታው ለተጠሪ በሶስት ቀናት ውስጥ ደርሶት ተጠሪው መጥሪያ በደረሰው ሶስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንደሁኔታው መልሱን በጽሁፍ ይዞ እንዲቀርብ ወይም በቃል ቀርቦ እንዲያስረዳ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

### 17. በፍርድ ቤት ስለሚሰጥ ውሳኔ

1. ፍርድ ቤቱ ተከራካሪዎቹን ከመረመረ በኋላ በአራት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ሆኖም በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን አቤቱታው በአመልካቹ ከቀረበለት ጊዜ ጀምሮ ባሉት በአስር ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

2. ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን የሻረው እንደሆነ

   ሀ. አመልካቹ ተወስዶብኛል በማለት አቤቱታ ያቀረበበት እና ለሌላ ሰው የተሰጠው የመለያ ምልክት እንዲሰረዝ ወይም

   ለ. አመልካች እንዳይጠቀም የተከለከለው የምርጫ መለያ ምልክት እንዲሰጠው ወይም

   ሐ. የአመልካቹን የምርጫ መለያ ምልክት እየተጠቀመ ያለው ሰው መጠቀሙን እንዲያቆም ወይም

   መ. አመልካች መለያ ምልክቱን እንዲቀይር ሊገደድ አይገባም ወይም ሊቀይር ይገባል በማለት ሊወስን ይችላል፡፡

## ምዕራፍ አምስት
## የስነ ምግባር ጥሰቶች በሚመለከት የአቤቱታዎች አቀራረብ እና ውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

**18. አቤቱታ ስለማቅረብ**

ማንኛውም ሰው ወይም የፖለቲካ ፓርቲ

1. በአዋጁ አንቀጽ 142 የተዘረዘሩትን መደለያ መስጠትን እና ኃይልን ወይም ሥልጣንን አለ አግባብ መጠቀምን፣
2. በአዋጁ አንቀጽ 143 የተዘረዘሩትን ፍርሀት በመቀስቀስ ወይም ሁከት በመፍጠር ማንኛውንም የምርጫ እንቅስቃሴ ማስተጓጎልን፣
3. በአዋጁ አንቀጽ 144 የተዘረዘሩትን በምርጫ ሂደት ሰላምና ጸጥታ የሚያናጉ መልዕክቶችን ማስተላለፍን፣
4. በአዋጁ አንቀጽ 145 የተዘረዘሩትን የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ዕጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ እንቅስቃሴ ማደናቀፍን፣
5. በአዋጁ አንቀጽ 146 የተዘረዘሩትን ከጋዜጠኞች ወይም ከታዛቢዎች ጋር አለመተባበርን እና
6. በአዋጁ አንቀጽ 147 የተዘረዘሩትን የሥነ ምግባር ድንጋጌዎችን አለማስተዋወቅ እና ህገ ወጥ ድርጊቶችን አለማውገዝን ወይም በአዋጁ ሌሎች ድንጋጌዎች የተደነገጉ የሥነ ምግባር ጥሰቶች ምክንያት በቦርዱ በተወሰደበት እርምጃ ቅር የተሰኘ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 149 መሰረት አቤቱታውን በአስር ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለማቅረብ ይችላል፡፡

**19. መጥሪያ እንዲደርስ ስለማዘዝ**

1. አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት አመልካቹ ለአቤቱታው መነሻ ምክንያት ያለው ስለመሆኑ መዝገቡ በቀረበለት በ48 ሰዓታት ውስጥ መርምሮ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
2. አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት አመልካቹ ያቀረበው አቤቱታ ለአቤቱታው መነሻ የሚሆን ምክንያት ያለው መሆኑን ያመነ እንደሆነ አቤቱታው ለተጠሪው በ48 ሰዓታት ውስጥ ደርሶት ተጠሪው መጥሪያ በደረሰው 48 ሰዓታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንደሁኔታው መልሱን በጽሁፍ ይዞ እንዲቀርብ ወይም በቃል ቀርቦ እንዲያስረዳ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

20. **በፍርድ ቤት ስለሚሰጥ ውሳኔ**

ፍርድ ቤቱ ተከራካሪዎቹን ከመረመረ በኋላ ደግሞ በአስር ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቱ በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን አመልካች አቤቱታው ከቀረበለት ጊዜ ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

## ምዕራፍ ስድስት
## ድምጽ አሰጣጥን የሚመለከቱ አቤቱታዎች አቀራረብ እና ውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

**21. አቤቱታ አቀራረብ**

1. ማንኛውም በመራጭነት የተመዘገበ ሰው ድምፅ ለመስጠት ተከልክያለሁ በማለት በአዋጁ አንቀጽ 154(4) መሰረት ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታ አቅርቦ ኮሚቴው በሰጠው ውሣኔ ያልተስማማ ከሆነ

   ሀ. አቤቱታው የቀረበው በአዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ከተማ ከሆነ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም

   ለ. አቤቱታው የቀረበው በክልል ከሆነ ለወረዳ ፍርድ ቤት
   አቤቱታውን ወዲያውኑ ወይም ቢያንስ በ24 ሰዓታት ውስጥ ለማቅረብ ይችላል፡፡
2. አንድ መራጭ ድምፅ መስጠት የለበትም የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ፓርቲ በአዋጁ አንቀጽ 154(5) መሰረት ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታ አቅርቦ ኮሚቴው በሰጠው ውሣኔ ያልተስማማ ከሆነ

ሀ. አቤቱታው የቀረበው በአዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ከተማ ከሆነ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

ለ. አቤቱታው የቀረበው በክልል ከሆነ ለወረዳ ፍርድ ቤት

አቤቱታውን ወዲያውኑ ወይም ቢያንስ በ24 ሰዓታት ውስጥ ለማቅረብ ይችላል፡፡

**22. <u>አቤቱታ ስለሚቀርብባቸው ምክንያቶች</u>**

1. ማንኛውም በአዋጁ ላይ ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጪ ድምጽ ለመስጠት ተከልክያለሁ የሚል ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የሚቀርበው ተቃውሞ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በአዋጁ አንቀጽ 18፣28፣39 እና 50 የተመለከተቱትን እና በአዋጁ ሌሎች ድንጋጌዎች የተገለጹ ምክንያቶችን የሚያካትት ሆኖ ድምጽ ሰጪው

ሀ. ኢትዮጲያዊ ዜጋ አይደለም፣

ለ. በምዝገባው ጊዜ ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች ነው፣

ሐ. በምርጫ ክልሉ የኖረው ከስድስት ወራት በታች ነው፣

መ. በአእምሮ ህመም ምክንያት ለመወሰን ብቃት የሌለው ለመሆኑ ሥልጣን ባለው አካል ወይም በበቂ ማስረጃ ተረጋግጧል፣

ሠ. የያዘው የምርጫ ካርድ ሀሰተኛ ነው፣

ረ. የያዘው የምርጫ ካርድ የሌላ ሰው ነው፣

ሰ. በመራጭነት አልተመዘገበም፣

ሸ. ቀደም ብሎ ድምጽ ሰጥቷል ወይም በድጋሚ ድምጽ ለመስጠት ቀርቧል ወይም

ቀ.በፍርድ ወይም በሕግ የመምረጥ መብቱ ተገድቧል በማለት መቃወሚያ ሊቀርብ ይችላል፡፡

**23. <u>መጥሪያ እንዲደርስ ስለማዘዝ</u>**

1. አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት አመልካቹ ለአቤቱታው መነሻ የሚሆን ምክንያት ያለው ስለመሆኑ መዝገቡ በቀረበለት ዕለት መርምሮ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ መጣራት ያለበት ተጠሪው ወይም ጉዳዩ የሚያገባው ሰው በተገኘበት መሆኑን በበቂ ምክንያት ያመነ እንደሆነ ተጠሪው ወይም ጉዳዩ የሚያገባው ሰው በ24 ሰዓታት ውስጥ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

**24. <u>የማገድ ስልጣን</u>**

ፍርድ ቤቱ በአዋጁ አንቀጽ 154(4) መሰረት የድምጽ መዳመሩ ሂደት እንዳይጀመር ወይም ተጀምሮ ከሆነም እንዲቆም ለማዘዝ ይችላል፡፡

**25. <u>በፍርድ ቤት ስለሚሰጥ ውሳኔ</u>**

1. ፍርድ ቤቱ በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን ጉዳዩ ከቀረበለት ሰዓት ጀምሮ በሚቆጠር በሶስት ቀናት ወይም እጅግ ቢዘገይ የድምጽ ማዳመሩ ከመጠናቀቁ በፊት ውሳኔውን ይሰጣል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ እንደአግባብነቱ የተሰጠው ጊዜያዊ ድምጽ መደበኛ ድምጽ ሆኖ እንዲቆጠር ወይም እንዲሰረዝ ይወስናል፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

## ድምጽ ቆጠራ ሂደትና ውጤት የሚመለከቱ አቤቱታዎች አቀራረብ እና ውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

### 26. አቤቱታ ስለማቅረብ

ማንኛውም በድምፅ ቆጠራ ሂደትና ውጤቱ ላይ ቅሬታ ያለው የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ወይም ወኪሉ ቅሬታውን በአዋጁ አንቀጽ 155(4) መሰረት ለቦርዱ አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ አቤቱታውን በ10 ቀናት ውስጥ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለማቅረብ ይችላል፡፡

### 27. አቤቱታ ስለሚቀርብባቸው ምክንያቶች

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ወይም ወኪሉ በዚህ ደንብ አንቀጽ 27 መሰረት የሚያቀርበው አቤቱታ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በአዋጁ አንቀጽ 59 እና 60 ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ 3 የተመለከተቱትን እና በአዋጁ ሌሎች ድንጋጌዎች የተገለጹ ምክንያቶችን የሚያካትት ሆኖ የአቤቱታውም ምክንያት

1. በአዋጁ አንቀጽ 59 መሰረት ዋጋ አልባ የሆኑ እና ጥቅም ላይ ያልዋሉ ወይም የተበላሹ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ተቆጥረዋል፣
2. በአግባቡ የተሰጠ ድምጽ ዋጋ አልባ ሆኗል፣
3. የድምጽ መቆጠሩ እና ማዳመሩ ወቅቱን እና ሥርዓቱን ጠብቆ አልተከናወነም፣
4. የምርጫው ውጤት ለህዝብ ይፋ ሳይደረግ አለአግባብ ዘግይቷል፣
5. ለግል ዕጩ ወይም ለፖለቲካ ፓርቲ ወኪል የውጤት መተማመኛ አልተሰጠም ፣
6. የምርጫ ውጤት መግለጫ ቅጾች በአግባቡ አልተሞሉም ወይም በምርጫ አስፈጻሚዎች አልተፈረሙም፣
7. የድምጽ መስጫ ሳጥን እሽግ ተቀድዷል፣ ተሰብሯል ወይም ብልሽት ደርሶበታል፣
8. ለምርጫ ጣቢያው ከደረሰው የድምጽ መስጫ ወረቀት ብዛት በላይ የሆነ የድምጽ መስጫ ወረቀት ተገኝቷል፣
9. የድምጽ ቆጠራው የተከናወነው በሕግ ከተፈቀደው ቦታ ውጪ ነው፣
10. የድምጽ ቆጠራው በቂ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ብርሃን በሌለበት ተከናውኗል ወይም
11. የድምጽ ቆጠራው ሲከናወን ታዛቢዎች፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ወይም የዕጩ ወኪሎች እንዳይገኙ ተከልክለዋል የሚል ሊሆን ይችላል፡፡

### 28. መጥሪያ እንዲደርስ ስለማዘዝ

1. አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት አመልካቹ ለአቤቱታው መነሻ የሚሆን ምክንያት ያለው ስለመሆኑ መዝገቡ በቀረበለት ዕለት መርምሮ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ አቤቱታው መነሻ ምክንያት ያለው መሆኑን ያመነ እንደሆነ የጉዳዩን ውስብስብነት ከግምት በማስገባት ተጠሪው ወይም ጉዳዩ የሚያገባው ሰው የሚቀርብበትን ጊዜ ይወስናል፡፡ ሆኖም በማኛቸውም ሁኔታ ቢሆን ተጠሪው ወይም ጉዳዩ የሚያገባው ሰው የሚቀርብበት ጊዜ ከ10 ቀናት በላይ ሊበልጥ አይችልም፡፡

### 29. ውጤት እንዳይገለጽ ስለማገድ

ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን በአዋጁ አንቀጽ 155(6) መሰረት ቅሬታ የቀረበበት የምርጫ ክልል ውጤት እንዳይገለጽ ሊያዝ ይችላል፡፡

### 30. በፍርድ ቤት ስለሚሰጥ ውሳኔ

1. ፍርድ ቤቱ አቤቱታው በቀረበለት በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ የቦርዱን ውሳኔ ያሻሻለው ወይም የሻረው ከሆነ እንደአግባብነቱ አቤቱታ የተነሳበት የምርጫ ጣቢያ ወይም የምርጫ ክልል ውጤት በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሰረዝ፣ ዳግም ቆጠራ እንዲካሄድ ወይም ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ሊወስን ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ስምንት
## የክርክር ሂደቶች

**31. የአቤቱታው ይዘት**

በዚህ ደንብ መሠረት ለፍርድ ቤት የሚቀርብ አቤቱታ

1. ለአቤቱታው መሠረት የሆነውን ፍሬ ነገር እና
2. በፍርድ ቤት ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነውን የመጨረሻ ውሳኔ በሰጠው አካል ዘንድ የቀረቡትን አቤቱታዎች፣ መልሶች፣ ማስረጃዎች እና የተሰጡ ውሳኔዎችን መያዝ አለበት፡፡

**32. የሪጅስትራር ኃላፊነት**

አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤት ሬጅስትራር በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ወይም በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ስልጣን እና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ

1. አቤቱታው በየደረጃው የታየ መሆኑን፣
2. አቤቱታው የቀረበው በአዋጁ አንቀጽ 151 ንዑስ አንቀጽ (13) እና በዚህ ደንብ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መሆኑን፣
3. በጉዳዩ ላይ ውሳኔ በሰጡ አካላት ዘንድ የቀረቡ ማስረጃዎችና የማስረጃ ዝርዝር መግለጫዎች በበቂ ቅጅ መቅረባቸውን፣
4. በጉዳዩ ላይ ውሳኔ በሰጡ አካላት ዘንድ የምስክሮች ቃል ተመዝግቦ ከሆነ የምስክሮቹ ቃል የተመዘገበበት ሰነድ መቅረቡን፣
5. በፍርድ ቤቱ የቀረቡት ሰነዶች በፍርድ ቤቱ የሥራ ቋንቋ ተተርጉመው መቅረባቸውን፣
6. አቤቱታው በወኪል የቀረበ እንደሆነ በዚህ ደንብ መሰረት ወኪል ለመሆን የተፈቀደለት ሰው የውክልና ማስረጃ ማቅረቡን እና
7. አመልካቹ ቅሬታውን በጉዳዩ ላይ ውሳኔ በሰጡ አካላት ዘንድ አቅርቦ ውሳኔ ሳያገኝ የቀረ ከሆነ ይህንኑ ያረጋገጠበት ቃለ መሃላ መቅረቡን በማረጋገጥ መዝገቡን ይከፍታል፡፡

**33. አቤቱታውን ስለመመርመር**

1. የፍርድ ቤቱ ሪጅስትራር መዝገቡ እንደተከፈተ መዝገቡን ወዲያውኑ ለችሎት ያቀርባል፡፡

2. መዝገቡ የቀረበለት ችሎት አመልካቹ ያቀረበው አቤቱታ ለአቤቱታው የሚሆን መነሻ ምክንያት ያለው ስለመሆኑ ይመረምራል፡፡

3. አመልካቹ ያቀረበው አቤቱታ ለአቤቱታው መነሻ ምክንያት የሌለው እንደሆነ አቤቱታውን ይሰርዘዋል፡፡

**34. የተጠሪ አለመቅረብ**

1. ተጠሪው መጥሪያ ደርሶት ያልቀረበ መሆኑ ከተረጋገጠ ጉዳዩ በሌለበት ይታያል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተመለከተው ቢኖርም ተጠሪው መጥሪያ ያልደረሰው መሆኑን ወይም መጥሪያ ደርሶት ያልቀረበው በበቂ ምክንያት መሆኑን ፍርድ ቤቱ የተረዳው እንደሆነ እና ውሳኔውም በዚህ ደንብ በተመለከቱት ውሳኔ የመስጫ ጊዜያት ውስጥ ሊሰጥ የሚችል መሆኑን በማገናዘብ ተጠሪው መከራከሪያውን እንዲያቀርብ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

35. **መጥሪያ ስላለማድረስ**

1. አመልካች የፍርድ ቤቱን መጥሪያ በአካል ለተጠሪው ማድረስ አለበት፡፡
2. አመልካቹ ፍርድ ቤቱ ለተጠሪ እንዲያደርስ ያዘዘውን መጥሪያ ወዲያውኑ ከፍርድ ቤቱ አለመውሰዱ ከተረጋገጠ ወይም መጥሪያውን ያለ በቂ ምክንያት ሳያደርስ የቀረ እንደሆነ ወይም ተጠሪው መልስ ለማቅረብ በማይችልበት በተጣበበ ጊዜ ውስጥ የሰጠው እንደሆነ አመልካች ጉዳዩን ለመከታተል እንዳልፈለገ ተቆጥሮ አቤቱታው ውድቅ ይደረጋል፤ መዝገቡ ይዘጋል፡፡

36. **በክርክሩ ተሳታፊ ስለሚሆኑ ወገኖች**

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን እየተመለከተ እያለ በጉዳዩ ውስጥ ገብተው መከራከር የሚገባቸው ሌሎች ሰዎች መኖራቸውን የተረዳ እንደሆነ ወይም በጉዳዩ ያገባናል የሚሉ ሰዎች በጉዳዩ ጣልቃ ገብተው ወይም መቃወሚያ አቅርበው ለመከራከር ካመለከቱ እና ፍርድ ቤቱ እነዚህ ወገኖች ወደ ክርክሩ መግባታቸው አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

37. **ጉዳዮችን ስለማጣመር**

በአንድ ፍርድ ቤት ቀርበው በመታየት ላይ ያሉ አቤቱታዎች ላይ የቀረበው የፍሬ ነገር እና የህግ ክርክር ተመሳሳይ ሲሆን እና በፍርድ ቤቱም የሚያዘው ጭብጥ አንድ አይነት ሲሆን ከባለጉዳዮቹ አንደኛው ወገን ባመለከተ ጊዜ ወይም ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን እና ውሳኔውም በዚህ ደንብ በተመለከቱት ውሳኔ የመስጫ ጊዜያት ውስጥ ሊሰጥ የሚችል መሆኑን ሲገነዘብ ጉዳዮቹ ተጣምረው በአንድነት እንዲታዩ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**38. የተጠሪ መልስ ይዘት**

ተጠሪው በጽሁፍ መልስ እንዲያቀርብ የታዘዘ እንደሆነ በመልሱ ውስጥ በአመልካች ለቀረበው አቤቱታ መከላከያ የሚሆነውን ፍሬ ነገር ዘርዝሮ ያቀርባል፡፡

**39. ክርክር ስለሚመራበት ስርዓት**

1. ፍርድ ቤቱ አመልካች የሚያቀርበውን አቤቱታ እና ተጠሪው የሚሰጠውን መልስ መርምሮ ወዲያውኑ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በሚያደርገው ምርመራ ውሳኔ ላይ ለመድረስ እንደማይችል ሲረዳ አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነውን ማስረጃ እና ምስክር ብቻ አስቀርቦ ወይም ሰምቶ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**40. ማስረጃዎች**

1. በአንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ፍትሃዊ ለመወሰን ማስረጃ ማስቀረብ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን በራሱ አነሳሽነት ወይም በተከራካሪ ወገኖች አመልካችነት ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ አመልካች ወይም ተጠሪ ካቀረቧቸው የሰነድ እንዲሁም የሰው ምስክሮች መካከል ጉዳዩን መርምሮ ለመወሰን አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነውን ማስረጃ ብቻ ይቀበላል ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተመለከተው ማስረጃ የሚገኘው በሦስተኛ ወገን ዘንድ የሆነ እንደሆነ ይኸው አካል ማስረጃውን ፍርድ ቤቱ ባዘዘው ጊዜ ውስጥ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

**41. አቤቱታ እና መልስ ስለማሻሻል**

1. በዚህ ደንብ በሚመሩ ጉዳዮች ላይ የአቤቱታ ወይም መልስ ማሻሻል ጥያቄ ማቅረብ አይቻልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተመለከተው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ የአቤቱታው ወይም የመልሱ መሻሻል ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚያስፈልግ ነው ብሎ ሲያምን እና ውሳኔውም በዚህ ደንብ በተመለከቱት ውሳኔ የመስጫ ጊዜያት ውስጥ ሊሰጥ የሚችል መሆኑን በማገናዘብ አቤቱታው ወይም መልሱ እንዲሻሻል ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**42**. **ስለ ውሳኔ አሰጣጥ**

1. ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ክርክር ከመረመረ በኃላ ለአቤቱታው መነሻ የሆነውን የመጨረሻ ውሳኔ ሊያጸና፣ ሊያሻሽል ወይም ሊሽር ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ የውሳኔውን ቅጂ ለተከራካሪ ወገኖች ይሰጣል፡፡
3. ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ እንዲፈጸም እንደአስፈላጊነቱ ለቦርዱ፣ ለክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ፣ ለምርጫ ክልሉ፣ ለምርጫ ጣቢያው ወይም ለሌላ ለሚመለከተው አካል ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ትዕዛዙም የሚሰጠው ውሳኔ በተሰጠበት መዝገብ ላይ ይሆናል፡፡

**43. አፈጻጸም**

1. የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የደረሰው አካል ወዲያውኑ በውሳኔው መሰረት የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡
2. ፍርድ ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ውሳኔው ያልተፈጸመ እንደሆነ አመልካቹ ውሳኔው እንዲፈጸምለት ለፍርድ ቤቱ ለማመልከት ይችላል፡፡
3. የአመልካቹ የአፈጻጸም አቤቱታ ጉዳዩን በተመለከተው ችሎት እና ጉዳዩ በታየበት መዝገብ ይስተናገዳል፡፡
4. ፍርድ ቤቱ የአመልካቹን አቤቱታ ተቀብሎ ወዲያውኑ ፍርዱ እንዲፈጸም ወይም የማይፈጸምበት ህጋዊ ምክንያት ካለ ውሳኔው የደረሰው አካል ቀርቦ እንዲያስረዳ በድጋሚ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

44. **ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዙ ሌሎች ጉዳዮች ላይ በቦርዱ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ አቤቱታ**

1. ማንኛውም ሰው

   ሀ. በአዋጁ አንቀጽ 115 ንዑስ አንቀጽ (2) የተገለጸውን የአገር ውስጥ ታዛቢዎች ዕውቅና አሰጣጥ ወይም

   ለ. በአዋጁ አንቀጽ 125 ንዑስ አንቀጽ (2) የተገለጸውን የሥነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት የሚሰጡ ተቋማት ዕውቅና አሰጣጥን በሚመለከት ወይም

   ሐ. ሌሎች የምርጫ ሂደትን በሚመለከት ቦርዱ ባስተላለፋቸው የመጨረሻ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው

   ሰው አቤቱታውን በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ አቤቱታው በቀረበለት 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔውን መስጠት አለበት፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**45. የቀጠሮ አወሳሰን**

1. በዚህ ደንብ መሰረት ጉዳዮችን የሚያስተናግድ ማናቸውም ፍርድ ቤት ማናቸውንም አይነት ትዕዛዝ ሲሰጥ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ እና የምርጫ ጉዳዮችን ልዩ ባህሪያት ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ ደንብ መሰረት የሚታዩ ጉዳዮችን የሚመለከት ፍርድ ቤት በደንቡ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ጉዳዮችን ያስተናግዳል፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም ፍርድ ቤቱ ቀጠሮ ለመለወጥ የሚያስችል በቂ ምክንያት ያለው እና በዚህ ደንብ በተመለከቱት ውሳኔ የመስጫ ጊዜያት ውስጥ ውሳኔ መስጠት የሚችል መሆኑን ሲያረጋግጥ ብቻ ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠት ይችላል፡፡

**46. አጣዳፊ ጉዳዮች**

በአዋጁ እና በዚህ ደንብ ስለጉዳይ መወሰኛ ጊዜያት የተደነገገው ቢኖርም ጉዳዩ አጣዳፊ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የጉዳዩ ባህሪ በሚጠይቀው ፍጥነት ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

**47. በጊዜው ስላልቀረበ አቤቱታ**

በአዋጁ አንቀጽ 151 ንዑስ አንቀጽ (13) እና በዚህ ደንብ መሰረት የአቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡

**48. ፎርሞች**

1. በዚህ ደንብ መሰረት የሚቀርቡ አቤቱታዎች ፣መልሶች፣ በፍርድ ቤት የሚሰጡ ትዕዛዞች፣ ፍርዶች ወይም ውሳኔዎች እና ሌሎች ሰነዶች የሚጻፉበትን ፎርሞች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡
2. ፍርድ ቤቶች፣ ተከራካሪ ወገኖች እና ሌሎች አካላት በተቻለ መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት በሚዘጋጁት ፎርሞች መገልገል አለባቸው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ቢኖርም ፍርድ ቤት ወይም ተከራካሪዎች በዚህ ደንብ የተዘጋጁትን

ፎርሞች መጠቀሙ የማያመች ሆኖ ያገኙት እንደሆነ የራሳቸውን ፎርሞች መጠቀም ይችላሉ፡፡

**49. ጉዳዮች የሚስተናገዱባቸው ቀናት**

1. በዚህ ደንብ መሰረት ጉዳዮችን የሚያስተናግድ ፍርድ ቤት ጉዳዮችን ቅዳሜ፣ እሁድ እንዲሁም በህዝብ በዓላት ቀን ለማየት ሊወስን ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሱት ቀናት ጉዳዮች የሚስተናገዱ ከሆነ የፍርድ ቤት አስተዳደር ለዳኞች እና ለሌሎች ሰራተኞች አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

**50. ስለ ወኪል**

በዚህ ደንብ መሰረት ተከራካሪ የሆነ ሰው እራሱ በአካል ቀርቦ መከራከር የማይችል ከሆነ በወኪል መከራከር የሚችለው

1. መራጭ ከመሆን የተከለከለ ሰው ከሆነ በጠበቃው፣
2. የግል ዕጩ ተወዳዳሪ ከሆነ በአዋጁ መሰረት የዕጩው ወኪል ሆኖ እንዲሰራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም በጠበቃው፣
3. የፖለቲካ ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪ ከሆነ በጠበቃው ወይም በወከለው የፖለቲካ ፓርቲ ኃላፊ ወይም የፖለቲካ ፓርቲው በወከለው ሰው፣
4. የፖለቲካ ፓርቲ ከሆነ የፖለቲካ ፓርቲ ኃላፊ ወይም ኃላፊው የወከለው ሰው ወይም በጠበቃው ብቻ ነው፡፡

51. **ዳኝነት በድጋሚ የማይታይ ስለመሆኑ**

1. በዚህ ደንብ መሰረት በፍርድ ቤት ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ በድጋሚ ዳኝነት እንዲታይበት ጥያቄ ሊቀርብ አይችልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተደነገገው ቢኖርም ውሳኔው የተሰጠው በሀሰተኛ ማስረጃ መሆኑ ከተረጋገጠ እና ማስረጃው ውሳኔውን ሊያስቀይረው የሚችል ከሆነ እንዲሁም ጉዳዩን በአዋጁ በተቀመጠው የመወሰኛ ጊዜ መወሰን እንደሚቻል ፍርድ ቤቱ ካረጋገጠ ጉዳዩ በድጋሚ ዳኝነት ሊታይ ይችላል፡፡

**52. ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ**

በዚህ ደንብ መሰረት ጉዳዮችን ተቀብሎ የሚያስተናግድ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

53. **ጉዳዩ ወደ ወሰነው አካል የማይመለስ ስለመሆኑ**

በዚህ ደንብ መሰረት አንድ ፍርድ ቤት ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን በጉዳዩ ላይ አስቀድሞ ውሳኔ የሰጠው አካል በድጋሚ አይቶ እንዲወስን ሊመልስለት አይችልም፡፡

**54. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ፍርድ ቤት ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚሰጠውን ትዕዛዝ የማክበር እና ለትዕዛዙ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**55. የወንጀል ቅጣት**

ፍርድ ቤቱ ማስረጃ እንዲያቀርብ ወይም ሌላ ትዕዛዝ እንዲፈጽም ትዕዛዝ ያስተላለፈለት ሰው ማስረጃውን ለማቅረብ ወይም በትዕዛዙ መሰረት ለመፈጸም ፈቃደኛ ካልሆነ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ይቀጣል፡፡

**56. የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ተፈጻሚነት**

ይህ ደንብ በሚጸናበት ጊዜ በስራ ላይ ያለው የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ደንቡ ባልሸፈናቸው ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

57. **ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

ይህ ደንብ በሸፈናቸው ጉዳዮች በሥራ ላይ ያለው የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

58. **መመሪያ ስለማውጣት**

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዳ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**59. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከጸደቀበት ጥር....... ቀን .....2013 ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ሳህለወርቅ ዘውዴ

ፕሬዘዳንት